# የካፒቴኑ ሴት ልጅ



ከአሌክሳንደር
ፑሽኪን

ትርጉም

በመለሰ ጥላሁን

t.me/OLDBOOKSPDF

# የካፒቴኑ ሴት ልጅ

እና

ሌሎችም . . .

ከአሌክሳንደር ፑሽኪን

ትርጉም

በመለስ ጥላሁን

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፹፪

t.me/OLDBOOKSPDF

መታሰቢያነቱ

ለባለቤቴ

ለበላይነሽ ፋሪስ

እና

ለልጆቼ

ለዓለም መለሰ

ለቅድስት መለሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

## ማውጫ

አርእስት ገጽ


ተኩስ ........................................ 7

የበረዶ ውሽንፍር ........................... 26

የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ................ 44

የማረፊያ ጣቢያ ሹም ...................... 55

የካፒቴኑ ሴት ልጅ ........................ 73


t.me/OLDBOOKSPDF

# ቀኩስ

የተመደብነው በአንዲት ትንሽ ከተማ ውስጥ ነበር ። የጦር ሠራዊት መኰንን ኑሮ ምን እንደሚመስል ማንም ያውቀዋል ። ጠዋት ወታደራዊ ሰልፍና ፈረስ ግልቢያ መለማመድ ፣ ቀትር ላይ ከክፍለ ጦሩ አዛዥ መኖሪያ ቤት ወይም በአንድ ይሁዲ ሆቴል ምሳ መብላትና ማታ አረቄ እየተጎነጩ ካርታ መጫወት ነው ። በዚያች ከተማ ውስጥ አንድም የምንሔድበት ቦታ አልነበረም ። ለጋብቻ የምትበቃ አንዲት ኮረዳ እንኳ አልነበረችም ። በየመኖሪያ ክፍሎቻችን እየተሰባሰብን የደንብ ልብሶቻችንን ከማየት በስተቀር የምናደርገው ሌላ ምንም ነገር አልነበረም ።

ከመካከላችን ወታደር ያልሆነ አንድ ሰው ብቻ ነበር። ዕድሜው ወደ ሠላሳ አምስቱ ዓመት አካባቢ የሚገመት ሲሆን እምናየው እንደ ሽማግሌ ነው።በልምድ ያገኘው ዕውቀቱ በብዙ መንገድ ከኛ ልቆ እንዲገኝ አስችሎታል ። ከዚህ በቀር የዘወትር ጨፍጋጋነቱ ፣ ኮስታራ ጠባዩና መርዘኛ ምላሱ በለጋ አእምሮአችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሮብን ነበር ። ስለግል ሕይወቱ በውል የሚያውቅ ማንም አልነበረም ። ሩሲያዊ ቢመስልም የሚጠራው በባዕድ ስም ነበር ። በአንድ ወቅት በፈረሰኛ ጦር ውስጥ አገልግሏል ። በጊዜውም ከፍተኛ ደረጃ የመድረስ ዕድል ሲኖረው፣ በገዛ ፈቃዱ ከሥራው የተሰናበተበትንና በዚች አልባሌ ትንሽ ከተማ ውስጥ ለመኖር የመረጠበትን ምክንያት ማንም አያውቅም ። የነተበ ጥቁር ካፖርቱን አጥልቆ በእግሩ ከሥፍራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ሥፍራ እየተዘዋወረ ገንዘቡን ለአልባሌ ነገር ይረጫል። መኖሪያ ቤቱም ለክፍለ ጦሩ መኰንኖች መዝናኛ ክፍት ነው ። ሁለት ወይም ሦስት ዐይነት ምግብ በአንድ የቀድሞ ወታደር እየተዘጋጀ ይቀርብለታል ። በገበታ ሰዓት የሚቀዳው ሻምፓኝም ወሰን አልነበረውም። ስለ ሀብቱም ሆነ ስለ ገቢው የሚያውቅ ወይም ደፍሮ የሚጠይቀው አልነበረም። በእጁ ከሚገኙት አያሌ መጻሕፍት መካከል አብዛኞዎቹ ልብ ወለድና የጦር ስልት መማሪያ ነበሩ ። እነዚህን ለማዋስ ምንጊዜም ዝግጁ ነበር ። በውሰት የሰጠውን መጽሐፍ እንዲመለስለት አይጠይቅም ። እሱም የተዋሰውን መጽሐፍ ለባለቤቱ አይመስልም ። ዋነኛ የጊዜ ማሳለፊያው ሽጉጥ መተኮስ ነበር ። የክፍሉ ግድግዳዎች በጥይት ከመበሳሳታቸው የተነሣ የማር እንጀራ ይመስላሉ ። በሚኖር ቤት ደሳሳ ያጡብ ጐጆ ውስጥ ዋጋ ያለው ንብረት ቢኖር በብዛት ያጠራቀመው የሽጉጥ ዐይነት ነው ።

በተኳሽነት ሙያው ከፍተኛ ተደናቂነትን በማትረፉ ቆብ ላይ የተቀመጠች ዖም ነጥዬ እመታለሁ ቢል ከክፍለ ጦራችን ውስጥ ጭንቅላቱን የማያቀርብለት አንድም ሰው አልነበረም። አብዛኛው ጭውውታችን የሚያተኩረው ሥር በሰደደ ጠብ ወይም በዕለት ግጭት መነሾነት በሚደረጉ ፍልሚያዎች ላይ ነበር ። ሆኖም ይህ ባለ ታሪክ ፣ ሲልቪዮ ልበለው ፣ በጭውውቱ ተሳትፎ አያውቅም ። ቀድሞ ሲል ተፋልሞ እንደነበር ሲጠየቅም ወደ ዝርዝር ሳይገባ አጭር የአዎንታ መልስ ይሰጣል ። እንዲህ ያለ ጥያቄ እንደማያስከፋውም ገልጾ ነበር ። በዚህ በአደገኛ ሙያው ምክንያት ለሞት የዳረገው አንድ ምስኪን ሕሊናውን እየቆጠቆጠው ይሆናል ብለን ገመትን ። የፈሪነት ስሜት በልቡ ይኖራል የሚል ስሜት ግን ፈጽሞ አልነበረንም ። ላይ ላዩን ሲታዩ ገጽታቸው በእንደዚህ ዐይነት ነገር ፈጽሞ የማያስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠረጥራቸው እንዳንድ ሰዎች አሉ ። ይህ በዚህ እንዳለ ሁላችንም ያሳሰብነው ድርጊት ተፈጸመ ።

አንድ ቀን ዐሥር የምንሆን መኰንኖች ሲልቪዮ ቤት እራት በመብላት ላይ ነበርን ። እንደ ወትሮዋችን ከልክ ያለፈ ጠጣን ። ገበታ ከፍ ካለ በኋላ ፣ ካርታ ለመጫወት ተስማማንና ጋባዣችን ገንዘብ ያዥ እንዲሆንልን ለመን ነው ። ካርታ እምብዛም ስለማይጫወት ፈቃደኛ ለመሆን ብዙ አቅማማ ። በመጨረሻ ግን፣ካርታ እንዲመጣ አዘዘና የራሱን ድርሻና የሰበሰበውን ሃምሳ ባለዐሥር ሩብል ኖቶች ጠረጴዛው ላይ በየቦታው መድቦ ካርታ ማደል ጀመረ ። ሁላችንም በሱ ዙሪያ ቦታ ቦታችንን ያዝን ። ጨዋታው ተጀመረ ። ሲልቪዮ በሚጫወትበት ሰዓት ቃል አይተነፍ ስም፤ አይጨቃጨቅም ፤ የአጫዋወት ሕግም አይደረድርም፤ ከተጨዋቾቹ አንዱ የተሳሳተ ነጥብ ቢያስቆጥር ፣ ሲል ቪዮ ወዲያው ከፍሎ በትርፍ የሔደውን ገንዘብ ይመዘግባል። ሁላችንም ይህን ስለምናውቅ፣ ባሻው መንገድ እንዲያጫ ውት ዕድል ሰጠነው ። ነገር ግን፣በቅርቡ ወደ ክፍለ ጦራ ችን የተዛወረ አንድ መኰንን በመካከላችን ነበር ። ይህ ሰው በመጫወት ላይ እያለ ሳያውቀው የተመደበውን ገንዘብ በአንድ ነጥብ ከፍ አደረገው ። ሲልቪዮ የጠመኔ ቁራጭ ብድግ አድርጐ በተለመደው አሠራሩ ነጥቡን አስተካከለ። መኰንኑ ፣ ግን ትዕግሥቱ ስለአለቀ ብሩሹን አነሣና መልሶ አጠፋበት ። ሲልቪዮ ጠመኔውን ብድግ አድርጐ ቁጥሮ ቹን እንደገና ጻፈ ። መኰንኑ በወይን ጠጅ ፣ በቁማሩና በጓ ደኞቹ ሣቅ ስለ ተበሳጨና ከፍተኛ ውርደት የደረሰበት መስሎ ስለታየው ፣ ከነሐስ የተሠራ የሻማ መሰኪያ ከጠረጴ ዛው ላይ በድንገት አፈፍ አድርጐ ወደ ሲልቪዮ ወረወረ ። ግን ሲልቪዮ ዘወር በማለት ከመመታት ለጥቂት አመለጠ። ሁላችንም በጣም ተደናገጥን ። ሲልቪዮ በቁጣ የፊቱ ደም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥሮች ተግተርትረው፣ ዐይኖቹ እንደ እሳተ ነበልባል እየተ ንቀለቀሉ ብድግ አለ ። " ጌታው ! " አለው ፡ " በል ቀስ ብለህ ሒድ፣አድራጐትህ እኔው ቤት በመፈጸሙ እግዜርን አመስግን ። "

የዚህ ግጭት መጨረሻው ምን እንደሚሆን ስላልተ ጠራጠርን ፡ አዲሱን ባልደረባችንን እንደሞተ ሰው ቆጠር ነው ። እሱም ለተከናነበው ውርደት ጊዜ ሲያመቸው ብድ ሩን ለመመለስ ዝግጁ መሆኑን ገልጾ ሔደ ። ተቋርጦ የነበ ረው ጨዋታ ለጥቂት ደቂቃዎች ቀጠለ ። ሆኖም ጋባገር ችን የካርታ ጨዋታውን በሙሉ ልብ ሊከታተል አለመቻ ሉን ሁላችንም ስለ ተገነዘብን ፡ ከቤቱ አንድ ባንድ ሹልከ እያልን ወደየመኖሪያችን አመራን ፡ በቅርቡ በሞት ስለ ሚለየን ያ መኮንን እየተወያየን ።

በነጋታው ፈረስ ግልቢያ ትምህርት ላይ ሆነን ፡ ምስ ኪኑ የሙቶ አለቃ በሰላም ማደር አለማደሩን እርስ በርሳ ችን ስንጠያየቅ ፡ ራሱ በድንገት ከተፍ አለ ። ያንኑ መል ሰን ብንጠይቀው ከሲልቪዮ ገና አንዳችም ነገር አለመስማ ቱን ገለጸልን ። በሁኔታው እጅግ ተገርመን ወደ ሲልቪዮ ቤት አመራን። እንደ ደረስን አጥሩ በር ላይ በተለጠፈች አን ዲት ካርታ ላይ በማከታተል ሲተኩስ አገኘነው። ባለፈው ዕለት ስለ ተፈጸመው ድርጊት ቃል ሳይናገር እንደ ተለመ ደው አስተናገደን ። ሦስት ቀናት አለፉ ። ሙቶ አለቃው አሁንም በሕይወት አለ ። ምናልባት ሲልቪዮ ለመፋለም አላሰበ ይሆን እያልን እርስ በርስ ተጠያየቅን ። ሲልቪዮ አልተፋለመም ። እንዲያውም የእንግት በላይ ይቅርታ ጠይቆ ከሙቶ አለቃው ጋር ታረቀ ።

ይህ አድራጐቱ በወጣቶቹ ዘንድ ክብሩን ሳይቀንስ በት አልቀረም ። ድፍረቱን ከኃጢአት እንደሚያነጻ ታላቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተግባር አድርገው በሚመለከቱ ወጣቶች ዘንድ ፣ ወኔ ቢስ ነት ይቅርታ የማይደረግለት የመጨረሻ ውድቀት ነው ። ይሁን እንጂ ፣ ነገሩ እያደር እየተረሳ በመሔዱ ሲልቪዮ የቀድሞውን ክብሩን እንደገና ሙሉ በሙሉ አደሰው ።

እኔ ብቻ ስለ እርሱ ያለኝ ስሜት እንደ ቀድሞው ሊሆንልኝ አልቻልኩም ። በተፈጥሮዬ ሐሞተ ኮስታራ ስለሆንኩ ፣ ያን ምሥጢራዊ ሕይወት ያለውን ሰው ፣ ሲልቪዮን አከብረው የነበረው ከሁሉ አብልጨ መለኮታዊ ኃይል እንደተቀዳጀ ጀግና ነበር ። እሱም በጣም ይጠጋኝ ነበር ። የፈለገው ቢሆን ፣ ከተለመደው ትችቱ ተቆጥቦ በመገዘናናትና በደስታ መንፈስ የሚወያየው ከኔ ጋር ብቻ ነበር ። ሆኖም ያደፈ ክብሩን ለማጽዳት ሲል ምንም ላለማድረግ የወሰነባት የዛች አሳዛኝ ምሽት ትዝታ ከአእምሮዬ ባለመፋቁ እንደ ወትሮው ላከብረው አልቻልኩም። ዐይኑን ለማየት ዐፈርኩ ። ሲልቪዮ ኑሮ ብዙ ያስተማረው ብልህ ሰው ስለሆነ ፣ ሁኔታውን ለመገንዘብና ምክንያቱን ለማወቅ አልተሳነውም ። አድራጐቱም ሳያሳዝነው አልቀረም። የልቡንም ገልጦ ሊያጫውተኝ ፍላጐት እንደ ነበረው ከአንዴም ሁለቴ ተረድቻለሁ ። ይሁን እንጂ ፣ አጋጣሚዎቹን ሆን ብዬ ቸል ስላልኩበት ሲልቪዮ ተወት አደረገኝ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ከእርሱ ጋር የምንገናኘው ከሥራ ጓደኞቼ ጋር አብሬ በመሆን ነበር ። የቀድሞ ልባዊ ጭውውታችንም በዚያው አከተመ ።

ከተሜዎች የገጠር ወይም የትናንሽ ከተማ ነዋሪዎችን የተለመዱ አያሌ የደስታ ምንጮች ምንነት ሊረዱ አይችሉም ። ለምሳሌም ፣ ከነዚህ አንዱ ፖስታ የሚታደልበትን ቀን በናፍቆት መጠባበቅ ነው ። ዘወትር በየሳምንቱ ማክሰኞና ዓርብ በየክፍለ ጦሩ ዋና መሥሪያ ቤት ብዛት ያላቸው መኰንኖች ይሰበሰባሉ ። ጥቂቶቹ ገንዘብ ፣


t.me/OLDBOOKSPDF

ሌሎቹ ደብዳቤ፣አንዳንዶቹ ደግሞ ጋዜጣ ይላክልናል ብለው የሚጠባበቁ ናቸው ። አብዛኛውን ጊዜ ደብዳቢዎች የሚከፈቱት እዚያውና ወዲያውኑ ስለሆነ በአካባቢው ወሬ ይጠፋል ። ሲልቪዮም ከዚያ ተለይቶ አያውቅም ። አንድ ቀን ደብዳቤ ደርሶት እጅግ በመቅበጥበጥና በመጣደፍ ፖስታውን ከፈተው ። ደብዳቢውን በችኮላ በማንበብ ላይ እያለ ዐይኖቹ ይንተገተጉ ነበረ ። መኮንኖቹ በየራሳቸው ደብዳቤ ስለ ተመሰጡ ልብ አላሉትም ። “ ጐበዝ ” አለ ሲልቪዮ ከፍ ባለ ድምፅ “ ከዚህ በአስቸኳይ እንድሔድ ሁኔታዎች ያስገድዱኛል ። በዛሬው ምሽት ጉዞዬን መጀመር አለብኝ። ለመጨረሻ ጊዜ ከእኔ ጋር እራት ለመጋበዝ እምቢ እንደማትሉ ትምናለሁ ። እጠብቃችኋለሁ ” አለ ። ቀጠል አድርጐም ወደ እኔ እያየ “ አንተም መምጣት ትለብሀ ” አለኝ ። ይህን ተናግሮ ውልቅ አለ ። ሌሎቻችንም ሲልቪዮ ቤት ለመገናኘት ተስማምተን ተለያየን ።

በቀጠሮው ሰዓት ሲልቪዮ መኖሪያ ቤት ስደርስ ከጥቂቶች በስተቀር የክፍለ ጦሩ አባላት በሙሉ ተሰባስበው አገኘኋቸው ። ጓዙ በሙሉ ተጠቅሏል ። በጥይት ከተበሳሱት ባዶ ግድግዳዎች በቀር ሌላ ምንም የሚታይ ነገር የለም ። ለገበታ ቀረብን ። ጋባዣችን በደስታ ፈንጥዞ እኛንም አስፈነጠዘን ። ወይን ጠጅ በሽበሽ ሆነ ። ለሚለየን ባልደረባችን መልካም ጉዞና መልካም ዕድል እንዲገጥመው ያለንን ልባዊ ምኞታችንን ደጋግመን ገለጽን ። ከገበታ ስንነሣ ምሽቱ ተገባዶ ነበር።መለዮአችንን አንሥተን ለመሔድ ስንዘጋጅ ሲልቪዮ እያንዳንዱን በየተራ መሰናበት ጀመረ ። እኔም ተሰናብቼው ልወጣ ስል እጄን በመያዝ አስቀርቶኝ ዝግ ባለ ድምፅ “ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ” ስላለኝ ወደ ኋላ ቀረሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ተጋባገሮቹ ሔደው እኛ ቀረን ። ፊት ለፊት እየተያ የን በዝምታ ፒያኖችንን አቀጣጠልን ። ሲልቪዮ በሐሳብ ተውጧል ። ቀድሞ የነበረው የፈንጠዝያ ስሜት ጨርሶ ደብ ዛው ጠፍቷል ። የተጠበሰ ሳምባ የመሰለው ጨፍጋጋ ፊቱ፣ የሚንተገተገት ዐይኖቹና ከአፉ እየተቡለቀለቀ የሚወጣው ጢስ ተዳምረው የለየለት ጋኔን አስመስለውታል ። ከጥ ቂት ደቂቃዎች በኋላ ሲልቪዮ መናገር ጀመረ ።

“ ምናልባት እስከ መጨረሻው ላንገናኝ እንችላለን ” አለ ፤ “ ከመለያየታችን በፊት ግን ላነጋግርህ እሻለሁ ። ሌሎች ስለ እኔ ስላላቸው አመለካከት እምብዛም እንደማል ጨነቅ ሳትረዳልኝ አትቀርም ። አንተን ግን ፣ ከልብ ስለም ወድህ ስለእኔ የተሳሳተ ግምት ትቼልህ ብንለያይ ይጸጽተ ኛል ። ”

ንግግሩን አቋርጦ ፒፓውን እንደገና መሙላት ጀመ ረ ። ቃል ሳልተነፍስ ራሴን አቀረቀርኩ ። ንግግሩን በመቀጠል ፤ “ ከዚያ ሰካራም ጋር አለመፋለሜ እንግዳ ስሜት ሳያሳድርብህ አልቀረም ። የፈለግሁት መሣሪያ በእ ጄ እንደሚገኝ ሁሉ ፤ ሕይወቱም በመዳፌ ውስጥ እንደነበ ረች ፣ የኔ ሕይወት ግን እምብዛም ሥጋት ላይ እንደማ ትወድቅ ራስህ የምታምነው ጉዳይ ነው ። ታጋሽነቴን እንደ ርኅራኄህ ልትቆጥርልኝ ይገባል ። ሆኖም ልሸሽግህ የማል ፈልገው አንድ ሐቅ አለ—ይኸውም የራሴን ሕይወት ለም ንም ዐይነት አደጋ ሳላጋልጥ ለመበቀል አለመቻሌን ነው። ብችል ኖሮማ ፈጽሞ አልምረውም ነበር ። ”

በመገረም ትክ ብዬ አየሁት ። ሐቁን በመዘክዘኩ ደነ ገጥኩ ። ሲልቪዮ ቀጠለ ። “ እምን ሕይወቴን ላደጋ የማ ጋልጥ በት ምክንያት የለም ። ከስድስት ዓመት በፊት ፊቴን በጥፊ ተመትቻለሁ ። ደመኛዬም እስካሁን በሕይወት አለ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩን ለማወቅ ይበልጥ ጓጓሁ ። “ ታዲያ ‘ አልተፋለም ከውም ’ ማለት ነው ? ምናልባት ሳይመቻችሁ ቀርቶ እንዳ ይሆን ? ” በማለት ጠየኩት ።

“ እሱስ ተፋልሜዋለሁ ” አለ ሲልቪዮ ። “ የፍልሚያችን መታሰቢያም እኔ ዘንድ ይገኛል ። ”

ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ከካርቶን ውስጥ በጉንጉን የተከፈፈና ወርቅማ ቁንጮ ያለው ቀይ መለዮ አወጣና ራሱ ላይ ደፋው ። ከግምባሩ ጥቂት ከፍ ብሎ ጥይት የበሳው ቀዳዳ ይታያል ።

“ በአንድ ወቅት ፣ በአንድ የፈረሰኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ማገልገሌን እንዳጫወትኩህ ታስታውሳለህ ” በማለት ሲልቪዮ ቀጠለ ። “ ጠባዬን ታውቀዋለህ ። በሁሉም ነገር ልቆ መገኘት ልማዴ ነው ። ይህ ደግሞ ፣ ከወጣትነት ጊዜዬ እን ሥቶ የተቆራኘኝ ጽኑ ፍላጐት ነው ። ሞገደኛነት እንደ ትልቅ ሙያ ይቆጠር ፣ ስለነበር በመላው ክፍለ ጦር ውስጥ ቀንደኛው ጠብ አጫሪ እኔ ሆንኩ ። መስከርም ያኮራ ነበ ርና አንድ ጊዜ ጨን እስኪለኝ ጠጣሁ ። በክፍለ ጦራችን ውስጥ በየደቂቃው ፍልሚያ ይካሔድ ስለነበር ፣ በተሳታፊ ነት ወይም በታዛቢነት ያልተገኘሁበት ወቅት ጥቂት ነበር ። ታዲያ ጓደኞቼ እንደ ጣዖት ሲያመልኩኝ፣ በየጊዜው የሚቀ ያየሩት የክፍለ ጦሩ አዛዦች ደግሞ እንደ ሰይጣን ነበር የሚ መለከቱኝ ። በተደናቂነቴ ፣ ድምፄን አጥፍቼም ሆን ሳላ ጠፋ ፣ በመደሰት ላይ ሳለሁ ትውልዱ ከመኳንንት ቤተሰብ የሆነ ስሙን የማልጠቅሰው አንድ የናጠጠ ሀብታም ወጣት በክፍለ ጦራችን ውስጥ ተመደበ ። እንደሱ ያለ ብልህና ዕድ ለኛ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም ! እስቲ እንዲያው ነገሩን በጥሞና ተመልከተው ፤ ወጣት ፣ ብልህ መልከ መልካም ፣ ደፋር ፣ ዝነኛ፣እንዳሻው የሚመነዝርና የማይደርቅ የገንዘብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምንጭ ያለው ያ ሰው የሚያሳድርብንን ስሜት እስቲ ገምት ።
የበላይነት ሥፍራዬን አናጋብኝ።በተወዳጅነቴ ተማርኮ በመ
ጣ ሰሞን ከኔ ጋር ለመቀራረብ ሞከረ ። ግን ፊት ስለነሣሁት
ያለምንም ቅሬታ ሸሸኝ ። እኔም በሱ ላይ የመረረ ጥላቻ
ኦደረብኝ ። በክፍለ ጦሩ ወታደሮችና በሴቶች ዘንድ ያለው
ተወዳጅነት ጨርሶ ተስፋ አስቆረጠኝ ። ሆን ብዬ ከሱ ጋር
ጠብ ለመፍጠር አሰብኩ ። ግን ለምሰነዝርበት የዘለፋና የት
ንኮሳ ቃላት ሁሉ የሚሰጠኝ መልሶች ሁልጊዜም በአሥ
ቂኝነታቸው ለመቼውም ጥርስ የማያስከድኑ ነበሩ ። እንዳ
ውም የማነጣጥርበትን የነገር ቀስት መርዘኛነት እየጠቀሰ
ያፌዝብኝ ጀመር ። የፖላንድ ተወላጅ በሆነ አንድ የመ
ሬት ከበርቴ ቤት ባንድ ምሽት በተደረገ የራት ግብዣ ላይ
ወይዛዝርቱ በሙሉ እንደ ንብ ስለ ከበቡትና በተለይም
ወዳጇ የሆነችው የከበርቴው ባለቤት ዐይኗን ጥላበት በማየቴ
ወደጆሮው ጠጋ ብዬ አንድ ጸያፍ ስድብ ጣል አደረግሁ
በት ። ቱግ በሚለት ተንጠራርቶ በጥፊ አጮለኝ ። ሁለታ
ችንም ተሸቀዳድመን ሻምላዎቻችንን መዘዝን ። ወይዛዝ
ርቱ በድንጋጤ ራሳቸውን ሳቱ ። ተጋባዦዎቹ በአሳር በመ
ከራ ቢገላግሉንም ለፍልሚያ ቀጠሮ ተለዋወጥን ። በማግ
ሥቱ ጐህ ሲቀድ በቀጠሮው ቦታ ከሦስት እማኞቼ ጋር ቆሜ
ባላጋራዬን በመቁነጥነጥ እጠብቅ ጀመር ። የጸደይ ወራት
በመሆኑ ጀምበር ማልዳ ወጥታለች። ቀኑ ሞቅ እያለ ሲሔድ
ጠላቴ ሲመጣ ከሩቅ አየሁት ። ኮቱን ከታጠቀው ጐራዴ
እጀታ ላይ ጣል አድርጐታል ። የታጀበውም በአንድ እማኝ
ብቻ ነበር ። እኔና አብረውኝ የነበሩት ሰዎች ወደ እርሱ
አቅጣጫ አመራን ። እሱም ከመለዮው የሚያወጣውን
እንጆሪ መሳይ ፍሬ እየበላ ተጠጋኝ ። እማኞቼ በመካከላ
ችን የዐሥራ ሁለት እርምጃ ርቀት ቆጠሩ ። ለተኩስ ልውው
ጥም አዘጋጁን ። በቅድሚያ መተኮስ የነበረብኝ እኔ ሆኜ
ሳለሁ ፤ በንዴት እርር ድብን ከማለቴ የተነሣ የእጄን አነጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጣሪነት ስላልተማመንኩበት ፡ የመጀመሪያውን የተኩስ ዕድል ለእርሱ ሰጠሁት ። ተፋላሚዬ ግን ፡ በዚህ አልተስማማም ። ዕጣ እንዲጣል ተወሰነ ። ምንጊዜም ዕድለኛ በመሆኑ ለእርሱ ወጣ ። አነጣጥሮ በተመኮስ መለዮዬን ነደለው ። ቀጥሎ የኔ ተራ ነበር ። ሕይወቱ መዳፌ ውስጥ ገባች ። በገጹ ላይ የጭንቀት ምልክት ለማንበብ ስል በጉጉት አተኩሬ አየሁት ። የያዘውን ፍሬ ከመለዮው ውስጥ መራርጦ እየበላና ፍሬዎቹን እግሬ ሥር እየተፋ ከደገንኩበት ሽጉጥ ፊት ለፊት ቆመ ። የተረጋጋ ሁኔታው ይበልጥ ጭስስ አደረገኝ። 'ይህን ለገዛ ሕይወቱ የማይሳሳ ሰው ባጠፋው' አልኩ በልቤ ' ምን ጥቅም አለው ? ' አንድ አረመኔያዊ አሳብ ብልጭ አለልኝና ሽጉጥ የያዘውን እጄን ዝቅ አደረኩ ።

" ስለሞት ለማሰብ ጊዜ እንደሌለህ ተገንዝቤዋለሁ" አልኩት ፡ መብላትህን ቀጥል ። 'ላቋርጥህ አልሻም ። ቅንጣት ታህል ኦ ልደንግጥኩም' ሲል መለሰልኝ። "ይልቅስ ተኩስ ፡ እንዳሻህ ፡ ግን የምትተኩስብኝ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ለዚያም ዝግጁ ነኝ ። "

እኔም ወደ እማኞቼ ዞር ብዬ ለመተኮስ እንደማልፈልግ ነግሬአቸው ፍልሚያው በዚሁ አበቃ ።

" ከክፍለ ጦሩ በገዛ ፈቃዴ ተሰናብቼ እዚች በታ እኖር ጀመር ። ከዚያን ወዲህ ስለበቀል ሳላስብ የዋልኩበት አንድም ቀን የለም ። እነሆ አሁን ጊዜው ደረሰ ። "

ሲልቪዮ በዚያው ዕለት ጠዋት የደረሰውን አንድ ደብዳቤ ከኪሱ አውጥቶ እንዳነበው ሰጠኝ ። አንድ ግለሰብ አንዲት ቆንጆ ወጣት በቅርቡ እንደሚያገባ በመግለጽ ከሞስኮ የጻፈለት ነበር ።

" የዚህን ግለሰብ ማንነት በግምት ሳታውቀው አትቀርም " አለኝ ሲልቪዮ ። "ወደ ሞስኮ መሔዴ ነው ። ከዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም በመለዮው ሙሉ እንጀራ ታቅፎ እየበላ ሞቱን በግ ዱለኝነት እንደ ተጠባበቀ ሁሉ እስቲ ዛሬም በሥርጉ ዋዜማ የሞት ጽዋውን ይቀበለው እንደሆነ እናያለን ።"

ሲልቪዮ ይህን ተናግሮ እመር በማለት አደርጎት የነ በረውን ቆብ ወለሉ ላይ አሽቀንጥሮ ከጣለ በኋላ ፡ እንደተ ቆጣ ዳልጋ አንበሳ ወደላይና ወደታች ይንጉራደድ ገባ ። ካለሁበት ሳልንቀሳቀስ በተምታታና እንግዳ በሆነ ስሜት ጸጥ ብዬ እንደ ቆምኩ ጥሎኝ ወጣ ።

አሽከሩ ብቅ ብሎ ፈረሶቹ ለጉዞው መዘጋጀታቸውን ነገረው ። ሲልቪዮ በጋለ ስሜት ጨበጠኝ ፤ ተቃቀፍን ። ሸጉጦቹን የያዘ አንድ ሻንጣና ጓዙን ያጨቀበት ሌላ ሻንጣ በተጫኑበት ሠረገላ ላይ ተሳፈረ ፤ በድጋሚ ተሰነባበ ትንና ፈረሶቹ ነጐዱ ።

* * *

እያሌ ዓመታት ዐለፉ ። በአጋጣሚዎች ተገድጄ በዚ ያው ወረዳ በምትገኝ በአንዲት ድህነት በሚያጠቃት መን ደር ውስጥ እኖር ጀመር ። እርስቴ ላይ በሥራ ብጠመድም በፈንጠዝያና በጭፈራ ያሳለፍኩት የአፍላ ጊዜ ሕይወቴ ምንጊዜም እንደ ናፈቀኝ ነበር ። ከሁሉም ይበልጥ ልላመ ደው ያልቻልኩት ፡ በጸደይና በክረምት ወራት ምሽቶች የሚሰማኝን አስጨናቂ ብቸኝነት ነበር ። የእራት ሰዓት እስ ኪደርስልኝ ከመንደር አዛውንት ጋር በመወያየት ከቦታ ቦታ በሠረገላ እየተዘዋወርኩ የሥራውን አካሔድ በማየት እንደ ምንም ጊዜዩን አሳልፋለሁ ። ግን ጀምበር ካሽቆለቆ ለች በኋላ ምን እንደማደርግ መላ ቅጡ ይጠፋኛል ። ከቁ ምሳጥንና ከየመሳቢያው ያገኘሁዋቸውን ጥቂት መጻሕፍት እንደ ውዳሴ ማርያም በቃሌ እወጣቸዋለሁ ። ቤት ጠባቂዋ ኪሪሎቭና እያሌ ተረቶችዋን ደጋግማ ታወጋኛለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በየዕለቱ የማዳምጠው የሴቶቹ እንጉርጉሮ ትካዜ ያመጣብ ኛል ። ራስ ምታቱ ባያሳስበኝ ኖሮ ፣ ጠጪ ሳልሆን አልቀ ርም ነበር ። ከመስልቸቱ የተነሣ ሰካራም እንዳልሆን ፣ ማለ ትም በወረዳችን በብዛት ከሚገኙት የወጣላቸው ሰካራ ሞች እንዳልብስ ያሠጋኛል። ሁለት ወይም ሦስት ከሚሆኑ ከእንዲህ ዐይነቶች ምስኪኖች በስተቀር ሌላ ጐረቤትም አልነበረኝም ። እነሱም ቢሆኑ ጨዋታቸው በሳልና በትን ፋሽ አጥረት ስለሚቆራረጥ ከእነርሱ ጋር ከመግጠም ብቸ ኝነቴን እመርጥ ነበር ።

ከነበርኩበት ሥፍራ አራት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ያንዲት ልዕልት ለም እርስት ይገኛል ። ግን ከርስት ጠባቂ ው በስተቀር ሌላ ነዋሪ አልነበረበትም ። ልዕልቲቱም እርስ ትዋን የጐበኘችው አንድ ጊዜ ብቻ ፣ ትዳር በመሠረተች በት ዓመት ሲሆን ለዚያውም ከአንድ ወር የበለጠ አልቆ የችበትም ። እንደ ባሕታዊ በብቸኝነት መኖር በጀመርኩ በት በሁለተኛው ዓመት ላይ ግን ፣ ልዕልቷና ባለቤትዋ በበ ጋው ወራት እርስታቸውን እንደሚጐበኙ ይወራ ጀመር ። በእርግጥም በሰኔ ወር መባቻ ላይ መጡ ።

የአንድ ባለጸጋ መምጣትና ከእርሱም ጋር መጐራበት ለገጠር ነዋሪዎች ታላቅ ኩራት ነው ። ባለርስቶችና አሽከ ሮቻቸው ይኸው ጉዳይ ከመፈጸሙ ቀደም ብለው ሁለት ወር ሙሉ ሲወያዩበት እንደ መቆየታቸው ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ለሦስት ዓመታት ያኽኑ ሲያወሩ ይከርማሉ ። የአ ንዲት ቆንጆ ለግላጋ ወጣት ብቅ ማለትና ከእርሷም ጋር የመጐራበቱ ወሬ በእኔም ላይ ልብ የሚፈነቅል ስሜት አሳ ደረብኝ ። ዐይንዋን ለማየት ቋመጥሁ ። ስለዚህ ፣ በመጣች በመጀመሪያው እሑድ ከምሳ በኋላ ፣ የቅርብ ጐረቤታቸ ውና ታማኝ አሽከራቸው መሆኔን ለክብርትና ለክቡርነታ ቸው ለመግለጽ ወደዚያች መንደር ሔድኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የእልፍኝ አሽከሩ ወደ ልዑሉ ልዩ ክፍል ካደረሰኝ በኋላ መምጣቴን ለማስታወቅ ጐራ አለ ። ሰፋ ያለው ያ ክፍል እጅግ በተዋበ የቅንጦት ዕቃዎች አሸብርቋል።ግድ ግዳውን ተደግፈው የቆሙት መደርደሪያዎች በአያሌ መጻሕፍት ጢም ብለዋል ። በያንዳንዱ መደርደሪያ ጫፍ ላይ ከነሐስ የተሠራ የጊጣጌጥ ቅርፅ ተቀምጧል ። ከዕብነ በረድ ከተሠራው የእሳት መሞቂያው ከፍ ብሎ አንድ ሰፊ መስተዋት አለ ። አረንጓዴ ምንጣፍ በለበሰው ወለል ላይ ፡ ዐልፎ ዐልፎ ስጋጃዎች ተነጥፈዋል ። ተሽጉጬ ከምኖርባት ጐጆዬ ውስጥ ምኞት ባለመልመዴና ፡ የሌሎችን የቅምጥል ኑሮ ለብዙ ጊዜ ሳላይ በመቆየቴ ፡ በኃፍረት ተሸማቀቅሁ ። ጸቤቱታውን ለማስማት እንዳሰበ ሰው የልዑሉን መምጣት በፍርሃትና በጭንቀት እጠባበቅ ጀመር ። በሩ ተከፈተ ። ዕድሜው በግምት ሠላሳ ሁለት ዓመት የሚሆነው እጅግ መልከቀና የሆነ ሰው ገብቶ በጋለ የወዳጅነት ስሜት ቀረበኝ ። ረጋ ብዬ እራሴን ሳስተዋውቅ ስመቻች ቀደመኝ ። ተቀመጥን ። ከበሬታ የተመላበት አዝናኝ ጨዋታው ፡ ለረጅም ጊዜ ብቸኝነት ካቆራኘኝ ዐይን አፋርነት አላቀቀኝ ። መላ ሰውነቴ ዘና ማለት ሲጀምር ልዕልቲቷ ስለገባች ከበፊቱ የባሰ ጭንቀትና ፍርሃት ላይ ወደቅሁ ። በእርግጥም ቆንጆ ልጅ ነች ። ልዑሉም አስተዋወቀን ። የተዝናናሁ ለመምሰል ብሞክርም አልቻልኩም ። አእምሮዬን እንዳረጋጋና ከእነርሱም ጋር መቀላቀሉን እንድላመድ በማሰብ ሽርጉድ ሳያበዙ እንደ ቅርብ ጐረቤታቸው አስተናገዱኝ ። ፍርሃት ለቅቆኝ እኔም ወዲያና ወዲህ እየተንቀሳቀስኩ ያገኘኋቸውን መጻሕፍትና ሥዕሎች ተመለካከትኩ ። ስለ ሥዕል ጥበብ እምብዛም ባላውቅም ዐይኔ በአንድ ሥዕል ላይ ዐረፈ ። ሥዕሉ የሚያሳየው የስዊስን የተፈጥሮ መልከዐ ምድር ነበር ። ግን የተማረክሁት በውበቱ ሳይሆን ሥዕሉ ላይ በሚታዩት ሁለት የጥይት ቀዳዳዎች ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ድንቅ ተኩስ ነው " አልኩ ፊቴን ወደ ልዑል በማ
ዞር ።

" ግሩም እንጂ ! " ሲል መለሰልኝ ። " የተዋጣለት ተኩስ ነው ። አንተስ ጉበዝ ተኳሽ ነህ ? " በማለት እግረ መንገዱን ጠየቀኝ ።

" መጠርጠሩስ " በማለት መለስኩለትና ጨዋታ ችን እኔ ወደምወደው ርዕስ በማምራቱ ተደስቼ " በለመ ድኩት ሽጉጥ ከሆነ ፡ ካርታ እንኳ ከሠላሳ እርምጃ ርቀት አልስትም " አልኩት ።

" ከምርህ ነው ? " አለች ልዕልቲቱ ለነገሩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ። " በእርግጥ ካርታ ከሠላሳ እርምጃ ርቀት መምታት ትችላለህ ? "

" እስቲ አንድ ቀን እንሞክራለን " አለ ልዑሉ ። " እኔም በጊዜዬ ደህና ተኳሽ ነበርኩ ። ሆኖም ላለፉት አራት ዓመታት ሽጉጥ እጄም ገብቶ አያውቅ ። "

ቀጠል አድርጌ " አዬ ጌታዬ ! " አልኩት ። "እንዲያ ከሆነማ ካርታ ከሐያ እርምጃ ርቀት ለመምታት እንደማይ ችሉ ከክቡርነትዎ ጋር እወራረዳለሁ ። የሽጉጥ ተኩስ በየ ዕለቱ መለማመድን ይጠይቃል ። ይህን ራሴው ካገኘሁት ልምድ ተገንዝቤዋለሁ ። በክፍለ ጦራችን ውስጥ ተደናቂ ነትን ካተረፉት ተኳሾች መካከል አንዱ ነበርኩኝ ። አንድ ሰሞን ሽጉጦቼ በጥገና ላይ ስለነበሩ ፡ ያለምንም ልምምድ ለአንድ ወር ቆየሁ ። ታዲያ ምን የሆነ ይመስልዎታል ክቡር ሆይ ? በመጀመሪያው ሙከራዬ ከሐያ አምስት እርምጃ ር ቀት ላይ ያቆምኩትን አንድ ጠርሙስ አራት ጊዜ ሳትኩት። በጊዜው ተገኝቶ የነበረው ቀልደኛውና አሿፊው የሻምበል



t.me/OLDBOOKSPDF

አዛዦቻችን ‘ ጠርሙስ ጨክነህ መምታት እንዳልሆነልህ ማንም አይቷል ወዳጄ ’ አለኝ ! . . . . እናም ከመለማመድ በጭራሽ መቦዘን የለቦትም ። አለዚያ በአጭር ጊዜ ይረሱታል ። አንድ የማውቀው ጐበዝ ተኳሽ በየቀኑ ከምሳ በፊት ቢያንስ ሦስት ጊዜ እየተኮሰ እጁን ያለማምድ ነበር ። ከምግብ በፊት አንድ ብርጭቆ አረቄ የመጠጣት ሱስ እንዳለበት ሰው እርሱም እንዲዚሁ የመተኮስ ዐመል ነበረበት ።”
ልዑሉና ልዕልቲቱ በተፍታታ አንደበት ለመናገር በመቻሌ ደስ አላቸው ።

“ እስቲ ስለ ሰውዬው የተኩስ ችሎታ የበለጠ አብራራልኝ ” አለኝ ልዑሉ ።

“ እንዴት ብዬ ልንገርዎት ክቡር ሆይ ፣ አንዳንድ ጊዜ ዝንብ ግድግዳ ላይ ስታርፍ ያያል ። ነገሩ እያሣቅዎት ነው መሰለኝ ልዕልት ፣ ሆኖም የምናገረው ከምሬ ነው ። ታዲያ ዝምብዋን ያይና ‘ አንተ ኩሽካ ፣ ሽጉጤን ! ’ ይለዋል አገልጋዩን ። ኩሽካ የጐረሰ ሽጉጥ ያመጣለታል ። ቡም ! ዝንቧ ግድግዳው ላይ ትጨፈለቃለች ።”

“ ዕፁብ ድንቅ ! ” አለ ልዑሉ በመገረም ፣ “ ለመሆኑ ማን ይባላል ? ”

“ ሲልቪዮ ይባላል ክቡር ሆይ ! ”

“ ሲልቪዮ ! ” ብሎ ልዑሉ ዘሎ ተነሣ። “ሲልቪዮን ታውቀው ኖሯል ? ”

“ በሚገባ እንጂ ክቡር ሆይ ፣ እርሱና እኔ የልብ ወዳጆች ነበርን ፣ በክፍለ ጦራችን ተመድቦ በማገልገል ላይ ሳለ ። ሆኖም ባለፉት አምስት ዓመታት ስለእሱ አንድም የሰማሁት ነገር የለም ። ለካ ክቡርነትዎም ያውቁት ኖሮዋል ! ”



t.me/OLDBOOKSPDF

"እዎን ። ደህና አድርጌ ነው የማውቀው። ስለአንድ ነገ ር . . . ይኸ እንኳን ላይሆን ይችላል . . . በሕይወቴ ስለገ ጠመው አንድ አስገራሚ ድርጊት አጫውቶህም አያውቅ ?"

" አንድ ሴታሴት ጐረምሳ በጥፊ ያጮለውን ማለትዎ ነው ክቡር ሆይ ? "

" እዎ ፣ የጐረምሳውንስ ስም አልነገረህም ? "

" አይ ፣ አልነገረኝም ጌታዬ " አልኩ ። ከዚያም ሐቁ በድንገት ቦግ ብሎልኝ " ኧረገኝ ይቅርታ ጌታዬ . . . ይቅ ርታ ያድርጉልኝ ! አልገባኝም . . . እርስዎ ነበሩ እንዴ ? "

" እኔ ነበርኩ " አለ ልዑሉ በጥልቅ የሐዘን ስሜት ። " የጥይት ቀዳዳዎች የሚታዩበት ያ ሥዕል ለተገናኘንበት የመጨረሻ ጊዜ መታሰቢያዬ ነው ። "

" ኧረ ወዲያ ! " አለች ልዕልቲቱ ። " ስለሱ አታንሣብኝ ፣ እባክህ ። እስከ ምን ጊዜውም እንደሚዘገንነኝ ታውቃለህ . . . "

" ይገባኛል ፣ ግን ልንገረው " አለ ልዑሉ ። " ጓደኛውን ሲልቪዮን እንዴት እንዳዋረድኩበት ጠቅሶልኛልና ሲልቪዮም እኔን እንዴት እንደ ተበቀለኝ ይስማው ። "

ልዑሉ ባቀረበልኝ አንድ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ዐረፍ ብዬ ያን ልብ የሚያንጠለጥል ትረካውን በጥሞና አዳመጥሁ ።

" ከአምስት ዓመት በፊት ሚስት አገባሁ ። የመጀመሪያውን ወር ፣ የጫጉላ ጊዜዬን በዚች መንደር ውስጥ አሳለፍኩ ። እዚህ ቤት ውስጥ በሕይወቴ በጣም የሚያስደስቱና እጅግ የሚያሳዝኑ ጊዜያት አሳልፌያለሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በአንድ ምሽት ባለቤቴና እኔ አብረን በመጋለብ ላይ ነበርን ። የባለቤቴ ፈረስ ለገመ ። እደጋ ይደርስብኛል በማለት ስለ ሠጋች ልጓሙን ለእኔ አቀብላኝ በእግርዋ ወደ ቤት ተመለሰች ። እኔ ቀድሜያት ስደርስ በቅጥረ ግቢያችን ውስጥ የመጓጓዣ ሠረገላ አየሁ ። ስሙን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ከእኔ ጋር ጉዳይ እንዳለው ገልጾ ልዩ ክፍል ውስጥ እንደሚጠብቀኝ ተነገረኝ ። ወደ ክፍሉ ስገባ በዚያ ጨለማ ውስጥ አቧራ የለበሰና ጺሙን ያልተላጨ አንድ ሰው ልክ እዚች ምድጃ ፊት ለፊት ቆሞ አየሁ ። ወደሰው ዬው ቀረብ ብዬ በማየት ማንነቱን ለመለየት ሞከርኩ ። ‘አያውቁኝም እንዴ ልዑል ?’ አለኝ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ። እኔም “ ሲልቪዮ ! ” ብዬ ጮህኩ ። በወረረኝ ከፍተኛ የድንጋጤ ስሜት ጸጉሬ ሲቆም ይታወቀኛል ። ‘ ነኝ ! ዛሬ የመተኮሱ ተራ የኔ ስለሆነ የሽጉጤን ጥይት ለማራገፍ መጥ ቻለሁ ። ተዘጋጅተሃል ?’ አለኝ ። ሽጉጡን ደረቱ ኪስ ውስጥ ሻጥ አድርጎታል ። ዐሥራ ሁለት እርምጃ ቆጠርኩና እዚያች ጥግ ላይ ቆምኩ ። ባለቤቴ ከመመለስዋ በፊት በቶሎ እንዲተኩስ ለመንኩት ። እሱ ግን አልተጣደፈም ። መብራት እንዳበራ ጠየቀኝ ። ሻማዎች ተለኮሱለት ። በሩን መለስ ካደረግሁ በኋላ ፤ ማንም እንዳይገባ አስጠንቅቄ እን ዲተኩስ ደግሜ ጠየኩት ። ሽጉጡን መዞ አነጣጠረብኝ ። ሰኮንዶች ቆጠርኩ . . . . ስለ ባለቤቴ አሰብኩ . . . እጅግ በሚያሸብር ሁኔታ አንድ ደቂቃ ዐለፈ ። ሲልቪዮ እጁን አወ ረደ ። ‘ ሽጉጤ የጐረሰው የእንጆሪ ፍሬ ባለመሆኑ አዝና ለሁ ። ጥይቶች ደግሞ አይምሩም ። ይህ አድራጎቴ በእር ግጥ ተራ ግድያ እንጂ ፍልሚያ እንዳልሆነ ይሰማኛል ። መሣሪያ ባል ታጠቀ ሰው ላይ ማነጣጠርም አለመድኩምና” በማለት ሐሳቡን ቀየረ ። “ ይልቅስ እንደገና ‘ ሀ ’ ብለን እንጀምር — የመጀመሪያው ተኳሽ ማን እንደሚሆን ለመ ወሰን ዕጣ እንጣል ’ ሲል ንግግሩን ደመደመ ። ምድርና



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰማዩ ዞረብኝ ። መስማማቴም ትግ፤ አይለኝ . . . በመጨረሻ አንድ ሌላ ሽጉጥ አጐረሰን ። ሁለት ዕጣዎች ጠቀሰልንና ከዚህ ቀደም እኔ በጥይት በሸንቆርኩበት ቆቡ ውስጥ እስቀመጣቸው ። ያኔም እንደ ድሮው በመጀ መሪያ የመተኮሱ ዕጣ ለእኔ ወጣ ። ' ዕድለኛ ሆነህ ነው የተፈጠርከው ፤ ልዑል ' አለኝ ፈጽሞ በማይረ ሳኝ ፈገግታ ። ምን እንደነካኝና እንዴት እንዲያ ለማድረግ እንደ በቃሁ አይገባኝም . . . ተኮስኩና ያንን ሥዕል መታ ሁት " አለ ልዑል የጥይት ቀዳዳዎች የበሳሱትን ሥዕል በጣቱ እያመለከተኝ ። ጉንጮቹ ፍም መሰሉ ። በአንክሮ ስታዳምጥ የነበረችው ልዕልቲቷም የጨው ዓምድ መሰ ለች ። እኔም እድናቆቴን ላፍነው አልቻልኩም ።

" ተኮስኩ " አለ ልዑሉ በመቀጠል ። " ለእግዚር ምስጋና ይግባውና ሳትኩት ። ሲልቪዮ በዚያች ሰዓት እጅግ ያስፈራ ነበር ። በኔ ላይ ማነጣጠር ጀመረ ። ማሻ በድንገት በሩን በርግዳው ገባችና ጩኸትዋን እያቀለጠች ተጠመጠ መችብኝ ። እሷን በማየቴ ተረጋጋሁ ። ' አካሌዋ ' አልኳት፤ ' እየቀለድን ነውኮ ! አይዞሽ . . . ባይሆን ሒጂና እህል ውሃ ብጤ ቀምሰሽ ተመለሽ ። ከጥንት ወዳጁና የሥራ ጓዴ ከሆነው ከዚህ ጋር ላስተዋውቅሽ እሻለሁ ። ' ማሻ አላመ ነችኝም ። ' እስቲ ንገረኝ ፣ ባለቤቱ የሚለው እውነቱን ነው ? ' በማለት ወደአስፈሪው ሲልቪዮ ዞረች ። ' ሁለታ ችሁም እየቀለዳችሁ ነው ልበል ? እሱ እንኳ ሁል ጊዜ እንደ ቀለደ ነው እመቤት ሆይ ' በማለት መለሰ ላት ሲልቪዮ ። ' ከዚህም ቀደም በጥፊ የመታኝ ለቀልድ ነው ፤ ቆቤን በሽጉጥ ተኩሶ የበሳው ለቀልድ ነው ። አሁ ንም ተኩሶ የሳተኝ ለቀልድ ነው ። እኔም አሁን በተራዬ እንደ መቀለድ ይለኛል . . . ' እያለ በርስዋ ፊት በእኔ ላይ ማነጣጠሩን ቀጠለ ። ማሻ እግሩ ላይ ወደቀች ። ' በይ ተነሽ !



t.me/OLDBOOKSPDF

እታዋርጂኝ ! ’ ብዬ ሙሀኩባት በመቅበጥበጥ ። ‘ጊታው ፤ አንተም በዚህች ምስኪን ሴት ላይ ማፌዝህን አቁም ። ትተኩሳለህ ወይስ አትተኩስም ? አልኩት ሲልቪዮን በቁጣ ። ‘ አልተኩስም ’ በማለት መለሰልኝ ሲልቪዮ ፤ ‘ እንጀቴን አርሻለሁ ። በእኔ ላይ በቅድሚያ እንድትተኩስ ዕድል ሰጥቼህ እርብትብትነትህንና ወኔቢስነትህን አይቻል ሃለሁ ። ከእንግዲህ ይበቃኛል ። በሕይወት እስካለህ ድረስ እንደምታስታውሰኝ አምናለሁ ። ነገሩንም ለአንተው የሕሊና ፍርድ ትቼዋለሁ ’ ብሎኝ መንገድ ጀመረ ። ግን በሩ አካባቢ ቆም ካለ በኋላ ፤ እኔ በጥይት የመታሁትን ሥዕል አየት አድርጎ ምንም ያህል ሳያነጣጥርበት ተኩሶበት ተሰ ወረ ። ባለቤቴ አዞራትና ተዝለፍልፋ ወደቀች ። አሽከሮ ቹም ሊይዙት ስላልደፈሩ ፤ በድንጋጤ ባሉበት ደርቀው ቀሩ ። ሲልቪዮ ወደ በረንዳው ወጣ አለና ሠረገላውን አስቀ ርቦ ሸመጠጠ ፤ የዕለቱን ሁኔታ በውል ለመገንዘብ ከመ ቻሌ በፊት ። ”

ከዚያ በኋላ ልዑሉ ቃል አልተናገረም ። እንዲያ ልቤን አንጠልጥሎት የነበረውን ታሪክ መደምደሚያ በዚህ አኳኋን ደረስኩበት ። ባለታሪኩን ጀግና ሲልቪዮን ግን ዳግ መኛ አላገኘሁትም ። በአሌክዛንደር እስፒላንቲ ግርግር ጊዜ የተገንጣይ ጦር መሪ ሆኖ አስኩልየኒ በሚባለው ቦታ ላይ በተደረገው ጦርነት እንደ ሞተ ይነገራል ።


t.me/OLDBOOKSPDF

# የበረዶ ውሽንፍር

በ1811 ዓ. ም. መጨረሻ ገደማ ፣ በዚያ ከቶ ሊዘነጋን በማይችለው የታሪክ ወቅታችን ጋብሪላ ጋብሪሎቪች የሚ ባል ምስጉን ሰው ኔናራዶቮ በተባለው እርስቱ ላይ ይኖር ነበር ። በእንግዳ ተቀባይነቱና በደግነቱ ድፍን ወረዳው ያው ቀዋል ። ጐረቤቶቹም ለመብላት ፣ ለመጠጣትና ከባለቤቱ ጋር ካርታ ለመጫወት ወደቤቱ አዘውትረው ይመጣሉ ። አንዳንዶች ደግሞ የደም ገምቦ የሆነችውንና ዘለግ ያለች የዐሥራ ሰባት ዓመት ልጃቸውን ማሪያ ጋብሪሎቭናን ለማ የት ጐራ ይላሉ ። ተስማሚ የትዳር ጓደኛ እንደ ምትሆን በማመን ብዙዎች ሰዎች ለራሳቸው አለዚያም ለልጆቻቸው ለመዳር ይመኙዋት ነበር ።

የፈረንሣይን ልቦለድ ታሪኮች በማንበብ ያደገችው ማሪያ ጋብሪሎቭና በአንድ ወቅት በፍቅር ተጠመደች። የመ ረጠችው ፍቅረኛ በቂ ቅርስ የሌለው የጦር መኮንን ሲሆን የዓመት ፈቃዱን ወስዶ ከቤተሰቡ ዘንድ በዕረፍት ላይ የሚ ገኝ ነበር ። ወጣቱም በበኩሉ በማሪያ ፍቅር ተቃጥዷል ። የሁለቱን መዋደድና መቀራረብ የተገነዘቡት ወላጆችዋ ከእርሱ ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታቋርጥ አጥብቀው ከማስጠንቀቅ ወደ ኋላ አላሉም ። ወጣቱ ወደ ቤታቸው ሲመጣም በንቀት ዐይን እያዩት አቀባበላቸውን በማቀ ዝቀዝ ሊያራርቁቸው ሞከሩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ፍቅረኞቹ ግን ፣ ደብዳቤ መጻጻፋቸውን ቀጠሉ ። በየዕለቱም በአንድ ዋርካ ሥር ወይም በአቅራቢያቸው በሚገኝ እርጌ ጸሎት ቤት ውስጥ ይገናኙ ጀመር ። እዚያም ፍቅራቸው ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲኖር ቃል ኪዳን ይገባሉ ። በመፋቀራቸው ምክንያት እንደነርሱው ግፍ ስለደረሰባቸው ወጣቶች እያሰቡ ያዝናሉ ። ችግራቸውን ለመወጣት ልዩ ልዩ ዕቅዶች ሲነድፉና ስለዚሁ ጉዳይ ደብዳቤ ሲለዋወጡ ቆይተው ፣ የማይቀር ነውና በመጨረሻ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሱ ። " ተለያይተን ለመኖር አንችልም ። ጨካኝ ወላጆቻችን ለደስታችን ደንቃራ ስለሆኑብን ለምን ፈቃዳቸውን አንጥስም ? " የሚል ነበር ውሳኔያቸው ። በቅድሚያ ይህን ሐሳብ ያመነጨው ወጣቱ ሲሆን በፍቅር የጦፈችዋን ማሪያ ጋብሪሎቭናን እጅግ አድርጐ አስፈነደቃት ። ግን በመሐሉ ክረምት ገባና ግንኙነታቸውን አቋረጠው ። ሆኖም የሚጻጻፉት ደብዳቤ ይበልጥ እንዲነፋፈቁና እንዲተሳሰቡ አደረጋቸው ። ቭላዲሚር ኒኮላየቪች ለፍቅረኛው በሚጽፍላት በያንዳንዱ ደብዳቤ የእርሱ ብቻ እንድትሆንና በምስጢር እንድታገባው ፣ ተሸሽጋም ለጥቂት ጊዜ አብራው እንድትኖር አጥብቆ ይለምናታል ። ከዚያ በኋላም ወላጆችዋ ጫማ ላይ እንደሚወድቅ ፣ ቤተሰቦችዋም በሁለቱ ፍቅረኞች ጽኑ መተሳሰብና መጉላላት ልባቸው ተነክቶ " ልጆቻችን ፣ ኑ ፣ ክእቅፋችን ግቡ ! " ማለታቸው እንደማይቀር ያስረዳታል ።

ማሪያ ጋብሪሎቭና ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ብዙ ጊዜ ፈጀባት ። እያሌ የመኮብለያ ዘዴዎችን ሳትቀበል ቀረች ። በመጨረሻ ግን ተስማማች። በቀጠሮው ቀን ራቷን እንዳመማት አሳብባ በአራት ሰዓት እንዳትገኝና መኝታ ቤትዋ እንድትቆይ ታቀደ ። ሞግዚቷ የምስጢር ተካፋይዋ ሆነች ። በዕቅዱ መሠረት ፣ ሁለቱ ኮረዳዎች በጓሮ በር ወጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተው ወደ አትክልት ሥፍራው ካመሩ በኋላ፣ የሚጠብቃቸ ውን ሠረገላ ተሣፍረው ከኔናራዶቮ እስከ ዤርድሪኖ ድረስ ያለውን አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት በመንዝ በቀጥታ ቭላ ዲሚር እነርሱን ከሚጠብቅበት ቤተክርስቲያን እንደሚደ ርሱ ተመካከሩ ።

በዚያች ወሳኝ ቀን ዋዜማ ማሪያ ጋብሪሎቭና ሌሊቱን በሙሉ እንቅልፍ በዐይንዋ ሳይዞር አደረች ። ቁም ሣጥን ዋን ከፍታ ልብሶችዋን በአንድ ሻንጣ አጨቀች ። ለአንድ ሆደ ባሻ ወጣት ሴት ጓደኛዋ አንድ ረጅም ደብዳቤ ፣ አንድ ሌላ ደግሞ ለወላጆችዋ ጻፈች ። ልብ በሚፈነቅል ስሜት ወላጆችዋን ተሰናበተቻቸው ። ይህን እርምጃ የወሰደ ችው በኃይለኛ የፍቅር ሰንሰለት በመታሰርዋ መሆኑን አስ ረድታ እንደገና ተመልሳ መጥታ ውድ ወላጆችዋ ጫማ ላይ በመውደቅ ፈቃዳቸውን የምታገኝበትን ቀን እንደምትና ፍቅ ፣ ያች ቀንም በሕይወቷ ዋነኛዋ የደስታ ወቅት እንደ ምትሆን በደብዳቤው መደምደሚያ ላይ ገለጸች ። ሁለቱን ደብዳቤዎች በጥንድ ልቦች ሥዕል አስጊጣና በግርጌውም መግለጫ አስፍራበት ካሸገች በኋላ ሊነጋጋ አቅራቢያ አል ጋዋ ላይ ወደቀች ። ሸለብ ቢያደርጋትም በአስፈሪ ሕልም ከመባነን አልዳነችም ። አንድ ጊዜ ወደቤተ ክርስቲያን ለመሔድ ጋሪ ላይ ልትሳፈር ስትል ፣ አባትዋ ይዞ ሲያ ቆማትና በአሠቃቂ ፍጥነት በበረዶው ላይ እየጐተታት ወደ አንድ ጨለማ አዘቅት ውስጥ ሲያሽቀነጥራት ፣ እርስዋም በፍጥነት ቁልቁል ስትወርድ ፣ ልቧም ለመቆም ጥቂት ሲቀ ረው አየች ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ቭላዲሚር ፣ ፊቱ ጢስ የጠ ገበ ቋንጣ መስሎ ፣ ደሙን እያንዠቀዠቀ ሣር ላይ ተጋድሞ ታያት ። ከሞት አፋፍ ላይ ሆኖ በሚሰቀጥጥ ድምፅ ጋብቻ ቸው እንዲፋጠን የሚማፀናት መሰላት ። ሌሎችም የሚያስ በረግጉና ዝብርቅርቃቸው የወጣ ሕልሞች በአእምሮዋ ቦግ



t.me/OLDBOOKSPDF

እልም እያሉ ዐለፉ ። በመጨረሻም ፊትዋ ገርጥቶ እውነ ተኛ ራስ ምታት እያሰቃያት ተነሣች። እናትና አባትዋ ጭን ቀትዋን ተረዱ ። " ምን ሆንሽል ማሻ ? አመመሽ እንዴ ?" እያሉ ዘወትር የሚያቀርቡላት የደግነትና የመቆርቆር ጥያቄ ልቧን ነካው ። ሥጋታቸውን ለመቀነስ ስትል ደስተኛ ለመ ምሰል ብትሞክርም አልተሳካላትም ። እንደገና ምሽት መጣ ። በቤተሰብዋ ጉያ ውስጥ የምትቆይበትን የመጨረሻ ውን ቀኗን ማሰቡ ልቧን አሰቃየው ። በቅጡ መተንፈስ ተሣናት። በቅርብ የምታውቃቸውን ሰዎችና ቁሳቁሶች ሁሉ በሐሳብዋ ተሰናበተች ። እራት ቀረበ። ልቧ በኃይል ይመታ ጀመር ። በሚንቀጠቀጥ ድምፅ እራት አለመፈለግዋን አስ ታውቃ እናትና አባትዋን " ደህና እደሩ " አለች ። እንደ ተለመደው ስመው መረቅዋት። ለማልቀስ ቃጣት ፤ መኝታ ክፍልዋ እንደገባችም አንድ ምቹ ወንበር ላይ እንዘፍ ብላ እንባዋን አጐረፈችው ። ሐዘኗን ቻል አድርጋው እንባዋን እንድታደርቅ ሞግዚቷ ለመነቻት ። ሁሉም ነገር ተዘጋጅ ቷል ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ የወላጆችዋን ቤት ፣ የራስዋን የመኝታ ክፍልና ሰላም የሰፈነበትን የልጃገረድነት ሕይወ ትዋን እስከ ዘለዓለም ጥላ ልትሔድ ነው ። ውጭ የበረዶው ውሽንፍር ያፏጫል ። ነፋሱ ይጋረፋል ። የመስኮቶቹ መዝ ጊያዎች ከወዲያ ወዲህ ይላጋሉ ፤ ያንሲያጢጣሉ ፤ ሁሉም ነገር የሚያሠጋ ወይም የመቅሠፈት ምልክት መስሎ ታያት። ወዲያው መላው ቤተሰብ በእንቅልፍ ተዋጠ ። ማሻ ትከ ሻዋ ላይ ሻርፕዋን ጣል አድርጋ ፣ ሙቀት የሚሰጥ ካፖር ትዋን ደርባና የጌጥ ሙዳይዋን አንጠልጥላ በጓሮ በር ሹልክ አለች ፤ ሞግዚቷም ሁለት የተጠቀለሉ ጓዞች ይዛ እየተከተ ለቻት ወደ አትክልቱ ቦታ ሔዱ። የበረዶው ውሽንፍር ጋብ አላለም ። ነፋሱም ሴረኛቹን ላለማስኬድ ጥረት የሚያደ ርግ ይመስል ፊት ፊታቸውን ይገርፋቸው ጀመር ። እንደ ምንም ብለው ከአትክልቱ ዳርቻ ደረሱ ። ከዚያም አንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋሪ እየጠበቃቸው ነበር ። ቅዝቃዜው በሰውነታቸው ዘልቆ የገባቸው ፈረሶች አደብ ገዝተው ለመቆም አልቻሉም ። የቭላዲሚር ሠረገላ ነጂ የሚቁነጠነጡትን ፈረሶች ለማስ ታገሥ በጋሪ እስታንጋዎች ፊት ለፊት ሆኖ ላይና ታች ይንጎራደዳል ። ወጣትዋና ሞግዚቷ ጋሪው ላይእንዲወጡ፣ ሁለቱን የጓዝ ጥቅሎችና የጌጣጌጥ ሙዳይ አደላድለው እን ዲያስቀምጡም ረዳቸው ። ከዚያም ልጓሙን ሳብ ሲያደርግ ፈረሶቹ ዘልለው ወደፊት ተፈተለኩ ። እዚህ ላይ ባለታ ሪኳን ወጣት ለዕጣዋና ለሠረገላ ነጅው ጥበብ ትተን ወደ ወጣቱ ፍቅረኛዋ እንመለስ ።

ቭላዲሚር ቀኑን ሙሉ በሠረገላ ከቦታ ወደቦታ ሲዘ ዋወር ዋለ ። ማለዳ ዣድሪና ወደሚገኘው ቄስ ዘንድ ሔዶ የጠየቀውን እንዲፈጽምለት በብዙ ችግር ሊያግባባው ቻለ። ቀጥሎም ካካባቢው ባለ እርስቶች መካከል ለአባትነት የሚ ቆሙ ሰዎች ለመፈለግ ተሯሯጠ ። መጀመሪያ የጐበኘው ድራቪን የተባለ ከሥራ የተሰናበተ የዐርባ ዓመት መኰንን ነበር ። እርሱም ተደስቶ “ የቀድሞውን ዘመን የፈረስ ዘበ ኞች ጉበዝና ያስታውሰኛል ” በማለት ፈቃደኝነቱን ገለጸ ለት ። ሌሎቹን ሁለት ሽማግሌዎች ለማግኘት እንደማይቸ ገር ቭላዲሚር ዐውቋል ። ከድራቪን ጋር ምሳ በልተው ዐረፍ እንዳሉ ሪዙ እንደባላ የተቀሰረ ሽሚት የሚባል መሬት ቀያሽ ከቀበሌው የፖሊስ ሹም ልጅ ጋር ብቅ አለ ። ዕድሜው በዐሥራ ስድስት ዓመት ገደማ የሚገመት ይህ ወጣት የፈረሰኛ ጦር አባል የሆነው በቅርብ ጊዜ ነበር ። ሁሉም በቭላዲሚር ሐሳብ ከመስማማታቸውም በላይ ለእርሱ ሲሉ ሕይወታቸውን መሥዋዕት ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገለጹለት ። ቭላዲሚርም በጋለ ስሜት ሳማቸውና ዝግጅ ቱን ለማቀነባበር ወደቤቱ ሔደ ።

ከጨለመ ቆየት ብሏል ። ቭላዲሚር ለታማኝ አሽከሩ ቴሬሽካን አስፈላጊውን መመሪያ በመስጠት ከባለሦስት



t.me/OLDBOOKSPDF

ፈረስ ሠረገላው ጋር ወደኔና ራጸሽ ላከው ። ቭላዲሚርም ትንሹን ባላንድ ፈረስ ጋሪ አስጭኖ በሁለት ሰዓት ውስጥ ማሪያ ጋብሪሎቭና ወይምትመጣበት ዠድሪኖ ተጓዘ ። መን ገዱን ያውቀው ስለነበር ጉዞው ከሐያ ደቂቃ በላይ እንደማ ይወስድበት ተማምኗል ።

ቭላዲሚር ከመንደሩ ገና ወጣ ብሎ ቅልጥጥ ወዳለው ሜዳማ ገጠር ሲገባ ነፋስ በመቅስቀሱና የበረዶው ውሽን ፍር በማየሉ በዙሪያው ያለውን ማየት ቸገረው ። ከደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መንገዱ በበረዶ ተሸፈነ ። አካባቢው ደብዛዛና ብጫ በሆነ የበረዶ ጭጋግ ተዋጠ ። በመካከሉ ነጭ የበረዶ እንክብሎች እየተምዘገዘጉ ይወርዱ ጀመር ። ምድ ርና ሰማይ ተጋጠመ ። ቭላዲሚር በድንገት መንገዱን ሳተና ወደ አሰበው አቅጣጫ ተመልሶ ለመግባት ቢሞክርም ድካሙ ሁሉ ከንቱ ሆነ ። ፈረሱም ወደ አንድ ያልታወቀ ዓለም ገብቶ አንድ ጊዜ በረዶ ክምር ላይ እየወጣ ፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጉድጓድ ውስጥ እየወደቀ መዳከር ጀመረ ። ጋሪውም ደጋግሞ ተገለበጠበት ። ቭላዲሚር ከሁሉም ይልቅ ያሳሰ በው አቅጣጫውን መሳቱ ነበር ። ግማሽ ሰዓት ከተጓዘ በኋ ላም እንደ ፈራው ዠድሪኖ ሳይደርስ ቀረ ። ተስፋ ሳይቆርጥ ከዐሥር ደቂቃ በላይ ቢጓዝም ዠድሪኖን ማየት አልቻለም። ቭላዲሚር አያሌ የሚያንደረድሩ ተዳፋቶች በሚያቆራርጡት በዚያ አውላላ ሜዳ ላይ ጉዞውን ቀጠለ።የበረዶው ውሽን ፍር ገና ጋብ አላለም ። ሰማዩም ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ በከባድ ደመና ተሸፋፍኗል ። ፈረሱ ተዳከመበት ። ከደረሰበት ትኩሳት ለማምለጥ እስከ ወገቡ በረዶው ውስጥ ቢዘፈቅም ለመዳን አልቻለም ። ቭላዲሚር ላብ አጠመቀው ።

በመጨረሻም ያልሆነ አቅጣጫ ይዞ እንደሚጓዝ ተረዳ ። ልጓሙን አጥብቆ ይዞ የመንገዱን አቅጣጫ ለማስታወስ ሞከረ ። ወደ ቀኝ መታጠፍ እንደ ነበረበት ተገን


t.me/OLDBOOKSPDF

ዝቦ ያንን አቅጣጫ ያዘ ። ፈረሱ ግን መላወስ እንኳ ተሳነው ። ጉዞውን ከጀመረ ከአንድ ሰዓት በላይ ሆኖታል ። ከእንግዲህ ዣ ድሪና ብዙም አይርቅ የሚል ግምት አደረበት። ሆኖም ቢጓዝ ቢጓዝ ሜዳው አላልቅ አለው ። ከበረዶ ክምር በስተቀር ሌላ የሚታይ አልነበረም ። ጋሪው በየጊዜው ሲገለበጥ ቭላዲሚር ያለአንዳች መታከት ያቀናዋል ። ጊዜው ነጉዶ ። ቭላዲሚር ከባድ ጭንቀት ተሰማው ።

በኋላም የሆነ ጥቁር ነገር ከፊት ለፊቱ ብቅ አለለትና ቭላዲሚር ፈረሱን ወደዚያ አቅጣጫ መራው ። ቀረብ እያለ ሲሔድ አንድ ዘርዛራ ጫካ መሆኑን አየ ። ‘ ለእግዜር ምስጋና ይግባው ፣ ከእንግዲህ ተዳርሻለሁ ’ በማለት አሰበ ። ቀድሞ የሚያውቀውን መንገድ አገኛለሁ በሚል ተስፋና ዣድሪናም ከዘርዛራው ጫካ ማዶ መሆን አለበት በሚል ተስፋ ጫካውን ሰንጥቆ ዐለፈ ። በረዶው ቅጠሎቻቸውን በማርገፉ ቅርንጫፎቻቸው ብቻ በተንጨፈረሩ ዛፎች ሥር ጉዞውን ቀጠለ ። እዚያ ቦታ ነፋሱ እምብዛም ኀይለኛ አልነበረም ። መንገዱም ምቹ ነው ፤ ፈረሱም አዲስ ኃይል አገኘ ። የቭላዲሚርም መንፈስ ተረጋጋ ። ነገር ግን ፣ ቢጓዝ ቢጓዝ አሁንም ዣድሪኖ መድረስ አቃተው።ጫካው ማለቂያ የሌለው ሆነበት ። ብላዲሚር ከማያውቀው ዱር ውስጥ እንደገባ በተገነዘበ ጊዜ በከፍተኛ የድንጋጤ ስሜት ተርበተበተ ። ተስፋ ቆርጦ ፈረሱን ደጋግሞ ገረፈው።ምስኪኑ እንስሳም ለመጋለብ ሞከረ ። ነገር ግን ወዲያው ደከመ ። ያልታደለው ቭላዲሚር የተቻለውን ሁሉ ቢያደርግም ፈረሱ ጉልበቱ እየከዳው ይጐተት ጀመር ።

በመጨረሻም ቭላዲሚር ከጫካው ወጣ ። ዣድሪኖ ግን አይታይም ። እኩለ ሌሊት ገደማ የሆነ መሰለው ። እንባው በጉንጮቹ ላይ ጣምራ ጣምራ እየሆነ ወረደ ። ጉዞውም ዓላማቢስ ሆነበት ። ዓውሎ ነፋሱ ጋብ ብሏል ፤ ደመ


t.me/OLDBOOKSPDF

ናዎቹ ተበትነዋል ፤ ከፊት ለፊቱ በነጭ የበረዶ ግግር የተሸፈነ እውላላ ሜዳ ተደቅኗል ። ምሽቱ በመጠኑም ቢሆን የጠራ ነበር ። ትንሽ ራቅ ብሎ ትምችም ያሉ ቤቶች የሚገኙበት መንደር እየና ቭላዲሚር ወደ መንደሩ አመራ ። እንደደረሰም ከጋሪው ላይ ዱብ ብሎ ወደ መጀመሪያው ጐጆ መስኮት ሮጠና ነ ንኳኳ ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ተከፍቶለት አንድ ሽማግሌ ፡ ሽበቶ ጢሙን ብቅ አድርጐ ፡ "ምን ይፈልጋሉ ? " አለው ። " ዣድሪኖ ከዚህ ይርቃል ? " ሲል ጠየቀው ።

" አይ ፡ ብዙም አይርቅ ፡ ዐሥር ኪሎሜትር ያህል ቢሆን ነው ። " ቭላዲሚር ይህን መልስ ሲሰማ ጸጉሩን ነጨና የሞት ፍርድ እንደ ተቀበለ ሰው ነው በማለት በቆመበት ተገትሮ ቀረ ።

" ለመሆኑ ከየት ነው የመጡ ? " በማለት ጠየቀው ሽማግሌው ። ቭላዲሚር ጥያቄውን ለመመለስ አቅም አልነበረውም ። " ወደ ዣድሪኖ የሚወስደኝ ፈረስ ሊያገኙልኝ ይችላሉ ? " ሲል በተራው ጠየቀው ቭላድሚር ። " አየ ጉድ ! ፈረስ እንዳለው ሰው ቆጥረውኝ ! " አለ ገጠሬው ። " እሺ መንገዱን የሚያሳየኝ ሰውስ አያገኙልኝም ? የጠየቀውን እከፍላለሁ ። "

" ትንሽ ይቆዩ " አለው አዛውንቱ መስኮቱን እየዘጋ ፡ " ልጄን እልከውና መንገዱን ያሳይዎታል ።" ቭላዲሚር ጠበቀ ። ገና አንድ ደቂቃ እንኳ ሳይሞላ ቭላዲሚር መስኮቱን እንደገና ቆረቆረ ። መስኮቱ ተከፈተና የበፊቱ ጢም ብቅ አለበት ። " ምን ይፈልጋሉ ? " " የታለ ልጅዎ ? " " እየመጣ ነው ፡ ቡት ጫማውን እያጠለቀ ነው ። እስከዚያው ጐራ ይበሉና ይሙቅዎት ። " " ኧረ ግዴለም እግዜር ይስጥልኝ ። ይልቅ ልጅዎን ቶሎ ይላኩልኝ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

በሩ ሲጢጥ አለ ። ብትር የያዘ አንድ ወጣት ከቤት ወጥቶ ፊት ፊት በመሔድ መንገዱ በበረዶ ክምር ተሸፍኖ ስለነበር እንዳንዴም ቆም እያለ አቅጣጫውን በማሰብ ይመራው ጀመር ። “ ስንት ሰዓት ነው ? ” ሲል ቭላዲሚር ጠየቀው ። “ ከእንግዲህስ ወደ መንጋቱ ነው ” ብሎ መለሰ ልጁ ። ከዚያ በኋላ ቭላዲሚር ቃል አልተነፈሰም ። ገርድ ራኖ ሲደርሱ ዶሮ ጮሆ ሰማዩ የእህያ ሆድ መስሏል ። ካሰበው ቦታ ከቤተ ክርስቲያኑ ደረሰ ። በሮቹ ተዘግተዋል ። ቭላዲሚር መንገድ ለመራው ወጣት ገንዘብ ከፍሎ ካሰና በተው በኋላ ወደቄሱ መኖሪያ ቤት ሔደ ። በቅጥር ግቢው ውስጥ ባለሦስት ፈረስ ሠረገላ ? ልነበረም ። ከቶ እንዴት ያለጉድ ይሆን የጠበቀው ! እስቲ አሁን ደግሞ ወደ ተወዳጆቹ የኔናራዶቮ ሰዎች ተመልሰን ምን እንደ ተፈጠረ እንመልከት ። ለጊዜው ምንም እንግዳ ነገር አልተፈጠረም ።

አዛውንቱ ባልና ሚስት ማለዳ ተነሥተው ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍላቸው ሔዱ ። ጋቭሪላ ጋቭሪሎቪች የሌሊት ቆቡን ደፍቶ ስስ ኰቱን ለብሷል ። ፕራስኮቭያ ፒትሮቭና ረጅም የጠዋት ልብስ አጥልቃለች ። ሻይ ቀረበና ጋቭሪላ ጋቭሪሎቪች ልጁ ማሪያ ጋቭሪሎቭና ሌቱን እንዴት እንዳ ደደረች ለማስጠየቅ አንዷን ሠራተኛ ላከች ። ሠራተኛዋ ተመልሳ ወጣትዋ እመቤት ስትሰቃይ ብታድርም አሁን ሻል እንዳላትና በጥቂት ጊዜም ውስጥ ወደ እነርሱው እንደምትመጣ ገለጸችለት ። ወዲያውኑ በሩ ተከፈተና ማሪያ ጋቭሪሎቭና ገብታ አባትና እናትዋን እጅ ነሣች ።

“ ራስሽን ተሻለሽ ወይ ማሻ ? ” ብሎ ጠየቃት ጋቭሪላ ጋቭሪሎቪች ። “ ሻል ብሎኛል አባዬ ” በማለት መለሰችለት ማሻ ። ራስሽን ያሳመመሽ ምድጃው ሳይሆን አይቀርምኮ ማሻዬ ? ” አለቻት እናቷም ። “ አዎ ፤ ምናልባት እሱ ይሆናል እማዬ ” ነበር የማሻ መልስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀኑ እንደ ምንም አለፈ ። በዚያኑ ሌሊት ግን ማሻ በእ ርግጥ ታመመች ። ባቅራቢያው ከሚገኝ ከተማ ሐኪም ተፈልጐ እንዲመጣ ሰው ተላከ ። ሐኪሙ በማግሥቱ ወደ ማታ ገደማ ሲመጣ በሽተኛይቱ በመቃኀርት ላይ ነበረች። ሕክምናው እምብዛም አልረዳት ። ኃይለኛ ትኩሳት ለቅቆ ባት ምስኪንዋ ኮረዳ ለሁለት ሳምንታት በሞትና በሕይ ወት መካከል ሆና ስታጣጥር ቆየች ።

ቀደም ሲል ስለመኮብለል ስለ ተደረገው ሙከራ ከቤ ተሰቡ ማንም የሚያውቅ አልነበረም ። ያን ጊዜ የተጻፉት ደብዳቤዎች ተቃጥለዋል ። የማሻ ሞግዚትም፡ የጌታዋን ቁጣ በመፍራት አንድም ቃል ለማንም ሰው አልተነፈሰ ችም ። ቄሱ ፣ ለሽምግልና ታጭተው የነበሩት ከሥራ የተ ሰናበተው የቤታች መኰንን ፣ ሪዛሙ ቀላድ ጣይና ወጣቱ ባልደራስ ምስጢራቸውን ጠብቀዋል ።

ሠረገላ ነጂው ቲሬሽካም ፣ ለብ ባለው ጊዜ እንኳ ፣ አን ዲት ቃል አልተነፈሰም ። በዚህም አኳኋን ጉዳዩ ከስድስት በሚበልጡ ሴረኞች መሐል በምስጢር ተይዞ ቆየ ። ማሪያ ጋቭሪሎቭና ግን በቅዠት ዘከዘከችው ። ከአንደበትዋ የሚ ወጡት ቃላት ግልጽ ባይሆኑም ፣ ከአልጋዋ አጠገብ ፈጽሞ የማትለየት እናትዋ ልጅዋ በቭላዲሚር ኒኮላዮቪች ፍቅር ክፉኛ መነደፍዋንና ምናልባትም ለሕመም የዳረጋት ይኸው ሳይሆን እንዳልቀረ ለመገመት ቻለች። ባሏንና ጥቂት ጐረቤ ቶችዋን ስለ ጉዳዩ አማከረቻው የማሪያ ጋቭሪሎቭና ጣጣ ከፈጣሪ የተላከ መሆኑን ፣ ከዚያም ማምለጥ እንደማይቻል አመኑ ። ድህነትም ወንጀል አይደለምና ሰውም ከገንዘብ ጋር ሳይሆን ከሰብአዊ ፍጡር ጋር መኖር እንዳለበት ተስ ማሙ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

በመሐሉ ልጂቱ እያደር እየተሻላት ሔደ ። ቭላዲሚርም ወደ ጋቭሪላ ጋቭሪሎቪች ቤት ብቅ ሳይል ብዙ ጊዜ ሆነው ። የተለመደው ቀዝቃዛው አቀባበላቸው አስበርግጉታል ። ወ ለው አድረው ግን መልዕክተኛ ልከውበት ፤ ጋብቻቸውን ማጽደቃቸውን በማብሠር አስደሰቱት ። የማሪያን ቤተሰቦች ያስገረማቸው ላቀረቡለት ጥሪ ወፈፌ የሞነጫጨረው የመሰለ ደብዳቤ ወጣቱ መላኩ ነበር ። ዳግመኛ ደጃቸውን እንደማይረግጥ ፤ የመጨረሻ ተስፋው ሞት ብቻ እንደሆነና እንዲረሱት የሚማፀን ደብዳቤው ነበር የደረሳቸው ። ከጥቂት ቀናት በኋላም ወደ ነበረበት ጦር ክፍል መመለሱን ተረዱ ። ይህ የሆነው እ. ኤ. አ. በ1812 ነበር ።

በማገገም ላይ ለምትገኘው ማሻ ይህን መርዶ ደፍሮ የሚነግር በመጥፋቱ ሳትሰማ ለብዙ ጊዜ ቆየች ። ራስዋም ብትሆን ስለ ቭላዲሚር ጨርሶ እንዶሥታ እታውቅም ። ከጥቂት ወራት በኋላ ግን ፤ ቦሮዲኖ* ላይ በተደረገው ጦርነት በጽኑ ከቆሰሉትና የጀግንነት ሜዳይ ከተሸለሙት መካከል አንዱ እርሱ መሆኑን ከወጣው የስም ዝርዝር በተረዳች ጊዜ አዞሯት ወደቀች ። ትኩሳቷ ያገረሽባታል የሚል ሥጋትም ተፈጠረ ። ሆኖም ለእግዜር ምስጋና ይግባውና ድንጋጤዋ ክፉ ነገር ሳያስከትልባት ቀረ ።

ወዲያው አዲስ ሐዘን ደረሰባት ። አባትዋ መላ ሀብቱን አውርሿት በሞት ተለያት ። ይሁንና ያገኘችው ውርስ አላጽናናትም ። የምስኪን እናትዋ ፕራስኮቭያ ፔትሮቭና ሐዘን ተካፋይ እንደ መሆንዋ ፈጽሞ እንደማትለያት ቃል ገባችላት ። የአሳዛኝ ትዝታዋ ጉያ የሆነውን ኔናራዶቮን

---

* የቦሮዲኖ ጦርነት እ. ኤ. አ. በነሐሴ 26/ 1812 በሩሲያና በፈረንሣይ ወታደሮች መካከል ፤ ቦሮዲኖ በተባለችና ከሞስኮ 110 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኝ መንደር የተካሔደ ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ትተው በአንድ ሌላ መንደር በሚገኘው እርስታቸው ላይ ለመኖር ሔዱ ።

እዚህም ቢሆን ሸጋይቱንና ሀብታምዋን ወጣት ለማ ግባት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች ነበሩ ። ግን እርሷ ላንዳቸውም እንኳ ፊት አልሰጠችም ። እናትዋ አንዳንድ ጊዜ የንሮ ጓደኛዋን እንድትመርጥ ልታግባባት ብትሞክርም ፡ ማሪያ ጋቭሪሎቭና በእምቢታ ራስዋን በመነቅነቅ በሐሳብ ባሕር ትዋጣለች ። ቭላዲሚር በሕይወት የለም ። ፈረንሣዮች ሞስኮ በገቡበት ዋዜማ ከተማይቱ ውስጥ ሞቷል ። ማሻ የርሱን ትዝታ በታላቅ አክብሮትና ተመስጦ ይዛው ቆየች። እርሱን የሚያስታውሳትን ሁሉ ፤ ማለትም በአንድ ወቅት ያነበባቸውን መጻሕፍት ፡ ራሱ የሣላቸውን ሥዕሎች፣ ለእ ርስዋው የደረሰላትን የሙዚቃ ኖትና ግጥሞች ጠብቃ አኖረች ። ጉዳዩን ያወቁ የጐረቤት ሰዎች በሐሳበ ጽኑነትዋ እጅግ እየተደነቁ በልባዊ ሐዘን የምትቆራመደውን የዚችን ንጽሕት ወጣት ልብ ለመርታት የሚበቃውን ጐበዝ ለማየት በጉጉት መጠባበቅ ያዙ ።

ሁኔታው በእንዲህ እያለ ጦርነቱ በሩስያ ድል አድ ራጊነት ተፈጽሞ ወታደሮቻችን ተመለሱ ። ሕዝቡ ሊቀበ ላቸው ከየቤቱ ግልብጥ ብሎ ወጣ ። የእንኳን ደህና መጣ ችሁ ጥሪ አስተጋባ ። ዘፈኑና ዳንኪራው ቀለጠ ። ልጅ እግር ሆነው የዘመቱት ወታደሮች ጐልምሰው ተመለሱ ። ወታደሮቹ ፈረንሣይኛንና ጀርመንኛን በደባለቀ ቋንቋ በጋለ ስሜት ጭውውታቸውን ቀጠሉ ። የማይረሱ ቀናት ! የድልና የተስፋ ቀናት ! ሩሲያውያን ምን ያህል ፈንድቁ ! እንደገና የመገናኘቱ እንባ ምንኛ ጣፋጭ ነበር !

በዚያን ወቅት የሩሲያ ሴቶች ድርጊት በጣም የሚማ ርክ ነበር ። የተለመደው የዐይን አፋርነት ቀዝቃዛ ስሜታ ቸው ደብዛው ጠፋ ። ከድል አድራጊዎቹ ጋር በተገናኙ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጊዜ የተሰማቸው ደስታ ልብ የሚሰውር ነበር ። እልልታ ቸውን እያቀለጡ ሻሻቸውን ወደ ሰማይ አጓኑ ።

በዚያ ደማቅ ወቅት ማሪያ ጋብሪሎብና ከእናትዋ ጋር በአንድ አውራጃ ትኖር ነበርና ሁለቱ ዋና ከተሞች ለወታደሮቹ እንዴት ያለ የክብር አቀባበል እንዳደረጉላቸው አላየችም ። ሆኖም በየመንደሩም የነበረው የደስታ ስሜት የጋለ ነበር ። እንደዚህ ባሉ ሥፍራዎች አንድ የጦር መኰንን ብቅ ያለ እንደሆነ ፣ ማንኛዋም ኮረዳ ፍዳዋን ታያለች ።

ቀደም ብለን እንደ ገለጽነው ፣ ማሪያ ጋብሪሎብና ለማንኛቸውም ፊት ባትሰጥም ለትዳር የሚፈልጓት እያሌ ሰዎች ከዙሪያዋ አይጠፉም።የመንደሩ ሴቶች እንደሚሉት፣ አንድ የሚያስደነግጥ የገረጣ ፊት ያለው ፣ ኰሎኔል ብሩሚን የተባለ ቁስለኛ ባልደራስ በደረቱ ላይ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሜዳዩን አንገሮግጐ ቤትዋ ብቅ ሲል ሁሉም ማፈግፈግ ግድ ሆነባቸው ። ዕድሜው ወደ ሐያ ስድስት ዓመት ገደማ ሲሆን ፈቃድ ወስዶ ማሪያ ጋብሪሎብና መኖሪያ አጠገብ በሚገኘው እርስቱ ላይ የዕረፍት ጊዜውን በማሳለፍ ላይ ነበር ። ማሪያ ጋብሪሎብና ከሌሎቹ ይልቅ እርሱን በይበልጥ አቀረበችው ። አብርዋት በሚሆንበት ጊዜ የተቆራኛት ትካዜዋ እየተላቀቃት የደስታ ስሜት ይሰፍንባታል። የመዳራት ፍንጭ ባታሳየውም አኳኋንዋን ያጤነ ባለቅኔ ቢኖር ፣ “ ይህ ፍቅር ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ? ” ማለቱ ባልቀረ ነበር ።

በእርግጥም ብሩሚን ከመቅጽበት የሚማርክ ወጣት ነው ። ሴቶች የሚወዱት ዐይነተኛ ጠባይ ያለው ፣ ጨዋ ፣ በሙሉ ልቡ ሰውን የሚያከብርና የማያታክት ቀልደኛ ነው ። በማሪያ ጋብሪሎብና ፊት ያለመቅለስለስ በፍጹም ነጻነት ይገናናል ። ሆኖም ከእንደበትዋ የሚወጣውንና የም



t.me/OLDBOOKSPDF

ታደርገውን ነገር በሙሉ በሐሳቡና በዐይኖቹ ልቅም አድ ርጎ ይከታተላል ። ዝምተኛና ቁጥብ ቢመስልም በአንድ ወቅት ግን ቀበጥና አባጓዴለሽ እንደነበር ይወራል ። ግን ለማረያ ጋብሪሎብና ጉዳት አላስከተለም ። እንደ ብዙዎች ወጣት ሴቶች ቅብጡቱንና አጉል ድፍረቱን እርስዋም በይ ቅርታ ታልፈዋለች ።

ነገር ግን ከሁሉም ይልቅ የማወቅ ጉጉትዋን የቀሰቀ ሰባትና እጅግ ያስደነቃት ነገር የወጣቱ ባልደራስ ሽጋ ጠባይ ፣ ለዛ ያለው ጨዋታው ፣ አስገራሚውና የገረጣው ፊቱ ወይም በፋሻ የታጀለው ክንዱ ሳይሆን ቁጥብነቱ ነበር። ጥልቅ ስሜት ያሳደረችበት መሆኑን እርሷ ራሷ እንደተገ ነዘበች ሁሉ ፣ እርሱም በበኩሉ ከብስለቱና ከልምዱ በመነ ሣት ለእርሱ ያላት ፍቅር ከእንገት በላይ ያለመሆኑን እንደ ተረዳላት እልተጠራጠረችም ። ታዲያ እግርዋ ላይ ወድቆ “አፈቅርሻለሁ ” በማለት መውደዱን ያልገለጸላት ለምን ድነው ? ምንስ ከለከለው ? ከእውነተኛ ፍቅር የሚመ ነጭ ዐይን አፋርነት ነው ወይስ ኩራት ? ወይስ እንደ ልማዱ ሴት በእጁ ለማስገባት ሲል የሚያደርገው ብልጣብል ጥንት ? የማትፈታው እንቆቅልሽ ሆነባት ። በሐሳብዋ ብዙ ካወጣችና ካወረደች በኋላ፣የቁጥብነቱ ብቸኛ መንሥኤ ዐይነ አፋርነቱ ነው የሚል ውሳኔ ላይ ደርሳ ልታደፋፍረው ፣ ይበልጥ ልትስበውና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ረዳት መስላ ልትቀርበው አሰበች ። አንድ ፍጹም ያልታሰበ ነጥብ ለን ሥታበት ፍቅሩን የሚገልጽበትን ሰዓት በጉጉት ትጠባበቅ ጀመር ። ማንኛውም ምስጢር የሴትን ልብ ያስከነክንዋል ። የፈጠረችው ዘዴ ሠመረላት ። ብሩማን ልብ ውስጥ ገብታ ጥቋቁር ዐይኖቹ ከእርሷ ፊት ላይ እንዳይነቀሉ በማድረግ ፍቅሩን የሚገልጽላት ሰዓት እየተቃረበ የመጣ መሰለ ። ጐረቤቶቻቸው የጋብቻቸውን መቃረብ እንደማያውቁ ሲመ


t.me/OLDBOOKSPDF

ስሉ የዋህዋ እናቷ ፕራስኮቭያ ፔትሮቭና ግን ፡ ልጅዋ ተስማሚ የትዳር ጓደኛ ለማግኘት በመብቃትዋ እጅግ ደስ አላት ።

አንድ ቀን ኦርጊትዋ እንግዳ መቀበያ ክፍል ተቀምጣ ካርታ በመደርደር ላይ እያለች ብሩሚን ገብቶ ማሪያ ጋቭሪሎቭና የት እንዳለች ጠየቃት ። ኦርጊትዋም " አትክልት ውስጥ ነች ፡ እስቲ እዚያ ብቅ በል ። እኔ እዚህ እጠብቃችኋለሁ " አለችው ። ብሩሚን ወጥቶ እንደሔደ ኦርጊትዋ ካማተበች በኋላ በሐሳብዋ ' ምናልባት ዛሬ ይወስኑ ይሆናል ' አለች ።

ብሩሚን ማሪያ ጋቭሪሎቭናን ፡ ልክ በአንድ ልብወለድ ትረካ ውስጥ እንዳለች ገጸባሕርይ ነጭ ቀሚስ ለብሳና መጽሐፍ በእጅዋ ይዛ ፡ ከአንድ ዛፍ ሥር በሚገኝ ኩሬ አጠገብ ተቀምጣ አገኛት ። የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ማሪያ ጋቭሪሎቭና ሆን ብላ ጭውውቱን አቋረጠችው ፡ በመካከላቸው ያለው መተፋፈር እንዲባባስና ቁርጠኛ ውሳኔውን በድንገት እንዲገልጽላት በመመኘት ። በእርግጥም እንዳሰበችው ሆነላት ። ብሩሚን ሊያመልጥ አልቻለም ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲመኘው የነበረውንና የልቡን አፍረጥርጦ ሊነግራት የሚያስችለውን ይህን አጋጣሚ ተጠቀመበት ። ማሪያ ጋቭሪሎቭናም መጽሐፉን ዘግታ ያይኗን ቀብ ገርበብ በማድረግ ፈቃደኛነትዋን ገለጸችለት ።

" አፈቅርሻለሁ ፡ ነፍሴ እስክትወጣ እወድሻለሁ " አላት ብሩሚን ። ማሪያ ጋቭሪሎቭና ኃፍረት ተሰምቷት ፊትዋ ፍም ስለመሰለ አቀረቀረች ። " እንዳችም ይሉኝታ ሳይዘኝ ፡ አንቺን በየቀኑ የማየትና ድምፅሽን የመስማት አስደሳች ሱስ አድሮብኛል ። አሁን የሕይወቴን አቅጣጫ ለመለወጥ አልችልም ። ጊዜው አልፏል።ከእንግዲህ ወዲያ ትዝታሽ ፡ ውበትሽ ወደር የሌለው ቁመናሽ እስከ ምንጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውም የማይለየኝ የደስታና የሁቀቀን ምንጭ ሆኖብኛል ። ስለዚህ መፈጸም የሚገባኝ ነገር ግዴታ ይኖረኛል ። በመካከላችን የተጋረጠብንን እንቅፋት ማንሣት ቢከብደኝም ” ሲል ማርያ ጋብሪሎቭና ፈጥና አቋረጠችው ። “ እንቅፋቱ ለምን ጊዜም የሚኖር ነው ። ፈጽሞ ሚስትህ ለመሆን አልችልም ስትለው ” መቼ አጣሁት ብለሽ ነው ” ሲል መለሰላት ብሩሚን ለስለስ ባለ ድምፅ ። “ ከአሁን ቀደም ሌላ ሰው አፍቅረሽ እንደነበር ዐውቃለሁ ። ታዲያ ምን ይሆናል ፡ እሱ ሞቷል ። በሐዘን ላይ ከሀ ንሽ ይኸው ሦስት ዓመትሽ . . . ውድ ማሪያ ጋቭሪሎቭና ሆይ ! እባክሽን ተስፋዬን አታጨልሚብኝ ! . . . ምናልባትም እሺ በማለት ልታስደስችኝ ታስቢ ይሆናል . . . ቆይ . . . ትንፈ ታገሽኝ ፡ እባክሽን ዝም በይ ! እያሰቃየሽኝ ነው ። የኔ እንደምትሆኚም ነ ምናለሁ ። ታዲያ ምን ይሆናል ! ዕድለቢስ ሰው ነኝ ፡ አግብቻለሁ ! ”

ማሪያ ጋብሪሎቭና በመደነቅ ገርመም አደረገችው ። “አግብቻለሁ ” በማለት ቀጠለላት ብሩሚን ። “ ካገባሁ አራት ዓመት ሆኖኛል ፡ ግን ባለቤቴ ማን እንደ ሆነች ፡ የት እንዳለች ፡ ወደፊትም ላገኛት ፡ አላገኛት አላውቅም ። ” ምን አልክ ? ” አለች ማሪያ ጋብሪሎቭና ጮህ ብላ ። “የምትለኝ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ጉድ ነው ! በል ቀጥል . . . እኔም የማጫውትህ አለኝ ። ኧረ በፈጠረህ ቀጥል ! ” በማለት ጐተጐተችው ።

“ በ1812 መጀመሪያ ገደማ ” አለ ብሩሚን “ የጦር ሠፈራችን ወደ አለበት ወደ ቪልና በመጓጓዝ ላይ ነበርኩ። በጣም ሲመሽ አንድ ማረፊያ ጣቢያ ደረስኩና አዲስ ፈረሶች በአስቸኳይ እንዲጫኑልኝ አዘዝኩ ። አስከፊ የበረዶ ውሽንፍር በድንገት ስለተነሣ የጣቢያው ሹምና ሠረገላ ነጂዎቹ ፡ ማዕበሉ እስኪያልፍ ድረስ እንድቆይ መከ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሩኝ ። ምክራቸውን ብቀበለውም አንድ እንግዳ የሆነ የጭ ንቀት ስሜት ወረረኝ። እንዳጦ 'ሒድ ፡ ገሥግሥ' የሚል ነገር ተናነቀኝ ። የበረዶው ውሽንፍር ፈጽሞ ጋብ የማይል ሆነ ። ትዕግሥቴ ስለተሟጠጠ ፈረሶች እንዲጫኑልኝ በድ ጋሚ አዝገፔ በዚያ ማዕበል መካከል ጉዞዬን ጀመርኩ። ሠረ ገላ ነጂው መንገዱን በሦስት ኪሎሜትር ያህል ለማሳጠር እስቦ የወንዙን ሸለቆ በመከተል በአቋራጭ ተጓዘ ። መን ገዳችን በበረዶ ተሸፍኖ ስለነበር አቅጣጫ ስቶ ከማናው ቀው ሥፍራ ደረስን ። የበረዶው ማዕበል የማባራት ምል ክት አያሳይም ። አንድ ጭል ፡ ጭል የሚል መብራት ከሩቅ ስላየሁ ሠረገላ ነጂው ወደዚያው አቅጣጫ እንዲያመራ ነገ ርኩት ። ወደ አንድ መንደር ገባን ። ከእንጨት በተሠራው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መብራት ይበራል ። በሩ ክፍት ነው። በቅጥረ ግቢው ውስጥም ጥቂት ጋሪዎች ቆመው ነበር ። በረንዳው ላይ ወዲያና ወዲህ ይሉ ከነበሩት ሰዎች አንዱ 'ወደዚህ ! ወደዚህ !' ሲል ተጣራ ። ሠረገላ ነጂውን ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲያመራ አዘዝኩት ። ' ለመሆኑ ምን እንዲህ አዘገየህ ? ' በማለት ጠየቀኝ ፡ ያ የጠራኝ ሰው ። ' ሙሽራይቱ ተዳክማለች ። ቄሱም የሚያደርጉት ጠፍቷ ቸዋል ። እኛም ወደቤታችን ልንሔድ ምንም ያህል አልቀ ረን ነበር ። በል ቶሎ ግባ ! ' አለኝ ። ከሠረገላው ላይ ዘልዬ ዱብ አልኩና አንዳችም ቃል ሳልናገር ወደቤተክርስቲያኑ ገባሁ ። የሚበሩት ሻማዎች ጥቂት ስለነበሩ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያለው ብርሃን ደብዘዝ ብሏል ። አንዲት ኮረዳ አግ ዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጣለች ። ሌንዲት ሴት ግምባርዋን እያሸችላት ' ለእግዚር ምስጋና ይግባው ፡ በጊዜው መጥ ተሃል ፡ እመቤቴ ባንተ ምክንያት ልትሞት ምንም ያህል አልቀራትም ነበር ' አለችኝ ። ሌንድ ሽማግሌ ቄስም ወደ እኔ ቀረብ ብለው ' እንጀምራ ! ' አሉኝ ። እኔም ' ይጀምሩ፣ አባቴ ይጀምሩ' ስል በበድኔ መለስኩላቸው ። ልጂቱን ደጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግፊ.ው አቆምዋት ። እንከን የማይወጣላት ውብ ነች . . . መቼም ድርጊቱን ለመግለጽ የማ.ያዳግትና ምሕረት የማያ ሰጥ ቅብጠት ነው . . . መንበሩ ፊት ለፊት አጠገብዋ ቆምኩ። ቄሱ ቸኩለዋል። ሦስት ሰዎችና አንዲት ሴት ሙሽ ራይቱን ደግፈው ያዙዋት ። ባልና ሚስት ሆንን ። ' በሉ ተሳሳሙ ' አሉኝ ። ሚስቴ የገረጣውን ፊትዋን ወደእኔ ዘወር አደረገች። ልስማት ስል እሪታዋን ለቀቀችውና 'ኧረ ገኝ ! ኧረ እሱ አይደለም ! እሱ አይደለም ! ብላ ራስዋን ስታ ወደቀች ። ምስክሮቹም ማንነቴን ለማጣራት ከእግር እስ ከራሴ ትኩር ብለው አዩኝ ። እኔም ከቤተክርስቲያኑ ተንደ ርድሬ ወጣሁና ሠረገላዬ ውስጥ ገብቼ ' በል ንዳ ! ' ብዬ ጮህኩ ። ”

“ የፈጣሪ ያለህ ! ” አለች ማሪያ ጋቭሪሎቭና ። “እና ያቺ ያልታደለች ሚስትህ ማን እንደሆነች አታውቅም ማለት ነው ? ”

“ እንዴት ብዬ ? ” ሲል መለሰላት ብሩሚን ። “ያገ ባሁበትን ሥፍራ ስም እንኳ አላውቀውም ። የፈጸምኩት ጸያፍ ድርጊት ስላልከነከነኝ ከቤተክርስቲያኑ ተነሥተን ጉዞ እንደ ጀመርን በእንቅልፍ ተዋጥሁ። በማግሥቱ ጠዋት ሦስተኛው ማረፊያ ጣቢያ እስከ ደረስንበት ጊዜ ድረስ ከእንቅልፌ አልነቃሁም ። ያኔ አብሮኝ የነበረው አሽከሬ ዛሬ የለም ። ዘመቻ ላይ ሞቷል ። ያቺን በጭካኔ ያላገጥኩ ባትን ሴት ፈልጌ ለማግኘት ተስፋ የለኝም ። በእስዋ ላይ በፈጸምኩት ግፍ ይኸው እስከዛሬ ታስሬ እኖራለሁ ። ”

“ ወይ እግዚአብሔር ! ” አለች ማሪያ ጋቭሪሎቭና እጁን አፈፍ አድርጋ ፡ “ ለካስ አንተ ኖረሃላ ! እናም ልታ ስታውሰኝ አልቻልክም ! ”

ብሩሚን ፊቱ ይበልጥ ገርጥቶ . . . እግርዋ ላይ ወደቀ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው

የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው አድሪያን ፕሮኮሮቭ የመጨረሻውን የቤት ቁሳቁሱን በሬሳ ማጓጓገ ሠረገላ ላይ ጭኗል ። ሁለት ከሲታ ጌኛዎች ባስማኒያ ከተሰኘው መንገድ ተንሥተው እርሱ ከነቤተሰቡ ወደ ተዛወረበት ወደ ኒኪስቲካያ ጐዳና ለአራተኛ ጊዜ በማዝገም ላይ ናቸው ። አድሪያን ሱቁን ቆልፎ ቤቱ የሚከራይ ወይም የሚሸጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ደጃፉ ላይ ካንጠለጠለበት በኋላ ወደ አዲሱ መኖሪያው በእግሩ ሔደ ። እንደ ደረሰም ለብዙ ጊዜ ይመኘው የነበረውንና ከፍ ያለ ገንዘብ ከስክሶ የገዛውን ቤት ቢጫ ግድግዳ ሲመለከት የተመኘውን ያህል የሚያስደስት ሆኖ አላገኘውም ። ገና ያልተላመደውን ቅጥረ ግቢ አቋርጦ ወደ አዲሱ ቤቱ ገባ ሲል ዕቃዎቹ ተዝረክርከውና ተመሰቃቅለው በማየቱ ፡ ፀሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ ደንብና ሥርዓት የሰፈነባት የቀድሞዋ ደሳሳ ጐጆው ናፈቀችው ። ሁለቱን ሴት ልጆቹንና ገረዱን በስንፍናቸው ከገሠጻቸው በኋላ አብሯቸው ማስተካከል ጀመረ ። ቤቱ ወዲያውኑ መልክ አገኘ ።

የመላዕክት ምስሎች መደርደሪያው ፡ ቁም ሳጥኑ ፡ የብፌ ዕቃው ፡ ጠረጴዛው ፡ ድንክ አልጋውና ትልቁ ትልጋው በስተጀርባ ባለው ክፍል ውስጥ ሥፍራ ሥፍራቸውን ያዙ ። የተቀሩት ንብረቶቹ ፡ ማለትም በቀለምና በመጠን የተለያዩ የሬሳ ሣጥኖች ፡ የሐዘን ልብሶችና ባርኔጣዎች ፡ ካፖርቶችና ችቦዎች በወጥቤት እና በእንግዳ መቀበያው



t.me/OLDBOOKSPDF

ክፍል ተከመሩ ። በሁለት ጥቃቅን ክንፎቹ የሚበር ፡ ችቦ ዘቅዝቆ የያዘና እንደ ፍቅር አምላክ የሚታይ የድምቡሼ ልጅ ምስል ቢሮው መግቢያ ላይ እንጠልጥሎ ከግርጌውም "ልሙጥና ባለቀለም የሬሳ ሣጥኖች እንሸጣለን ፤ እናስጌጣለን ፡ እናከራያለን ፡ እንጠግናለን" የሚሉ ቃላትን አሠፈረ ። ሴት ልጆቹ ወደ መኝታ ክፍላቸው ሲገቡ አድሪያን ቤቱን ተዘዋውሮ ከቃኘ በኋላ ፡ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጦ ሻይ እንዲፈላለት አዘዘ ።

ሼክስፒርና ሰር ዎልተር ስኮት የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚዎችን እንደ ተካገሮች ሳይሆን ፡ በተቃራኒው እንደ ቀልደኞችና ጦልጧሎች እየሣሉ የሰዎችን ግንዛቤ እንደ ለወጡ ጥንቁቅ ንባቢ የሚያውቀው ነው ። ይህ ጽሑፍ ግን፡ሐቁን ተመርኩዞ የነርሱን ምሳሌነት ወደ ጐን በመተው በዚህ ታሪክ ውስጥ የቀረበውን የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚ ባሕርይ ከሚዘገንን ሥራው ጋር ለማዛመድ ይሞክራል ። አድሪያን ፕሮኮሮቭ ግምባሩ የማይፈታ ጨፍጋጋ ሰው ነው ። አፉ የሚከፈተው ዐልፎ ዐልፎ ሴት ልጆቹ ሥራ ፈተው አላፊ አግዳሚውን በመስኮት ሲመለከቱ ባያቸው ጊዜ ሲቆጣ ወይም የሬሣ ሣጥን ሊገዙ የሚመጡ ደንበኞችን ድሆች ይሁኑ ሀብታሞች ለአገልግሎቱ ከፍ ያለ ዋጋ ሲጠይቅ ነው ። አድሪያን መስኮቱ አጠገብ ተቀምጦ ለሰባተኛ ጊዜ በፍንጃል ያስቀዳውን ሻይ ፉት እያለ እንደ ተለመደው በሐዘንና በትካዜ ተውጦ ያስባል ። ባለፈው ሳምንት ፤ የአንድ በጡረታ የተገለለ ብርጋዴየር ሥርዓተ ቀብር በተፈጸመበት ዕለት ለቀስተኞቹን ያበሰበሰ ከባድ ዝናም ትዝ አለው ። በዚያ ሳቢያ የብዙ ሰዎች ልብስ ቀለሙ እንደለቀቀና የብዙዎቹም ባርኔጣ እንደ ተጨራመተ አስታወሰ ። ያ ዶፍ በመጋዘኑ ውስጥ ያከማቸውንም የከፈን ጨርቅ ስለ አበላሸበት ብዙ ወጭ እንደሚጠብቀው ገመተ ። ሆኖም



t.me/OLDBOOKSPDF

ያን ወጪውን ፤ ንጋዴ ባልዋ በሞተባትና እርሷው ራሷ እንድ ዓመት ሙሉ ከዛሬ ፣ ከነገ ትሞታለች ተብላ ለምት ጠበቀው በትሪያኪና ሥርዓተ ቀብር እንደሚመልሰው ተስፋ አደረገ ። ዳሩ ግን የትሪያኪና መኖሪያ ራቅ በማለቱ ፤ ምንም እንኳ ወራሾችዋ ቀደም ሲል ቃል ቢገቡለትም ፣ እርሱን ከመጥራት ይልቅ በአቅራቢያቸው ከሚገኝ ሌላ ሠው ጋር እንዳይዋዋሉ ሠጋ ።

በሩ በድንገት ሦስት ጊዜ ስለተቆረቆረ ከሐሳቡ ባንኖ፣ "ማነው ? " ሲል ጮኸ ። በሩ ተከፈተ ። የጀርመን ተወላጅ የሆነ አንድ ሰው ጉራ ብሎ ደስታ በተሞላበት መንፈስ ወደ ቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ተጠጋ ። ሲሰሙት በሚያሥቅ የተሰባበረ ሩሲያዊኛ ፡ "ይቅርታ ያድርጉልኝ ውድ ጐረቤቴ ፤ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፤ ሥራዎን አቋርጬ እንደ ሆነ ፡ ሳልውል ሳላድር ልተዋወቅዎት ፈልጌ ነው የመጣሁት ። ጫማ ሰፊ ነኝ ፡ ጐት ሊብ ሹልትዝ እባላለሁ ። የምኖረውም በመስኮትዎ በኩል በምትታየውና ከመንገድ ባሻገር በምትገኘው በዚያች ትንሽ ውስጥ ነው ። ነገ ሐዩ አምስተኛውን የጋብቻዬን ኢዮቤልዩ ስለማከብር ከልጆችዎ ጋር መጥተው ምሳ እንዲጋብዙልኝ ጠርቼዎታለሁ " አለው ። አድሪያን ጥሪውን በአክብሮት ተቀበለ ። የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ጫማ ሰፊውን እንዲቀመጥና ሻይ አብሮት እንዲጠጣ ጋበዘው ። ጐትሊብ ሹልትዝ በጠባዩ ግልጽ ሰው ስለነበር ልባዊ ጭውውት ጀመረ ። " ሥራ እንዴት ነው ?" በማለት ጠየቀው አድሪያንን ። " አይሄሄ ! " አለ ሹልትዝ። "የእኛው ገበያ እንደ ነገሩ ነው ። ቢሆንም ይመስገነው። በእርግጥ የእኔ ሸቀጥ እንዳንተው ቶሎ ቶሎ አይነካም ። በሕይወት ያለ ሰው ያለጫማ ሊሔድ ይችላል ። የሞተ ሰው ግን ያለሬሣ ሳጥን አይሆንለትም " አለው ። አድሪያንም በነገሩ በመስማማት " እርሱስ እውነት ነው " አለው ። "እን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዳልከው በሕይወት ያለ ሰው ጫማ የሚገዛበት ገንዘብ ካጣ ባዶ እግሩን መሔድ ይችላል ። አንተ ዘንድ የሚያመጣው ጉዳይ አይኖረውም ማለት ነው ። ግን የሞተ ሰው ለማኝ እንኳ ቢሆን የሬሳ ሳጥን ያስፈልገዋል ።" ጭውውታቸው በዚህ አኳኋን ለጥቂት ጊዜ ቀጠለ ። ከዚያም ጫማ ሰፊው ተነሥቶ የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው እንዳይቀርበት አደራ ካለው በኋላ ተሰናብቶት ወጣ ።

በማግሥቱ ልክ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚውና ሴት ልጆቹ ከአዲሱ ቤታቸው ቅጥረ ግቢ ወጥተው ወደ ጎረቤታቸው ዘንድ ሄዱ ። አድራያን ፕሮኮሮቭ የለበሰውን ልዩ ዐይነት የባህል ልብስ ለመግለጽ አልሞክርም ። ሆኖም ሁለቱ ልጆቹ ለክት ያስቀመጧቸውን ቢጫ ባርኔጣዎችና ቀያይ ነጠላ ጫማዎች ማድረጋቸውን ብጠቅስ ነገሬን እንዳጓተትሁ አይቆጠርብኝ ።

የጫማ ሰፊው ጐጆ በእንግዳ ጢም ብላለች ። አብዛኞቹም ከሚስቶቻቸውና ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር የመጡ የጀርመን ሞያተኞች ናቸው ። በግብዣው ላይ የተገኘው ሩሲያዊ ዩርኮ የሚባለው ፖሊስ ብቻ ሲሆን ምንም እንኳ ማዕረጉ ዝቅተኛ ቢሆን ጋባዡ ያቆላምጠው ነበር ። ዩርኮ እንደ ከተማዋ ፖስታ አዳይ ላለፉት ሐያ ኣምስት ዓመታት በታማኝነት ያገለገለ ሰው ነው ። እ. ኤ. አ. በ1812 ጠላት ያስነሣው የእሳት ቃጠሎ ጥንታዊቷን ከተማቸውን ሲያወድም የዩርኮም ባለቢጫ ቀለም የዘብ ቤት አብሮ ዐመድ ሆኖ ነበር ። ነገር ግን፣ ጠላት እንደ ተባረረ ወዲያውኑ ግራጫ ቀለም የተቀባችና በምሰሶዎች ያጌጠች ሌላ የዘብ ቤት በምትኩ ተሠርታለት ዩርኮ መኖሪያውን አንግቦ በዙሪያዋ ወደላይና ወደታች መንጐራደዱን እንደገና ቀጥሏል ። በኒኪስትኪ መግቢያ ላይ የሚኖሩትን አብዛኞቹን ጀርመኖች ያውቃቸዋል ፤ እንዲያውም አንዳንዶቹ እሑድ እሑድ ለጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

በቃ አብረውት ከዘብ ቤቱ ያድራሉ ። አድሪያንም የርኮ
ለከፉ ቀን ይሆነኛል በማለት ፈጥኖ ተዋወቃቸውና እንግዶቹ
ለማዕድ ሲቀርቡ ጎን ለጎን ተቀመጡ ። ባልና ሚስቱ እና
ሹልትዝ እንዲሁም የዐሥራ ሰባት ዓመት ሴት ልጃቸው
ሉትኪን የቀረበላቸውን ከእንግዶቹ ጋር ሆነው እየቀማ
መሱ አንዳንዴም ቁጭ ብድግ እያሉ በማሳለፍ ወጥ ቤቱን
በመርዳት ላይ ናቸው ። ቢራው ይመርዳል ። የርኮ ለአራት
ሰዎች የሚሆን ምግብ ጨረሰ ። አድሪያንም አልሰነፈም ።
ሴት ልጆቹ ጠባያቸውን አሳምረው ተቀምጠዋል ። የጋባ
ዦቹና የተጋባዦቹ ጭውውት እየደራ ሔደ ። ጋባዡ ሰውዬ
ለአንዳፍታ እንዲያዳምጡት በመጠየቅ የሻምፓኝ ጠር
ሙስ ቡሽ ከፍቶና ድምፁን ከፍ አድርጎ በሩሲያዊኛ ‘‘ለው
ዷቷ ባለቤቴ ለሊዊዚ መልካም ጤንነት ’’ አለ ። ሻምፓኙ
ተንሿሿ ። ጋባዡም ለጋ ውበት የተላበሰውን የአረጋዊት
ባለቤቱን ጉንጭ ሳም አደረገ ። ተጋባዦቹም ለተወዳጅቱ
ለሊዊዚ ጤንነት ያላቸውን መልካም ምኞት በጉላ ድምፅ
እየገለጹ መጠጣቸውን ጨለጡ ። ጋባዡም ሌላ ጠርሙስ
እየከፈተ ‘‘ ለተወዳጆቹ እንግዶቹ ጤንነት ’’ ሲል እንግ
ዶቹ መለኪያቸውን እያጋቡ ምስጋናቸውን ገለጹ ። ከዚህ
በኋላ ጽዋ ማንሣቱ በድምቀትና በፍጥነት ቀጠለ ። ለእያን
ዳንዱ ተጋባዥ ጤንነት ተጠጣ ። ለሞስኮ ከተማና ዐሥራ
ሁለት ለሚሆኑ የጀርመን ትናንሽ ከተሞች ጽዋቸውን
አነሡ ። ከዚያም በጥቅሉ ለተግባረ ዕድ ሙያ እና ለእያንዳ
ንዱ ሙያ በተናጠል ፣ እንዲሁም ለሞያተኞቹና ረዳቶቻ
ቸው ጽዋቸውን አጠነፈፉ ። አድሪያን ጠንቀቅ ብሎ ሲጠጣ
ቆየ ። በኋላ ግን ለብ ስላለው ጽዋውን አንሥቶ አንድ አደና
ጋሪ ሐሳብ ሰነዘረ ። ከዚያም ከተጋባዦቹ መካከል ሰውነቱ
ደልደል ያለ ዳቦ ጋጋሪ ፣ ‘‘ ለአሠሪዎቻችን መልካም ጤን
ነት ’’ ሲል በተጋነነ ስሜት ተናገረ ። ቀደም ሲል እንዳደረ
ጉት ሁሉ በአንድነትና በደስታ ጽዋቸውን አነሡለት ። ተጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ባገሮቹ እርስ በርሳቸው እጅ መነሣሣት ጀመሩ። ልብስ ሰፊው ጫማ ሰፊውን እጅ ነሣ ፡ ጫማ ሰሪው ልብስ ሰፊውን እጅ ነሣ ፡ ዳቦ ጋጋሪው ሁለቱንም እጅ ነሣ ። መላው ተጋባዥ ደግሞ ዳቦ ጋጋሪውን ፡ እንዲህ እያለ ቀጠለ ። በዚህ የሰላምታ ልውውጥ መኻል ዩርኮ ወደ ቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ዘወር ብሎ ጉላ ባለ ድምፅ " በል እንጂ ጉረቤቴ ፡ አንተም ለሙታኖችህ ጤንነት ጽዋህን አንሣ ! " አለው ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ከጣራ በላይ ሣቁ ። የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ግን ስለ ተቀየመ ፊቱን አጨማተረ ። ይህን ልብ ያለ አልነበረም ። እንግዶቹም መጠጡን መኮምኮም ቀጠሉ ። ከንጋቱ ሲነሡም የጸሎት ደወል ተሰማ ።

እንግዶቹ አምሽተውና አብዛኞዎቹም ሞቅ ብሏቸው ወደየቤታቸው ሔዱ ። ዩርኮ በጣም ስክሮ ስለነበር ግድን ግዱ ዳቦ ጋጋሪና ፊቱ ፍም የመሰለ አንድ መጽሐፍ ጠራዥ " ደግ መሥራት ለራስ ነው " በማለት ፖሊሱን በብብቱ እንጠልጥለው ከዘብ ቤቱ አደረሱት ። የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚውም ቆሽቱ አሮና ጥንብዝ ብሎ እቤቱ ገባ ። ለብቻውም ድምፁን ከፍ አድርጎ " እንዲያው ለመሆኑ የኔ ሥራ ከሌሎች በምን ያንሳል ? የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚ ነፍሰ ገዳይ አይደለም ፡ ሰዎችን የሚያሥቃቸው ከቶ ምን ይሆን ? እንዲህ የማንም መሳለቂያ ልሁን ? የቤት ምረቃ ግብዣ ላደርግላቸው አስቤ ነበር ። ባፍንጫዬ ይውጣ ! ፈጽሞ አላደርገውም ! የማገለግላቸውን እነዚያን ሙታን ብጋብዝ ይሻለኛል " በማለት ምሬቱን ገለጸ ።

" ኧረ ምነው የኔ ጌታ " አለች በጉ ጫማውን በማውለቅ ላይ የነበረችው ገረዱ ፡ " ምን እንደ ተናገሩ ዐውቀዋል ? ኧረ በስመአብ ብለው ያማትቡ ! ሙታንን ለቤት ምረቃ ሊጋብዙ ! እጅግ የሚዘገንን ነው ! "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው እጋብዛችዋለሁ ! ” በማለት ቀጠለ ኦድሪያን ። “ ያጠም ነገ ነዋ ! እንቺም ልጆቹም ነገ ማታ ግብዣው ላይ እንድትገኙ ። ያለኝን ሁሉ ትቋደሳላችሁ ።” ይህን እንደ ተናገረ አልጋው ውስጥ ገብቶ ወዲያው ያንኳርፍ ጀመር ።

አድሪያን ሲቀሰቀስ ውጭው ገና ጨለማ ነበር ። የሚ ቹ ነጋዴ ሚስት ትርዮኪና ሌሊቱን ሞታ አድራ ኖሮ ከአ ሽከርቿ አንዱ መርዶ ለአድሪያን ለመንገር በፈረስ ጋልቦ ከች አለ ። የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ለሰውየው የኦረቁ መጠሜ የሚሆን ዐሥር ኮፒክ ሸጉጦለትና በጥ ድፊያ ለባብሶ በሠረገላ ወደ ሚቿ ወደ ትርዮኪና ሠፈር ገሠ ገሠ። በሚችዋ ቤት ደጃፍ ላይ ፖሊሶች ቆመዋል ። ነጋዴ ዎችም ጥንብ እንዳዩ አሞራ ዙሪያቸውን ያንዣብባሉ ። ሬሣው በአንድ ጠረጴዛ ላይ ተዘርግቶአል።መልኳ ሰም ይመ ስላል ። ሆኖም ገና ስላልፈረሰ ቅርፁ አልተበላሸም ። ዘመድ አዝማድ ፣ ጐረቤቶችና የቤት አሽከሮች በዙሪያዋ ተሰባስበዋል። መስኮቶች በሙሉ ተከፋፍተዋል። ሻማዎች በርተዋል ። ቀሳውስቱም ጸሎተ ፍትሐት እያደረሱ ነበር።

አድሪያን ዘመናዊ ጥቁር ኮት ወደ ለበሰውና የሚችዋ የወንድም ልጅ ወደሆነው ወጣት ነጋዴ ቀረብ ብሎ የሬሣ ሣጥን ፣ ሻማና ሌላም የሥርዓት ቀብር ዕቃ ሁሉ በቶሎ እን ደሚያቀርብ አሳወቀው ። ወጣቱ ወራሽ ሳይሆን አልቀረም። በሒሳብ ተውጦ ስለነበር ከአንገት በላይ አመስግኖት በዋ ጋው እንደማይከራከርና ማንኛውንም ነገር ለእርሱው በእ ምነት እንደሚተወው ገለጸለት ። ልማድ ሆኖበታልና የቀ ብር ሥርዓት አስፈጻሚው ከዋጋ በላይ አንድ ኮፒክ እንኳ እንደማይጠይቅ ቃል ገብቶለት ዝግጁቱን ለማጠናቀቅ ወደ ቤቱ በሠረገላ ተመለሰ ። ቀኑን ሙሉ ከቤቱ ወደ ለቅሶው ቤት ሲመላለስ ዋለ ። ወደማታ ገደማ ሁሉም ነገር መልክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያ፱ ። ሡረገላ ነጂውን አስናብቶ ወደቤቱ በእግሩ ጉዞውን ቀጠለ ። ጨረቃ ደምቃ የወጣችበት ሌሊት ነበር ። የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው ሡፊሩ በደህና ደረሰ ። ከቤቱ ኦቅራ ቢያ የሚገኝ አንድ ቤተክርስቲያን አለፍ ሲል ዩርኮ አስቁ ሞት እርሱ መሆኑን እንዳረጋገጠ " በሰላም እደር ! " ብሎት አሳለፈው። በጣም መሽቶት ል። የቀብር ሥርዓት አስ ፈጻሚው ወደቤቱ ሲቃረብ በድንገት አንድ ሰው የአጥር ግቢውን በር ከፍቶ ጥልቅ ካለ በኋላ ወዲያው ሲሰወር ያየ መሰለው ። 'ማን ሊሆን ይችላል ?' አለ አድሪያን በሐ ሳቡ ። ማን ይሆን የሚፈልገኝ ? ሰርሳሪ ይሆን ? ምናልባት የእኔን ምስኪን ቂላቂሎች በሌሊት ከሚጐበኛቸው ጐረምሶች አንዱ ይሆን ? እንዲያውም ለእርዳታ እንዲደርስለት ወዳጁን ዩርኮን ሊጠራው ቃጥቶት ነበር ። ወዲያው ደግሞ አንድ ሌላ ሰው ከአጥር ግቢው በር ደርሶ ሊገባ ሲል አድሪያንን ሲጣደፍ በማየቱ ቆም አለና ለሰላምታ ያህል ባርኔጣውን ከራሱ ላይ ነ ነሣ ። ጥድፊያ ላይ ስለነበር አጥርቶ ሊያየው ባይችልም ሰውዬውን የሚያውቀው መሰለው ። " ሊጠይቁኝ የመጡ መሰለኝ ፡ ጐራ ይበሉዋ " አለው አድሪያን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለበት ። " ወዳጄ ሆይ ፡ ስለመ ስተንግዶው ብዙም አይጨነቁ ፡ እርስዎ ቀድመው ይግቡና ለእንግዶችዎ መንገዱን ይምሩዋቸው " አለ እንግዳው ሰውዬ በሰለለ ድምፅ ። አድሪያን በጣም ቸኩሎ ስለነበር ጊዜ አላጠፋም ። ሰውዬው እየተከተለው አጥር ግቢውን አቋርጦ ደረጃውን በመውጣት ወደበሩ አመራ ። አድሪያን በቤቱም ውስጥ ሰዎች የሚተራመሱ መሰለው ። " ምንድነው ነገሩ ? " አለ ለመግባት እየተጣደፈ ። ከዚያም ጉልበቱ ከዳው ። ቤቱ ሬሣ በሬሣ ሆኗል ። በመስኮት በኩል የገባው የጨረቃ ብርሃን የሬሳዎቹንየ ገረጡና የጠወለጉ ፊቶች፣ የተከፈቱ አፎች ፣ የፈዘዙና በከፊል የተዘጉ ዐይኖች ፣ የተመዘዙ የአፍንጫ ጫፎች ወለል አድርጐ ያሳያል። አድሪ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያን የቀብር ሥርዓታቸውን በመፈጸም የሸኛቸው ሰዎች መሆናቸውን ለይቶ ባወቀ ጊዜ ክፉኛ ደነገጠ ። ተከትሎት የገባውም ያ ቀደም ሲባል የተወሳው ዶፍ ይወርድ በነበረበት ቀን የተቀበረው ጄኔራል መሆኑን አስ ታወሰ ። ወንዶቹም ሴቶቹም በሙሉ በቀብር አስፈጻሚው ዙሪያ ተሰብስበው እጅ በመንሣት ሰላምታ አቀረቡለት ። አንድ በቅርብ ቀን ሞቶ በነጻ የተቀበረ መናጢ ድሃ ብቻ በተሸከመው ቡትቶ ያፈረ ይመስል ከአንድ ጥግ ራቅ ብሎ ተሸማቆ ቆሟል ። ከእርሱ በስተቀር ሁሉም ሽክ ብለ ዋል ። ሴቶቹ ባለጥብጣብ ባርኔጣ ደፍተዋል ፡ ሹማምንቱ ጢማቸውን ባይላጩም በማዕረግ ልብሶቻቸው አሸብር ቀዋል ። ነጋዴዎቹም በክት ልብሶቻቸው አምረዋል ። "ሰማህ ወይ ፕሮኮሮቭ" አለው ጄኔራሉ ። " ሁላችንም ከሙታን ዓለም የመጣነው ጥሪህን ለማክበር ስንል ነው ። ያልመጡት እምብዛም ተስፋ የሌላቸው ፡ ጨርሶ የበሰበሱ ትና ሥጋቸው ተላቅቆ በዐፅማቸው ብቻ የቀሩት ናቸው ። ከእነዚሁ ዐፅሞች መካከል ግን አንዱ ሊያይህ ጽኑ ፍላጐት ስላለው ለመምጣት አላንገራገረም " በማለት በእንግዶቹ ስም ንግግር አደረገ ። ወዲያው አንድ ትንሽ ዐፅም በሰዎቹ መሐል እየተሹለከለከ አድራያን ፊት ከቸች አለ ። ሥጋ አልባ ፊቱ አድሪያንን በፍቅር ስሜት ትክ ብሎ አየው ። በዐ ፅሙ ላይ ደማቅ አረንጓዴና ብጫ ቀለም ያላቸው ትልታ ዮችና እንዲሁም አንድ የነተበ የሐር እራፊ አጠና ላይ የተ ንጠለጠሉ ይመስላሉ ። ረጅም ቦት ጫማ ውስጥ የቆሙት ቅልጥሞቹ መጋጠሚያዎች ልክ ባዶ ሙቀጫ ውስጥ እንደ ሚያርፍ ዘነዘና ይንቋቋሉ ። " አታስታውሰኝም እንዴ ፕሮ ኮርቭ ? " አለው ዐፅሙ ። " የክብር ዘበኛ የሃምሳ አለቃ የነበርኩ ፓይት ፔትሮቪች ኩሪስኪን መሆኔን አታ ስታውስም ? ከነምልክቱ በ1799 የመጀመሪያውን የሬሣ ሣጥንህን የጥድ ነው በማለት አታልለህ የሸጥክልኝ ትዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይልህም ? ” ብሎ ዐፅሙ አቅፎት ሊስመው ሥጋ አልባ እጆቹን ቢዘረጋበት አድሪያን እምባርቆበት ባለ በሌለ ኃይሉ ገፈተረው ። ፓይተር ተንገዳግዶ ከመሬት ላይ ተዘረ ረና ወዲያ ውኑ ውልቅልቁ ወጥቶ የዐፅም ክምር ሆነ ። በዙ ሪያው የነበሩት ሙታን በሙሉ በቁጣ አጉረመረሙ ። የጓ ደኛቸው ክብር በመነካቱ ሁሉም ለመበቀል የዛቻ እና የስ ድብ መዓት እያወረዱ አድሪያንን ለመቀራመት አሰፈሰፉ። ምስኪኑ ጋባዥ ጩኸታቸው ስላደነቆረውና ባደረሱበት የበትር ውርጅብኝ ስለዛለ ፡ ሕሊናውን ስቶ በሚቹ የክብር ዘብ ሃምሳ አለቃ ዐፅም ላይ ወደቀ ።

ሌሊቱ አክትሞ የፀሐይዋ ውጋጋን የቀብር ሥርዓት አስፈጻሚው የተኛበትን አልጋ ወለል አድርጐ ያሳያል ። ዐይኑን ሲገልጥ ገረዱ በጣደችው ጀበና ሥር ያለውን እሳት ስትቆሰቁስ አየ ። አድሪያን ባለፈው ምሽት የተፈጸመውን ድርጊት በፍርሃት አስታወሰ ። ትርዩኪና ፡ ጀኔራሉ እና አምሳ አለቃ ኩሪልኪን በዐይነ ሕሊናው ይመላለሱበት ጀመር ። ገረዲቱ አስቀድማ ስለ ምሽቱ ሁኔታ እንድትነግ ረው በዝምታ ተጠባበቃት ።

“ ማታ እኮ በጣም አምሽተው ነው የተኙት ጌታ እን ድሪያስ ” አለችው እስኪንያ ልብሱን እያቀበለችው ። “ ልብስ ሰፊው ጐረቤታችን ሊጠይቅዎት መጥቶ ነበር። ዩርኮ፡ የፖሊሱ ተቆጣጣሪም ፡ የልደት ቀኑ መሆኑን ሊነግርዎ ብቅ ብሎ ነበር ። እርስዎ ግን በእንቅልፍ ተውጠው ስለ ነበር ልንቀሰቅስዎት አልፈለግንም ። ”

“ ለመሆኑ ከሟችዋ ትርዩኪና ቤት የመጣ ሰው ኖሯል ? ”

“ ከትርዩኪና ቤት ? ምን ሊፈጥር ? ሞተች እንዴ ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ምን ዐይነትዋ እንከፍ ነሽ በይ ? ለሥርዓት ቀብርዋ ዝግጅት ትናንት ስትረጅኝ አልነበረም ? ”

“ ጌታዬ አበዱ እንዴ ! ወይስ የትላንቱ የዞረ ድምር ገና አልለቀቀዎትም? ትናንት እንዳችም ቀብር አልነበረም ! ትናንት ቀኑን ሙሉ ሲፈነጥዙ አምሽተው አልጋዎ ላይ ወደቁ ። እስካሁን ድረስም እንቅልፍ ድብን አድርገው ወስደዎት ነበር ። የቅዳሴ ደወሉም አቋሚል ። ”

“ እንደዚያ ነው እንዴ ነገሩ ? ” አለ በእፎይታ ስሜት

“ ታዲያስ ፡ ነውና ” በማለት መለሰችለት ገረዲቱ ።

“ እንደዚያ ከሆነስ ሻዩን በቶሎ አድርሺና ልጆቹን ጥሪልኝ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

# የማረፊያ ጣቢያ ሹም

የማረፊያ ጣቢያውን ሹም የማያወግዝ ወይም ከእርሱ ጋር የማይነታረክ ሰው አይኖርም ። ቁጣው በሚገነፍልበት ወቅት የዚያን ሰው ግዴለሽነት ፡ ብልግናውንና ሰዓት አለማክበሩን አስመልክቶ ፋይዳቢስ ክሱን ለማስፈር ያን መከረኛ መዝገብ የማያገላብጥ ሰው የለም ። የማረፊያ ጣቢያ ሹሞችን በሰው አምሳል እንደ ተፈጠሩ ነውሬዎች፣ ከደረጃቸው ዝቅ እንደ ተደረጉ መሠሪ ባለሥልጣኖች ወይም እንደቀማኞች የማይቆጥራቸው ሰው አይገኝም ። ሆኖም ፣ በጣቢያ ሹሞች ቦታ ሆነን ያለባቸውን ችግር ጠለቅ ብለን በመመርመር ስለእነርሱ ትክክለኛ አስተያየታችንን ለመስጠት እንሞክር ። የማረፊያ ጣቢያ ሹም ምንድነው ? የማረፊያ ጣቢያ ሹም በበታች ሠራተኞች ዘንድ እንደ እውነተኛ ሰማዕት ሲቆጠር ፣ ባለሥልጣን ተብሎም ከበላዮቹ ቡጢና ጥፊ የሚያመልጥ ይመስላል ። ግን ሁልጊዜ አያድነውም ። የዚህን ጣጠኛ ሰው ሥራ አስቸጋሪነት የሚገነዘቡ በጣም ጥቂት ናቸው ። መተዳደሪያው የለየለት አድካሚ ሥራ ነው ። ሌትም ሆነ ቀን ዕረፍት የለውም ። መንገደኛው ሁሉ በአድካሚ ጉዞው ላይ የደረሰበትን ንዴት የሚወጣው በዚህ ሰው ላይ የስድብ ናዳ በማውረድ ነው ። አየሩ ከፍቷል ፣ መንገዱ ያስጠላል ፣ ሠረገላ ነጂው መንቻካ ነው ። ፈረሶቹ ልግመኞች ናቸው ። ታዲያ ይህ ሁሉ የሚሳበበው በጣቢያ ሹም ላይ ነው ። ያቺን የደሀ ጐጆውን የረገጠ መንገደኛ ሁሉ እንደ ደመኛ ያየ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዋል። ይህ ሰው ሳይታሰብ የሚመጣበትን እንግዳ ሁሉ በቶሎ ለመሸኘት ከቻለ ዕድለኛ ነው ። ለጉዞ የሚያስፈልጉት ፈረሶች ከሌሉትስ ? ይሄማ አያድርስ ነው ። የሚወርድበት እርግማንና ዛቻ አይጣል የሚያሰኝ ነውና ይህንኑ ፍራቻ ለማስወገድ በዝናምና በጭቃ ከአንድ ቤት ወደ ሌላው መዳ ከር ግድ ይሆንበታል ። የበረዶው ቅዝቃዜ አጥንት ሰብሮ በሚገባበት በጥር ወር እንኳ ከብስጩ መንገደኛ ጩኸትና ንዝንዝ ጥቂት ለማረፍ ሲል ወደ በረንዳው ወጣ ብሎ ይቆ ማል ። አንድ ጄኔራል ብቅ ሲልበት ይርበተበትና ለፖስታ ማመላለሻ የተመደበለትን ሠረገላ እንኳ፡አንድ ሌላ ሠረገላ ጨምሮለት ያስረክበዋል ። ጄኔራሉም እንዳችም የምስ ጋና ቃል ሳይጥልለት ተንዶቆ ሸው ይላል።ከአምስት ደቂቃ በኋላ ደግሞ የደወል ድምፅ ያንቃጭልና አንድ የመንግ ሥት መልዕክተኛ ከች ብሎ ትኩስ ጉልበት ያላቸው ፈረ ሶች የመጠየቂያ ቅጽ ጠረጴዛው ላይ ይወረውርለታል ። ይህን ሁሉ ስናመዛዝን ለጣቢያ ሹሙ ልባችን በቁጣ ሳይ ሆን በርኅራኄ ይሞላል። ስለዚህ ጉዳይ ጥቂት ጨመር አድ ርጌ ላወሳችሁ እፈልጋለሁ ። ባለፉት ሐያ ዓመታት ውስጥ በጉዞ መላውን ሩሲያ አዳርሻለሁ ። የማረፊያ ጣቢያዎች የተሠሩላቸውን መንገዶች ከሞላ ጐደል በሙሉ አውቃቸ ዋለሁ ። በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሠረገላ ነጂ ዎችም ጋር ተዋውቄያለሁ ። የማላውቀውና ያላነጋገርኩት የማረፊያ ጣቢያ ሹምም ኦይገኝም ። በጉዞዬ ላይ ስላስተ ዋልኳቸው አያሌ አስገራሚ ነገሮች በቅርብ ጊዜ እንደማሳ ትም ተስፋ ን ለኝ ። ለጊዜው ግን ፣ ስለጣቢያ ሹሞች የማነ ዛው ወሬ ሐሰትና መሠረተ ቢስ መሆኑን ለመግለጽ እወ ዳለሁ ። ስማቸው ያለአግባብ የሚጐድፈው የጣቢያ ሹሞች ባጠቃላይ እንግዳ ተቀባይ ፡ ተግባቢና ሰላማዊ ሰዎች ናቸው ። ከሚገባቸው በላይ ጥቅም ለማጋበስ አይፈልጉም። ስፍሳፎችም አይደሉም ። ከጨዋታቸው ከፍ ያለ ቁም ነገ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርና ትምህርት ለመጎብየት ስለማይቻል፡ብዙ መንገደኞች ቸል ማለታቸው ትልቅ ስሕተት ነው ። በበኩሌ ግን፡አንዳንድ ባለሥልጣኖች በሥራ ጉብኝት ወቅት ከሚያደርጉት ንግግር ይልቅ የጣቢያ ሹሞች ጨዋታ ይጥመኛል ።

መልካም ስም ካተረፉ የጣቢያ ሹሞች መካከል ወዳጆች ነበሩኝ ። ትዝታው ምንጊዜም ከልቤ የማይጠፋ አንድ የጣቢያ ሹም አለ ። ከዚያ ሹም ጋር የተገናኘ ነው በአንድ አጋጣሚ ነበር ። ለውድ አንባቢዬም ላወጋ የምሻውም የዚህን ሰው ታሪክ ነው ።

እ. አ. አ. በግንቦት ወር 1816 አንድ አውራጃ በምታቋርጥ መንገድ እጓዝ ነበር ። ያቺ መንገድ አሁን የለችም ። ማዕረጌ ዝቅተኛ እንደ መሆኑ የያዝኩት ገንዘብ የሁለት ፈረሶች ኪራይ ብቻ የሚሸፍንልኝ ነበር ። በዚህም ምክንያት የጣቢያ ሹሞች የሚያደርጉልኝ አቀባበል የግብር ይውጣ በመሆኑ በመብቴ ላገኘው የሚገባኝን ነገር ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ በማስገደድ ነበር የምወስደው ። ገና ጎፍላ ወጣትና ችኩል በመሆኔም አንዳንድ የማመላለሻ ሹሞች ከወራዳነታቸውና ከፈሪነታቸው የተነሣ ፡ ለእኔ የተዘጋጀውን ፈረስ ለሌላ ባለሥልጣን አሳልፈው ከሰጡብኝ በቀላሉ አንላቀቅም ነበር ። በገበታም ላይ የሚደርስብኝን ንቀት የተገነዘብኩት በአንድ ዕለት ከአንድ አገረ ገዥ ጋር በመመገብ ላይ ሳለሁ አንድ የማይረባ አሳላፊ እኔን ቸል ብሎ ለዚያ ሰው ሲያሽቃብጥ ባየሁ ጊዜ ነበር ። አሁን ግን፡ እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ተላምጃቸዋለሁ ። በነገራችን ላይ ፡ “ሰው እንደ ማዕረጉ” የሚለው ደንብ ተሽሮ “ ሰው እንደ አእምሮው ” በሚለው ቢተካ ምን ይውጠን ነበር ! ከፍ ያለ ብጥብጥ በተነሣ ! አሳላፊዎቹስ በቅድሚያ ማንን ያስተናግዱ ነበር ? ዳሩ ግን ይህን ወደጉን ልተውና ወደጀመርኩት ታሪክ ልመለስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀኑ ሞቃት ነው ። ቀድም ሲል የጠቀስኩላችሁ ማቢያ ለመድረስ ሦስት ኪሎሜትር ሲቀረኝ ፤ ማክፋት ጀመረ ። ጥቂት ቆይቶም የወረደው ዶፍ ከእግር እስከ ራሱ አበሰበሰኝ ። ከማቢያው እንደ ደረስኩ መጀመሪያ ልብሴን በቶሎ መቀየርና ከዚያም ሻይ ማዘዝ ነበረብኝ ። “ ሰማሽ ዲንያ ” አለ የማቢያው ሹም በፌዘኝት ድምፅ ፤ “ በይ የሻይ ጀበናውን ማጂ ፤ ሒደሽም ውተት ትምጪ ። ” ትእዛዙን እንደ ሰማች ዐሥራ አራት ዓመት ገደማ የሚሆናት አንዲት ወጣት ከጓዳ ወጥታ ወደ በረንዳው ገሠገሠች።ውበትዋ ልቤን ትር ክክ አደረገው ። “ ልጅዎ ናት እንዴ ? ” በማለት ጠየኩት የማቢያ ሹሙን ። “ አዎን ልጄ ናት ” ሲል መለሰልኝ በኩራት መንፈስ።ቀጥሎም “እንደ ሟች እናትዋ አስተዋይና ንቁ የሆነች ልጅ ነች ” አለ ። ወዲያው ማዘጋጃውንም መገልበጥ ጀመረ ። እኔም ቅልብጭ ባለውና በንጽሕና በተያዘው አነስተኛ መኖሪያ ቤት ውስጥ የተሰቀሉትንና ለቤቱ ድምቀት የሰጡትን ሥዕሎች መመልከት ጀመርኩ ። ሥዕሎቹ የሚያመለክቱት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ የአንድ አባካኝ ልጅ ታሪክ ነው ። በመጀመሪያው ሥዕል ላይ ቆብ የደፋና ኸርንግርግር ልብስ ያጠለቀ አንድ አረጋዊ ጉዞ ለመጀመር ልቡ የቆመውን ልጁን ሲሰናበተው ፤ ልጁም ያባቱን ምርቃትና አንድ ከረጢት ሙሉ ገንዘብ ሲቀበል ይታያል ። ሌላው ሥዕል የወጣቱን የዘማዊነት ጠባይ ፤ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በከንቱ ወዳጆችና በዐይን አውጣ ሴቶች ተከብቦ ያሳያል ። ቀጥሎ ያለው ሥዕል ደግሞ ያ አባካኝ ልጅ የተቀዳደደ ልብስ ለብሶ ፤ የተጨረማመተ ባርኔጣ ደፍቶ ዓሣማ ሲጠብቅና ምግባቸውን ሲካፈል ያመለክታል። በልጁ ፊት ላይ ጥልቅ የሐዘንና የመጸጸት ስሜት ይነበባል ። የመጨረሻው ሥዕል ፤ ልጁ ወደ አባቱ ሲመለስ የሚያሳይ ነው ። ያ አባቱም ያንኑ ቆቡን እንደ ደፋና የቀድሞውን ልብሱን እንደ ለበሰ ሊቀበለው ሮጦ ሲወጣ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

ብኩኑ ወጣትም አባቱ እግር ላይ ሲወድቅ ፡ ራቅ ብሎም አንድ ሰው ሙከት ሲባርክና የአባካኙ ልጅ ታላቅ ወንድም የፈንጠዝያው ምክንያት ምን እንደሆነ ሲጠይቀው ያሳያል። በዚያ ክፍል የተቀመጠው ጽጌረዳ ፡ በጥልፍ በተጌጠ መጋረጃ የተጋረደው አልጋና ባካባቢው የነበሩት ሌሎች ዕቃዎች . . . እነዚያ ነገሮች ሁሉ እስካሁን ድረስ ቁልጭ ብለው ይታዩኛል። ወደ ሃምሳ ዓመት የሚጠጋ ዕድሜ ያለው ያ ብርቱ ፡ ጤናማና ደስተኛ የቤቱ ጌታ ረጂም ኮረን ጓደኬ ኮቱን እንደ ለበሰና ቀለማቸው በደበዘዘ ጥብጣቦች ላይ ሦስት ሜዳዮቹን እንዳንዠረገገ ዛሬም በዐይኔ ይመጣል ።

ሒሳቡን ከፍዬ ያደረሰኝን ሠረገላ ነጂ እንዳሰናበትኩት ዱንያ ሻይ አቀረበችልኝ ። ያች ሲያይዋት የምታፈዝ ለግ ላጋ ልጅ ስለእርሷ የነበረኝን ስሜት ለመረዳት ጊዜ ኦል ፈጀባትም። እንደ ማፈር ብላ የሚያባብሉ ዐይኖችዋን ወደ መሬት ከምበል ብታደርጋቸውም ጨዋታ ጀመርኩኝ።በደ ንብ እንደምታውቀኝ ሁሉ እርስዋም ያላንዳች ኃፍረት አነጋገረችኝ ። አባትዋን አንድ መለኪያ አረቄ ጋበዝኩት። ለዱንያ ደግሞ አንድ ፊንጃል ሻይ ሰጠኋት ። የብዙ ዘመን ትውውቅ እንዳለን ሁሉ ሦስታችንም ጭውውታችንን እሚ ሚቅነው ።

ፈረሶቼ ተዘጋጁ ። እኔ ግን ከጣቢያው ሹምና ከልጂቱ መለየት ጠላሁ ። ቅር እያለኝ ተሰናብቻቸው ወደ በሩ ሳመራ፡ አባትዬው፡ "መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ" አለኝ ። ልጂቱም እስከ ሠረገላዬ ድረስ ሸኘችኝ ። በረንዳው ላይ ቆም ብዬ እንድትስማት ፈቃድዋን ጠየቅሁ ። ዱንያም ፈቀ ደችልኝ ። የሳምኳቸው ሴቶች ስፍር ቁጥር የላቸውም ። ሆኖም ይህችን ወጣት የሳምኩትን ያህል ያረካኝና ፈጽም የማይረሳ ትዝታ የጣለብኝ የለም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂት ዓመታት ካሳለፍኩ በኋላ፣በአንድ ወቅት በአጋጣሚ በዚያው መንገድ ተጉዤ እዚያው ሥፍራ ደረስኩ ። የጣቢያ ሹሙ ልጅ ትዝ አለችኝና በአንድ በኩል እርሷን የማግኘት ተስፋ ሲያስፈነድቀኝ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጣቢያ ሹም ከሥራ ተባሮ ይሆናል ፡ ዱንያም እስካሁን ሳታገባ አትቀርም ብዬ አሰብኩ ። ከሁለት እንዳቸው ሞተው ይሆናል የሚል ጭንቀትም በአእምሮዬ ላይ ብልጭ አለብኝና በሐዘንና በፍርሃት ስሜት እንደ ተዋጥኩ ወደማረፊያ ጣቢያው ተቃረብኩ ።

ፈረሶቼ ወደጣቢያ ሹሙ ትንሽ ጐጆ ተጠጉ ፡ ወደ ክፍሉ ጐራ እንዳልኩ የአባካኙን ልጅ ታሪክ ወደሚገልጹት ሥዕሎች አማተርኩ ። እንደ ተሰቀሉ ናቸው ። ጠረጴዛውና አልጋውም ቀድሞ ቦታቸው ላይ አሉ ። ከመስኮቱ ደፍ ላይ ግን አበባ የለም ። ክፍሉ ባጠቃላይ እርጅናና ጉስቁልና ይታይበታል ። የጣቢያ ሹሙ ከበግ ቆዳ የተሰፋ ካፖርት ብጤ አጥልቆ እንቅልፉን ይለጥጣል ። እኔ ስመጣ ባንኖ ተነሣ ። . . . በእርግጥም ያው ሰው ራሱ ነው ። ግን እንዴት አርጅቷል ! ማዘግየዬን እያገላበጠ ሳለ የሸበተውን ጸጉሩን ፡ ባልተላጨ ጉንጩ ላይ የተሸበሸበ ቆዳውንና የጉበጠ ትከሻውን ተመለከትኩ ። ያን የመሰለ ጐበዝ በሦስትና በአራት ዓመት ውስጥ ተለውጦ እንዲህ ዐቅመቢስና እርጅና የተጫጫነው ሰው ሆኖ መገኘቱ አስገረመኝ ። “ለመሆኑ አያውቁኝም እንዴ? እርስዎና እኔ እኮ የጥንት ወዳጆች ነን” አልኩት ። “ ሊሆን ይችላል ” አለኝ ፊቱን አጨፍግጎ ፡ “ በዚህ አላፊ አግዳሚው ብዙ ነው ። አያሌ መንገደኞች ወደዚህ ይመጣሉ ። ” “ ኧረ ለመሆኑ ልጅዎ ዱንያስ ደህና ነች ? ” በማለት ቀጠልኩ ። ሽማግሌው ግምባሩን ቋጥሮ “ እግዜር ይወቅ ” አለኝ ። “ አገባች እንዴ ?” ስል ጠየቅሁት ። ሽማግሌው ጥያቄዬን ያልሰማ በመምሰል



t.me/OLDBOOKSPDF

ማዘገየዬን ዝቅ ባለ ድምፅ ማንበቡን ቀጠለ ። እኔም መጠየ ቄን ተወት አድርጌ ሻይ አዘዝኩ ። የማወቅ ፍላጐቱ እየጐ ተጐተ ስላስቸገረኝ፣ምናልባት ንረቂ ምላሱን ያፍታታለት ይሆናል በሚል ተስፋ ጋበዝኩት ።

አልተሳሳትኩም ። ሽማግሌው ግብዣዬን ለመቀበል አላንገራገረም ። አረቂው ከመቅጸበት ከትካዜው አላቀ ቀው ። ሁለተኛውን መለኪያ አረቂ እንደ ከለበሰ ማን ነቱን ያስታወሰ በመምሰል መለፍለፍ ጀመረ ።

“ ለካስ ልጇን ዱንያን ያውቋት ኖሯል ? ” አለ በድን ገት ። “ እሷን የማያውቅ ከቶ የት ይገኛል ! አየ ዱንያ ! ኦይ የሷ ነገር ! እንደዔት ያለች ልጅ ነበረች ! እዚህ የሚመ ጣው ሁሉ የሚያደንቃት እንጂ ስምዋን በክፉ የሚያነሣ ማንም አልነበረም ። ቤት ወይዛዝርቱ እንኳ ልብስና የጆሮ ጉትቻ ሳይቀር ስጦታ ያበረክቱላት ነበር ። መኳንንቱም ምሳ ወይም እራት ያስፈለጋቸው በመምሰል እዝዘው የሚ ቆዩት እሷን በዐይናቸው እስኪጠግቧት ድረስ ለማየት ነበር ። በነገር ሊለክፈኝ ያቀበቀበ መንገደኛ እንኳ እሷን ሲያይ ቀዝቀዝ ይልና በአክብሮት ያነጋግረኛል ። ብነግር ዎት ላያምኑኝ ይችላሉ ። ነገር ግን፣ባለሥልጣኖች ራሳቸው ከእርስዋ ጋር ሲያወሩ ነበር የሚውሉ ። እሰኝታዬ ነበረች። ቤቴን የምታጸዳ ፡ ምግቤን የምታዘጋጅና ማንኛውንም ሥራ የምታከናውንልኝ እስዋ ነበረች ። ታዲያ እኔም ስለም ሳሳላት ዐይኔን ከእርስዋ ላይ ነቅዬ አላውቅም ፡ አይቼ አል ጠግባትም ነበር ። ዱንዬን እወዳት ፡ እንከባከባት ነበር ። እቀማጥላት ነበር ። ምን ይደረግ ! መዓትን በጸሎት ለማስ ወገድ አይቻል ። ከታዘዘው ለማምለጥ ትይቻል ” ካለኝ በኋላ ልብ የሚነካ ታሪኩን እንደሚከተለው አጫወተኝ።

ጊዜው ከሦስት ዓመት በፊት ፡ ወራቱም ክረምት ነበር ። አንድ ምሽት ላይ የሒሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ወረ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀት ላይ ሳስምርና ልጇም ጓዳ ተቀምጣ ልብስ ስትሰፋ እንድ ሁረገላ ከች አለ ። ቆብ የደፋ ፡ ረጅም የወታደር ካፖርት የለበሰና ወፍራም ያንገት ልብስ አንገቱ ላይ የጠመጠመ መንገደኛ ገብቶ ፈረሶች እንዲዘጋጁለት አዘዘ ። ፈረሶቹ በሙሉ ተሰማርተው ነበር ። መንገደኛው ይህን ሲሰማ እያምባረቀ አለንጋውን አወናጨፈ ። እንደዚህ ያለውን ድርጊት የተላመደችው ዱንያ ከጓዳ እየሮጠች መጥታ፡መንገደኛውን ረጋ ባለ እንደበት እህል ብጤ ይቀምስ እንደሆን በትሕትና ጠየቀችው ። የዱንያ ብቅ ማለት የተለመደውን መልካም ውጤት አስገኘ። የመንገደኛው ቁጣ ወዲያው ድምጥማጡ ጠፋ ። ፈረሶቹ እስኪመጡ ለመጠበቅ ተስማምቶ እራት አዘዘ ። የበግ ጸጉር ቆቡን ሲያወልቅ ፡ የጠመጠመውን ያንገት ልብሱን ሲፈታና ፡ ረጅም ካፖርቱን አውልቆ ሲታይ ቀጭን ፡ ጥቁር ሪዝ ያለውና ዘለግ ያለ ወጣት ፈረሰኛ ሆኖ ተገኘ ። ወጣቱ ፍጹም ቤተኛ ሆኖ ከጣቢያ ሹሙና ከልጁ ጋር በሣቅ በፈገግታ ይጨዋወት ጀመር ። እራት ቀረበ ። በእንዲህ እያሉ ፈረሶቹ ተመለሱ ። ፍሩሽካ እንኳን ሳይቀሙ ወዲያው በመንገደኛው እንዲጫኑ የጣቢያው ሹም ከአዘዘ በኋላ ፡ ወደ ቤት ተመልሶ ሲገባ ወጣቱ በጠና በመታመሙ እግዳሚው መቀመጫ ላይ ተጋድሞ አገኘው። ድካም ስለ ተሰማውና ራስ ምታት ስለያዘው ጉዞውን ለመቀጠል እንደተሳነው መንገደኛው ገለጸ ። ምንም ለማድረግ አልተቻለም ። የጣቢያ ሹሙ አልጋውን ለቀቀለት ። በማግሥቱ ስላልተሻለው ሐኪም እንዲመጣለት ተወሰነ ። ሕመሙም እየበረታበት ሔደ ።

ሐኪም እስከሚደርስለት ፡ ዱንያ በኮምጣጤ የራስ መሐረብ ራሱ ላይ ሽብ አድርጋለት አልጋው ጐን ተቀምጣ ልብስ ትሰፋለች ። የጣቢያ ሹሙ ሲኖር ሕመምተኛው እያቃሰተ አንድ ቃል አይተነፍስም ። ሆኖም ካጠገቡ የማ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትለየውን ዱንያን የሚጠጣ ነገር ስጭኝ እያለ ያለማቋረጥ ይወተውታታል ። እርሷም ካዘጋጀችው የሎሚ ጭማቂ በኩባያ እየቀዳች ትሁንም አሁንም ታቀርብለታለች ። ሕመምተኛው ከንፈሮቹን እያረጠበ ኩባያውን በመለሰላት ቁጥር በሚንቀጠቀጡ እጆቹ የዱንያን እጅ ጨበጥ በማድረግ ምስጋናውን ይገልጻል ። ሐኪሙ በምሳ ሰዓት ላይ መጣ ። የሕመምተኛውን ልብ ካዳመጠ በኋላ፡ የሚያስፈልገው ዕረፍት ብቻ እንደሆነና በሁለት ቀናት ውስጥ ጉዞውን ለመቀጠል እንደሚችል ገለጸለት ። ሐኪሙ ስላደረገለት ምርመራ መንገደኛው ሐያ አምስት ሩብል ከፍሎት እራት ጋበዘው ። ሐኪሙም ግብዣውን ተቀበለና አብረው እራታቸውን እየኮመኮሙ እንደ ጠርሙስ የወይን ጠጅም አጋቡ ።

ካንድ ቀን በኋላ መንገደኛው ሙሉ ጤንነቱ ተመለሰለት፡እጅግ ከመደሰቱ የተነሣ አንዴ ከዱንያ ፡ አንዴ ከጣቢያ ሹሙ ጋር እየቀለደ በፉጨት ሲያንጐራጉር ፡ ከመንገደኞች ጋር ሲጨዋወትና እንደ ረዳት ሆኖ ተቀያሪ ፈረስ መጠየቂያ ደብዳቤአቸውን መዝገብ ላይ ሲያሰፍር ዋለ ። በዚህ የተነሣ የጣቢያው ሹም በጣም ወደደው ። በሦስተኛው ቀን ጠዋት ለመሔድ ሲነሣም ከዚያ ፍልቅልቅ ሰው ጋር መለያየቱ ቅሬታ አሳደረበት ። ቀኑ እሑድ ስለነበር ዱንያ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሔድ ተዘጋጅታለች ። የመንገደኛው ሠረገላ ቀረበ ። ለተሰጠው የመኝታና የምግብ አገልግሎት ለጣቢያ ሹሙ ጠቀም ያለ ገንዘብ ሰጥቶ ተሰናበተው ። ዱንያንም ከተሰናበታት በኋላ ፡ ከመንደሩ ወጣ ብሎ ከሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ድረስ ሊያደርሳት ፈቃደኛነቱን ገለጸላት ። ዱንያ ነገሩ ግር አላት ። “ ምን አስፈራሽ ? ” አላት አባትዬው ፡ “ ክቡርነታቸው ተኩላ አይደሉ ፡ አይነክሱሽ ፡ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ያድርሱሽ ” በማለት አበረታታት ። ዱንያ ሠረገላው ላይ ወጥታ መንገ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደኛው ጕን ተቀመጠች ። ሠረገላ ነጂው ዘሎ ፊት መቀመጫው ላይ ቂጥ አለና አፏጨ ። ፈረሶቹም እያጋለቡ ነጐዱ።

ምስኪኑ የጣቢያ ሹም ልጁ ዱንያ ከመንገደኛው ጋር አብራ እንድትሔድ ለምን እንደ ፈቀደላት ፣ ልቡን ምን እንደሰወረው፣ ምን አዚም እንደ ያዘው ሊገባው አልቻለም ። ገና ግማሽ ሰዓት ሳይሆን ሆዱ ባባ፣ ጭንቀትና ሥጋት ስላሸነፈው ሊፈልጋት ወደቤተክርስቲያኑ ሔደ ። እንደ ደረሰም ሰዎች በመውጣት ላይ መሆናቸውን አየ ። ዱንያ ግን ቅጥር ግቢ ውስጥም ሆነ በረንዳው ላይ አልነበረችም ። ወደ ቤተክርስቲያኑ ዘው አለ ። ቄሰ ገበዙ ሻማዎቹን በማጥፋት ላይ ነበር ። ሁለት አሮጊቶች ጥግ ይዘው ይጸልያሉ ፤ ዱንያ ግን የለችም ። አባት መላ ቅጡ ቢጠፋው ከቄሰ ገበዙ ጋር ይተዋወቁ ነበርና ዱንያ ለጸሎት መጥታ እንደሆን ቢጠይቀው እንዳልነበረች ገለጸለት ። የጣቢያ ሹሙ በድኑን ወደ ቤቱ ተመለሰ ። የቀረው አንድ ነገር ብቻ ነበር ። ይኸውም ዱንያ ምናልባት ልጅነት አታሏት የክርስትና እናትዋ ወደምትኖርበት ቀጥሎ ወደአለው መንደር ሔዳ እንደሆን የሚለው ነው ። ከሠረገላው ጋር የላካቸውን ፈረሶች እስኪመለሱ ድረስ በጭንቀትና በጉጉት ሲጠባበቅ ቆየ ።ሆኖም በጊዜው አልተመለሱም ። ሠረገላ ነጂውም ሳይመለስ ውሎ ወደማታ ገደማ ሞቅ ብሎት ብቻውን እየጋለበ ብቅ አለ ። ይዞት የመጣውም አስደንጋጭ ወሬ ፡“ ዱንያም ከመንገደኛው ጋር ጭልጥ ብላለች ” የሚል ነበር ።

ሽማግሌው ሰውዬ ከደረሰበት ሐዘን ሊላቀቅ አልቻለም ። የዚያኑ ዕለት ማታም ያ ቀጣፊ ጐረምሳ ከአንድ ቀን በፊት ተጋድሞበት ከነበረው አልጋ ላይ ተኛ ። የጣቢያ ሹሙ ድርጊቱን ሁሉ እንደገና መለስ ብሎ ሲመለከተው ወጣቱ ታመምኩ ያለው የውሸቱን እንደሆነ ገመተ ። ምስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኪኑ ሽማግሌ ኃይለኛ የትኩሳት በሽታ ስላጣደፈው ወደ ሆስፒታል ተወሰደ ።

በእርሱ እግርም ሌላ የጣቢያው ሹም ለጊዜው ተተካ። ሽማግሌውን የሚያክመው ከዚህ ቀደም መንገደኛውን የመ ረመረው ዶክተር ሲሆን ፥ ያ ሰው ሙሉ ጤናማ እንደነበ ርና በዚያን ወቅት ሽር ማስቡን ቢያውቅም ያልተናገረው ይገርፈኛል ብሎ በመፍራት እንደነበር ለጣቢያ ሹሙ አረ ጋገጠለት ። ሐኪሙ የተናገረው እውነቱን ይሁን ወይም ብልጣ ብልጥ መሆኑ ባይታወቅም ፣ ምስኪኑን ሽማ ግሌ የጣት ቅንጣት ታህል ሊያጽናናው አልቻለም ። የጣ ቢያ ሹሙ ገና ከሕመሙ ሳያገግም ከዚያው መንደር ከሚ ገኘው የበላይ ኃላፊ የሁለት ወር ፈቃድ ተቀብሎ ዕቅዱን ለማንም ሳይገልጽ ልጁን ፍለጋ በእግሩ መንገድ ቀጠለ ።

ልጁን ያስኮበለለበት ካፒቴን ሚንስኪ ከእስምለን ስክ ወደ ፒተርስበርግ እንደ ተጓዘ ሲያልፍ ስሙን ካሠፈረ በት መዝገብ ላይ ሊያውቅ ቻለ ። ምንም እንኳ ዱንያ የተ ከተለችው በውዴታ ቢሆንም በጉዞዋ ላይ ያለማቋረጥ ታለ ቅስ እንደነበር ካጓጓዛቸው ሰው ተረድቷል ።

“ በእግዜር ፈቃድ ” ሲል አሰበ የጣቢያው ሹም “የጠ ፋቸውን የበግ ግልገሌን ወደቤቴ አመጣታለሁ ። ” በዚህ ሐሳብ ተንማሥቶ ፒተርስበርግ ከተማ ደረሰ ። ከዚያም ወደ ውስማይሎቭ ጦር ሰፈር አምርቶ በወታደርነቱ ጊዜ ወዳጁ ከነበረውና አሁን በጡረታ ከተገለለ አንድ መኰንን ቤት ዐረፈ ። ካፕቴን ሚንስኪ ፒተርስ በርግ እንደሚገኝና ከአ ንድ ከታወቀ ሆቴል እንዳረፈ ወዲያው ደረሰበት ። በግም ባር ለመገናኘትም ቆረጠ ።

በማግሥቱ ማለዳ ላይም ወደዚያው ሆቴል ሔዶ ከመ ግቢያው በር ላይ በመቆም አንድ ሽማግሌ ወታደር ሊያን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋግረው እንደሚፈልግ አስተናጋጇን እንዲነግርለት ለመ ነው ። አስተናጋጇም ከሚጠለውለው ቡት ጫማ ቀና ሳይል ሰውዬው መኝታ ውስጥ መሆኑንና ከአምስት ሰዓት በፊት ማንንም እንደማይቀበል ነገረው ። የጣቢያ ሹሙ ከዚያ ዘወር አለና በቀጠሮው ሰዓት ተመለሰ።ሚንስኪ ራሱ ፒጃማ እንደ ለበሰ ሊቀበለው ወጥቶ " ምን ልርዳህ ? " አለው ። የሽማግሌው ልብ በሐዘን ስሜት ቀለጠና ዐይኖቹ እንባ አቀ ረሩ ። እንደቡ፡ ስለ ተሳሰረበትም እየተርበተበተ ፡"ክቡር ጌታዬ ! ስለ እግዚአብሔር ብለው ፡ ክቡር ሆይ " አለው ። ሚንስኪ ገርመም አደረገው ፡ ፊቱ ፍም መሰለ ። እጁን ይ ዞም ወደልዩ ክፍሉ ካስገባው በኋላ በሩን ከውስጥ ቆለ ፈው ። " ክቡር ሆይ " በማለት ቀጠለ ሽማግሌው ፡ " የፈ ሰሰ ውሃ አይታፈስም ፡ ምስኪን ልጄን ዱንያን መልሰው ይስጡኝ ። እንደ የልብዎን አድርሰዋልና ጨርሰው አያስ ቀሩብኝ ። " " እንደ የተበላሸን ነገር መልሶ እንደነበረ ማድረግ ያዳግታል " አለ ወጣቱ በመጸጸት ስሜት ። " በእ ርግጥም በድየሃለሁ ። ይቅርታህን እጠይቃለሁ ። ነገር ግን ዱንያን ለቀን ጅብ ይዳርጋታል ብለህ አታስብ ። በደስታ እንደምትኖር ቃል እገባልሃለሁ ። ደግሞስ ካሁን ወዲያ ላንተ ምን ታደርግልሃለች ? ታፈቅረኛለች ። የጥንት ኑሮ ዋንም ረስታዋለች። የሆነውን ነገር አንተም ሆንክ እሷ ብት ረሱት ይበጃችኋል ።" ይህን ተናግሮ በጣቢያ ሹሙ እጅጌ ውስጥ የሆነ ነገር ወሽቆለት በሩን ከፈተለት ።

ሽማግሌው ሳያውቀው መንገዱን ቀጠለ ።

ሽማግሌው ረዘም ላለ ጊዜ የጨው ዐምድ መስሎ ቆመ ። በመጨረሻም ጥቅል ወረቀት እጅጌው ውስጥ እንዳለ ተገ ነዘበ ። መዞ ቢዘረጋው የተጣጠፈ ብዙ የአምስትና የዐሥር ሩብል ኖቶች ሆነው አገኛቸው ። እንደገና ዐይኖቹ ትኩስ እንባ አቀረሩ ፤ ከውርደት ስሜት የመነጨ እንባ ። ኖቶቹን ጨረማምቶ እንደኳስ ካድቦለቦለ በኋላ ወደመሬት አሽቀ



t.me/OLDBOOKSPDF

ንጥር በመጣል በተረከዙ ረጋግጦ መግገዱን ቀጠለ ። ጥቂት ራመድ አለና ቆም ብሎ ካሰላሰለ በኋላ ድርጊቱን ወደፊጸ መበት ሥፍራ ተመለሰ ። ነገር ግን፣ ኖቶቹ ከቦታቸው አል ነበሩም ። አንድ ሽክ ያለ ወጣት ሽማግሌውን ባየው ጊዜ ወደ አንድ ሠረገላ ሮጦ በፍጥነት በመሳፈር ፤ ጮክ ብሎ "በል ንዳ !" አለው ። የጣቢያ ሹሙም አሳዶ ለመያዝ አል ቃጣም ። ወደ መኖሪያ ጣቢያው ለመመለስ ቢያስብም፣ምስ ኪን ልጁን ዱንያን ለአንዳፍታም ቢሆን ሊያያት ስለ ፈለገ ከሁለት ቀን በኋላ ወደሚንስኪ ሆቴል ለዳግመኛ ጊዜ ሔደ። ሆኖም አስተናጋጁ ጌታው ማንንም ሰው እንደማይቀበል ኮስተር ብሎ ነገረውና ገፍትሮ ከአዳራሹ በማስወጣት በሩን እፊቱ ላይ ደረገመበት ። የጣቢያ ሹሙ ከውጭ ለጥቂት ጊዜ ከቆመ በኋላ ተጓዘ ።

የዚያን ዕለት ማታ ቤተክርስቲያን ጸሎት አድርሶ ወደ ረፈበት ቤት በእግሩ በመሔድ ላይ እያለ አንድ በጌጣጌጥ ያሸበረቀ ሠረገላ ባጠገቡ ሽው ሲል አየ ። የጣቢያ ሹሙ ባለሠረገላው ሚንስኪ መሆኑን ዐውቋል ። ሠረገላው ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ ፊት ለፊት እንደ ቆመ ሚንስኪ ወደ በረን ዳው ወጣ ። በጣቢያ ሹሙ አእምሮ አንድ ሐሳብ ተሠረጸ። ወደ ሠረገላው ቀረብ ብሎ፡"ወንድም ፤ ይህ ፈረስ የማነው? የሚንስኪ አይደለምን ? " በማለት ነጂውን ጠየቀው ። "አዎን ፤ የሚንስኪ ነው " አለው ሰውዬው ። " ግን ምን አስጠየቀዎ ?" . . . " ምክንያቱንማ እነግርሃለሁ ። ጌታህ አንድ ማስታወሻ ወደ ዱንያ እንድወስድ አዞኝ ነበር። ግን ይቺ ዱንያ የተባለች ሴት የምትኖርበትን ቦታ ዘንጋሁት" አለ የጣቢያ ሹሙ ። " እስዋም እዚሁ ፎቅ ላይ ነው የምት ኖር ። ሆኖም ወንድሜ ፤ መልእክቱን አዘግይተውታል ። ጌታዬ ራሳቸው አሁን አብረዋት ነው ያሉት ። " " አይ ፤ ግዴለም " አለ የጣቢያ ሹሙ ልቡ ታምቡር እየመታ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ቤቱን ስላሳየኸኝ አመሰግናለሁ ፤ ሆኖም ቃሌን ማክበር አለብኝ ” ሲል ተናግሮ ደረጃውን ወጣ ።

በሩ ተቆልፏል ። መጥሪያውን ደወለና በከባድ ጭን ቀት ተውጦ ለጥቂት ጊዜ ሲጠባበቅ ቆየ ። መክፈቻው ተን ቀጫቅጮ በሩ ሲከፈትለትም ፤ “ አቨዶትያ ሳምሶኖቭና እዚህ ነው የምትኖር ? ” ሲል ጠየቀ ።“አዎን ” በማለት መለሰች ወጣትዋ ገረድ ። ከዚያም “ ለምንነው የሚፈል ጓት ? ” አለችው ። የጣቢያ ሹሙ ግን፡መልስ ሳይሰጥ ወደ ውስጥ ስተት ብሎ ገባ። ገረዲቱ እየተከተለችው፡“ እረ ለመ ግባት አይችሉም ! ” አለችው ። ቀጥላም “ አቨዶትያ ሳም ሶኖቭ ከእንግዳ ጋር ነች ” አለችው ። ሆኖም የጣቢያው ሹም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ መንገዱን ቀጠለ ። ያለፈባቸው ሁለት ክፍሎች ጨለማ ናቸው ። ሦስተኛው ውስጥ ግን መብራት አለ ። ወደ ተከፈተው በር ተጠግቶ ቆሞ ዐይኖቹን ወደ ውስጥ ወረወረ ። ሚንስኪ በውድ ዕቃዎች በተመላው ክፍል ውስጥ ተቀምጦ በሐሳብ ተውጧል ። ዱንያም እጅግ በተዋበ ዘመናዊ ልብስ ተሽቀርቅራ በጐን ተቀምጠው ፈረስ እንደሚጋልቡ የእንግሊዝ ሴቶች ሚኒስኪ ከተቀመጠ በት ወንበር እጀታ ላይ ቁጥጥ ብላለች ። ሚንስኪን በሚ ስለመለሙት ዐይኖችዋ እየተመለከተችው ጥቁር ጸጉሩን በዕንቁ በተንቆጠቆጡት ጣቶችዋ ታፍተለትላለች ። አይ ምስኪኑ የጣቢያ ሹም ! ልጁ እንዲህ ተውባ አይቷት አያ ውቅም ነበርና በከፍተኛ አድናቆት ፈዝዞ ይመለከታት ጀመር ። “ ማን ነው ? ” ስትል ጮኸች ራስዋን ቀና ሳታደ ርግ ። ሽማግሌው ድምፁን አጥፍቶ ቆሟል ። ዱንያ መልስ ባለማግኘትዋ ቀና ብላ አየች ። . . . ወዲያው በድንጋጤ ጮኻ ምንጣፉ ላይ ተዘረረች ። ሚንስኪም ደንግጦ ሊያ ነሣት ተጣደፈ ። በሩ ላይ የተገተረውን ሽማግሌ ባየ ጊዜ ዱንያን ትቶ ቁጣ ሰውነቱን እያንቀጠቀጠው ወደ እርሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተንደረደረ ። “ ምንድነው የምትፈልገው ? ” አለው ጥር ሱን ነክሶ ። “በየሔድኩበት እንደሌባ የምትከታተለኝ ለም ንድነው ? ሕይወቴን ለማጥፋት ትፈልጋለህን ? በል ሒድ ውጣ ” ካለው በኋላ፡ትከሻታውን በጠንካራ እጁ ለቀም አድ ርጎ ወደ ደረጃው ገፍትሮ አስወጣው ።

ሽማግሌው ወደማረፊያው ተመልሶ ሔደ።ጓደኛው ነስ እንዲመሠርት ቢመክረውም፡የጣቢያ ሹሙ ስለጉዳዩ ካወጣ ካወረደ በኋላ ችላ በማለት ነገሩን እርግፍ አድርጎ ለመ ተው ወሰነ ። ከሁለት ቀን በኋላም ከፒተርስበርግ ወደራሱ መኖሪያ ተመልሶ ሥራውን እንደቀጠለ በዝርዝር ነገረኝ።

“ ከዱንያ ከተለየሁና ወሬም ከጠፋብኝ እነሆ አሁን ሦስት ዓመት ገደማ ሆኖኛል ” አለ ታሪኩን ሲደመድም ። “ ዛሬ በሕይወት መኖርዋን ወይም መሞትዋን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው ። በሰው ላይ ብዙ ነገር ሊደርስ ይችላል ። አመንዝራ መንገደኛ ያስኮበለላትና ቅምጡ ያደ ረጋት ፡ ከዚያም የከዳት የመጀመሪያዋም ፣ የመጨረሻዋም ሴት የእኔ ልጅ ብቻ አይደለችም ። በሐርና በከፋይ ልብስ ሲሽሞነሞኑ ቆይተው የኋላ፣ የኋላ ከመንገድ ወድቀው የሚ ቀሩ ወጣት ነሆለሎች ፒተርስበርግ ውስጥ በብዛት ይገ ኛሉ ። ዱንያም እንዲያ ስትሠቃይ እንዳንዴ በሐሳቤ ድቅን ትልብኝና ‘ ምነው ሞታ በተቀበረች ! ’ የሚል ክፉ ምኞት ያድርብኛል ” አለኝ ።

እነሆ የዚያ የሽማግሌው ወዳጄ የጣቢያ ሹም ታሪክ ይህ ነበር ፣ ያለማቋረጥ የሚወርድ እንባውን በኮቱ እጅጌ እያበሰና ሲቃ እየተንናቀው ያጫወተኝ ታሪክ። እንባውን ያዘነመለት የጠጣው አምስት መለኪያ አረቄ ቢሆንም ሽማ ግሌው እንጀቴን ነው የበላው ። ከተለየሁት በኋላ ትዝታው ለብዙ ጊዜ ከአእምሮዬ ሊጠፋ አልቻለም። ስለ ምስኪንዋ ዱንያም ማሰላሰሌን ለመተው ብዙ ጊዜ ወሰደብኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን በቅርቡ እንኳ በአንዲት መንደር ሳቋርጥ የጥ ንቱን ወዳጄን አስታወስኩት ። እርሱ ያስተዳድረው የነበ ረው ማረፊያ ጣቢያ አለመኖሩን ባውቅም፡“ ሽማግሌው ግን በሕይወት ይኖር ይሆን ? ” ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ የሚሰጠኝ ሰው አጣሁ ። ፊት የማውቃቸውን ስፍ ራዎች ለመጐብኘት ፍላጐት ስላደረብኝ፡ፈረሶች ተከራይቼ በመጀመሪያ ወደዚያቹ መንደር ገሠገሥኩ ።

የጸደይ ወራት ነበር ። ሰማዩ በግራጫ ደመና ተሸፍ ኗል ። ከታጨደው ማሳ አቅጣጫ የሚነፍሰው ቀዝቃዛ ነፋስ እግረ መንገዱን ከየዛፉ ላይ ያረገፈውን ቀይና ቢጫ ቅጠ ሎች እያዘለ ያልፋል ። ጀምበር ስታዘቀዝቅ ከዚያች መን ደር ደረስኩና ከጣቢያ ሹሙ ቤት ፊት ለፊት ቆምኩ ። ሰው ነትዋ ደልደል ያለ አንዲት ሴት ወደ በረንዳው፡ ምስኪንዋ ዱንያ ከዚህ ቀደም እኔን ከሳመችበት ሥፍራ ፡ ብቅ አለ ችና ሽማግሌው የጣቢያ ሹም ከአንድ ዓመት በፊት እንደ ሞተ ፡ ቤቱ የአንድ ቢራ ጠማቂ ንብረት መሆኑንና እርሷም የቢራ ጠማቂው ባለቤት እንደሆነች ገለጸችልኝ ። በከንቱ ያባከንኩት ጉዞና ያላግባብ ያጠፋሁት ሰባት ሩብል ቆጨኝ። “ ምን ሆኖ ነው የሞተው ? ” ስል የቢራ ጠማቂውን ሚስት ጠየቅኋት ። “ በመጠጥ ልቡ ፈንድቶ ነው የሞተው ጌታዬ ” አለችኝ ሴትዮይቱ ። “ የት ነው የተቀበረ ውስ ? ”

“ ከመንደሩ ወጣ ብሎ ከሚስቱ መቃብር ጐን ነው ።”

“ ወደሱ መቃብር ሊወስደኝ የሚችል ሰው ቢኖር ?”

“ እንዴታ ፡ አለ እንጂ ። ስማ አንተ ቫንካ ! በል ድመ ትዋን ለቀቅ አድርጋትና ለእኚህ ሰው የጣቢያ ሹሙን መቃብር አሳያቸው ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

. ቡትቶ ያጠለቀ ፡ ጸጉሩ የቀላና ዐይኑ የተንሸዋረረ ልጅ ሲሮጥ መጣና ወደ መንደሩ ጠርዝ እየመራ ወሰደኝ ።

" የጣቢያ ሹሙን ታውቀው ነበር ? " አልኩት እየሔድን ሳለን ።

" በጣም እንጂ ፡ ዐውቀው ነበር ፡ ፊሽካ መሥራት አስተምሮኛል ። ከመሸታ ቤት ሲወጣ ፡ እግዜር ነፍሱን ይማረውና ፡ በሩጫ እየተከተልን ' አባባ ! አባባ ! እስቲ አቾሎኒ ስጠን ' እያልን ስንለምነው የያዘውን ሁሉ አቾሎኒ ይሰጠን ነበር ። በየቀኑም ከእኛ ጋር ይጫወት ነበር ። "

" ለመሆኑ ሌሎች መንገደኞች ስለሱ ይጠይቃሉ ? "

" ዛሬ እንኳ እንደ ድሮው ብዙ መንገደኞች የሉም ፤ በጉዞ ላይ የሚሠየም ዳኛ ካልሆነ በቀር ዛሬ ዝር የሚል እንግዳ የለም ። ታዲያ እንዲያ ያለውም ዳኛ ቢሆን ለሙታን ደንታ የለውም ። ሆኖም በዚህ በጋ ወራት አንዲት ሴት ወደ ዘሮ መጥታ ስለሽማግሌው የጣቢያ ሹም ጠያይቃ መቃብሩን ጐብኝታለች ። "

" እንዴት ያለች ሴት ነበረች ? " ስል በጉጉት ጠየቅሁት ።

" አንዲት ውብ የሆነች ሴት ወዩዘሮ ነበረች " አለ ትንሹ ልጅ ። " የመጣችው በባለ ስድስት ፈረስ ሠረገላ ነበር ። ሦስት ልጆች ፡ አንድ ሞግዚትና አንድ ጥቁር ድንክ ውሻ አብረዋት ነበሩ ። የጣቢያ ሹሙ መሞቱን ባነገርናት ጊዜ አለቀሰችና ከመኪና መቃብሩ ድረሳ እስክትመለስ ድረስ ልጆችዋ ጸጥ ብለው እንዲጠብቋት አስጠንቅቃ ወደ ዚያው አመራች ። ከመቃብሩ ሥፍራ ላደርሳት ጠይቂያት ነበር ፤ " እራሴው መንገዱን ዐውቀዋለሁ " አለችኝና ባለ



t.me/OLDBOOKSPDF

አምስት ኮፒክ የብር መሐለቅ ሰጠችኝ ፤ እንዲያ ያለች ደግ ሴት ! ”

ይህን እያወጋን ከመካነ መቃብሩ ደረስን ። በታው ቀፋፊና ያልታጠረ ፤ የእንጨት መስቀሎች እዚያና እዚህ የተተከሉበትና ለፀሐይ ሐሩር የተጋለጠ ነበር ። እንደዚህ ያለ ቅስም የሚሰብር የመቃብር ሥፍራ በሕይወቴ አይቼ አላውቅም ።

ትንሹ ልጅ አንድ አሸዋ ክምር ላይ ዘሎ ወጣና “የጣቢያ ሹሙ መቃብር ይሄ ነው ” አለኝ ። ከክምሩ ላይ ከነሐስ የተሠራ የመላዕክት ምስል ያለበት ጥቁር መስቀል ተተክሏል ።

“ ታዲያ ሴትየይቱ የመጣችው እዚህ ነበረ ? ” ስል ጠየቅሁት ።

“ አዎን፣እዚሁ ነበር የመጣችው”ሲል መለሰ ሻንካ - “ ከሩቅ ሆኜ እመለከታት ነበር ። እዚህ ጋደም ብላ ለረጅም ጊዜ ቆየች ። ከዚያም ወደ መንደር ተመልሳ ፤ አንድ ቄስ አስጠርታ ጥቂት ገንዘብ ሰጠችው ፣ ለእኔም የባለ አምስት ኮፒክ የብር መሐለቅ ሰጥታኝ ነበር ። እንዲያ ያለች ደግ ሴት ! ”

እኔም በበኩሌ ለዚሁ ሕፃን የአምስት ኮፒክ መሐለቅ ሰጠሁት ። ያን ከሰጣሁ በኋላ ያደረግሁት ጉዞም ሆነ ያወጣሁት ሰባት ሩብል አልቆጨኝም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የካፒቴኑ ሴት ልጅ

## ምዕራፍ አንድ

### ሃምሳ አለቃው የክብር ዘብ

"ታጭቶ ነበርኮ ለመኮንንነት !"
"የተራ ወቴን ቁርስ ይቅመስ ምናለበት !"
"እዎ ፡ ልክ ብለዋል ፤ ይየዋ ልፋቱን ።"
"በነገራችን ላይ . . . ያውቁታል አባቱን"
('ጉረኛው' ከሚለው የያኮቭ ክኒዚኒን
( 1742—1791) ኮሜዲ የተወሰደ ።)

አባቴ አንድሬ ' ፒትሮቪች ግሪኔቭ፣ በወጣትነት ዘመኑ በጦር መኰንንነት ሲያገለግል ቆይቶ ፣ ከሥራው በጡረታ ተገለለ ። ከዚያም ሲምቢርበክ ከሚገኘው እርስቱ ላይ መኖር እንደ ጀመረ በዚያ ነዋሪ የሆነና አግኝቶ ያጣ የአንድ ሁነኛ ሰው ልጅ የሆነችውን አቭዶቲያ ባዚልዮቭናን አገባ። ዘጠኝ ልጆች ተወለዱ ። ወንድሞቼና እህቶቹ በሙሉ በሕፃንነታቸው ተቀጠፉ ።

ገና ከእናቴ ማሕፀን ሳልወጣ ነበር የቅርብ ዘመዳችን በሆነው የክብር ዘብ ሻምበል አዛዥ ልዑል ቢ—መልካም ፈቃድ በሃምሳ አልቅና ማዕረግ ታጭቼ ሲሞኖቭ ክፍለ


t.me/OLDBOOKSPDF

ጦር የተመደብኩት ። እናቴ ሴት ልጅ ብትወልድና የወላጆቼ ምኞት ቢጨናገፍ ኖሮ አባቴ ያንን አዲስ ቅጥር ሃምሳ አለቃ ድንገት በሞት እንደተለየ እስታውቶ ጉዳዩ በዚያው ባከተመ ነበር ። ግን አልሆነም ። ትምህርቴን እስከምገፋ ድረስ በዕረፍት ላይ እንደምሆን ተቆጠረልኝ ። የዚያን ጊዜ ትምህርት እንዳሁኑ ዐይነት አልነበረም ። አምስት ዓመት ሲሞላኝ ጥንቁቅና ቁም ነገረኛ የሆነ ፣ ሳቪሊች የሚባል ሞግዚትና የግል አስተማሪ መጣልኝ ። እሱ እያስተማረኝ በዐሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜዬ አፍ በፈታሁበት ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ቻልኩ ። ከዚያም አባቴ ዜግነቱ ፈረንሣዊ የሆነ ፣ ሙሴ ቦፕሬ የሚባል አስተማሪ ከሞስኮ አስመጥቶ የዓመት ቀለቡን በመስፈር ቀጠረልኝ ። የአስተማሪው መምጣት ሳቪሊችን በጣም በሳጨው ። “ ለእግዜር ክብር ምስጋና ይግባውና ልጁ እንደሁ እስካሁን ድረስ ንጽሕናው ሲጠበቅለት ፣ ጥሩ ሲለብስና በሚገባ ሲቀለብ ቆይቷል ! ” ሲል አጉረመረመ ፣ “ አገራችን ብቃት ያላቸው ሰዎች ያጣች ይመስል ለምን ለውጭ አገር ዜጋ ገንዘባቸውን ያባክናሉ ? ”

በፕሬ ትውልድ አገሩ ሳለ ጸጉር አስተካካይ ነበር ። ቀጥሎም በፕሩሲያ ክፍለጦር ውስጥ ሲያገለግል ቆይቶ ፣ በመጨረሻም በአስተማሪነት ሞያ ወደሩሲያ ይገባል ። “ አስተማሪ ” የሚለውን ቃል ፍች እንኳ አያውቀውም ። ከመጠን ያለፈ ቀልበ—ቢስና ልክስክስ ቢሆንም ጨዋታ የሚጣፍጥለት ሰው ነበር ። የተጠናወተው ዋነኛው በሽታው ግን፣ የሴት ዓመል ሲሆን መጐንተል በማብዛቱም በየጊዜው በሚደርስበት ድብደባ ለብዙ ቀናት ይማቅቃል ። ከዚህም በላይ ፣ ራሱ እንደሚለው ፣ “ ጠርሙስ ማነቅ ” ይወዳል ፤ በሌላ አባባል ፣ ጥንብዝ ብሎ እስኪሰክር የመጠጣት ሱስ ነበረበት ። ደግነቱ ከቤታችን ወይን ጠጅ በእራት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዓት ብቻ ነበር የሚቀርበው ፤ የሚታደለውም አንዳንድ ብርጭቆ ብቻ ሲሆን ለዚያውም አብዛኛውን ጊዜ ቦፕሬ ይታለፋል ። ታዲያ ያም ሆኖ ቦፕሬ የሩሲያን አልኮል መጠጥ ፈጥኖ ተላመደው ። ምግብ ያንሸራሸራል በሚል ሰበብ ከራሱ አገር ወይን ጠጅ አስበልጦ ያዘወትረው ጀመር ። ጓደኛሞች ሆንን ። ኃላፊነቱ “ ፈረንሣይኛ ፣ ጀር መንኛ እና ሌሎች ትምህርቶችን እንዲያስተምረኝ ” ቢሆ ንም፣ከማስተማር ይልቅ ጥቂት የሩሲያ ቃላት ከእኔው መለ ቃቀሙ ቀለለው ። ስለዚህ በየበኩላችን የየልባችን ስለ ደረ ሰልን፣ተከባብረን በደስታ ጊዜያችንን ገፋነው ። ዓለማች ንን ቀጨን ። ከእርሱ የተሻለ መምህር አልተመኘሁም ። ግን የዕድል ጉዳይ ሆነብንና ፣ ቀጥዬ እንደማወሳችሁ ወዲ ያው ለመለያየት በቃን ። ፊትዋን ፈንጣጣ የጠቀጠቀው ወፍራሟ ልብስ አጣቢያችን ፖላሽካና ባለአንድ ዐይንዋ ወተት አላቢያችን አኩልካ ፣ እናቴ ጫማ ላይ ወድቀው የፈጸሙትን ኃጢአት ፣ ቦፕሬም የዋህነታቸውን አይቶ ያደ ረሰባቸውን በደል በዝርዝር አስረዱዋት ። እናቴም ለእን ዲህ ያለ ነገር ክብደት ስለምትሰጥ ቅሬታዋን ለአባቴ ነገረ ችው ። ወዲያውኑ አባቴም ያን ወራዳ ፈረንሣዊ ቢያስ ጠራው ፣ እኔን በማስተማር ላይ መሆኑ ተነገረው ። ገሥግሦ ወደ ክፍሌ ቢመጣ ሙሴ ቦፕሬ አልጋው ላይ ተንጋሎ እን ቅልፉን ሲለጥጥ አገኘው ። በበኩሌ ግን፣በሥራ ተጠምጄ ነበር ። መማሪያ እንዲሆነኝ ታስቦ ከሞስኮ ድረስ የመጣ ልኝ አንድ ትልቅ ካርታ ነበር ። ካርታው ያላንዳች ጥቅም ግድግዳ ላይ ቢንጠለጠልም የታተመበት ወረቀት ስፋቱና ጥራቱ ለብዙ ጊዜ ይስበኝ ነበር ። የዚያን ዕለት ቦፕሬ በእ ንቅልፉ መዋጡን ሳይም ያን ካርታ ቀድጄ ‘ ካይት ’ የሚ ባል መጫወቻ ልሠራ ተነሣሁ ። አባቴ የደረሰብኝም ቆራ ርጬው ለካይቱ ጅራት በምቀጥልበት ወቅት ነበር ። የጅ አግራፊ ትምህርቴ እንዲያ መሆኑን ሲገነዘብም በጆሮዩ



t.me/OLDBOOKSPDF

እየገ ተ  ተኝ ወደ ሙሴ ቦፕሬ ገሠገሠ ። የለምንም ይሉኝታ ቀስቅሶትም ስድቡን አወረደበት ። ቦፕሬ እጅግ ተደናግጦ ብድግ ለማለት ቢሞክር ጥምቢራው እስኪዞር ሰክሮ ነበርና አልቻለም ። ለጥፋቱ የሚጠብቀው አንድ ቅጣት ብቻ ነበር ። አባቴ በኮቱ ኮሌታ አንጠልጥሎት ከክፍሉ ገፍትሮ አስወጣውና የዚያኑ ዕለት ከቤት አባረረው ። ሳቪሌች በደስታ ጮቤ ረገጠ ። በዚህ አኳኋን ትምህርቴ ተቋረጠ ። ከለማዳ ርግቦች ጋር ስቦርቅና እርስታችን ላይ ካሉት ልጆች ጋር ስዘል ደንቆሮ ሆኜ አደግሁ ። በዚያ አኳኋን ዐሥራ ስድስተኛ ዓመቴን ያዝኩ ። ከዚያን ወቅት አንሥቶም ሕይወቴ እየተለወጠ ሔደ ።

አንድ ቀን ፤ በመጸው ወራት እናቴ ከሳሎን ሆና አንጆሪ በማር ስትቀቅል አጠገብዋ ቆሜ ሲፍለቀለቅ እያየሁ ለመቅመስ እቋምጣለሁ ። አባቴ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጦ በየዓመቱ የሚደርሰንን “ ዜና ቤተመንግሥት ” የሚባል መጽሔት ያገላብጣል ። መጽሔቱ አባቴን ሁልጊዜም ያመራምረዋል ። ሳይጨነቅና ሳይጠበብ አንብቦት አያውቅም ። በጥንቃቄ በተመለከተው ቁጥር ደሙ ይፈላል ። ጠባዩንና ዓመሉን በሚገባ አብጠርጥራ የምታውቀው እናቴ ሥራዬ ብላ ያን መከረኛ ጽሑፍ ራቅ ካለ ስዋሪ ሥፍራ ስለምትደብቅበት ለሁለትና ለሦስት ወራት ዐይኑ ሳያርፍበት ይቆያል።ባጋጣሚ እጁ ከገባ ግን፡ለብዙ ሰዓት ሙጭጭ ይልበታል ። ታድያ አባቴ እያነበበ ሳለ ዐልፎ ዐልፎ ትከሻውን በመነቅነቅ፡“ ሌተና ጄኔራል . . . በእኔ ክፍለ ጦር ውስጥ ሃምሳ አለቃ ነበር ። አሁን ደግሞ ከፍተኛዎቹን ሁለት የሩሲያ ፈረሰኛ ኒሻኖች ተሸላሚ ሆነ . . . እሱና እኔ . . . ትናንትና . . . ” እያለ ያጉተመትማል ። በመጨረሻም ጽሑፉን ሶፋው ላይ አሽቀንጥሮ በሐሳብ ይዋጣል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታውም ለመላው ቤተሰብ የሚበጅ አልነበረም ።

በድንገት ወደ እናቴ ፊቱን ዞር አድርጎ " አብዶትያ ቫሲሊየቭና ፣ ለመሆኑ የፔትሩሻ ዕድሜ ስንት ነው ? " አላት ።

" ጁረገኝ ፣ አሁንማ ዐሥራ ስድስት ዓመት ሞላው " ስትል መለሰችለት ። " ከነምልክቱ ፔትሩሽካ እኮ የተወ ለደው አክስቱ ናስታስያ ጀራሲሞቭና ዐይንዋን በታወረ ችበት ዓመት ነው . . . "

" እንግዲያውስ መልካም ! " አለ አባቴ አቋርጧት ። " ወደ ውትድርና አገልግሎት መሔጃ ጊዜው አሁን ነው ። ከሴቶች ጓዳና በእርግቦች ጐጆ አካባቢ መንገላወዱ ይበቃ ዋል ። "

የማይቀረው ስንብታችን እናቴን ክፉኛ ስላስደነገጣት ማንኪያውን ብረት ድስቱ ውስጥ ለቀቀችው ። እንባዋም በጉንጮችዋ ላይ መንታ መንታ ሆኖ ወረደ ። በበኩሌ ግን ከመጠን ያለፈ ፈንደቅሁ ። ስመኘው የኖርኩት የውትድርና አገልግሎት ለእኔ ነጻነትን የሚያጐናጽፈኝ ፣ እንደልቤ በፒ ተርስበርግ ከተማ ለመደሰት የሚያስችለኝ ዕድል መስሎ ታየኝ ። በዐይኔ ሕሊናዬ ራሴን እንደ አንድ የጦር መኮ ንን እየተመለከትኩ፣ለሰው ልጅም ከዚህ የበለጠ ደስታ እን ደማይኖር ገመትኩ ።

አባቴ ውሳኔዎቹን ለመለወጥም ሆነ ለማዘግየት አይ ወድም ። የምሔድበት ቀን ተወሰነ ። በዋዜማውም ለወደ ፊቱ የበላይ አዛዤ የማደርሰው ደብዳቤ እንደሚሰጠኝ አስ ታውቆኝ ብዕርና ቀለም እንዲቀርብለት አዘዘ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ለልዑል ጌታዬ የእኔንም ሰላምታ አቅርብልኝ ” አለችው እናቴ “ ለፔትሩሻም እርዳታዎ እንደማይለየው ተስፋ አደርጋለሁ በልልኝ ። ”

“ የምን መቀባጠር ነው ! ” ሲል መለሰላት አባቴ ግምባሩን ቋጥሮ ፣ “ ለምን ብዬ ነው ለልዑሉ የምጽፍ ላቸው ? ”

ለፔትሩሻ የበላይ አዛዡ ደብዳቤ ልጽፍ ነው አላልከም እንዴ ? እረገኝ ! ”

“ እና ፣ ታዲያ ብልሳ ? ”

“ ታዲያ ልዑሉ ናቸው የበላይ አዛዡ ። ፔትሩሻ የተ መደበው አሲሞናቭ የክብር ዘበኛ ጦር ውስጥ አይደል እንዴ ? ”

“ የተመደበው ! . . . በክብር ዘበኛ ውስጥ ! . . የክ ብር ዘበኛ አይሆንም ። ፔትሩሻ ወደ ፒተርስበርግም አይሔ ድም ። ፒተርስበርግ በመቆየቱ ምን ይማራል ? ለብኩን ነትና ለሞራል ውድቀት ከመዳረግ በቀር የሚያተርፈው ነገር የለም ። ይልቅ በጦር ሠራዊትነት ያገለግላል ። እስቲ ጠመንጃ ያንግብ ፣ ባሩድ ይሽተተው ፣ ሴት አውልነቱን ትቶ ቆፍጣና ወታደር ይውጣው ። ‘ በክብር ዘብነት ተመድ ቧል!’ . . . የታል መታወቂያው ? በይ እኮ ስጪኝ ! ”

እናቴ ክርስትና ከተነሣሁበት መታቀፊያ ጋር አኑራው የነበረውን መታወቂያዬን ከሳጥን አውጥታ እጅዋ እየተ ንቀጠቀጠ ለአባቴ ሰጠችው ። አባቴ አገላብጦ ካየው በኋላ በስተፊቱ እጠረጴዛው ላይ አስቀምጦት ደብዳቤውን መጻፍ ጀመረ ።

የሚለውን ለመስማት ጓጓሁ ። ወደ ፒተርስበርግ ካል ሆነ ከቶ ወዴት ሊልክ ይሆን ? በወረቀቱ ላይ በዝግታ ከሚ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኀዘው የአባቴ ብዕር ላይ ዐይኔ ጨርሶ አልነቀል አለ ። በመ ጨረሻም ደብዳቤውንና መታወቂያዬን በፖስታ አሽጎ ፣ መነጽሩን አውልቆ ጠራኝና “ ይህ ደብዳቤ ለጥንቱ የሥራ ጓዴና ወዳጄ ለአንድሬ ካርሎቪች በእጁ የምትሰጠው ነው። ወደኦሬንበርግ ሒደህ በእርሱ ሥር ታገለግላለህ ” አለኝ።

በዚህ አኳኋን ሕልሜ ተጨናገፈ ! በፒተርስበርግ ከተማ በሚጠብቀኝ ደስታ ምትክ የአንድ ቀፋፊና አልም ባለ ገጠር አሰልቺ ኑሮ ተጋረጠብኝ ። ከጥቂት ጊዜ በፊት እጅግ እጓጓለት የነበረው የውትድርና አገልግሎት አሁን ብርቱ ፈተና መስሎ ታየኝ ። አሻፈረኝ ማለቱም ጠቃሚ ውጤት እንደማይኖረው ተረዳሁ ። በነጋታው የምንዝበት ጋሪ ፊት ለፊት ወዳለው በረንዳ ቀረበ ፣ ሻንጣዬ ፣ የሻይ ማፍያ ዕቃዎችና የእናት ጓዳ ትዝታዎች መግለጫ የሆኑት የትኩስ ዳቦና የብስኩት ጥቅሎች በአንድ ላይ ተጫኑ ። አባ ትና እናቴ የወላጅነት ምርቃታቸውን ሰጡኝ ። አባቴም እንደዚህ አለኝ ፡ “ ደህና ሁን ፓይተር ። ትዕዛዙን ለመፈጸም ቃል የገባህለትን ሰው በታማኝነት አገልግል ። የበላዮችህን ትዕዛዝ አክብር ። በእነርሱ ዘንድ ተወዳ ጅነትን ለማትረፍ ብለህ አጉል አታሽቃብጥ ። ሳትጠየቅም ለማገልገል ሽብ ረብ አትበል ። ስትጠየቅ ግን ዕውቀትህ ንና ጉልበትህን አትንፈግ ። ስሕተት ገና በእንጭጩ ካል ተቀጨ ይበልጥ ይበክላልና በወጣትነት ጊዜህ ክብርህ እን ዳይጉድፍ ተጠንቀቅ ። ይህን ምክሬን ዘወትር አስታውስ” አለኝ ። እናቱ እያነባች ጤንነቴን እንድጠብቅ ተማፀነ ችኝ ። ሳቪሊችም እንዲንከባከበኝ አደራ ጣለችበት ። ስስ የቆዳ ኮት አለበሱኝ ፣ ከጨርቅ የተሠራና በቀበሮ ጸጉር የተ ከፈፈ ካፖርትም ደረቡልኝ ። ስቅስቅ ብዬ እያለቀስኩ ከጋ ሪው ላይ ወጣሁና ከሳቪሊች ጐን ተቀምጬ ጉዞዬን ጀመ ርኩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሲመሽ ሲምቢርስክ ከተማ ገባን ። አንዳንድ አስፈ ላጊ ዕቃዎች ለመግዛት እስከሚቀጥለው ቀን እዚያው መቆ የት ነበረብን ። ዕቃ የመግዛቱ ኃላፊነት የሳቪሊች ነበር ። አንድ ሆቴል ዐረፍን ። ሳቪሊች በማግሥቱ ማለዳ ላይ ገበያ ወጣ ። መስኮቱ ላይ ተንጠልጥዬ ያን አስቀያሚ መንገድ ማየት ሰለ ሰለችኝ የሆቴሉን ክፍሎች በሙሉ እየተዘዋወ ርኩ መጐብኘት ጀመርኩ ። ከከረምቦላው ክፍል ውስጥ ቁመተ ረጅም ፣ ዕድሜው ወደ ሠላሳ አምስት ዓመት የሚ ጠጋና ዝርገድ ያለ ጥቁር ሪዝ ያለው ሰውዬ አየሁ ። ፒጃማ የለበሰው ይህ ሰው በእጁ የከረምቦላ ድንጋይ ፣ በጥርሶቹ መሐልም ፒፓ ይዟል ። ከንጥብ ቆጣሪው ጋር እየተጫወተ ነበር ። ንጥብ ቆጣሪው ባሸነፈ ቁጥር አንድ ብርጭቆ ቮድካ ይጨልጣል ። ሲሸነፍ ደግሞ በብስጭት ከጠረጴዛው ሥር ገብቶ ይድሃል ። ቆም ብዬ ጨዋታቸውን ተመለከትኩ ። ጨዋታቸው በረዘመ ቁጥር ንጥብ ቆጣሪው ቶሎ ቶሎ ሲድህ ቆይቶ በመጨረሻ ላይ ከከረምቦላው ጠረጴዛ ሥር ገባና ከዚያም ተቀርቅሮ ቀረ ። ሰውዬውም ጸሎተ ፍታት እንደ ሚያደርስ ሰው ጥቂት ካልጎመጎመ በኋላ አብሬው እንድ ጫወት ጠየቀኝ ። መጫወቱን ስለማላውቅበት እምቢ አል ኩኝ ። ፍጹም እንግዳ ነገር ሆነበትና በአዘኔታ ተመለከተኝ። ነገር ግን ወዲያው ውይይት ጀመርን ። ሰውዬው ኢቫን ኢቫኖቪች ዙሪን መባሉን ፣ የፈረሰኞች ሻምበል መሆኑን ፣ ሲምቢርስክ የመጣው ወታደር ለመመ ልመል እንደሆነና ያረፈውም በዚያ ሆቴል እንደሆነ አስረዳኝ ። ምሳም አብሬው እንድበላ ጠየቀኝ ። ያለ ማመንታት ተስማማሁ ። ለማዕድ ቀረብን ።

ዙሪን ብርጭቆውን ያለማቋረጥ እየጨለጠና እየሞላ የው ትድርና አገልግሎት ሕይወትን እንዴት መላመድ እንዳ ለብኝ ሰፊ ትምህርት አቀረበልኝ ። በውትድርና ኑሮ ውስጥ


t.me/OLDBOOKSPDF

ስላጋጠሙት አሥቂኝ ታሪኮች ሲያጫውተኝ ልቤ እስኪፈርስ ሣቅሁ ። ከማዕድ ስንነሣ የልብ ወዳጆች ሆነን ዐረፍነው ። የኮረምቦላ ጨዋታ ሊያስተምረኝም ቃል ገባልኝ። "ለእኛ ለወታደሮች በጣም አስፈላጊ ነው ። ለምሳሌ በዘመቻ ላይ እንዳለህ አንድ የሆነ ሥፍራ ትደርሳለህ ። ምን የምታደርገው አለ ? ጠላት ፈጥረህ ግብግብ አትገጥም ። ወደ አንድ ሆቴል ሔደህ ከረምቦላ ከመጫወት በስተቀር አማራጭ አይኖርህም ። ስለዚህ ጨዋታውን የግድ ማወቅ አለብህ ። " ያቀረበውን አሳብ ሙሉ በሙሉ አምኜለት በትጋት ጨዋታውን መማር ጀመርኩ ። ዡሪን ፈጣን እርምጃዬን እያደነቀ ከልቡ አበረታታኝ ። ለሙከራ ያህል ጥቂት ዙሮች እንደ ተጫወትን ለትርፍ ሳይሆን በነጻ መጫወት እንዳያጃጅለን አነስተኛ ገንዘብ በመመደብ እንድንቀጥል አሳብ አቀረበ ። በነጻ መጫወትን የመሰለ መጥፎ ልማድ የለም የሚል እምነት አለው ። በዚህም አባባሉ ተስማማሁ ። ዡሪን መጠጥ አዘዘ ። የወታደር ኑሮን ካሁኑ መለማመድ እንዳለብኝ በድጋሚ ገልጾልኝ መጠጡንም እንደ ሞክረው ገፋፋኝ ። " የውትድርና ሕይወት ያለ አረቄ ምን ትርጉም አለው ? " ባለኝ መሠረት ፉት እያልኩ ጨዋታችንን ቀጠልን ። በተጉነጨሁ ቁጥር ይበልጥ ድፍረት ተሰማኝ ። የምወረውራቸው ድንጋዮች በተከታታይ ከጠረጴዛው እየተሽቀነጠሩ ወደውጭ ይወጡ ጀመር ። በንዴት ጦፍኩ ። ነጥብ ቆጣሪው ማጫወት ስላልቻለ በስድብ ወረድኩበት ፤ የውርርዱን ገንዘብ ከፍ ከፍ ማድረጌን ቀጠልኩ። ባጭሩ ፤ መረን እንደ ተለቀቀ ሕፃን ሆንኩ ። ሳይታወቀኝ ጊዜው በረረ ። ዡሪን የእጅ ሰዓቱን አየት አድርጎ የያዘውን ድንጋይ ካስቀመጠ በኋላ አንድ መቶ ሩብል እንደተበላሁ አሳወቀኝ ። ይህ በመጠኑም ቢሆን አስደነገጠኝ ። ገንዘቤ ሳቬሊች ዘንድ ስለነበር ለጥቂት ጊዜ እንዲታገሠኝ ይቅርታ ጠየቅሁት ። ዡሪን አቋረጠኝ " ኧረ ግዴለም ! ፈጽሞ



t.me/OLDBOOKSPDF

አትቸገር ! ለመቆየት እችላለሁ ። እስከዚያው ግን ማዳም ዋል አሪኑሽካን እስቲ ብቅ ብለን እንይት ” አለኝ ።

ከእንግዲህ ምን ይምጣ ? ቀኑን በማይረባ ነገር እንደ ጀመርኩት ሁሉ ምሽቱንም በከንቱ ገፋሁት ። ማዳም ዋዜል አሪኑሽካ ቤት እራት በላን ። ዙሪን በማከታተል ብር ጣቶቹን እየሞላ ይጋጋም የውትድርናን ሕይወት መለ ማመድ እንዳለብኝ ይነግረኛል ። ብድግ ለማለት ስሞክር መቆም እንደ ተሳነኝ ተረዳሁ ። እኩለ ሌሊት ላይ ዙሪን ከሆቴሉ ድረስ ሸኘኝ ።

ከሳቪሊች ጋር ከበሩ ላይ ተገናኘን ። ለውትድርና አገ ልግሎት የቱን ያህል እንደ ተዘጋጀሁ የሚጠቁሙ ግልጽ ምልክቶችን ከገጼ ላይ አንብቦ አፉን ከፍቶ ቀረ ። “ ምን ስታደርግ ቆየህ ጌታዬ ? ” አለኝ ሐዘን ባዘለ ቃና ። “ የት ይሆን እንዲህ ጨርቅ እስክትሆን የጠጣኸው ? የእግዜር ያለህ ! ያንተ ያለህ ! እንዳው . . . እንዲህ ያለ ጥፋት ይሠ ራል ? ”

“ በል ዝም በል ፡ አንተ የጃጀህ ዘላባጅ ” አልኩት በጐርናና ድምፅ ። አንተው ራስህ ሳትሰክር አልቀረህም ! ሒድ ተኛ . . . እኔንም አስተኛኝ ። ”

በበነጋው ጠዋት ስነቃ ራስ ምታት ለቀቀብኝ ። ባለ ፈው ቀን የፈጸምኳቸው ድርጊቶች ብዥ ብዥ አሉብኝ ። ከሐሳቤ ሰመመን የወጣሁት ሳቪሊች አንድ ፍንጃል ሻይ ባመጣልኝ ሰዓት ነበር ። “ ገና አንዱንም ሳትይዘው መጠ ጥና ከንቱ ደስታ ጀመርክ እኮ ፓይዮር አንድሬች ” አለኝ ራሱን እየነቀነቀ ።“ እንዳው በማን ወጥተህ ይሆን ? አባት ህም ሆኑ አያትህ ጠጪዎች አልነበሩም ። እናትህም ቢሆኑ ከሉሚ ጭማቂ በስተቀር ሕይወታቸውን ሙሉ መጠጥ የሚባል ንክች አድርገው አያውቁም ። ታዲያ ለዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተጠየቀው ማነው ? ያ እርጉም አስተማሪህ መሆን አለበት። 'ማዳም ፡ እባክዎን ሾድካ ' እያለ ግምጃ ቤትዋን ሁልጊዜ ይነዘንዛት ነበር ። ይኸው አሁን ተራህን ' እባክዎን ' የም ትለው አግኝተሃል ። በእርግጥም ያ ወራዳ እንዲህ እንዲህ ያለውን አስተምሮሃል ! በቤታቸው አገልጋይ ያጡ ይመ ስል ያን ሀረመኔ መቅጠራቸው ግርም ይለኛል ። ''

ዕፍረት ተሰማኝ ። ፊቱን ወደጉን አዞሬ፡ '' ሒድልኝ ሳቪሊች ፡ ምንም ሻይ አልፈልግም '' አልኩት ። ሳቪሊች እንደዬ ምክር መለገስ ከጀመረ ፊቀቅ የሚያደርገው ምንም ኃይል አይኖርም ። '' መጠጥ ምን እንደሚያስከትል እየው፣ ፓይቶር አንድሬቭ ። ራስህን ይበጠብጥሃል ። መብላት አት ችልም ። ጠፊ ሰው ፈጽሞ አይረባም . . . ራስ ምታት ህን ያስታግሥልህ እንደሆን እስቲ የፍሬ ጭማቂ ጠጣ ፡ ወይስ ግማሽ ብርጭቆ ቮድካ ልዘዝልህ ? '' እያለ ነዘነዘኝ ።

ወዲያውኑ አንድ ልጅ ከዙሪን የተላከ ማስታወሻ ይዞ ብቅ አለ ። ሥስታውን ከፍቼው ቀጥሎ ያለውን መልዕክት አነበብኩ ።

'' ወዳጄ ፓይቶር አንድሬየቪች ፡ እባክህ ትናንትና ማታ የበላሁህን አንድ መቶ ሩብል ለልጁ ላክልኝ ። ገንዘብ በጣም አስፈልጎኛል ።

ታማኝ አሽከርህ
ኢቫን ዙሪን ''

ምንም ማድረግ አይቻልም ። በግድየለሽነት መንፈስ ወደ ግምጃ ቤቴ ሹምና ጉዳይ ፈጻሚው ሳቪሊች ዞወር ብዬ ለልጁ አንድ መቶ ሩብል እንዲሰጠው አዘዝኩት ። ''ምን ለምን ? '' ብሎ ጠየቀኝ ሳቪሊች በመገረም ። '' ዕዳ አለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብኝ ” ስል መለስኩ ረጋ ብዬ ። “ ዕዳ አለብኝ ?” በማለት እንባረቀብኝ ሳቪሊች ይበልጥ ተገርሞ ። “ ምን ጊዜ ነው ዕዳ ውስጥ የተዘፈቅኸው ጌታዬ ? እንዳች ጣጣ ሳይፈጠር አልቀረም ። የፈለግኸውን በል ጌታዬ ፤ እኔ እንዲሁ ገንዘ ቡን አልሰጥም ” ብሎኝ በረፈው ።

በዚያች ቀውጢ ሰዓት ያ መንቻካ ሽማግሌ ትእዛዜን እንዲቀበል ካላደረግሁት ወደፊት ከተጽዕኖው ለመላቀቅ እቸገራለሁ የሚል አሳብ አደረብኝ ። ስለዚህም ቀብረር በማለት ገላምጬው፤“ እኔ ጌታህ ነኝ ። አንተ ደግሞ አሽ ከሬ ነህ ። ገንዘቤ የኔ ነው ። ያጠፋሁትም ወድጄ ነው ። አጉል ተቆርቋሪነትህን ትተህ የታዘዝከውን ፈጽም ” አልኩት ።

ሳቪሊች በሰነዘርኩት ቃል እጅግ ከመደንገጡ የተ ነሣ እየተንቀጠቀጠ እጆቹን ከማወራጨት በቀር ምንም ሊያደርግ አልቻለም ። “ አፍክን ከፍተህ አትገተርብኝ ! ” ብዬ በቁጣ ጮሁኩበት ። ሳቪሊች በድንገት እንባውን አዘ ነመው ። “ ኧረ ምነው ጌታዬ ፓዩቶር አንድሬች !” አለኝ እየተርበተበተ ። “ እንጂቴን አትቁረጠው ! ያይኔ ብርሃን ፤ የእኔን የሽማግሌውን ምክር ስማ ! ውርርድ የገባኸው ለቀ ልድ እንደ ነበርና ያን ያህል ገንዘብም እንደሌለህ ገልጸህ ለዚያ ወሮበላ ጻፍለት ። አንድ መቶ ሩብል ! . . . የሥላሴ ያለህ ! ቤተሰቦችህ በጠጠር እንጂ በሌላ ነገር ቁማር እንዳ ትጫወት አጥብቀው እንደ ከለከሉህም ንገረው ። ”

“ በቃህ ! ” አልኩት ፊቴን በመከስከስ ። “ ገንዘ ቡን አሁኑኑ አስረክበው ፤ አለዚያ አባርርሃለሁ ! ” ሳቪ ሌች ቅስሙ ተሰብሮ እያዘነ ገንዘቡን ሊያመጣ ሔደ። እኔም ለሽማግሌው አዘንኩለት ። ሆኖም የማያወላውል አቋም



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመያዝና ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ልጅ አለመሆኔን ለማረጋገጥ ቆረጥኩ ። ገንዘቡም ለዙሪን ተላከለት ። ሳቪሊች ከዚያ ከተረገመ ሆቴል ሊያወጣኝ ተጣደፈ ። ፈረሶች እንደ ተዘ ጋጁልኝም ነገረኝ ። ሲምቢርስክን የለቀቅሁት በተረበሸ ሕሊናና ውስጥ ውስጡን በሚያቃጥል ጸጸት ተውጬ ስለ ነበር ዙሪንን ፣ ' አዲሱን አስተማሪዬን ' ዳግም አገኘው ይሆናል በሚል ተስፋ አልተሰናበትኩትም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሁለት

### እግረኛው

እንተ የሩቅ ምድር
የማላውቅህ አገር !
ላይህ አልተመኘሁ ፤
ወዳንተም አልጋለብሁ ።
ደፋር ልጅ ነበርኩኝ ፤
አፍላ ጉርምስና እያንደረደረኝ ፤
በስካር ድንፋታ ካንተው ዘንዳ ጣለኝ ።

(ጥንታዊ ዘፈን)

በጉዞዬ ላይ የማስበው ሁሉ እምብዛም የሚያስደስት አልነበረም ። የተበላሁት ሩብል በወቅቱ በጣም ከባድ ገንዘብ ነበር ። በሲምቢርስ ሆቴል ያሳየሁት ጠባይ አጉል እንደነበርና ሳቬሊችንም እንዳስቀየምኩት ከልቤ አመንኩ ። ይህ ሁሉ ጸጸት አሠቃየኝ ። ሽማግሌው ፊቱን አጨፍግጎና ጀርባውንም ሰጥቶኝ ከመቀመጫው ላይ ቁብ ብሏል ። አንዳንዴ ጉሮሮውን ከመጥረግ በስተቀር ጨርሶ ድምፁን አጥፍቷል ። በመካከላችን መግባባትን ለማስፈን ብመኝም መላው ጠፋኝ ። በመጨረሻም እንዲህ አልኩት ። “ በል እንጂ ሳቬሊች ፤ ይበቃል—እንታረቅ ፤ በደለኛው እኔ ነኝ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

በደለኛነቴ ለራሴም ተሰምቶኛል ፤ ትናንት ስጃጃል ነው የዋልኩት ። እንደዚያ ላመናጭቅህ ባልተገባኝም ነበር ። ጠባዬን እንደማርምና ወደፊትም ቀጥ ብዬ እንደምታዘዝህ ቃል እገባለሁ ። በል እንግዲህ ቂጣው ይቅር — እንታረቅ !

" አዬ ጌታ ፓይቶር አንድሬች " ሲል መለሰ ሳቬሊች ቁና ቁና እየተነፈሰ ፤ " የተቆጣሁትስ እራሴኑ ነው ። ስሕ ተቱ ሙሉ በሙሉ የእኔው ነው ። ሆቴሉ ውስጥ ብቻህን መተው አይገባኝም ነበር ። ግና ምን ይሆናል ! የቄስ ገበዝ ሚስት የሆነችና ናፍቆቷ የተቀሰቀሰብኝን አንዲት የጥንት ወዳጄን ለመጠየቅ በመሔዴ የሆነው ሊሆን በቃ ። ይኸ ውልህ እንግዲህ ፤ ጓደኛ ጥየቃ ሔጄ አንተን ለወጥመድ ዳረግሁህ እግዚኦ ! ጌታዬና እመቤቴ ፊት እንዴት አድርጌ እቀርብ ይሆን ? ልጃቸው ጠጪና ቁማርተኛ መሆኑን ሲሰሙ ከቶ ምን ይሉ ይሆን ? "

የተከፋውን ሳቬሊች ለማጽናናት ስል ሳላስፈቅደው ቤሳ እንደ ማላጠፋ ቃል ገባሁለት ። እያደር ቢረጋጋም አንዳንዴ ራሱን እየነቀነቀ " አንድ መቶ ሩብል ! ቀልድ አይደለምኮ " በማለት ብቻውን ማጉመትምቱ አልቀረም ።

ወደ መድረሻዬ በመቃረብ ላይ ነኝ ። ዙሪያው አው ላላ ሜዳ ሲሆን ዐልፎ ዐልፎ ጉብታና ገደላ ገደል ይታይ በታል ። ሥፍራው በሞላ በበረዶ ተሸፍኗል ። በስተምዕ ራብ አድማስ ጀምበር እያሽቆለቆለች ነበር ። ጋሪዬ አንድ ጠባብ መንገድ ይዞ ወይም በትክክል ለመግለጽ የገበሬዎች ሠረገላዎች የቀደዱትን ፈር በመከተል እየተጓዘ ነው ። ሠረ ገላ ነጂው ሳይታሰብ ፤ በጭንቀት ተወጥሮ ወደ አንድ አቅ ጣጫ ዐይኑን ከተከለ በኋላ፤ባርኔጣውን አውርዶ ፊቱን ወደ



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ዘወር በማድረግ “ ጌታዬ ፣ ብንመለስ የተሻለ ነው ” አለኝ ።

“ ለምን ? ”

“ የአየሩ ጠባይ አስተማማኝ አይደለም ። ነፋሱ በመ ነሣት ላይ ነው ። አሁን የወረደውን በረዶ እንዴት እንደሚ ያንገዋልለው ይመልከቱ ። ”

“ ታዲያ ምን ይሆናል ብለህ ነው ? ”

“ እስቲ ወደዚያ ይመልከቱ” ብሎኝ ነጂው ወደ ምሥ ራቅ አለንጋውን ቀሰረ ።

“ ሻሽ ከመሰለው ሜዳና ከጠራው ሰማይ በስተቀር የማየው ነገር የለም ። ”

“ እዚያ — ያ ደመና ...”

በጣም በመራቁ የኮረብታ አናት የሚመስል አነስተኛ የደመና ቁልል አድማስ ላይ ተንጠልጥሏል ። ነጂውም ይህ ደመና የማዕበል ምልክት መሆኑን አስረዳኝ ። በዚህ አካ ባቢ የሚነሣው የበረዶ ውሽንፍር አያሌ የሠረገላ ተጓዥ ዎችን ቀብሮ እንዳስቀራቸው ሰምቻለሁ ። ሳቬሊች የነጂውን ሐሳብ በመደገፍ እንድንመለስ መከረኝ ። እኔ ግን ነፋሱ በጣም የሚያይል ስላልመሰለኝና ከሚቀጥ ለው ማረፊያ ጣቢያ ለመድረስ ጊዜ እንደሚኖረን በማመን ነጂው ፈረሶቹን እንዲቀሰቅስ ነገርኩት ።

ዐልፎ ዐልፎ ወደምሥራቅ አየት እያደረገ በፍጥነት መንዳት ቀጠለ ። ፈረሶቹ በፈቃዳቸው ሽምጥ ጋለቡ ። ነፋሱ እጅግ እየበረታ መጣ ። ነጥብ ይመስል የነበረው ደመናም እየሰፋ ሔዶ በሚያስፈራ ግርማ መላውን ሰማይ ከዳር እስ ከዳር ሸፈነው ። የበረዶ ብናኝ መውረድ ጀምሮ ከዚያም



t.me/OLDBOOKSPDF

በድንገት አየሩ በትላልቅ የበረዶ ቅራፊ ተሞላ ። ነፋሱ አፏጨ ። የበረዶው ውሽንፍር ወረደብን ። ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጥቁሩ ሰማይ ከበረዶው ውቅያኖስ ጋር አንድ አካል እንደ አምሳል ሆነ ። ጉልተው የሚታዩ ምልክቶች ሁሉ ደብዛቸው ጠፋ ።

" ይኸውልዎታ ጌታዬ " ሲል ጮኸ ነጂው " እንግዲህ አልቀረልንም ። " በሠረገላው ጣሪያ ሥር አሾልቄ ወደውጭ አየሁ ። አካባቢውን ከዋጠው መንፈስ ከሚያስጨንቅ ሰውሎ ነፋስ በስተቀር ምንም ነገር የለም ። የነፋሱ ማጓራት ሥፍራውን በአውሬዎች የተወረረ አስመሰለው ። ሳቬሊችና እኔ ወዲያው በበረዶ ተሸፈንን ። ፈረሶቹ ሲያዘግሙ ቆያዩና ቀጥ አሉ ።

" ለምን ወደፊት አትቀጥልም ?" በማለት ጠየቅኩት ነጂውን በመቅበጥበጥ ።

" ምን ሊበጀን ? " ሲል መለሰልኝ ከሠረገላው ላይ በመንገዳገድ እየወረደ ። " የት እንዳለን እንኳ አላውቅም። መንገዱ አይታይ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው ። " ስድብ አወርድበት ጀመር ። ሳቬሊች ግን የእርሱ ደጋፊ ሆነ ።

" ለምን ያለህን አትሰማም ነበር ? አለኝ በመቆጣት ። ወደ ቀድሞው ሆቴላችን ተመልሰን ፡ ትኩስ ሻይ ፉት እያልን ማዕበሉ እስኪያልፍልን ከዚያው ማደሩና ጉዞአችንን እንደገና መጀመሩ ሌላው አማራጭ ነበር ። " የተለየ አስቸኳይ ጉዳይ የለንም ፡ አለን እንዴ ? የሠርግ ጥሪ ያለብን ይመስል ምን አስሮጠን " አለ ሳቬሊች ። ትክክል ነበር ። ችግር ላይ ወደቅን ። የበረዶው ዝናም እየከፋ ሔደ። በጋሪያችን ዙሪያ በረዶው ተከመረ ። ፈረሶቹ ፡ አንዳንዴ ብቻ እንደ መበርገግ እያሉ ፡ አንገታቸውን ሰብረው ተገ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሩ ። ነጂውም ሥራ ላለመፍታት ሲል እየተዘዋወረ ፣ የፈረስ ዕቃውን ያስተካክላል ። ሳፎሊች ለብቻው ያጉረመርማል ። እኔም ሕይወት ያለው አንዳች ነገር ወይም መንገዳችንን ለማግኘት ስል ዙሪያዬንእ ማተርኩ ። ነገር ግን ከበረዶው ክምር በቀር በመጀመሪያው ሙከራዬ ምንም ለማየት አልቻልኩም ። ጥቂት ቆየት ብዬ ግን ዐይኔ አንድ ጥቁር ነገር ላይ ዐረፈ ።

" ስማ እስቲ " ; ልኩኝ : " ተመልከት : እዚያ ያለው ጥቁር ነገር ምንድነው ? " ነጂው ወዳመለከትኩት አቅጣጫ አተኩሮ " እግዜር ይወቀው ጌታዬ " አለኝ ወደ መቀመጫው እየተመለሰ ። " ሠረገላ ወይም ዛፍ አይመስልም ። ስለሚንቀሳቀስም ተኩላ ወይም ሰው መሆን አለበት ። "

ወደኛ በማምራት ላይ ወዳለው ያልታወቀ ነገር እንዲነዳ ; ዘዝኩት ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ ሰው አጠገብ ቆምን ። " ስማህ ወይ አንተዬ ! " አለው ነጂው ድምፁን ከፍ ; ድርጎ። "መንገዱ የት እንዳለ ታውቃለህ ?"

" መንገዱማ እዚችው ነው ። ጥብቅ መሬት ላይ ነው የቆምኩት " ሲል መለሰለት መንገደኛው ። " ግን ምን ፋይዳ አለው ? "

" ወንድም አዳምጠኝ " አልኩት እኔ : " ይህን አካባቢ ታውቀዋለህ ? ሌሊቱን ለማሳለፍ ወደምንችልበት ሥፍራ የሚወስደውን መንገድ ልታሳየን ትችላለህ ? "

" ይህን አካባቢ ዐውቀዋለሁ " ሲል መለሰልኝ መንገደኛው " ላውቀውም ይገባኛል ። በእግርና በፈረስ : ከዳር እስከዳር ደጋግሜ ተመላልሸበታለሁ ። ሆኖም ያየኑን ጠባይ ይዩት እስቲ።ለቅጣጫችንን በቀላሉ ሊሰውርብን ይችላል ። እላችሁበት ሆናችሁ ብትጠብቁ ይሻላል ። ማዕበሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማለቶና ሰማዩ መጥራቱ አይቀርም ። በዚያን ጊዜ በከዋከ ብት እየተመራን ሁንገዳችንን ለማግኘት እንችላለን ። ”

የሰውየው የተረጋጋ መንፈስ አዲስ ተስፋ አሳደ ረብኝ ። ሁሉንም ነገር ለእግዜር ትቼ ሌሊቱን ቅልጥጥ ባለው ሜዳ ላይ ለማሳለፍ ወሰኜ እያለሁ መንገደኛው ከነ ጂው መቀመጫ ላይ በቅልጥፍና ወጥቶ ጉብ በማለት ነጂ ውን እንዲህ አለው “ እግዜር ይከበር ይመስገን ፣ ከዚህ እምብዛም ሳይርቅ አንድ ቢት አለ ። ወደቀኝ ታጠፍና ቀጥታ ወደፊት ንዳ ። ”

“ ለምንድነው ወደቀኝ የምታጠፍ ? ” ብሎ ጠየቀው ነጂው በማንገራገር ። “ ምንም መንገድ አይታየኝም ። ” “ ንዳ ” ማለት ቀላል ነው ። ፈረሶቹ የሌላ ሰው ናቸው ፣ ጋሪው የሌላ ሰው ነው ። አንተው እንዳሻህ ንዳ ። ምንቸገ ረህ ፣ አትከፍልበት ! ” የሚል ቁጣ ያዘለ ምላሽ ሲሰጠው ነጂው ትክክል ነው ብዬ አሰብኩ ። “ ባቅራቢያችን ቤት መኖሩን እንዴት ዐወቅህ ? ” ስል ጠየኩት እኔም በተራዬ ። መንገደኛው “ ነፋሱ ከዚያ አቅጣጫ ስለሚነፍስና ጭስ ስለ ሸተተኝ ነዋ! ይህም በአቅራቢያችን መንደር አለ ማለት ነው ” በማለት መለሰልኝ ። ብልህነቱና ንቁነቱ አስደነ ቀኝ ። ነጂው ጉዞውን እንዲቀጥል አዘዝኩት ። ፈረሶቹ በሚያጠልቀው የበረዶ ክምር ላይ እየተጉተቱ መንገዱን ተያያዙት ። ጋሪው የበረዶውን ክምር እያረሰ ፣ ሞገድ እንደ ሚያንገላታው መርከብ ወደ ግራና ወደ ቀኝ እየዋዠቀና ገደ ላገደል ውስጥ ለመከንበል እየቃጣው ጉዞውን በዝግታ ቀጠለ።ሳቬሊች እያጉረመረመ ከእኔ ጋር ይላተማል ። የሠ ረገላውን መጋረጃ ወደታች ለቀቁ ፣ በቆዳ ኮቴ ከተጠቀለ ልኩ በኋላ የማዕበሉን ፋጨትና የጋሪውን ቋቋታ እያዳመ ጥኩ አሸለብኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍጹም ሊረሳኝ የማይችል ፣ በሕይወቴ ከገጠሙኝ እንግዳ ነገሮች ጋር እያዛመድኩት እስከዛሬ እንደ ራዕይ የምቆጥረው ሕልም አየሁ ። ለእንዲህ ያለ አጉል እምነት መገዛቱን ቢጠላውም ምናልባት ደርሶበት ይሆናልና አንባቢዬ ይቅርታ እንደሚያደርግልኝ አምናለሁ ።

እውነታና ሕልም ተደባልቀው ደብዘዝ ባለ መልካቸው እየተንጸባረቁ አፍላ እንቅልፌን በሚያውኩበት ደረጃ ላይ በሕይወትና በሞት ዓለም መካከል እየተንሳፈፍኩ ነበር ። የበረዶው ማዕበል አሁንም እንደ ቀጠለ ይመስለኛል ። በረዶ በተነጠፈበት አውላላ ሜዳ ላይ እየኳተንኩ ነው።በድንገት ከፊት ለፊቴ አንድ መዝጊያ አየሁና ወደ ቅጥር ግቢው እየነዳሁ ስገባ መኖሪያ ቤት ሆኖ አገኘዋለሁ።የመጀመሪያ ሥጋቴ ያለፈቃድ ወደ ወላጆቼ ቤት በመመለሴ አባቴ ውሳኔውን እንደ ማስኩ ቆጥሮ ይቆጣኛል የሚል ነበር በድንጋጤ ከጋሪው ላይ ዘልዬ እንደ ወረድኩ እናቴ በጥልቅ ሐዘን ተውጣ ልትቀበለኝ ስትመጣ አየኋት ። "እሽሽሽ...!" አለችኝ ። አባትህ በጠና ታሟል — ከሞት አፋፍ ላይ ነው ። ሊሰናበትህ ይፈልጋል ። " በፍርሃት ደንዝዤ ተከተልኳት ። ጭልጭል የሚል ብርሃን ያለበት ክፍል ገባንና ፊታቸው በሐዘን የጨለመ ወንዶችና ሴቶች አልጋውን ከብበው አያለሁ። በቀስታ ወደ አልጋው ስቀርብ እናቴ መጋረጃውን ገለጥ አድርጋ፡" አንድሬ ፔትሮቪች፡ፔትሩሻ መጣኮ ፣ መታመምህን ሰምቶ ተመልሷል ። መርቀው " አለችው ። ተምበርክኬ ያን ሕመምተኛ ተመለከትኩት ። ግን ምን አየሁ መሰላችሁ ? በአባቴ ፋንታ በዚያ አልጋ ላይ ተጋድሞ በፈገግታ የሚመለከተኝ አንድ ባለጥቁር ጺም ገጠሬ ሆነ ። ግራ ተጋብቼ ወደ እናቴ መለስ አልኩኝና " ምን ማለትሽ ነው ? " በማለት ጠየቅኳት ። እሱ አባቴ አይደለም ። አንድ ገጠሬ እንዲመርቀኝ የምለምንበት ምን


t.me/OLDBOOKSPDF

ምክንያት አለ ? ” ግዴለም፣ ፒትሩሻ”አለችኝ እናቴ “በሠ ርግህ ላይ አባትህን ተክቶ ይገኝልሃል ። እጁን ሳምና ይመ ርቅህ ። ” እኔ ግን አልተስማማሁም ። በዚህ ጊዜ ገጠሬው ከአልጋው ዘሎ ወርዶ ፣ መጥረቢያ ከበስተጀርባው ካነሣ በኋላ በየአቅጣጫው ያወናጭፈው ጀምር ። እግሬ አው ጭኝ ለማለት ሞከርኩ . . . ግን ተሳነኝ ። ክፍሉ ሬሳ በሬሳ ሆነ ። ሬሳ እያደናቀፈኝና እየተንሸራተትኩ በደም ተለወ ስኩ ። አስፈሪው ገጠሬ በፍቅር ስሜት ድምፁን ከፍ አድ ርጐ “ አይዞህ አትፍራ ፣ ቀረብ በልልኝና ልመርቅህ ” አለኝ ። ፍርሃቱና መደናገሩ ሰነከለኝ ። . . . በዚያች ወቅት ነቃሁ ። ፈረሶቹ ቆመዋል ፤ ሳቬሊች እጅጌዬን እየጐተተ “ውረድ እንጂ ጌታዬ ፣ ደርሰናልኮ ” አለኝ ። “ ደርሰናል ? የት ? ” ስል ጠየቅሁት ዐይኔን እያሸሁ ። “ ከሆቴሉ ፣ በእ ግዜር ቸርነት ከአጥሩ ጋር ተጋጨን ። በል ጌታዬ ቶሎ ውረድና ሙቀት ወዳለበት ግባ ። ”

ከጋሪው ወረድሁ ። የበረዶው ብዛት ቢቀንስም ውሽ ንፍሩ እንደ ቀጠለ ነበር። ዙሪያው ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ተዳ ፍኗል ። የሆቴሉ ባለቤት በኮቱ ከለላ ፋኖስ አንጠልጥሎ በር ላይ ተቀበለን ። እኔም ወደ አንዲት ጠባብ ፣ ግን በመጠኑም ቢሆን ንጽሕናዋ የተጠበቀ ክፍል መራኝ ። አን ዲት ሻማ ብቻ ትበራበት ነበር ። አንድ ጠበንጃና በቅርፁ የመነኩሴ ቆብ የሚመስል የኮዛክ መለዮ ከግድግዳው ላይ ተሰቅለዋል ።

ባለሆቴሉ ስድሳ ዓመት ገደማ የሚሆነው ፣ ፈርጠም ያለና ንቁ ኮዛክ ነው ። ሳቬሊች የሻይ ማፍያ ቁሳቁስ የተከ ተተበትን ሣጥን ይዞ እየተከተለኝ ሻይ ለማፍላት እሳት ጠየቀ። እኔ ግን እስከዚህም አስፈላጊ አልመሰለኝም ። ባለ ሆቴሉ ራሱ ጉድ ጉድ ሲል ሔደ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

" የታለ መንገድ መሪያችን ? " ስል ጠየቅሁት ላቪ ሊችን ።

"እዚህ ነኝ ጌታው" የሚል ድምፅ ከበስተ እናቴ መጣ። ከፍ ብሎ ከማድግዳው ጋር ተያይዞ የተሠራውን ቆጥ እንጋ ጥጩ ስመለከት ጥቁር ጺምና ሁለት የሚንተገተጉ ዐይ ኖች አየሁ ። " ይበርዳል አይደል ወንድም ? " አልኩት ። "ይቺን ስስና የተበጫጨቀች ኮት ለብሼ እንዴት አይበር ደኝም ? " በማለት መለሰልኝ ። " አንድ ከ. ጕዛ የተሠራ ኮት ነበረኝ ። እውነቱን ልንገርዎት ፣ ትናንትና ማታ አን ድ መጠጥ ቤት አስይዤው ገንዘብ ተበደርኩ ። ውርጩ እን ዲህ የሚከፋ አልመሰለኝም ነበር ። " ወዲያው ባለሆቴሉ ትኩስ ሻይ የተሞላበት ጆበና ይዞ መጣ ። ለመንገድ መሪያ ችን አንድ ፍንጃል ሻይ ጋበዝኩትና ከቆጡ በአሳር በመከራ ወረደ ። ለየት ያለ ሰው ሆነብኝ ። ዕድሜው ወደ ሀርባ ዓመ ት የሚጠጋ መሆኑ አያጠራጥርም ። ቁመቱ መካከለኛ ፣ ቀጭንና ትከሻ—ሰፊ ነው ። ጥቁር ጺሙ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት ሲሆን ሕይወት የተመላባቸው ቦግ ያሉት ዐይ ኖቹ ያለማቋረጥ ይንከባለላሉ ። ገጹ የደስ ደስ ያለው ቢመስ ልም ተንኮልም ይነበብበታል።ጸጉሩን በኩዛክ ሞድ ተስተካ ክሏል። የተቀዳደደ የአጐዛ ኮትና ጠባብ ሱሪ ለብሷል። ሻሂ ውን አቀበልኩትና አንዴ ፉት እንዳለለት ፊቱን አጨማትሮ "ጌታዬ ፣ ላስቸግርዎትና አንድ ብርጭቆ ቮድካ ይዘዙልኝ፤ በኮዛኮች ዘንድ ሻይ እንደ መጠጥ አይቆጠርም " አለኝ ። ወዲያው ፍላጐቱን አሟላሁለት ። ባለሆቴሉ ጠርሙስና አንድ ብርጭቆ ከቁምሳጥን አውጥቶ ወደ እርሱ እየተጠጋ ፣ " አሆ ! ወደ አገራችን ተመልሰህ መጣህ ! ምንድን ነው የሚያመላልስህ ? " አለው ። መንገድ መሪዬ መልእክት ያዘለ የዐይን ጥቅሻ ካሳየው በኋላ መልሱን እንዲህ በመስለ እንቆቅልሽ አስቀመጠለት ። " ማሳ ገብቼ እሸት ስለቃቅም



t.me/OLDBOOKSPDF

እያቴ ድንጋይ ወረወረችብኝ ። ግን ሳተችኝ ! ለመሆኑ እካ ባቢያችሁ እንደዚት ነው ? ”

“ እኛ ? ” አለ ባለሆቴሉ እርሱም ምላሹን ክርር በማድረግ።ለምሽት ጸሎት ሕዝቡን በቤተክርስቲያን ይወል ልንሰበስብ አስበን ነበር ፣ ግን የቄስ ሚስት ከለከለችን ። ቄሱ የሉም ፤ ዲያብሎስም እየፈሶለ ነው ። “ ዝም በል እባ ክህ ! ” አለው መንገድ መሪያችን “ ዝናም ካለ እንጉዳይ ይፈላል ። እንጉዳይ ካለ ደግሞ ለመሰብሰቢያ የሚሆን ቅር ጫት አይታጣም ። ከእንግዲህ ” ሲል ( እንደገና ጠቀስ አድ ርጎት) መጥረቢያህን ፥ ዘጋጅ ፤ እንጨት ፈላጩ በአቅራ ቢያህ ነው ። ለክበርንትም ጤንነት ! በማለት ብርጭቆውን እንምቶ ካማተበ በኋላ ውስጡ የነበረውን በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው ። ከዚያም እጅ ነሥቶኝ ወደ መኝታው ሔደ ።

በዚያን ጊዜ ያህ የአሬዳ ቋንቋቸው አልገባኝም ነበር ። ውዬ አድሬ እንደ ደረስኩበት ግን፡የተነጋገሩት ለካስ በ1772 ዓ ም ዐመፅ አምንስተው ድል ስለ ተመቱ የያይክ ወታደሮች ኖሯል ። ሳቬሊች የተባባሉትን ሁሉ በከፍተኛ ቅሬታ ካዳ መጠ በኋላ ፥ ባለሆቴሉንና መንገድ መሪያችንን በጥርጣሬ ገረመማቸው ። ሆቴሉ የሚገኘው ከመንገድ ወጣ በማለ ቱና ሰው ከሚኖርበት አካባቢ በመራቁ የወሮበሎች ጉረኖ ሳይሆን አይቀርም የሚል ሥጋት አደረብኝ ። ነገር ግን ሌላ አማራጭ አልነበረንም ። ጉዟችንን ወዲያው የመቀጠሉ ጉዳይ የሚታሰብ አልነበረም።የሳቬሊች ጭንቀት አሣቀኝ። በበኩሌ ባለሁበት ሥፍራ ሌሊቱን ለማሳለፍ ቆርጬ ነበርና በአግዳሚው መቀመጫ ላይ ጋደም አልኩ ። ሳቬ ሊች ምድጃው ጠርዝ ላይ ተኛ ። ባለሆቴሉ ወለሉ ላይ ጎኑን አሳረፈ ። ወዲያውኑ ቤተኛው በሙሉ አንኳረፈ ። እኔም እንቅልፍ ድብን አድርጐ ወሰደኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በማግሥቱ ጠዋት እርፍጂ ስንቃ ማዕበሉ ጋብ ብሏል ፤ ፀሐይዋ ትፍለቀለቃለች ። በዚያ አውላላ ሜዳ ላይ የተን ጣለለው የበረዶ ምንጣፍ ያጥበረብራል ። ፈረሶቹ ተጭነ ዋል ፤ ለባለ ሆቴሉ የከፈልኩት ሒሳብ መጠነኛ በመሆኑ እዘውትሮ ይከራከር የነበረው ሳቬሊች እንኳ አልተቃወመም ። ያለፈው ሌሊት ጥርጣሬውም ከአእምሮው ጠፍቷል ። መንገድ መሪያችንን ጠርቼ ስለ እርዳታው ካመሰገንኩት በኋላ ፤ ለመጠጥ የሚሆነው ጥቂት ገንዘብ እንዲሰጠው ሳቬሊችን ነገርኩት ። ሳቬሊች ግምባሩን ቋጠረ ። “ ለመጠጫ እሚሆነው ! ” አለኝ ሳቬሊች ። ለምን ? መልካም ፈቃዱ ሆኖ ሆቴል ድረስ በጋሪ ስላደረስነው ? እንደፈቀድህ ጌታዬ ፤ በበኩሌ ግን እንዲህ በከንቱ የምናባክነው ገንዘብ የለንም ። ለመጠጫ እያልክ ላላፊው ላግዳሚው ገንዘብ ከሰጠህ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንተው ራስህ ልመና ትገባለህ ። ” ከሳቬሊች ጋር መከራከር አልቻልኩም ። ከዚህ ቀደም ቃል በገባሁት መሠረት ገንዘቤ በሙሉ ያለው በእርሱ እጅ ነው ። ከአደጋ ባይሆንም ከአንድ አሳሳቢ ሁኔታ ላወጣኝ ሰው ወሮታውን ልከፍል ባለመቻሌ ተበሳጨሁ ። “እሺ እንግዲያ ” አልኩት ረጋ ብዬ ። “ ገንዘብ እንዳልሰጠው ከፈለግህ ከልብሶቼ አንዱን እንኳ ስጠው ። በቂ ልብስ የለውም ። ”

“ ለምን ብዬ ጌታዬ ፖይቶር እንድሬይች ” አለ ሳቬሊች ። “ ምን ያደርግለታል ? ይኽ ልክስክስ ሰው ከሚቀጥለው መሸታ ቤት ሸጦት ይጠጣበታል ። “ ለመጠጥ ብሸጠው ባልሸጠው አንተን አያገባህም፤ ውዳቂ ሽማግሌ” አለው ያ ዱርዬ ብጤ መንገድ መሪያችን ። “ ክቡርነታቸው ኮታቸውን ሊሸልሙኝ ቆርጠዋል ፤ ደስታቸውም ነው ። አንተም አሽከር እንደ መሆንህ መከራከር ሳይሆን መታዘዝ አለብህ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" አንተ ቀጣፊ ፣ አታርፍም ? " ሲል ጮኸበት ሳቬ ሊች በቁጣ ። " ይህ ሰው ነገር አዙሮ የማያይ የዋህ መሆ ኑን ተገንዝበህ ልትዘርፈው አስበሃል ። የእርሱ ኮት ለአን ዳንተ ያለው ምን ያደርግልሃል ? ይህን ጠርብ እሚያህል ትከሻህን በትግል እንኳ ልታስገባበት አትችልም ። "

" ንትርኩን ተውህ " አልኩት ሳቬሊችን " ሒድና ኮቱን አምጣለት ። "

" የእግዚር ያለህ ! አለ ሳቬሊች እያቃሰተ ። "ኮቱ እኮ ገና አዲስ ነው፡ለአንድ ሰካራም ዱርአዳሪ ሊሰጥ ? . . . . "

ያም ሆነ ይህ ኮቱ መጣለት ። ሰውዬውም ወዲያውኑ ለካው ። ለኔ እንኳ ጠቦኝ የነበረው ኮት እሱንማ አስጨነ ቀው ። ሆኖም እንደምንም ታግሎ ሲያጠልቀው እጅጌው ተተረተረ ። ሳቬሊች የስፌቱን መተርተር ሲሰማ ሊጮህ ምንም አልቀረው ። ዱር አዳሪው ባደረግለት ስጦታ እጅግ ፈነደቀ ። ሠረገላው ድረስ ተከትሎኝ ራሱን ዝቅ አደርጉ "አመሰግናለሁ ክቡር ሆይ ፣ አምላክ ውለታዎን ይከፈልዎ። ውለታዎን ፈጽሞ አልረሳውም " ብሎኝ ሔደ ። እኔም የሳ ቬሊችን ንዝንዝ ቸል ብዬ ፣ የትናንቱን የበረዶ ውሽንፍር ፣ መንገድ መሪዬንና ቆዳ ኮቴን ሁሉ ወዲያውኑ ረስቼ ጉዞ ዬን ቀጠልኩ ።

ኦሬንበርግ እንደ ደረስኩ በቀጥታ ጄኔራሉ ዘንድ ሔድ ኩ ። በጣም ግዙፍ የሆነና ዕድሜ ያጕበጠው አንድ ሰው አየሁ። ያጕፈረው ጸጉሩ ሻሽ ይመስላል። አሮጌውና ቀለሙ የለቀቀው የደንብ ልብሱ የጥንት ጦረኛ ሲያስመስለው ካነ ጋገሩም ጀርመናዊ መሆኑ ያስታውቃል ። ያባቴን ደብዳቤ ሰጠሁት።ስሙን እንደ ሰማ በፍጥነት አየት አድርጎኝ "በተ ሰቀለው ! " አለ ። " አንድሬ ፔትሮቪች አንተን ያህል



t.me/OLDBOOKSPDF

የነበረበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ። ይገርማል ፤ አንተን የመሰለ ኅበዝ አድርስዋል ! ጊዜው እንዴት ይበራል ! ” ፖስታውን ከፍቶ ደብዳቤውን ዝቅ ባለ ድምፅ እያነበበ እግረ መንገዱን ይተቸው ጀመር ። “ ወዳጄ እንድሬ ካርሎቪች . . . ክቡርነትዎ . . . ተስፋ አለኝ . . . እቤት ሽርጉድ ስናበዛ ! ኤዲያ ! . . . ሊያፍርበት ይገባል ! በእርግጥ ሥነ ሥርዓት ከሁሉም መቅደም አለበት . . . ለአንድ የቀድሞ የልብ ወዳጅ እንዲህ ተብሎ ይጻፋል ? . . . ክቡርነትዎ አልረሳውም . . . እም . . . “ እናም ሚቹ ፊልድ ማርሻል ሚን . . . ዘመቻ . . . ካሮሊናካም . . . ” ኤዲያ ! የጥንቱን ጨዋታችንን አሁንም ያስታውሳል . . . “ አሁን ወደ ቁም ነገሩ ልመለስና . . . የኔን ማጋጣ እርስዎ ዘንድ ልኬዋለሁ . . . ” . . . “በብረት እጅዎ ጠበቅ አድርገው ይያዙት” . . . “በብረት እጅዎ ?” ሲል ያነበበውን መልስ በማስተጋባት ወደእኔ አዞረ ። “ በብረት እጅ ማለት ምን ማለት ነው ? አልገባኝም ” አለኝ ።

“ ይህን ሲል አባቴ ” አልኩት ምንም የማላውቅ የዋህ መስዬ ፡ “ በንክብካቤ እንዲይዙኝ ፣ ጥቃቱን እየተከላከሉልኝ በነጻነት እንዲያኖሩኝ ያለውን ፍላጉት መግለጹ ነው ” ስል በሰፊው አብራራሁለት ።

“ አሃ ! ገባኝ . . . ‘ ከልክ ያለፈ ነጻነት አትስጠው ’ ማለት አይደለማ ! ግንኮ የብረት እጅ ትርጉሙ አንተ እንደምትለው አይመስለኝም ” ብሎኝ ወደ ደብዳቤው ተመለሰ ።

“ . . . ‘ መታወቂያውን ከዚህ ጋር ልኬልሃለሁ . . . ’ . . . የት አለ ? አሃ ! ይኸውና . . . ‘ የሴሚኖቭ ክፍለ ጦር እንዲያውቀው . . . ’ መልካም . . . መልካም . . . ይሁና ! . . . ‘ ማዕረግህን እያከበርኩ እንደ ቀድሞ ጓድህና



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዳጅህ ሆኜ ሳቅፍህ ደፈረኝ አትበለኝ ' . . . እሃ ! ያሁኑ ይሻላል . . . ታዲያስ ጌታው ? " አለኝ ደብዳቤውን እንቦ ክጨረስና መታወቂያ ወረቀቱን ካኖረ በኋላ ። " እንደጠ የቀው ይፈጸምለታል ፣ በሆነ ክፍለ ጦር ውስጥ የመኰንን ንት ማዕረግ ይሰጥሃል ። ጊዜም ሳናባክን በነገው ዕለት ወደ ቪሎጉርስክ ጦር ሠፈር ሔደህ በስመ ጥሩና በተከበረው ካፒቴን ሚኖቭ ሥር ታገለግላለህ ። እዚያ ነው የእውነተኛ አገልግሎትን ምንነት የምትገነዘብና ሥነ ሥርዓትን የም ትማር ። ኦሬንበርግ ወስጥ የምታደርገው እንዳችም ነገር የለም ። ስንፍና ለጎረምሳ አጥፊው ነው ። እናም ዛሬ በምሳ ሰዓት ባገኝህ ደስ ይለኛል ። "

'ከደጡ ወደማጡ ! እናቴ ማኅፀን ውስጥ እያለሁ የከ ብር ዘብ ሃምሳ አለቃ መሆኔ ምን በጀኝ? ወደ ምን አመጣኝ' በማለት ራሴን ጠየቅሁ ። ጠረፍ ላይ የሚገኝ አገር ቂጥ የሆነ ጦር ሠፈር ልላክ ! ከአንድሬ ጋካርሎቪች ጋር ምሳ በላሁ — ሦስት ነበርን ፣ እሱ ፣ በዕድሜ የገፋው ልዩ ረዳቱ እና ራሴው ። ሰውዬው የለየለት ስስታም መሆኑ ከምግብ አቀራረቡ ያስታውቃል ። እኔን ወደ ተባለው ጦር ሠፈር በጥድፊያ መላኩም ምግቡን እንዳልጋራው ሳይሆን አይቀ ርም ። በሚቀጥለው ቀን ጀኔራሉን ተሰናብቼ ወደ ተባለው ጦር ሠፈር ተጓዝኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሦስት

### ምሽጉ

"በዚያ በቀዝቃዛው እና ምሽጋችን
ዳቦና ውሃ ነው ሁሌም ቀለባችን ።
ጠላትም ቢመጣ ሊገበይ ደስታ
ይቆየዋል ድግስ ፣ ምንም አያመንታ ።
የመድፍና ጥይት ወይም የባሩድ ጢስ
' በል ከስክስ ! ' ይባላል እስኪበቃው
ድረስ" (1742—1791) ኮሜዲ የተወሰደ)

የቬሎጉርስክ ምሽግ ከኦሬንበርግ ዐርባ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል ። መንገዱ የተሠራው የያይክን ወንዝ ገደልማ ጠርዝ ተከትሎ ሲሆን ወንዙ ገና ባይረጋም ጢም ብሎ የሚንኳለለው ውሃው በበረዶ ከተሸፈነው አካባቢው ጋር ሲነጻጸር ጠቆር ያለና አስፈሪም ነው ። የኪርጂዝ አውላላ ሜዳ ከወንዙ ግራና ቀኝ ለጥ ብሏል ። በሐዘንና በትካዜ ተጨብጬ ጥልቅ ሐሳብ ውስጥ ተዘፍቄያለሁ ። የጦር ሠፈር ሕይወት እምብዛም አላጓጓኝ ። የወደፊት አለቃዬን ካፕቴን ሚሮኖቭን በዐይነ ሕሊናዬ ስቀርፀው ፣ የማያፈናፍን ፣ ግልፍተኛ ፣ ከሥልጣኑ በቀር ለሌላው ሁሉ ደንታ የሌለው ፣ ለጥቃቅን ጥፋቴ እንኳ እያሰረኝ ከደረቅ ዳቦና ከውሃ ጋር ሊያጋትረኝ የተዘጋጀ ሽማግሌ መሰለኝ ። ቀኑ ድንግዝግዝ ብሏል ። በመጠነኛ ፍጥነት እየ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተጓዝን ነበር ። "ምሽጉ እሩቅ ነው ?" በል ነጂውን ጠየ ቅሁት ። "ብዙም አይርቅ ፤ ያው ይታያልኮ ።" ዙሪያዬን ቃኘት አደረግሁ ፤ ቀፋፊ ምሽጎችና ግምቦች ፍለጋ ። ሆኖም በአጠና አጥር ተከልለውና እፍግፍግ ብለው ከተሠሩ የእንጨት ቤቶች ሌላ ምንም አልታየኝም ። ከመንገዱ በስ ተቀኝ በረዶ በከፊል የሸፈናቸው ሦስት ወይም አራት የሚ ሆኑ የሣር ክምሮች ጉብ ጉብ ብለዋል ። በስተግራ ደግሞ አንድ የፈራረሰና ከአገልግሎት ውጭ የሆነ ወፍጮ ቤት ይገኛል ። "የታለ ምሽጉ ?" ብዬ ጠየቅሁት በመገረም ። "ያውና" አለኝ ነጂው ወደምን ሔድባት መንደር አቅጣጫ እያመለከተ ። ከበራፉ ላይ አሮጌ የብረት መድፍ አየሁ ። መንገዶቹ ጠባብና ስርጉጥጉጥ ያሉ ፤ ቤቶችም ትናንሽና አብዛኞዎቹም ባለሣር ክዳን ናቸው ። ነጂውን ወደ አዛዡ ቢሮ እንዲያመራ ነግሬው ከአንድ ደቂቃ በኋላ ሠረገላችን ከደሳሳ ቤተክርስቲያን አጠገብ ፤ ከአንዲት ጉብታ ላይ የተ ሠራች ጐጆ ደጃፍ ላይ ቆመ ። እኔን ለመቀበል ማንም ብቅ አላለም ። በረንዳውን ዐልፎ ወደ ውስጥ የሚያዘልቀውን በር ከፈትኩ ። አንድ አካለ ስንኩል ወታደር ከጠረጴዛው ላይ ፊጥ ብሎ አረንጓዴ የደንብ ልብሱን በሰማያዊ እራፊ ሲጥፍ ተመለከትኩ።መምጣቴን እንዲነግርልኝ ጠየቅሁት። "መግባት ይችላሉ ጌታዬ ፤ እቤት ናቸው" ሲል መለሰ ልኝ ። ንጹሕና ቅልብጭ ያለች ፤ በጥንት ዕቃዎች የተ ጌጠች ወደ አንዲት ክፍል ገባሁ ። ከአንድ ጥግ ላይ ሸክላ ሳህኖችና ሲኒዎች የያዘ ቡፌ ፤ በግድግዳው ላይ ደግሞ የአንድ መኮንን ዲፕሎማ በባለመስታወት ፍሬም እንዲ ሁም ከጉኑ የኪስትሪንና * የኦቻኮቭ ** ምሽጎች ሲወረሩ

---

* እ.አ.አ. በ1758 በሩሲያ ወታደሮች የተከበበ የጀርመን ምሽግ ሲሆን፣

** እ.አ.አ. በ1797 በሩሲያ ወታደሮች የተማረከ የቱርክ ምሽግ ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያሳዩ እንደነገሩ የተሳሉ ምስሎች፣"የሙሽሪት ምርጫ" እና " የውሮ ሥርዓተ ቀብር " የተሰኙ ሥዕሎችም ተሰቅለዋል ። የሱፍ ጃኬት የለበሰችና ሻሽ ራስዋ ላይ ሸብ ያደረገች እንዲት ባልቴትም ከመስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ ለች ። ባለ አንድ ዐይና የሆነ ሽማግሌ የደንብ ልብሱን እን ዳጠለቀ ከፊት ለፊቷ ቆሞ የያዘላትን የሱፍ ድር ታጠነጥና ለች ። " ምን ልርዳዎት ጌታዬ ? " ስትል ጠየቀችኝ ፣ ሥራ ዋን ሳታቋርጥ ። በጦሩ ውስጥ ለማገልገል እንደ መጣሁና መድረሴንም ለካፕቴኑ ማስታወቅ እንዳለብኝ ገለጽኩላት። ባለ አንድ ዐይናው ሽማግሌ አዛዡ ስለ መሰለኝ ወደ እርሱ ም ዞር አልኩኝ ። ሴትዮዋ ግን የጀመርኩትን ንግግሬን አቋርጣ ፣ "ኤቫን ኩዝሚች ወጣ ብሏል ። አባ ጀራዚምን ለመጠየቅ ነው የሔደው ። ሆኖም ግዴለም ፣ ጌታዬ ። እኔ ባለቤቱ ነኝ ። እንኳን ደህና መጡ ። ዐረፍ ይበሉ ፣ ጌታዬ " በማለት ገረዲቱን ጠርታ ሃምሳ አለቃው ዘንድ ላከቻት ። አጠገቤ ቆሞ የነበረው ሽማግሌ ስለእኔ የማወቅ ጉጉት ስላ ደረበት የተረፈችውን ዐይኑን እኔ ላይ ተከለ ። " ለመሆኑ የትኛው ክፍለ ጦር ውስጥ ነበሩ ? " ብሎ ጠየቀኝ ። መለ ስኩለት።" ያን የጦር ሠፈር ትተው ወደዚህ ለምን መጡ?" አለኝ ። በበላዩቼ ትዕዛዝ እንደ መጣሁ ነገርኩት ። " እንዲ ያው በመላ ከአንድ የክብር ዘብ መኰንን የማይጠበቅ ጥፋት በመፈጸምዎ ሳይሆን አይቀርም " በማለት ቀጠለ ያ ልብ አውልቅ ሰው ። " በል ፣ መቀባጠሩ ይብቃህ " አለችው ባልቴቷ ። " ወጣቱን ጉዞው እንዳደከመው አታይም ? ተወት አድርገው ፣ ጉሽ ! በል እጆችህን ከፍ እርስዎ ደግሞ ጌታዬ " አለችኝ ፣ "እንዲህ ከመሰለው ሩቅ ሥፍራ ስለ ተወረወሩ አይዘኑ ። ለእንደዚህ ያለው ዕጣ እርስዎ የመ ጀመሪያም የመጨረሻም አይደሉም ። እንዴ ከተላመ ዱትማ ከቁም ነገር አይጥፉትም ። አሌክሲ ኢቫኔቪች ሻብሪን ነፍስ በማጥፋት ወደ እኛ ከተዛወረ ይኸው ዘንድሮ



t.me/OLDBOOKSPDF

አራት ዓመት አለፈው። ያን ግድያ ለምን እንደ ፈጸመ አም
ላክ ይወቅ ። አዬ፣ እሱና የሆነ መቶ አለቃ ጐራዴዎቻቸ
ውን ታጥቀው ወደ ከተማው ዳር ይዘልቁና ይማዘዛሉ። አሌ
ክሲ ኢቫኒች በሁለት እማኞች ፊት ባላንጣውን በሆድዕቃ
ው ሻጠበት ። ምን ይደረግ ! ብቻ አያድርስ ማለት ነው ።"

ወዲያው አንድ ጀርጋዳ የኮዛክ ወጣት ሃምሳ አለቃ
ዘው አለ ። "ማክሲሚች" አለችው አሮጊቷዋ "ለመኰ
ንኑ ንጹሕ የመኖሪያ ክፍል ስጣቸው ።" "እሺ ፣ ቫሲሊሳ
ዬጐርቭና" ሲል መለሰላት ሃምሳ አለቃው ። "ክቡርነታ
ቸውን ከኢቫን ፖሊዥዬቭ ጋር ላዳብላቸው ?" "እንዴ ?
አይሆንም ፣ ማክስሚች" አለችው የካፕቴኑ ባለቤት ፣ "የ
ክፍል ባሁኑ ይዞታው እንኳ ተጣቧል ። ደሞም ኮ ፖሊዥ
ዬቭ ወዳጄ ነው ። የበላዮቹ መሆናቸውን አሳምሮ ያውቃ
ል ። በል መኰንኑን ይዘህ ሒድ . . ." "ስምዎን ማን ልበል
ጌታዬ ?" "ፒዮቶር አንድሮች" "ፒዮቶር አንድ ሮይችን
ወደ ሰሚን ኰዞቭ ዘንድ ውሰዳቸው ። የ ወስላታ እኮ
ይሄኔ ጉኛውን አትክልት ውስጥ ለቆታል ! ማክሲሚች ፣
ለመሆኑ አካባቢያችን እንዴት ነው ? "

"ሰላም ነው ፣ እግዜር ይመስገን !" አለ ኮዛኩ ፣ "ብቻ
የዐሥር አለቃ ፕሮኮሮቭና ዑስቲኛ ኑጐሌና መታጠቢያቤት
ውስጥ በአንድ ጣሳ ሙቅ ውሃ አምባጓሮ ፈጥረው ነበር ።"

"ኢቫን ኢግናቲች" አለች የካፕቴኑ ሚስት ባለ
አንድ ዐይናውን ሽማግሌ እያየች "ፕሮኮሮቭና ዑስቲኛን
አነጋግርና ጥፋተኛውን ለይ ። ታዲያ ሁለቱንም ቅጣቸው።
ማክሲሚች ፣ በል ሒድ ። ፓዮቶር አንድሬች ፣ ማክሲሚች
መኖሪያዎን ያሳይዎታል ። "

እጅ ነሥቼ መሰስ አልኩኝ። ሃምሳ አለቃው ከወንዙ
አፋፍ ላይ ፣ ከምሽጉ ዳርቻ ወደምትገኝ አንዲት ጐጆ ወሰ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደኝ ። የቤቱን አጋማሽ ሲሞን ከነቤተሰቡ ይዞታል ። ገሚሱ ለኔ ተሰጠኝ። ንጹሕ የሆነችና በካርቶን የተከፈለች አንዲት ክፍል ነች ። ሳቤሊች ጓዛችንን በመፈታታት ላይ ሳለ በጠ ባብዋ መስኮት በኩል ወደ ውጭ ተመለከትኩ ። ለጥ ያለው አውላላ ሜዳ ከፊት ለፊቱ ተንጣልሏል።ከቆምኩበት ትይዩ በጣት የሚቆጠሩ ጐጆዎች ሲኖሩ በመንገዱም ላይ ዶሮዎች ሽቅብ ቁልቁል እያሉ ይጭራሉ ። ሳሩ የያዘች አንድ አሮ ጊት ከቤትዋ ደጃፍ ላይ ቆማ ዓሣማዎቿን ስትጠራቸው እየ ፋገሩ ወደ እርስዋ ይንጋጋሉ ። ታዲያ እንዲህ ካለ ቦታ ላይ ነው አፍላ ዕድሜዬን እንዳሳልፍ የተፈረደብኝ ! ሐዘንና ትካዜ ዋጠኝ ። ከመስኮቱ ዘወር አልኩና እራት እንኳ ሳል በላ ተጠቅልዬ ተኛሁ ። ቅር የተሰኘው ሳቤሊች “ አይ እግዚአብሔር ! ደግሞ ዛሬ እህል አልቀምስም አለ ! ልጁ ቸው በሽታ ላይ ቢወድቅ እሜቴ ከቶ ምን ይሉኝ ይሆን ? ” እያለ ሲያጉተመትም አመሸ ።

በበነጋው ፡ ጠዋት መለባበስ እንደ ጀመርኩ በሩ ተከ ፈተ ። ቁመቱ አጠር ፡ ፊቱ ጠቆር ያለ ፡ መልከ ቀና ባይባ ልም ዛላው ያማረ ወጣት መኰንን ገባ ። “ በድንገት ልተ ዋወቅዎት በመምጣቴ ይቅርታ ” አለኝ በፈረንሣይኛ ። “ መምጣትዎን የሰማሁት ትናንት ነበር ። አዲስ ሰው ለማ የት ጓጓኝ ነበርና አላስችል ብሎኝ መጣሁ ። እዚህ እስከ ቆዩ እርስዎም በጥቂት ቀናት ውስጥ እንዲህ ያለ ስሜት ሳይ ደርስብዎ አይቀርም ። ” በጠቡ ምክንያት ከክብር ዘብ የተ ዛወረው መኰንን እንደሆነ ገመትኩ ። ወዲያውኑ ጓደኞች ሆነን ቁጭ አልን ። በጣም አስተዋይ የሚመስለው ሽቫ ሪን ፡ ቀልደኛና አሥቂኝ ነው ። አዛዡንና ቤተሰቡን ፡ ሕብ ረተሰቡንና ፡ ዕድሌ መርቶኝ የመጣሁበትን ይህን አካባቢ በስፋት ገለጸልኝ ። ልቤ እስኪፈርስ በመሣቅ ላይ እያ ለሁ ትናንት አዛዡ ቤት የደንብ ልብሱን ሲደርት ያየሁት



t.me/OLDBOOKSPDF

ወታደር ገብቶ በቫሲሊሳ ዩጎሮቭና ስም እራት ጠራኝ ። ሽቫሪንም ወደዚያው ሊወስደኝ ፈቃደኛ ሆነ ።

ከአዛዡ ቤት እንደ ተቃረብን ሐያ የሚሆኑ ሽማግሌ ዎች ፥ ደባባይ ላይ በሰልፍና በተጠንቀቅ ቆመው አየን ። የሁሉም ጸጉር ተጎንጉኖ እንደ ጅራት ወርዷዋል ። ሁሉም ባለሦስት ማዕዘን ኮፊያም እራሳቸው ላይ ደፍተዋል ። መለ ሎውና ንቁው አዛዣቸው ከፊት ለፊታቸው ቆሟል ። ፒጃ ማውን እንደ ለበሰ ነው ። ሽቫሪንና እኔን እንዳየን ቀረብ ብሎን በተለይ ለእኔ የማበረታቻ ቃላት ከወረወረልኝ በኋላ ወታደሮቹን ማለማመዱን ቀጠለ ። ቆሞ ማየቱ ምንኛ ደስ ባለን ። ነገር ግን ቫሲሊሳ ዩጎሮቭና ዘንድ እንድንሔድና ራሱም ፈጥኖ እንደሚደርስብንም ነገረን ። “ ከዚህ መቆ የቱ ያስለቻችኋል ብዬ ነው ! ” አለ ።

ቫሲሊሳ ዩጎሮቭና በትሕትና ተቀብላን እኔንም እንደ አንድ አብሮ አደግ ጓደኛዋ አስተናገደችኝ ። እካለ ስንኩሉ ወታደር ገበታውን በማዘጋጀት ገረዲቱን እየረዳት ነበር ። “ ዛሬስ ፡ ባለቤቴ ኢቫን ኩዝሚች የልምምዱን ሥራ ዋለ በት ” አለች የአዛዡ ባለቤት ፡ “ ፖላሻ ፡ የቤቱን ጌታ ና ምሳ ብላ በይው ፡ ማሻስ የታለች ? ” በዚህ ጊዜ ፊትዋ ክብ የሆነ ፡ ጽጌረዳ የመሰለችና ነዶ ጸጉሯን እንደ እንጆሬ በቀ ሉት ጆሮችዋ ሥር ወደኋላ የላገች የዐሥራ ስምንት ዓመት ገዶማ ኮረዳ ወደ ነበርንበት ክፍል ገባች ። መጀመሪያ ሳያት እምብዛም አልተሳብኩም ። የተመለከትኳትም በጥላቻ ዐይን ነበር ። ከዚህ ቀደም ሽቫሪን ስለማሻ እንከፍንት አጫ ውቶኛል ። ጥግ ይዛ በመቀመጥ ልብስ መስፋትዋን ቀጠ ለች ። ወዲያው የጉመን ሾርባ ቀረበ ። ቫሲሊሳ ዩጎሮቭና ባለቤትዋን ስላጣችው “ እንግዶች እየጠበቁ ነው . . . ሾር ባውም ቀዘቀዘ ፡ ልምምዱ ሊቆይ ይችላል ፡ ስዎቹ ላይ ለማ ንባረቁ እንደሆነ ገና ስፊ ጊዜ አለህ” በይው ብላ ፖላሻን



t.me/OLDBOOKSPDF

ላከችበት ። ብዙም ሳይቆይ ካፕቴኑ ባለ አንድ ዐይናውን ሽማግሌ አስከትሎ ብቅ አለ። "እስኪ ምን ይባላል ጌታዬ ? ምሳ ከቀረበ ዘመን የለውም ። አንተ ብትጠራም ቶሎ አል መጣ አልክ ።" "እይው . . . . አዳምጨኝ ቫሲሊስ ዩጉሮ ቭና" ሲል መለሰላት ኢቫን ኩዝሚች ፤ "ሥራ በዝቶብኝ እኮ ነው ። ሽማግሌዎቹን በማለማመድ ላይ ነበርኩኝ ።"

"እረ ወዲያልኝ እቴ !" አለች ባለቤቱ በማመና ጨቅ ። "ማለማመዱ ምን ሊጠቅማቸው ብለህ ? እነሱ እን ደሁ ጭራሽ የሚገባቸው አይደሉም ። አንተም ብትሆን ብዙም ዕውቀት የለህ ። ይልቅስ ከቤትህ ተቀምጠህ ጸሎት ብታደርስ ነው የሚበጅህ ። በሉ እንጂ ጉበዝ ወደ ገበታው ቅረቡ ።"

ለማዕድ ቀረብን ። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና አፍዋ ለአፍታ እንኳ ሳያርፍ በጥያቄ አጣደፈችኝ ። ወላጆችህ ማን ነበሩ ? በሕይወት አሉ ? የት ነው የሚኖሩት ? ሀብታሞች ናቸው ? አባቴ ሦስት መቶ ገባሮች እንዳሉት ስነግራት በመደነቅ ፤ "አጀብ ! አንዳንዱ ምንኛ ቱጃር ነው እናንተ ! የእኛ አገ ልጋይ ይችው ፖላሻ ብቻ ናት ። ቢሆንም ተመስገን ነው ። ኑሮዋችን እስከዚህ አያስከፋም ። የምናዝነው በማሻ ብቻ ነው ። ልታገባ ነው ። ጥሎሽዋ ምን እንደሚሆን ትገምታ ለህ ? አንድ ሚዶ ፤ አንድ መጥረጊያና አንድ የብር መሐ ለቅ ! አበስኩ ገበርኩ ጌታዬ ! ለዚያውስ ሁነኛ ሰው ቢመ ጣላት በጀ ። አለዚያ እኮ ዕድሜ ልክዋን ቆማ — ቀር ልት ሆን ነው ።" ማሻን አየት አደረግሁ ። ፊትዋ ቲማቲም መስ ሏል ። እንባዋም እሳህንዋ ላይ እየረገፈ ነበር ። አንጀቱን በላችውና ወዲያውኑ ጨዋታችንን ለመለወጥ አሰቤ ፤ "ባሽ ኪሮች ከምሽጋችሁ ላይ አደጋ ለመጣል አስበዋል የሚል ወሬ ሰው ብሎኝ ነበር" አልኩኝ ። "ለመሆኑ ከየት ነው የሰሙት ጌታዬ ?" ሲል ጠየቀኝ ኢቫን ኩዝሚች ። "እሬ



t.me/OLDBOOKSPDF

ንበርግ እያለሁ ነበር ” ብዬ መለስኩለት ። “ መሠረተ ቢስ ወሬ ነው ” አለ አዛገፉ ፤ “ እዚህ ሁሉም አማን ነው ። ባሽኪሮች ከፉኛ ደነግጠዋል ። ኩርኪዞችም ዋጋቸውን አግኝተዋል ። ከእንግዲህ ወዲያ እምብዛም አያስቸግሩንም ። ከቃጣቸው ግን ፤ እስከ ፀሥር ዓመት የማይረሱትን በትር ነው የማቀምሳቸው ። ”

“ ይህን ለመሰለ አደጋ በተጋለጠ ምሽግ መኖር ትያ ሳስባችሁም ? ” ስል ቀጠልኩ ጥያቄዬን ፤ ወደ ቫሲሊሳ ዬጎርቭና ዞር ብዬ ። እስዋም ስትመልስ “ ለምጄዋለሁ የኔ ጌታ፤ የዛሬ ሐያ ዓመት ከክፍለ ጦር ወደዚህ በተዛወርንበት ጊዜ እኒያ አረመኔዎች እንዴት ያስፈሩኝ እንደነበር የሚያውቀው ) ንድዬ ብቻ ነው ። ያን ጸጉራም ቆባቸውን ሳይ ወይም ጩኸታቸውን ስሰማ ልቤ ቀጥ የምትልብኝ ይመስለኝ ነበር—እውነቴን ነው የምልዎ ጌታዬ ! · አሁን ግን በጣም ስለተላመድኳቸው ፤ የሆነ ሰው መጥቶ እኒያ ወሮበሎች ለምግብ እንደሚያነፈንፍ ዱር አራዊት በምሽጉ ዙሪያ ይርመሰመሳሉ ቢለኝ ፍንክች አልልም ። ”

“ ቫሲሊስ ዬጎርቭና በጣም ደፋር ሴት ናቸው ” አለ ሽቫሪን ቀልጠፍ ብሎ ፤ ኢቫን ኩዝሚች ይመሰክራሉ ። ”

“ እንዴታ ” አለ ኢቫን ኩዝሚች ። “ እሷኮ እንደ ሐሞተ ቢሶቹ ሴቶቻችሁ አይደለችም ። ”

“ ማሪያ ኢቫኖቭናስ ? ” ስል ጠየቅሁ ፤ “ እሷም እን ደርስዎ ጀግና ነች ? ማሪያ ደፋር ናት ? ” አለች እና ትዮዋ ፤ በሽርደዳ ቃና ። “ አይደለችም ፤ ማሻ ቡቡ ነች ። ሌላው ይቅርና የጠበንጃ ተኩስ እንኳ እስካሁን ለመልመድ



t.me/OLDBOOKSPDF

አልቻለችም ፤ የተኩስ ድምፅ የሥራ አካላትዋን ያርገፈግ ፈዋል ። የዛሬ ሁለት ዓመት ልደቴ ሲከበር ባለቤቴ መድፍ እንዲተኮስ ባዘዘ ጊዜ የኔይቱ ጫጩት ተርበድብዳ ልትሞት ጥቂት ነበር የቀራት ። ከዚያን ወዲህ መድፍ ተኩሰን አናውቅም ። ”

ሁላችንም ከማዕድ ተነሣን ። ካፕቴኑና ባለቤቱ ወደ መኝታ ክፍላቸው ሔዱ ። እኔም ወደ ሸፋሪን ክፍል ሔጄ ሌሊቱን አብሬው አሳለፍኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አራት

### ፍልሚያው

"ጌታው ፡ እስኪ ተነሥ አድምጠህ ቃሌን ፤
በዶረትህ ልሻጥ ታማኝ ሾተሌን ፤
ወዶኋላም አልል ከቶም አልቦዝን ።"
(ከያኮቭ ክንያዝኒን ኮሜዲ)

ጥቂት ሳምንታት ዐለፉ ። የቬሎግርስክ ምሽግ ኑሮዬ የሚገፋና እንዲያውም የሚያስደስት ሆነ ። በአዛዡ ዘንድ ፍጹም ቤተኛ ሆንኩኝ ። አዛዥና ባለቤቱ ለምድር ለሰ ማይ የከበዱ ሰዎች ናቸው ። ለመኮንንነት የበቃው ኢቫን ኩዝሚች ያልተማረና የተራ ወታደር ልጅ ቢሆንም እውነ ተኛና ደግ ሰው ነው ። ሚስቱ ታዘዋለች ። ይህም ከአባግ ዶለሽ ጠባዩ ጋር ይሔዳል ። ቫሲሊሳ ዩጎሮቭና እንደግል ጎዳዋ የምታየውን ምሽግ እንዳሻት ታገዘበታለች ። ብዙም ሳይቆይ ማሪያ ኢቫኖቭና እኔን ማፈር አቆመች ። ጎደኛሞች ሆንን ። ውስጣዊ ስሜት የሚያብሰለስላትና አስተዋይ ወጣት ሆና አገኘኋት።ሳላውቀው በዚሁ ደግ ቤተሰብ መኻል ፍቅር መሠረትኩ ። ከገረዲቱ ጋር ይማግጣል በማለት ሽቫ ብሪን በአግቦ የሚወርፈውን ባላንድ ዐይና የክፍለ ጦሩን መቶ አሊቃ ኢቫን ኢግናቲችን እንኳን ሳይቀር ወደድኩት። መቶ አለቃው ገረዲቱን ወዷል የሚለው ጥርጣሬ መሠረት አልነበረውም፤ሆኖም ይህ ለሽቫብሪን ደንታ አልሰጠውም።


t.me/OLDBOOKSPDF

በተወሰነው ጊዜ የማዕረግ ዕድገት አገኘሁ ። ኃላፊነቴ ከባድ አልነበረም ። በዚህ ቀፋፊ ምሽግ ውስጥ ከሰልፍ ጉብኝት ፣ ከጦር ልምምድ ወይም ከዘብ ጥበቃ ነጻ ነበርኩ። አዛዡ ዐልፎ ዐልፎ ፣ ወታደሮቹን የማለማመድ ተግባሩን ቢገፋበትም ግራና ቀኛቸውን እንዲለዩ እንኳ ሊያስችላ ቸው ልበቃም ። እንዲያው ብዙዎቹ እንዳይሳሳቱ ስለሚ ፈሩ ቀኝ ኋላ በዞሩ ቁጥር ያማትቡ ነበር ። ሽቫብሪን ጥቂት የፈረንሣይኛ መጻሕፍት ነበሩት ። ማንባበብ ጀመርኩና የደራሲነት ፍላጐት ተሠረፀብኝ ። አዘውትሬ እያነበብኩ የትርጉም ችሎታዬን ከመሞከር ዐልፌ አንዳንዴም ግጥም እደረድር ጀመር ። በየዕለቱ ምሳዬን አዛዡ ቤት እየበላሁ ቀሪውን ጊዜዬን እዚያው አሳልፋለሁ ። አባ ጌራዚምና ድፍን ወረዳው የሚያውቃት የወሬ ቋት ሚስቱ እኩሊና ፖምፈሉቭና አንዳንድ ጊዜ ምሽት ላይ እዚያ ጐራ ይላሉ። ሽቫብሪንን እንኳ በየዕለቱ አገኘዋለሁ ። ነገር ግን ጨዋ ታው እያደር ከቸሮ ሆነብኝ ። በአዛዡ ላይ ድጋግሞ መቀ ለዱና ፣ በተለይም በማሪያ ኢቫኖቭና ላይ የሚሰነዝረው ሽሙጥ ከፉኛ አስቆጣኝ ። በምሽጉ ውስጥ የምቀርበው ሌላ ሰው አልነበረም ። እኔም ሌላ አልተመኘሁም ። ምንም እን ኳን ወሬው ቢስፋፋም ባሽኪሮች አንዳችም የዐመፅ ምል ክት አላሳዩም ። በምሽጋችን አካባቢ ሰላም ሰፍኗል ። ነገር ግን፣ ባልታሰበ የውስጥ አለመግባባት ጸጥታችን ደፈረሰ።

ራሲው ግጥም መጻፍ እንደ ጀመርኩ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ ። የዚያን ወቅት ሙከራዎቼ በጣም ጥሩ ነበሩ ። ከጥቂት ዓመታት በኋላም አሌግዛንደር ፒትሮቪች ሲማርኮቭ *እነዚያን ሙከራዎቼን ከልብ አድንቋቸዋል ።

---

* የ18ኛው ክፍለ ዘመን ደራሲና ለዘመኑ የሩሲያ ሥራዎች በአብነት የሚጠቀስ



t.me/OLDBOOKSPDF

በአንድ ወቅት የተዋጣለት ግጥም ለመድረስ ቻልኩ ። ደራ ሲያን ምክር የሚጠይቁ መስለው ጽሑፋቸውን በጥሞና የሚያዳምጣቸው ሰው ይፈልጋሉ ። ታዲያ እኔም የፍቅር ግጥም ከደረስኩ በኋላ ፣ በምሽት ውስጥ እንዲህ ያለውን ሥራ በመገምገም ብቸኛ ባለሞያ ወደሆነው ወደ ሽቫብሪን ዘንድ ወሰድኩት ። ለመግቢያ ያህል ጥቂት ቃላት ተናግሬ ከኪሴ የማስታወሻ ደብተሬን አወጣሁና ቀጥሎ ያሉትን ስንኞች አነበብኩለት ።

“ ከውበቷ ማሻ ራቅ ባልኩኝ ጊዜ
ገለል ይልልኛል ያ የፍቅርዋ አባዜ ፣
ያች የምወዳት ልጅ ካይኔ ስትሰወር
አገኛለሁ ፋታ እንደ ጐኔ ላድር ።
እኒያ ውብ ዐይኖችዋ ልብ የሚሰውሩት
ሰላም ነሥተውኛል ቀንም ሆነ ሌሊት ።
ፊቴ ላይ ሲያበሩ ያይንዋ ውጋገን
ድራሼ ይጠፋል ፣ እንዲያው ምን ልሁን !
አንቺ የኔ ማሻ የልቤ ወለላ
ተሠቃየሁልሽ ፈልጊልኝ መላ ፣
በድን ለሆነ ሰው ዝሎ በፍቅርሽ
ፍቱን መድኃኒቱ አንቺው ብቻ ነሽ ።
(ከሩሲያ ስብስብ ዘፈኖች የተወሰዱ) ”

“ ምንድነው አስተያየትህ ? ” ብዬ ጠየቅሁት ሽቫ ብሪንን ፣ አድናቆቱን እየተጠባበቅሁ ። ብዙውን ጊዜ ቀና አስተያየት ይሰጠኝ የነበረው ሽቫብሪን ግጥሜ ፈጽሞ እን ደማይረባ ገለጸልኝ ። በንዴት ጦፍኩ ። “ እኮ ለምን ? ” ስል ጠየቅሁት ንዴቴን በማመቅ ።

“ ምክንያቱም ” አለ ሲመልስልኝ “ እንደዚህ ያሉ ግጥሞች የአስተማሪዬን የባሲሊ ኪሪሊች ትሬድየኮቪስ ኪን የፍቅር ግጥሞች በሚገባ ያስታውሱኛል ። ”


t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን እንደ ተናገረ ማስታወሻዬን ወስዶ ሥራዬን ከፉኛ እያንኳሰሰ በያንዳንዱ መስመርና ቃል ላይ የከረረ ሒስ መስጠት ጀመረ። ትዕግሥቴ ስለ ተሟጠጠ ፣ ደብተሬን ከእጁ መንጪኩና ዳግመኛ ግጥሞቼን እንደማላሳየው ነገር ኩት ። ሸቫብሬን በዛቻዬ ሥቆ "እስቲ በቃልህ ስትገኝ እና ያለን " አለኝ ። " ኢቫን ኩዝሚች ከምሳ በፊት አንድ ወይም ሁለት ብርጭቆ ቮድካ መወርወር እንዳለበት ሁሉ ፣ ባለቅኔም አድማጭ ያሻዋል ። ለመሆኑ እምቡጥ የፍቅር ስሜትክን የምታውጅላትና እንዲህ ባለ የደስታ ሲቃ የም ታቅበጠብጥህ ይቺ ማሻ ማን ናት ? ማሪያ ኢቫኖቭና እን ዳትሆን ? " ሲል ሸቫሬን ጠየቀኝ ።

" ስለ ማንነትዋ አያገባህም !" አልኩት ፊቴን ከስ ክሼ ፣ " አስተያየትህንም ሆነ ፣ ሳታውቅ የምትቀባጥረ ውን ለመስማት አልፈልግም ። "

" እሆ ! ሆይ — ባሻው ባለቅኔና ትሑቱ ፍቅረኛ !" ሲል ቀጠለ ፣ ይበልጥ ሲያናድደኝ ። " ይልቁንስ የወዳጅ ነት ምክሬን ስማ ፣ እንዲሳካልህ ከፈለግህ ፣ የማይረባ ግጥም ከመደርደር ተቆጠብ ። "

" ምን ማለትህ ነው ? ለማለት የምትፈልገውን በግ ልጽ አስረዳኝ ! "

" በደስታ ፣ ማሻ ሚሮኖቭና ጀምበር ስታቆለቁል እን ድትጐበኝህ ከፈለግህ ፣ ከግጥም ይልቅ የጆሮ ጉትቻ አበ ርክትላት " ማለቴ ነው ።

ደሜ ፈላ ። " ለመሆኑ እስዋን እንዲህ የምታራክሳት ለምንድነው ? " በማለት ጠየቅኩት ቁጣዬን ለመቆጣጠር እየተሳነኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

" ምክንያቱም " አለኝ በማጥላላት እየገለፈጠ ፣ "ሞራልዋንና ዐመልዋን ከልምድ ስለማውቀው ነው ። "

" አንተ ወሽሽካታ ! መልቲ ! " ብዬ አምባረቅሁበት ፣ በቁጣ ። " ዐይን ያወጣህ ውሸታም ነህ ! "

ሸቫብሪን ፊቱ ዐመድ ለበሰ ። " ይህን ቃል በዋዛ አላልፈውም" አለ እጄን ለቀም በማድረግ። "እንፋለማለን።"

" ደስታውን አልችለውም ! በፈለግህ ጊዜ ! " ስል መለስኩለት በታላቅ እፎይታ ። በዚያች ሰዓት ጐማምጄ ብጥለው ዝግጁ ነበርኩ ።

ወዲያውኑ ኢቫን ኢግናቲችን ፍለጋ ሔድኩ።የአገልጋ ባልተቤት ባዘዘችው መሠረት ያ አዛውንት ለክረምት የሚሆን እንጉዳይ ለማድረቅ በመርፌ እየወጋ በክር ላይ ያንጠለጥል ነበር ። " ነወር ፣ ፖይቶር አንድሬይች ! " አለ ሲያየኝ ። "ግራ በል እንጂ ! ምን እግር ጣለህ በል ? ደፈረኝ አትበለኝና ምን ጉዳይ አለህ?" ከአሌክሲ ኤቫኒች ጋር መጣላቴንና እማኝ እንዲሆነኝ መፈለጌን ባጭሩ አስረዳሁት ። ኢቫን ኢግናቲች ያችኑ አንዲቱን ዐይኑን ከፈት ከደን እያደረገ በጥሞና አዳመጠኝ ። " የአሌክሲ ኢቫኒችን ሆድቃ ለመዘርገፍ ማሰብክንና ለዚሁ ምስክርነት እንድቆምልህ መሻትህን ነው የገለጽክልኝ ፣ አይደል ? "

" አዎን ጌታዬ ! "

" ሠዓሊ ለነ ቅድስት ! ምነው ፖይቶር አንድሬይች ! ምን ዐይነት ክፉ አስተሳሰብ ነው የተጠናወተህ ? ታዲያ ብትጣሉ . . . ስድብ አጥንት አይሰብር ። ቢሰድብህ መልሰህ ትሰድበዋለህ ፣ በጥፊ ቢያጮልህ ፣ ጆሮ ግንዱን ታጋልለታለህ ። እንዲያ ተባብላችሁ ትለያያላችሁ ፣ እኛም እናስ


t.me/OLDBOOKSPDF

ታርቃችኋለን እንጂ የጐረቤትህን ሆድቃ በጉራዴ ብትዘ ረግፍ ፣ መጨረሻው አያምርም ። ብታሳርፈውማ ባልከፋ ! አሌክሲ ኢቫኒች ፎጋንነብ ቢገባ ጉዳዬ አይደለም ። ጨርሶ አልወደውም ። እንዲያው ለነገሩ ፣ በጉራዴ ሆድቃህን የሚ ዘረግፈው እሱ ቢሆንስ ! ያኔ እንዴት ሊኮን ነው ? ምኑ ማን ሊሆን ነው በል ? ”

የአስተዋዩ መቶ አለቃ አስተሳሰብ አላስደነገጠኝም ። በአሳቡ ጠናሁ ። “ እሱስ እንደ ፈቀደህ” አለ ኢቫን ኢግና ቲች ። “የሚበጅህ የመሰለህን አድርግ ። ግን እኔ ለምንድ ነው የማየው ? ከቶ ለምን ? ሰዎች ለእንዲያ የመሰለው ጥፋት ሲፋጠጡ አይቼ የማላውቅ መስሎህ ይሆን ? ከቱርኮ ችና ከስዊድኖች ጋር ተዋግቻለሁ ። በጊዜዬ እስኪበቃኝ ድረስ ውጊያ አይቻለሁ ። ”

የእማኝ ተግባር ምን እንደሆነ በሚቻለኝ መንገድ አስ ረዳሁት ። ሆኖም ኢቫን ኢግናቲች የምለው ሊገባው አል ቻለም ። “እንዳልክ ጌታዬ” አለኝ ። በመቀጠልም “በዚህ ጉዳይ ያለኝ ድርሻ ፣ የመንግሥትን ዓላማ የሚፃረር አስከፊ ተግባር በምሽጋችን ውስጥ ሊፈጸም እየታቀደ መሆኑን ለኢቫን ኩዝሚች ማሳወቅና አዛዡም መልካም ፈቃዱ ሆኖ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማሳሰብ ብቻ ነው ። ”

በጣም ስለሠጋሁ ፣ ለአዛዡ እንዳይናገርብኝ አጥብቄ ተማፀንኩት ። በእሣር በመከራም እሺ አሰኘሁት ። በመ ጨረሻም ትንፍሽ እንደማይል ቃል ገብቶልኝ ተለያየን ። ምሽቱን እንደ ወትሮዬ አዛዡ ቤት አሳለፍኩኝ። ለጥርጣሬ መንገድ ላለመክፈትና ሊሰነዘሩብኝ የሚችሉ ጥያቄዎችን ለማስወገድ ስል ደስተኛና ግዴለሽ መሰልኩ ። ሆኖም አድ ራጐቱ ፍርሃት ያደረባቸው ሰዎች ፍራቻቸውን በጉራ እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚሸፋፍኑት ዐይነት ነበር ለማለት አልፈልግም ። በዚያን ምሽት ሆዴን ባር ባር እያለው እንደ መተከዝ ብዬ ነበር። ማሪያ ኢቫኖቭና እንደዚያን ዕለት ማራኪ ሆና የታየችኝ ጊዜ የለም ። ምናልባትም ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ ነው የማ ያት ብዬ በማሰቤ የሚሳሱላት ዐይኖቼ ተጨማሪ ውበት አላብሰዋት ሊሆን ይችላል ። ሽቫብሪንም እዚያው ነበር ። ወደ ጐን ሳብ አድርጌው ፣ ከኢቫን ኢግናቲች ጋር ስለተነ ጋገርነው አወሳሁት ። " ምን ምስክር ያስፈልጋል ?" አለኝ ረጋ ብሎ " ያለ ምስክር ልናደርገው እንችላለን ። " ከም ሽት እምብዛም ሳይርቅ ከሚገኘው የሳር ክምር ጀርባ በማግ ሥቱ ጠዋት ልክ በአንድ ሰዓት ለመገናኘት ተስማማን ። የባልንጀርነት ጭውውት የምናደርግ ስለ መሰለው ኢቫን ኢግናቲች ደስታ ልቡን ፈንቅሎት ፣ አፉን ነጠበው ።" እን ዲያ ነው እንጂ !" አለ ፊቱ በደስታ ፈክቶ ። " ከኩር ፊያ ይልቅ የሆድን በሆድ አምቆ መጨዋወት ይሻላል ። ከመሞት መሰንበት ይበጃል ።"

" ምን አልክ ኢቫን ኢግናቲች ?" ስትል ጠየቀችው የአዛዡ ባለቤት ። ጥግ ይዛ በካርታ ትጠነቁል የነበረችው " ያልከውን አልሰማሁም ። "

ኢቫን ኢግናቲች የቅሬታ ምልክት ፊቴ ላይ በማን በቡና የገባውን ቃል በማስታወስ ፣ ስለ ተደናገረው ምን መልስ እንደሚሰጣት ቸገረው ። ሽቫብሪን ፈጥኖ ቀበል አደረገና ፣ " ኢቫን ኢግናቲች እንደገና በወዳጅነት ተሳ ስረን በማየቱ ፈንድቋል " አላት ።

" ከማን ጋር ነበር የተጣላኸው ጌታዬ ?"

" ፖይቶር አንድሬይች እና እኔ እጅግ ከባድ ክርክር ገጥመን ነበር ።"

" ስለምን ?"


t.me/OLDBOOKSPDF

"አይ ፣ አይረባም ! ዘፈን ነው ፣ ቫሲሊሳ ዩጎሮሮቭና።

" ዘፈን ? ይኸስ የሚያጣላ አይደለም ። ለመሆኑ ጠቡ እንዴት ተነሣ ?"

" እንዲህ ነበር ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ፖይቶር ፖንድሬቭ አንድ ግጥም ቢጤ ጽፎ እፊቴ አንጐራጐረ ። እኔም የምወዳትን ስንኝ አነበነብኩለት ።

' የካፕቴኑ ልጅ ከትት በይ ቢትሽ

በጨፈረቃ ብርሃን መዞር ይቅርብሽ ።'

በዚህ ዓይነት በመካከላችን ጠብ ተጫረ ። ፖይቶር ሊያመር ቃጥቶት ነበር ። ግን ማንጐራጐር መብቱ እንደ ሆነ ወዲያው ተገንዝቦ ነገሩ በዚሁ አከተመ ። "

የሽቫብሪን ብልግና ክፉኛ አስቆጣኝ ። ግን እንደ እሳት የሚጋረፍ አሽሙሩን ከኔ በቀር ማንም አልተረዳ ውም ፤ ማንም ቁም ነገር አላለውም ። የዘፈን ጉዳይ በመነ ሻቱ ባለ ቅኔዎችን የሚመለከት ጭውውት ቀጠለ ። አዛዡ ባለቅኔዎች ጊዜያቸውን በዋዛ በፈዛዛ የሚያጠፉ ሰካራም መሆናቸውን ፤ ግጥም መድረስ ከውትድርና አገልግሎት ጋር እንደማይጣጣምና እንደማይጠቅም ገልጾ መጻፌን እን ድተው የወዳጅነት ምክሩን ለገሡኝ ።

የሽቫብሪን መኖር ትዕግሥቴን አሟጠጠው ። ወዲ ያው ብድግ ብዬ አዛዡንና ቤተሰቡን ተሰናበትኩ ። ቤቴ ተመልሼ ጐራዴዬን ከፈተሽኩ በኋላ ጉሀ ሲቀድ እንዲ ቀሰቅሰኝ ሳቬሊችን አዝዤው ተኛሁ ። በበነጋው በቀጠ ሮው ሰዓት ከግሩ ክምር ጀርባ ሆኜ ባላንጣዬን እጠባበቅ ጀመር ። ብዙም ሳላስጠብቀኝ ። " እንዳንያዝ መፍጠን አለብን" አለኝ ከቦታው እንደ ደረሰ ። ልብሶቻችንን አው



t.me/OLDBOOKSPDF

ልቀን በውስጥ ሱሪና በካናቴራ ቆምን ፤ ጉራደ፮ዎቻችን መዘዝን ። ኢ.ቫን ኢ.ግናቲች አራት ወይም አምስት ከሚ. ሆኑ ወታደሮች ጋር ከሣሩ ክምር በስተጀርባ ድንገት ብቅ ብሎ ወደ አዛገፉ እንድንሔድ ጠየቅን ። በከፍተኛ ቅሌት እጃችንን ሰጠን ። ወታደሮቹ ከበቡንና ኢ.ቫን ኢ.ግናቲችም በኩራት ስሜት እየመራን ወደ ምሽጉ ሔድን ።

አዛገፉ ቤት ገባን ። ኢ.ቫን ኢ.ግናቲች በሩን በርግዶ“ አምጥቻቸዋለሁ !” አለ ተኩሳትሮ ። ከቫሲ.ሊ.ሳ ዩገሮቭና ዘንድ ቀረብን ። “ የፊ.ጣሪ ያለህ ! ምንድነው ይህ ሁላ ? ምን ? በምሽ.ጋችን ውስጥ ነፍስ ለማጥፋት ማሴር ! ኢ.ቫን ኩዝሚ.ች ! በል አሁኑኑ ጠፍርልኝ ! ፓዩተር እንደ ሬች ! አሌክሲ. ኢ.ቫኔች ! ! ጉራዲ.ዩችሁን አስረክቡ ! አሁኑኑ አስረክቡ ! ፖላሻ ፡ ጉራደ፮ዎቹን ከቁም ሳጥኑ ውስጥ አኑሪ ። ፓዩቶር አንድሬይች ! አንተም እንዲህ ታረግ ? አታፍርም ? አሌክሲ. ኢ.ቫኒች ሰው አይምሰልህ ። ከነበረበት ወደዚህ የተዛወረው ሰው በመግደሉ ነበር ፤ እግዚ.አብሔር የተጣላው ነው ። ግን እንዲ.ያው ፡ አንተ ፤ አንተም እንደሱ መሆን ትፈ.ልጋለህ ?”

ኢ.ቫን ኩዝሚ.ች ከሚስቱ ጋር ሙሉ በሙሉ ተስማ ምቶ እየደ.ጋገመ ፡ “እውነቱን ልንገራችሁ ፤ ቫሲ.ሊ.ሳ ዩጉሮ ቭና ትክክል ነች ። በውትድርና ዓለም እንዲ.ያ ያለ ፍል ሚ.ያ አጥብቆ የተከለከለ ነው” አለ ። በዚ.ሁ መካከል ፖላሻ ጉራደ፮ዎቻችንን ከእኛ ወስዳ ከቁም ሳጥን ውስጥ አስቀ መጠች ። ሣቄን መቆጣጠር ተሳነኝ ። ሽቫብሪን ግን በጉራ እንደ ተወጠረ ነበር ። “ክብርዎ እንደ ተጠበቀ ሆኖ” አላት ቫሲ.ሊ.ሳ ዩጉሮቭናን ረጋ ብሎ ። “ እኛን ለመዳኘት እራስ ዎን መሰየምዎ አግባብ አለመሆኑን ለመግለጽ ወደ ኋላ አልልም ። ይህን ለኢ.ቫን ኩዝሚ.ች ይተውት ። የእርሳቸው ጉዳይ ነው “አለ ። እረ ገኝ !” አለች የአዛገፉ ሚስት ቁጣዋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገንፍሎባት ። “ ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል አይደሉም እንዴ ? ኢቫን ኩዝሚች ! ለምን አንድ ነገር አታደርግም ? በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ አስረህ የሰፈረባ ቸው ሰይጣን እስኪለቃቸው ድረስ ከደረቅ ዳቦና ውሃ ጋር ብቻ አጋትራቸው ፤ አባ ጄራዚም ንስሐ እንዲያስገቡዋ ቸውም አድርግ ፤ ምሕረቱን እንዲያወርድላቸው ፤ እግዚ አብሔርን እንደሚማፀኑና ለፈጸሙት ኃጢ' ት በአደባባይ እንዲጸጸቱ ።”

ኢቫን ኩዝሚች የሚያደርገው ቸገረው ። የማሪያ ኢቫ ኖቭና ፊት ዐመድ መስሏል ። ቀስ በቀስ ማዕበሉ ጋብ አለ ። የአዛገዡ ሚስት ቁጣዋ በርዶላት አሳሳመችንና ፖላሽ ጉራ ዴዎቻችንን መለሰችልን ። የታረቅን መስለን ከቤት ሹልክ አልን ። ኢቫን ኢግናቲች ተከተለን ።“ እንደማትናገር ቃል ከገባህልኝ በኋላ በእኛ ላይ በማሳበቅህ ልታፍር ይገባ ሃል ” አልኩት በቁጣ ። እሱም ሲመልስ “ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ፤ ለኢቫን ኩዝሚች አልተናገርኩም። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ነች ያውጣጣችኝ ። ሁሉንም ያቀነባበረችው እሷው ነች ፤ አዛገዡ ሳያውቀው ። ነገሩ በዚሁ በማክተሙ ለፈጣሪ ምስጋና ይግባው።” ይህን ተናግሮ ወደ ቤቱ ሔደ። ሽቫብሪንና እኔ ብቻችንን ቀረን ።“ ጠባችን በዚህ ሊያቆም አይችልም ” አልኩት ። “ በፍጹም !” ሲል መለሰልኝ ሽቫብሪንም ። “ ለብልግናህ ምላሹን የምትሰጠው በደ ምህ ነው ፤ ግን ምናልባት ባያነቁራኛ እየተከታተሉን ይሆናል ። ለጥቂት ቀን ጓደኛሞች መስለን እንቆይ ።ደህና ሁን !” ምንም ቁርሾ በመካከላችን እንደ ሌለ አስመስለን ተለያየን ።

ወደ አዛገዡ ቤት ተመልሼ እንደ ተለመደው ማሪያ ኢቫኖቭና አጠገብ ዐረፍ አልኩ ። ኢቫን ኩዝሚች ከቤት አልነበረም። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭናም በጓዳ ሥራ ተጠምዳለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከማሪያ ጋር በሹክሹክታ እናወራ ጀመር ። ከሽዋብሪን ጋር
መጣላቴን ሁሉንም ጭንቀት ላይ እንደ ጣላቸው በማው
ሳት በለዘበ እንደበት ተቆጣችኝ ። "በጉራዴ ለመፋለም
ማሰብክን በነገሩኝ ጊዜ ፤ ነፍሴን ልስት ምንም አልቀረኝ"
አለች ፤"ወንዶች ስትባሉ ግርም ትሉኛላችሁ ። በሳምንት
ውስጥ ልትረሱት በምትችሉት ጉዳይ ለመጋደል እየተጋ
በዛችሁ የገዛ ሕይወታችሁን ብቻ ሳይሆን ሕሊናችሁን በመ
ሳታችሁ የቤተሰቦቻችሁን ደህንነት . . . አጉል መሥዋዕት
ብቻ ቆስቋሹ አንተ እንዳልነበርክ እርግጠኛ ነኝ ። ሽቫብ
ሪን መሆን አለበት ። "

"እንዲህ ያሰኘሽ ምን ይሆን ማሪያ ኢቫኖቭና?"

"እኔ እንጃ ! . . . ሁሌ ያንንጥጠኛል አሌክሴ ኢቫ
ኒችን አልወደውም ፤ አልወደውም ። ከመሬት ተነሥቶ ስለ
ጠላኝ በጣም ነው የማዝነው ።ጥላቻው ያስጨንቀኛል ።

"ግንኮ . . ማሪያ ኢቫኖቭና እሱ እየወደደሽ አንቺ
ስለማታቀርቢው ይሆናል ።" ማሪያ ፊትዋ ፍም መሰለ ።

"ይመስለኛል " አለች በመንተባተብ ።

"እንዲያ የሚያሰኝሽ ምንድን ነው ? "

"እንዳገባው ጠይቆኝ ነበራ ።"

"ሊጋብቻ ጠየቀሽ ? እውነት ጠየቀሽ ? መቼ ?"

"አምና ! አንተ ከመምጣትህ ከአንድ ወይም ከሁ
ለት ወር በፊት ። "

"እና አልተቀበልሽውም ?"

"እንደምታየው ነው ። አሌክሴ ኢቫኒች የወጣለት
መሠሪ ነው።በእርግጥም ከጨዋ ቤተሰብ ነው የተወለደው፤



t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብትም አለው ። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ጋብቻ ፈጽሜ በሕዝብ ፊት ስስመው ማሰቡ ! . . . የመጣው ቢመጣ ፤ መሬት ከፍ ሰማይ ዝቅ ቢል አላደርገውም !”

ማሪያ ኢቫኖቭና የተናገረችው ዐይኔን ከፈተልኝ ። ብዙ ነገር አብራራልኝ ። ሽቫብሪን ሥራዬ ብሎ ሳያሥልስ በጥላቻ የሚያብጠለጥላት ለምን እንደሆነ ተረዳሁ ። ምናልባትም ልብ ለልብ መቀራረባችንን አይቶ በመካከላችን ተንኮል ለመሸረብ መሞከሩ ይሆናል ። ለጠባችን መነሻ የሆኑት ቃላት ቀጥተኛ ዘለፋ ከመሆናቸውም በላይ ፤ ሆን ተብለው ስም ለማጥፋት የተሠነዘሩ መሆናቸውን በተገነዘብኩ ጊዜ ይበልጥ ወራዳ ሆኖ ታየኝ ። ይህን ጋጠ ወጥ ስም አጥፊ ለመቅጣት ያለኝ ፍላጎት በረታብኝ ። አጋጣሚውንም በመቁነጥነጥ ጠበቅሁ ።

ብዙም አልጠበቅሁ ። በሚቀጥለው ቀን አንድ የሐዘን ግጥም በመጻፍ ላይ ሆኜ የብዕሬን ጫፍ እየነካከስኩ ቤት የሚመታ ቃል ስፈልግ ፤ ሽቫብሪን ከመስኮቴ ሥር ያለውን ግድግዳ መታ መታ አደረገ ። ብዕሬን አሽቀንጥሬ ጥዬ ፤ ጐራዴዬን ይዤ ወጣሁና ወደ እርሱው ተንደረደርኩ። “ ለምን ጊዜውን እናራዝማለን ?” አለኝ ሽቫብሪን ። “ አሁን ማንም አያየንም ። ወደ ወንዝ እንውረድ ። ከዚያ ማንም ገላጋይ አይደርስብንም ። ” ድምፃችንን አጥፍተን ገሠገሥን ። ጠመዝማዛውን መንገድ ይዘን ቁልቁል ከወረድን በኋላ ከወንዙ አፋፍ ላይ ቆመን ጐራዴዎቻችንን መዘዝን ። ሽቫብሪን የጐራዴ አሰነዛዘር ችሎታው ከእኔ የላቀ ነበር ። እኔ ደግሞ የድፍረትና የጉልበት ብልጫ ነበረኝ ። በአንድ ወቅት በጦር ሠራዊትነት ያገለግል የነበረው ሙሴ ቦፕሬ በሻምላ አመካከትና ስንዘራ የሰጠኝ ትምህርት ጠቀመኝ ። ሽቫብሪን እኔን እንዲህ ያለ አደገኛ ተፋላሚ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይወጣዋል ብሎ አላሰበም ነበር ። ለረጅም ጊዜም ለመጉዳዳት አልቻልንም ። በመጨረሻም ሽቫብሪን መዳከም ጀምሮ በአዲስ ጉልበት እያጠቃሁት ወደ ውሃው አስገድጄ ላስገባው ጥቂት እንደቀረኝ ድንገት በከፍተኛ ድምፅ ስሜ ሲጠራ ሰማሁ ። ዙሪያዬን ስማትር ሳቬሊች በተራራማዋ መንገድ ወደ እኔ እሽቆልቁሎ ሲሮጥ አየሁት ። ወዲያው ከቀኝ ትከሻዬ ሥር በደረቴ በኩል ሹል ነገር ሲሽጥብኝ ተሰማኝ ። ራሴን ስቼ እንዘፍ አልኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አምስት

### ፍቅር

" አንቺ ሊጋ ወጣት እንዳላገባሽ
ዕድሜሽ አልፈቀደም ገና ትንሽ ነሽ !
አማክሪያቸው እስቲ ወላጆችሽን ፤
እንዲሁም ጠይቂ ዘመድ አዝማድን ፤
ጥሎሽ እስኪመጣ ፤ ላቅ እስኪል ብስለትሽ
አንቺ የደም ገምቦ ትዕግሥቱን ያድልሽ !
እኔን የሚያስንቅ ሰው ድንገት ቢያጋጥምሽ ፤
አይጠረጠርም እኔን ቸል ማለትሽ ።
ምናልባትም ያ ሰው ከሆነብሽ እንከፍ
ከልብሽ አልወጣም ሕይወትሽ እስከታልፍ ።"

ነፍሴ መለስ ቢልልኝም የሆነውን ለማስታወስ ጊዜ ፈጀብኝ ። በማላውቀው ክፍል ውስጥ አልጋ ላይ ተጋድሚያለሁ ። ብርቱ ድካም ተጫጭኖኛል ። ሳቢሊች ሻማ በእጁ ይዞ አልጋዬ አጠገብ ቆሟል ። የሆነ ሰው በትከሻዬና በደረቴ ዙሪያ የተጠመጠመውን ፋሻ እየተረተረ ነው ። ቀስ በቀስ ነገሩ ወለል አለልኝ ። ፍልሚያውን አስታወስኩና መቁሰሌን ተረዳሁ ። ወዲያው መዝጊያው ተንሳጠጠ። "እንዴት ነው?" የሚል በሡራ አካላቱ የሚርመሰመስ ሹክሹክታ ጆሮዬ ገባ።"ያው ነው" ሲል መለስ ሳቢሊች እያዘነ " በድን እንደሆነ ይኸው አምስት ቀኑ ።" አልጋው ውስጥ ለመገለባበጥ ብሞክር ተሳነኝ ። " የት ነው ያለሁት ? ማን



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ?" አልኩኝ የሞት ሞቴን ። ማርያ ኢቫኖቭና ወደ እል ጋዬ ጐንበስ በማለት "እንዴት ነህ ?" አለችኝ ። "ይመ ስገነው" ብዬ መለስኩላት በሰለለ ድምፅ ። "ማሪያ ኢቫ ኖቭና ነሽ እንዴ ? ንገሪኝ እንጂ . . ." ለመቀጠል አቅም ስላነሰኝ ዐረፍተ ነገሩን ከመኻል ላይ አቋረጥኩት ። ሳቬ ሊች ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ። ፊቱ በደስታ ፈካ። "ነፍስ ዘርቷል ! ፈጣሪ ሆይ ፣ ምስጋና ይግባህ !" ሲል ደጋግሞ ተናገረ ። "አይ ፖይቶር አንድሬች ፤ አስደንግጠኸኝ ነበር እኮ ጌታዬ ! እስቲ እንዲያው ይታይህ፤አምስት ቀን ሙሉ" እያለ ሲተክዝ ማሪያ ኢቫኖቭና ከአፉ ነጥቃው "ብዙ አታ ናግረው ሳቬሊች ፤ ገና ሰውነቱ አልጠናምኮ" በማለት በሩን ዘግታ ሔደች ። ብዥ እንዳለብኝ ነበር ። ለካስ አዛዡ መኖሪያ ቤት ነው ያለሁት ። ማሪያ ኢቫኖቭናም ጠያቂዬ ኖራለች ። ለሳቬሊች አንዳንድ ጥያቄ ባቀርብለት አንገቱን ነቅንቆ ጆሮ ዳባ ልበስ አለ ። በንዴት ዐይኖቼን ጨፍኘ አሸለብኩና ሁሉንም ነገር ወዲያው ረሳሁ ።

ስነቃ ሳቬሊችን አስጠራሁት ። በእርሱ ፈንታ ግን ማሪያ ኢቫኖቭናን ከአጠገቤ አገኘኋት ። እርሷም እንደ ሙዚቃ በሚጥም ድምጽዋ ሰላም አለችኝ ። በዚያች ሰዓት በሁለንተናዬ የተሠራጨውን የፍቅር ወላፈን ጣፋጭነት በቃላት ልገልጸው አልችልም ። እጅዋን ለቀም አድርጌ በደስታ እንባ አጠብኩት ። እርሷም ልትነጥቀኝ አልሞከረ ችም ። እንዲያውም የዋህነት የተላበሰ የፍቅር ስሜት ፈን ቅሏት በከንፈሮችዋ ጉንጮቼን አበስ አደረገቻቸው ። በሠራ አካላቴ የፍቅር ነበልባል ተንቀለቀለብኝ ። "ውዲቷና ደግዋ ማርያ ኢቫኖቭና" አልኳት "ሚስቴ ሁኚ ፤ ቀሪ ሕይወቴን እንደምታስደስችኝ ቃል ግቢልኝ !" እስዋም ተረጋጋችና ፣ "ስለ እግዜር ብለህ፤አደብ ግዛ" አለችኝ እጅ ዋን በመሰብሰብ ። "ገና አልዳንክም ፤ ቁስሉ ሊያመረቅዝ


t.me/OLDBOOKSPDF

ይችላል ። ሌላው ቢቀር ለእኔ እንኳ ስትል ራስህን ጠብቅ’’ በማለት የደስታ ሲቃ ውስጥ እስጥማኝ ከክፍሉ ወጣች ። ደስታ ሕይወት ዘራልኝ ። የእኔው ትሆናለች ! ታፈቅረኛለች ! አእምሮዬ በዚሁ ስሜት ተዋጠ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያደር ጤንነቴ ተመለሰ ።በክፍለ ጦሩ ውስጥ ሌላ ሐኪም ባለመኖሩ የሚንከባከበኝ የክፍለ ጦሩ ጸጉር አስተካካይ ነበር ። እግዜር ይስጠው ፡ እንዳችም የሕክምና ሙከራ በእኔ ላይ ባለማድረጉ ። ወጣትነቴና ተፈጥሮ ጤንነቴን አፋጠኑልኝ ። መላው የእህገዙ ቤተሰብ ሽብ ረብ አለልኝ ። ማሪያ ኢቫኖቭና ከአጠገቤ አልተለየችኝም ። በልቤ የታመቀውን ፍቅር በዚያ አጋጣሚ መናዘዝ ነበረብኝና ማሪያ ኢቫኖቭናም በጥሞና አዳመጠችኝ ። ስለ እኔ ያላትን ስሜት አፍረጥርጣልኝ ፣ የእርስዋ መደሰት ወላጆችዋንም እንደሚያስደስት ገለጸችልኝ ። “ ግን እስቲ በቅጡ አስበበት’’ በማለት ቀጠለች ።“ወላጆችህ እንቅፋት አይሆኑብንም ?’’

አወጣሁ አወረድኩ ። የእናቴን ሩኅሩኅነት አልተጠራጠርኩም ። ሆኖም ያባቴን ጠባይና አስተሳሰብ ዐውቀዋለሁና ስለያዘኝ ፍቅር ባነበንብለት ፍንክች እንደማይልልኝ ፣ ምናልባትም ከጉርምስና መንፈስ እንደሚመነጭ ጋጠ ወጥነት ይቆጥርብኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ ። ይህንኑ ለማሪያ ኢቫኖቭና በግልጽ ከአዋየኋት በኋላ የማግባባት ችሎታዬን ሁሉ በመጠቀም ፣ ለአባቴ ደብዳቤ ጽፌለት የወላጅነት ፈቃዱን ለመለመን መወሰኔን አበሠርኋት ። ደብዳቤውንም አሳየኋት ፣ ልብ የሚነካ ሆኖ አገኘችው ። የማግባባት ኃይሉን መዝናና እሽት ዕድሜዋና አፍላ ፍቅር ገፋፍተዋት ፍጹም በሆነ እምነት ልቧን ሰጠችኝ ። በዳንኩ ሰሞን ከሽቫብሪን ጋር እኩል ለመቆም በቃሁ


t.me/OLDBOOKSPDF

ኢቫን ኩዝሚች። "አይ ፖይቶር አንድሬይች ! እስራት ይገባህ ነበር ። ሆኖም እስኪበቃህ ተቀጥተሃል ። አሌክሲ ኢቫኒች ዳቦ ጋጋሪው ቤት በእስር ላይ ይገኛል ። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭናም የእርሱን ጉራጌ ቆልፋበታለች ። ስለ እኩይ ምግባሩ እያሰበ ይጸጸት ” በማለት ተግሣጹን አወረደው ። ከደስታዬ ብዛት የተነሣ በዚያን ወቅት በማንኛውም ሰው ላይ ክፉ ለማሰብ አልቻልኩም ነበርና ለሽቫብሪን እማላጅ ሆንኩኝ ፤ ልበ - ገሩ አዛዡም ባለቤቱን ካማከረ በኋላ በነጻ ሊለቀው ወሰነ ። እንደ ተፈታም ሽቫብሪን ሊጠይቀኝ መጣ ። በመካከላችን ተፈጥሮ በነበረው ድርጊት እጅግ አድርጎ መጸጸቱን ገልጾልኝና ጥፋቱም ሙሉ በሙሉ የእሱ መሆኑን አምኖ ይቅር ለእግዚአብሔር እንድንባባል ጠየቀኝ ። ቂርሾ የመያዝ ጠባይ ስለሌለኝ ላደረሰብኝ በደልና ጉዳት ከልብ ይቅርታ አደረግኩለት ። ስም አጥፊነቱ የመነጨው ክብሩ በመነካቱና ፍቅር በመነፈጉ አሳብቤለት ለምስኪኑ ባላንጣዬ ከፍ ያለ ይቅርታ አደረኩለት ።

ወዲያው ጤንነቴ ተሟልቶ ወደ መኖሪያዬ ለመመለስ ቻልኩኝ ። ስለ ማርያና እኔ ጋብቻ በቤተሰቦቼ ላይ እምብዛም ተስፋ ባላሳድርም፣ያን ፍርሃት ለመደበቅ እየጣርኩ የደብዳቤዬን መልስ በጉጉት እጠባበቅ ጀመር ። እስካሁን ለቫሲሊሳ ዩጉሮቭና እና ለባልዋ ስለ ሕልሜ ምንም ያልኳቸው ነገር ባይኖርም ፣ የጋብቻ ጥያቄዬ እስከዚህም ዱብዕዳ እንደ ማይሆንባቸው ተገንዝቤያለሁ ። ማሪያ ኢቫኖቭናም ሆነች እኔ ስሜታችንን ከእነሱ ለመሸሸግ ስላልተጨነቅን እንደ ማያሳፍሩን ባለሙሉ ተስፋ ነበርን ።

በመጨረሻም አንድ ቀን ጠዋት ሳቬሊች ደብዳቤ አንጠልጥሎልኝ ከተፍ አለ። አላስችል ብሎኝ መነጨኩት፤ አድራሻው የሠፈረው በአባቴ የእጅ ጽሕፈት ነው ።ይህ ራሱ ያልጠበቅሁት ሌላ ጭንቀት ውስጥ ከተተኝ ፤ ምክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ንያቱም በአብዛኛው ትጽፍልኝ የነበረችው እናቴ ስትሆን እሱ በስተግርጌው ጥቂት መስመሮች ብቻ ነበር የሚያ ክልበት ። ደብዳቤውን ለመክፈት ስላልደፈርኩ ፤ " ለልጄ ፖይቶር አንድሬይች ግሪኔቭ ፣ ኦሬንበርግ ክፍለ ሀገር ፣ ቤሎጉርስክ ምሽግ " በሚለው ጽሑፍ ላይ በማተኮርና ደብዳበው በምን ዐይነት ስሜት እንደ ተጻፈ ከፊደሎቹ አጣጣል በመገመት ብቻ ልመናዬ እንደ ከሸፈብኝ ተገነ ዘብኩ ። የደብዳቤው ሙሉ ቃል ቀጥሎ ያለው ነበር ።

" ልጄ ፖይቶር ! ከሚሮኖቭ ልጅ ማሪያ ኢቫኖቭና ጋር ለመጋባት የእኛን ፈቃድና ምርቃት በመጠየቅ የጻፍከው ደብዳቤ በዚህ ወር አጋማሽ ላይ ደርሶናል። ስለ ጋብቻችሁ ፈቃዴንም ሆነ ምርቃቱን ለመስጠት አልቃጣም ። የመኮንንነት ማዕረግ ቢኖርህም ለአጉል ቅብጠትህ ፣ እንደ ሕፃንነት ዘመንህ እጅህን ይገፔ ብጠበጥብህ ደስ ባለኝ ፤ ምክንያቱም አገርህን እንድ ትጠብቅበት የተሰጠህን ጐራዴ ለመታጠቅ አልበ ቃህም ። እንዳንተ ካለ አንድ ሞገደኛ ጋር መፋለምህን ሰምቻለሁ ። ይህን ርካሽ ጠባይህን ወደምታርምበት ከቤሎ ጉርስክ ምሽግ በጣም ወደሚርቅ ሥፍራ እን ዲያዛውርህ ለአንድሬ ካርሎቪች በአስቸኳይ እጽፍ ሊታለሁ ። እናትህ መፋለምህንና መቁሰልህን ስት ሰማ ከማዘንዋ የነተነጣ በሽታ ላይ ወድቃ ይኸው እስከዛሬ የአልጋ ቁራኛ ሆናለች ። እንዲያው መጨ ረሻህ ምን ይሆን ? ታላቁን ምሕረቱን ያወርድልሃል ብዬ እምብዛም ተስፋ ባላደርግም ልብ እንድትገዛ ወደ እግዜር እጸልያለሁ ።

አባትህ አ.ግ."



t.me/OLDBOOKSPDF

በጥንቃቄ ያነበብኩት ይህ ደብዳቤ ምስቅልቅል ስሜት አሳደረብኝ ። አባቴ ለነገ ሳይል የተጠቀመባቸው አጥንት የሚሰብሩ ቃላት እርር ኩምትር አደረጉኝ ።ማሪያ ኢቫኖቭናንም ያንኳሰሰብኝ መሰለኝ ። ከቤሎጎርስክ ምሽግ የመዛወሩ ጉዳይ ክፉኛ አስደነገጠኝ ፤ እናቴ መታመምዋን መረዳቴ ግን ከሁሉም ይልቅ ሐዘንና ትካዜ ላይ ጣለኝ ። ወላጆቼ ስለ ፍልሚያው የተረዱት ያለ ጥርጥር ከሳቪሊች መሆኑን ደረስኩበትና ከባድ ቂም ያዝኩበት ። በጠባብዋ ክፍሌ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ተንጐራደድኩና እፊቱ ተገተርኩ ። በጥላቻና በደም ፍላት እያየሁት ። “ እህ ? አንድ ወር ሙሉ ከሞት አፋፍ ላይ ላንጠለጠለኝ አደጋ ጦስ መሆንህ አልበቃ ብሎህ እናቴንም ለሞት ልትዳርጋት ትሻለህ ? ” አልኩት ። ሳቪሊች አፉን ከፍቶ ቀረ ። “ ምነው ጌታዬ ” አለኝ በድንጋጤ እያቃሰተ ፤“ ምንድ ነው የምትለኝ ? እኔ ለመቁሰልህ ምክንያት ሆንኩ ? የሮጥኩት የአሌክሲ ኢቫኒችን ጐራዴ በሰውነቴ ልመክትልህ እንደነበር ፈጣሪ ያውቃል ! እርጅናዬ እንቅፋት ሆነብኝ እንጂ ! ደግሞስ እናትህን ምን በደልኩዋቸው ? ”

“ ምን በደልኩ ? ” ጥያቄውን አስተጋባሁለት ። “ እንድታሳብቅብኝ ማን ገፋፋህ ? በሰላይነት ነው እንዴ የተመደብክብኝ ? ” “ እኔ አሳብቅብሃለሁ ? ” በማለት ሳቪሊች ጮኾ እያለቀሰ ፤ “ የፈጣሪ ያለህ ! እባክህ ጌቶች የጻፉልኝን ደብዳቤ አንብብና እንዳላሳበቅሁብህ ተረዳልኝ።” ይህን ተናግሮ አንድ ደብዳቤ ከኪሱ አወጣ ። ተቀብዬ ውም ቀጥሎ ያለውን አነበብኩኝ ።

“ አንተ ውሻ ውላጅ ፤ ጥብቅ መመሪያ ብሰጥህም ስለ ልጄ ፖይቶር ምንም ያስታወቅኸኝ ባለመኖሩና ስለ እጉል ቅብጠቱ ካንተ ሳይሆን ካልታወቁ ሰዎች በመስማቴ ልታፍርበት ይገባሃል ። ተግባርህን የምት



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣውና የጌታህን ትእዛዝ የምትፈጽመው በዚህ አኳኋን ነውን ? አንት ሙትቻ ፤ እውነቱን በመደበ ቅህና ከእንዲያ ያለ ሕፃን ጋር በመዶለትህ አስመ ጥቼ እረኛ ነው የማይርግህ ። እየተሻለው መም ጣቱ ቢነገረኝም ፣ ይህ ደብዳቤ እንደ ደረሰህ ስለ ጤንነቱ ፤ ከምኑ ላይ እንደ ቆሰለና በንክብካቤ መያዝ አለመያዙን በመግለጽ እንድትጽፍልኝ አዝዝሃለሁ።''

ሳቪሊች እንዳልበደለኝ ግልጽ ነው ። በጥርጣሬ ተገ ፋፍቼ የቁጣ ናዳ ላወርድበት ባልተገባኝ ነበር ። ይቅርታ ብጠይቀውም ሽማግሌው እሚጽናና አልሆነም ።'' መጨ ረሻዬ እንዲህ ሆነ '' አለ በማቃሰት ።'' ከጌቶቹ ያገኘሁት ውለታ ይህ ነው ! እኔ ውሻ እኔ እረኛ ነኝ ፤ አሁን ደሞ ለጉዳትህ ምክንያቱ እኔው ሆንኩ ! ግን ፖይቶር አንድሬች ጌታዬ ጥፋተኛው እኔ አይደለሁም ፤ ሊወቀስ የሚገባው ያ ቦፕሬ የተባለው እርጉም ሰው ነው ፤ ሰምሰማ እያስረገ ጠህ በዲጂና እንድትዋጋ ያስተማረህ ! ሰምሰማ እየረገጡ ድምቡልቅኝ ማስነሣት ገፍቶ ከመጣብህ ጠላት ያድንህ ይመስል ! እንዲያ ያለ አስተማሪ ቀጥረው ያን ሁሉ ገንዘብ ማባከናቸው ያሳዝናል !''

ስለ ራሴና ስለ ጠባዬ ለአባቴ ለማሳበቅ አፉን የበላው ማን ሊሆን ይችላል ? ጀኔራሉ ? በዚህ ጉዳይ ስለእኔ እም ብዛም የሚጨነቅ አልመሰለኝም ። ኢቫን ኩዝሚችም ስለ ፍልሚያው ማሳወቅ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም ።እን ዱን ሳነሣ ሌላውን ስጥል ቆየሁና ጥርጣሬዬ ሽቫብሪን ላይ ዐረፈ ። ባንጠለጠለብኝ ስብቀት እኔ ከምሽጉ ብወገድና ከእዛዝዋ ቤተሰብ ብርቅ የሚጠቀም ቢኖር እሱ ብቻ ነው ። ስለ ሁኔታው አንድም ሳላስቀር ላጫውታት ወደ ማሪያ ኢቫኖቭና ዘንድ ሔድኩኝ ። ከበረንዳው ላይ ተገናኘን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ምን ሆነሃል ?” አለችኝ ፊቴን አይታ ። “ እንዴት ገር ጥተሃል ልጄ !”

“ ሁሉም አከትሟል ! ” ብዬ የአባቴን ደብዳቤ አቀበልኳት ። በተራዋ ፊቷ ዐመድ ለበሰ ። ደብዳቤውን እንብባ ከጨረሰች በኋላ ጣቶችዋ እየተንቀጠቀጡ መለሰ ችልኝ ። ስብርብር ባለ ድምፅ “ አየህ ፡ ፊቱንም አላለል ንም . . .ወላጆችህ እንድቀርባቸው አይፈልጉም ። እግዜር ያለው ይሆናል ! እግዜር ለእኛ የሚበጀውን ከእኛ አስበ ልጦ ያውቃል ። ምንም ማድረግ አይቻልም ፖይቶር እንድሬይች ፡ አንተ ደስ እስካለህ ድረስ . . ” አለች ።

“ እንደዚህ ሊሆን አይችልም !” አልኳት እጅዋን ጨበጥ አድርጌ ። “ ታፈቅሪኛለሽ ፤ እኔም ለምንም ነገር ዝግጁ ነኝ ። ነይ ፡ ከወላጆችሽ እግር ላይ እንወድቃለን። ቀና ሰዎች ናቸውና ልባቸው በኩራት አልደነደነም ።እነሱ ይመርቁናል ፤ እንጋባለን . . . ከጊዜ በኋላም ከአባቴ ጋር መታረቅ እንደምንችል እርግጠኛ ነኝ ። እናቴ ከኛ ጐን ነች ፤ አባቴ ይቅርታ እንዲያደርግልን ትማፀነዋለች ።”

“ አይሆንም ፖይቶር እንድሬይች ” አለችኝ ማሻ ። ያለወላጆችህ ፈቃድ አላገባህም ። ያለ እነሱ ምርቃት ደስታ አይኖርህም ። ለእግዜር እንተወው ። ላንተ የተባለ ችልህን ወጣት ካገኘህ ፡ ሌላ ካፈቀርክ የእግዚአብሔር ቸርነት ከናንተ ጋር ይሁን ። ፖይቶር እንድሬይች ፡ ለሁ ለታችሁም እጸልያለሁ . . . ” እዚህ ላይ በድንገት ተንሰቀሰቀችና ተለየችኝ ።

ወደ ቤት ተከትያት የመግባት አሳብ ብልጭ ብሎ ልኝ ነበር ። ግን ስሜቴን ለመቆጣጠር እንደማልችል ስለ ገመትኩ ወደ መኖሪያዬ ሔድኩኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከክፍሌ ተቀምጬ በሒሳብ ስማስን ሳቢሊች አባን ነኝ ።“ ይኸው ጌታዬ ” አለ በብዕር የተጠቀጠቀ ወረቀት እያቀበለኝ ።“ እስቲ በጌታዬ ላይ መስለሌንና አባትና ልጅ ማቃቃሬን እይ ። ” ወረቀቱን ተቀበልኩት ። ሳቢ ሊች ለተላከለት ደብዳቢ የሰጠው መልስ ነበር ። ቃል በቃል አቀርበዋለሁ ።

“ የተከበሩ አንድሬ ፒትሮቪች ፡ ደጉ ጌታዬ !

እኔ ባሪያዎ ትእዛዝዎን ባለማክበሬ ቁጣዎን ያሠፈ ሩበትና በእድራጐቴም እንዳፍር የሚያስገነዝበኝ የተከበረ ደብዳቤዎ ደርሶኛል ። ግን እኔ ውሻ አይደለሁም ፤ ታማኝ አሽከርዎ እንጂ ። የእርስዎን የጌታዬን ትዕዛዝ እያከበርሁ በታማኝነት ሳገለግልዎ ይኸው ሁለት ጸጉር እስከማብ ቀል ደርሻለሁ ። ስለ ፖይቶር አንድሬይች መቁሰል ያልጻ ፍኩልዎ ሥጋት ላይ በከንቱ እንዳይወድቁ በመፍራት ነው ። እመቤቴ ውድ አቭዶትያ ቫሲሊየቭናም ደንግጠው የእልጋ ቁራኛ መሆናቸውን ሰማሁ ። እግዚአብሔር ምሕ ረቱን እንዲልክላቸው እጸልያለሁ ። ፖይቶር አንድሬይች የቆሰለው ከቀኝ ትከሻው ሥር ከሰባራ ስንጥሩ ጥቂት ዝቅ ብሎ ከደረቱ ላይ ሲሆን የቁስሉ ጥልቀት አምስት ሳንቲ ሜትር ነው ። ከወንዙ አፋፍ እንሥተነው ወደ እዛዡ ቤት ወስደን አስተኝተነዋል ። የሚንከባከበውም ጸጉር አስተ ካካዩ እስቴፎን ፖራሞኖቭ ነው ። አሁን ግን እግዜር ይመ ስገን ፖይቶር አንድሬይች ድኗል ። ስለ እሱም በጐ በጐ ውን እንጂ ሌላ ለመጻፍ አልችልም ። የበላይ አዛዦቹ እንደሚወዱት ዐውቃለሁ ። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭናም የምታ የው እንደ ራስዋ ልጅ ነው ። አምባጓሮ መግጠሙ እሌ አይባልም ፤ ታዲያ በወጣት ትከሻ ላይ የሽማግሌ ጭንቅ ላት ለመስካት አይቻል ። አራት እግር ቢኖረውም ፈረስ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንኳ አንዳንዴ ያደናቅፈው የለ ! መልሰውኝ የዓሣማ እረኛ እንደማያደርጉኝ ገልጸውልኛል ፤ ጌታዬነዎትና እንዳሻዎ ሊያደርጉኝ ይችላሉ ።

" የትሕትና ሰላምታዬን ይቀበሉኝ ይላል
ታማኝ ሎሌዎ አርኪኝ ሳሺልዮቭ "

የየዋሁን ሽማግሌ ደብዳቤ በጥንቃቄ ሳነብ ዐልፎ ዐልፎ ሣቅ ማለቴ አልቀረም ። ለአባቴ ደብዳቤ መልስ ለመስጠት ፍላጎት አልነበረኝም ። የሳቪሊች ደብዳቤ የእናቴን ጭንቀት ለማርገብ በቂ የሚሆን መሰለኝ ።

ከዚህ በኋላ ሁኔታዬ ተለወጠ ። ማሻ እምብዛም አታናግረኝ ። በተቻላት መጠን ከዐይኔ ገለል ትላለች ። የአዛዡ ቤት አስጠላኝ ። ቀስ በቀስ ከክፍሌ ለብቻዬ መቀመጡን ተላመድኩት ። በዚህም አድራጐቴ ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና በመጀመሪያ ተቆጣችኝ ። ቁርጠኛነቴን ስትረዳልኝ ግን ተወት አደረገችኝ ። በሥራ ሰዓት የሚያጋጥመኝ ኢቫን ኩዝሚች ብቻ ነበር ። ከሽቫብሪን ጋርም የምንገናኘው ዐልፎ ዐልፎ ያውም ያለ ውዴታዬ ነበር ፤ ምክንያቱም ቂም እንደ ያዘብኝ ትክሻዬ ይነግረኛል ። ኑሮዬ የማይገፋ ሆነብኝ ። በሐዘንና በትካዜ ተዋጥኩ ። ብቸኝነትና ያለ ሥራ መጐለት ሥቃዬን አባባሱት ። በብቸኝነቴ ላይ የያዘኝ ፍቅር በውስጤ እንደ እሳት እየተንቀለቀለና የማልችለው ዕዳ እየሆነብኝ መጣ ። የማንበብና የመጻፍ ፍላጐቴ ጭራሹኑ እልም አለብኝ ። ራሴን ለመጥላት ተገደድኩ ። ወፈፍ እንዳያደርገኝ ፣ እለዚያም መሸተኛ እንዳልሆን ሠጋሁ ። ከዚያም ሕይወቴን ሊለውጥ የቻለ አንድ ያልታሰበ ነገር ተፈጥሮ የሚበጀኝን አቅጣጫ አስያዘኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ስድስት

## ቮጋቺክና ሰዎቹ

እናንት ታዳጊዎች ስሙን ከልባችሁ
እኛ አዛውንቶቹ ስናወጋላችሁ ።

የጥንት ዘፈን

የዐይን ምስክር ስለሆንኩበት እንግዳ ነገር ከማተቴ በፊት በ1773 መገባደጃ ላይ ይታይ ስለነበረው ስለ ኦሬንበርግ ግዛት ሁኔታ በጥቂት ላወጋችሁ እሻለሁ ።

ይህ ሰፊና ለም ግዛት የንጉሡን አገዛዝ ገና በቅርቡ የተቀበለና ሥልጣኔ ያልገራቸው ሰዎች የሚኖሩበት አገር ነበር ። የማያቋርጥ ዓመፃቸው ፣ ለሕግና ለማኅበራዊ ግዴታዎች ያለመበገራቸው አዝማሚያ የመንግሥትን ያላሰለሰ ትኩረት ጠይቋል ። አመች በየሆኑ ሥፍራዎች ላይ ምሽጐች ተገንብተው በያይክ ወንዝ ዳርቻዎች ነባር የሆኑ ኮዛኮች ሠፍረውባቸዋል ። ነገር ግን ሰላምንና ደህንነትን ያሰፍናሉ ተብለው እምነት የተጣለባቸው እነዚሁ ኮዛኮች ራሳቸው ለዓመፅ የታጠቁ የመሆናቸው ጉዳይ መንግሥትን ይበልጥ እያሠጋው ሔደ ። በ1772 ሜጀር ጄኔራል ትሮቢንቤርግ እነርሱኑ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ሲል በወሰደው ከባድ የቅጣት ርምጃ ምክንያት ይብሱን ከፍተኛ ዓመፅ ተቀሰቀሰ ። ውጤቱም የትሮቢንበርግ በአሠቃቂ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታ መገደል ሲሆን አስተዳደሩም በመጠኑ ቢሻሻልም ዓመፀኞቹ ተጨፍጭፈው ነበር ።

ይህ ሁሉ የሆነው ወደ ቢሎጉርስክ ምሽግ ከመምጣቱ ቀደም ብሎ ነው ። በደረስኩ ሰሞን ጸጥታው ሰፍኗል ። ወይም የሰፈነ ይመስል ነበር ። ቂም በቀላቸውን በየሆዳቸው አምቀው ውስጥ ውስጡን ሌላ ዓመፅ ለማስነሣት ቀናቸውን ይቆጥሩ የነበሩትን መሠሪዎች ዛቻ ባለሥልጣኖቹ ችላ ብለውታል ።

ታሪኬን ልቀጥል ።

በአንድ ምሽት ላይ በጥቅምት 1773 መጀመሪያ፥ በክፍሌ ውስጥ ብቻዬን ሆኜ የሚያፏጨውን የበልግ ነፋስ እያዳመጥኩ የሚንጓለለውን ደመና በመስኮት በኩል እመለከታለሁ ። አንድ ሰው ሲሮጥ መጣና አዛዡ ዘንድ እንደምፈለግ ነገሮኝ ወዲያውኑ ወደዚያው ሔድኩ ። ሽቫብሪንን ፣ ኢቫን ኢግናቲችንና የኮዛክ ሃምሳ አለቃውን ከዚያው አገኘኋቸው ። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭናም ሆነች ማሪያ ኢቫኖቭና በሥፍራው አልነበሩም ። አዛዡ በሐሳብ እንደ ተዋጠ ሰላምታ አቀረበልኝ ። ቀጥሎም በሩን ቀርቅሮ ዘብ ከቆመው ሃምሳ አለቃ በስተቀር ሌሎቻችንን እንድንቀመጥ ጋበዘንና አንዲት ወረቀት ከኪሱ መዘዝ አድርጎ፣ “ እስቲኳይ ጉዳይ አለኝ ክቡራን ። ጀኔራሉ የጻፉትን ስሙ” አለን ። መነጽሩንም ደንቅሮ የሚከተለውን ደብዳቤ ጉላ ባለ ድምፅ አነበበልን ።

“ ለሻለቃ ሚሮኖቭ ፣ የቤሎጉርስክ ምሽግ አዛዥ ።

ጥብቅ ምስጢር !

“ ተገንጣዩና የኮዛኮች መሪ ነኝ ባዩ ኢሚሊያን ፑጋቼቭ ከእስር ላይ አምልጦ ራሱን በሟቹ በፀሤ ጴጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮስ ሳልሳዊ መሰየሙ ይቅርታ የማይደረግለት ድፍረት ከመሆኑም በላይ ፤ ወንበዴዎችን በዙሪያው እየሰባሰበ በያ ይክ መንደሮች ውስጥ ዓመፅ በማቀጣጠል በየሥፍራው ምሽጎችን እየማረከና እያወደመ በዝርፊያና በግድያ ተግ ባራት ተሠማርቷል ። ስለዚህ ይህ መልዕክት እንደ ደረ ሰህ ስሙ ከላይ የተጠቀሰውን ወንጀለኛና አወናባጅ ግለ ሰብ ለመግታት ፤ በሥርህ የሚገኘውንም ምሽግ ለመው ረር ከቃጣ ቢቻል ለመደምሰስ አስፈላጊውን ርምጃ እንድ ትወስድ አሳስብሃለሁ ።"

"አስፈላጊውን ርምጃ እንድትወስድ !" ሲል አስ ተጋባ አዛዡ መንጽሩን እያወለቀና ደብዳቤውን እያጣጠፈ ። "ከማድረግ ማውራት ይቀላል ! ወንበዴው እሚቻል አይደለም ፤ ያሉን አንድ መቶ ሠላሳ ሰዎች ብቻ ናቸው ፤ ለዚያውም ስለማይታመኑ ኮዛኮችን ሳንጨምር ፤ አትቀ የመኝ ማክሲሚች !" አለ በአቅራቢያው ወደ ቆመ ወታ ደር ዘወር ብሎ ፤ ሃምሳ አለቃው ኮዛክም ሣቅ አለ ። "ግን ምንም ማድረግ አይቻልም ፤ ወንድሞቼ ግዴታችሁን ለመወጣት አርአያ ሁኑ ፤ የዘብ ተግባራችሁንና የማታ ጥበቃችሁን አጠናክሩ ። አደጋ ሲመጣም በር በሮቹን ዘግታችሁ ወታደሮቹን ቀስቅሱ ። አንተ ማክሲሚች ፤ ኮዛኮችህን በዐይነ ቁራኛ ተከታተል ።መድፉን አገላብጣ ችሁ በሚገባ ወልውሉት ። ይህን ጉዳይ ማንም ሰው እን ዳይሰማ በምስጢር ጠብቁት ።"

ይህን ትእዛዝ አስተላልፎልን ፤ ኢቫን ኩዚሚች አሰናበተን ። ሽቫብሪንና እኔም ስለዚሁ እያወጋን በአን ድነት ወጣን ።"እንዳው መጨረሻው ምን እሚሆን ይመ ስልሃል ?" አልኩት ። "እግዜር ይወቀው " ሲል መለ ሰልኝ ፤ "እስቲ እናየዋለን ። እስካሁን በበኩሌ ምንም



t.me/OLDBOOKSPDF

እንግዳ ነገር አልታየኝም ። በእርግጥ . . . '' እዚህ ላይ ንግግሩን አቋርጦ በፉጨት እያንጐራጐረ በሐሳብ ተዋጠ ።

ከፍተኛ ጥንቃቄ ብናደርግም የጉጋቼቭ መምጣት መርዶ በምሽጉ ውስጥ ተሠራጨ ። ኢቫን ኩዚሚች ባለ ቤቱን ቢያከብራትም ፣ የተላከለትን ወታደራዊ ምስጢር ያካፍላታል ማለት ዘበት ነው ። የጄኔራሉ መልዕክት እንደ ደረሰውም አባ ጌራዚም ከኦሬንበርግ በምስጢር የሚጠብቁት ዜና እንደ ተላከላቸው ለቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ሹክ ብሏት በዘዴ አግልሏት ነበር ። እርሷም ወደ ቄሱ ቤት ወዲያውኑ እንድትሮጥ ከመገፋፋቱም በላይ ብቻዋን እን ዳትቀር በሚል ሰበብ ማሻንም ይዛለት እንድትሔድ አድ ርጓል ። የቤቱ ብቸኛ ባለቤት በመሆኑም በፍጥነት ካስ ጠራን በኋላ ፖላሻ እንኳ ጉዳዩን እንዳትሰማበት ሲል ቁም ሳጥን ውስጥ ቆልፎባት ነበር ።

ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ከቄሱ ሚስት ምንም ዐይነት ፍንጭ ሳታገኝ ወደ ቤቷ እንደ ተመለሰችም ፖላሻን ቁም ሳጥን ውስጥ አሽጓት ባሏ ስብሰባ ማካሔዱን ደረሰችበት። እንደ ተጫወተባት ተገንዝባም ስለ ጉዳዩ አጥብቃ ጠየ ቀችው ። ሆኖም ኢቫን ኩዚሚች ተዘጋጅቶበት ነበርና ነገሩ እንዲህ ነው ወዳጄ ፤ ሴቶቻችን ምድጃዎቻቸውን በድርቆሽ ሣር ማሟሟቃቸውን ሥራችን ብለው ተያይዘውታል። እናም ይህ ደግሞ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል ወደፊት በጭራሮና በቅጠላ ቅጠል እንጂ በድርቆሽ እንዳይሞክሩ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ አስተላልፌያለሁ '' በማለት ያላን ዳች መረበሽ አሥቂኝ መልሱን አስቀመጠላት ። " ታዲያ ፖላሻን ቁም ሳጥን ውስጥ ለምን ቆለፍክባት ?'' አለችው ። " እኔና ማሻ እስከምንመለስ ድረስ ቁም ሳጥን ውስጥ የታሸገበት ምክንያት ምን ይሆን ?'' ኢቫን ኩዚሚች ያልጠበቀው ጥያቄ ስለ ተደቀነባት መላቅጡ የጠፋ



t.me/OLDBOOKSPDF

መልስ አገተመተመ ። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና የባሏን እስስ ትነት ተረድታና አጥጋቢ ምላሽም እንደማታገኝ ገምታ ጥያቄዋን ወደ ጐን በመተው ስለ አኩሊና ፓምፊሎቭና ባልትና ማውሳቷን መረጠች ። ባሏ የደበቃት ጉዳይ ምን እንደሁ ለማወቅ ስታሰላስል እንቅልፍ በዐይኗ ሳይዞር አደረች ።

ጠዋት ከቤተ ክርስቲያን ስትመለስ ኢቫን ኢግናቲች የምሽጉ ብቸኛ መድፍ አፈሙዝ ውስጥ ሕፃናት ያጉሩትን ቡትቶ ፣ ድንጋይ ፣ የእንጨት ስንጣሪ አጥንትና ሌሎች ቅራቅምቦዎችን ሲያራግፍ ተመለከተችው ። " ይህ ወታደራዊ መሰናዶ ለምን ይሆን ? " ስትል ራሷን ጠየቀች። " የኪርጊዞችን ወረራ ፈርተው ይሆን ? እንዲህ ያለውን ቀላል ጉዳይ ደግሞ ኢቫን ኢግናቲች በምንም አኳኋን አይደብቀኝም ። " ያቅበጠበጣትን ይህን ዕንቆቅልሽ እን ዲፈታላትም ኢቫን ኢግናቲችን ጠራችው ።

ልታዘናጋው ብላም ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ስለ ገጠ ማቸው ችግር ዙሪያ ጥምጥም ጥያቄዎች ከደረደረችለት በኋላ በረጅሙ ተንፍሳ ራሷን እየነቀነቀች ፣ " የእግዜር ያለህ ! የፈጣሪ ያለህ ! ምን ዐይነት መርዶ ነው ! እንዳው መጨረሻችንስ ምን ይሆን ?" አለችው ።

" አይጨነቁ እመቤቴ " አላት ኢቫን ኢግናቲች ። " እግዜር መሐሪ ነው ። በቂ ወታደሮችና ባሩድ አለን ። መድፉንም ይኸው አጽድቼዋለሁ ። ፑጋቼቭን እንደም ንደመስሰው ተስፋ እናደርጋለን ። አምላክ ምሕረቱን ካወ ረደልን የአውሬ እራት አንሆንም ።"

" ለመሆኑ ፑጋቼቭ ማን ነው ?" ስትል ቫሲሊሳ ዩጉ ሮቭና ጥያቄዋን ደቀነችበት ። ኢግናቲች ነገር እንዳመ ለጠው ተገንዝቦ ምላሱን ነከሰ ። ግን የፈሰሰ ውሃ አይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታፈስ ። ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ለማንም ሰው እንደማትተነፍስ ቃል ገብታለት እንዲነግራት ወጥራ ያዘችው ። እርሱም በዝርዝር አወጋላት ።

በእርግጥ ቫሲሊሳ የገባችለትን ቃል ኪዳን ጠብቃለች፤ ከቄሱ ሚስት በስተቀር ለሌላ ሰው ትንፍሽ አላለችም ። ለዚያውም ሜዳ ለሜዳ የምትዞረውን የቄሱን ሚስት እንዲት ላም የፑጋቼቭ ተከታዮች እንዳይነዱባት ስለ ሠጋች ብቻ ነበር ሹክ ያለችላት ።

ወዲያው ሠፈርተኛው በሙሉ ስለ ፑጋቼቭ ያወካ ጀመር ። ወሬው ቀንደና ጭራ እያበቀለ ተዛመተ ። በአቅራቢያ ያሉ መንደሮችንና ምሽጎችን እንዲሰልልለት አዛዡ ሃምሳ አለቃውን ኮዛክ ላከው ። ማክሲሚችም በሁለት ቀናት ውስጥ ተመልሶ ከምሽጋቸው ጥቂት ፈቀቅ ብሎ በተንጣለለው መስክ ላይ እሳት በየሥፍራው ሲንቀለቀል ማየቱንና ከባሽኪሮች እንደ ሰማውም የጠላት ጦር ወደ ምሽጋቸው በመትመም ላይ እንደሆነ አረዳው ።ርቆ ለመሰለል በመፍራቱም ተጨማሪ መረጃ እንዳላመጣለት ነገረው ።

በምሽጉ ውስጥ የሚኖሩ ኮዛኮች በዚያው ሰሞን ያልተለመደ እንቅስቃሴ ማሳየት ጀመሩ ። በየጉዳናው መኻል እጅብ ብለው እየቆሙ ሲንሾካሾኩ ይቆዩና ወታደር ብቅ ሲልባቸው ይበታተናሉ ። ሰላዮች በመካከላቸው እንዲሰገሰጉም ተደረገ ። ዩላይ የተባለ ሰው ጠቃሚ መረጃዎችን ለአዛዡ ማገረፍ ያዘ ። እንደ ዩላይ አባባልም ሃምሳ አለቃው ቀደም ሲል ያቀረበው መረጃ አሳሳች መሆኑንና እንዳውም ያ መሠሪ ኮዛክ ራሱ ወደ ወንበዴዎቹ መንደር በመዝለቅ መሪያቸው ዘንድ ቀርቦ እንደ ነበር ፥ እጁን ለመሳም መታደሉንና ከእርሱ ጋር ረጅም ውይይት ማድረጉን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለብጤዎቹ እንዳበሠራቸው በማውሳት ሃምሳ አለቃውን ኮዛክ አጋለጠው ። አዛገዞም ሃምሳ አለቃውን ወደ እስር ቤት አስገብቶ በቦታው ዩላይን ተካበት ። ይህም ርምጃው በኮዛኮች ዘንድ ግልጽ ቅሬታን ፈጠረ ። ኢቫን ኢግናቲች እንኳ ራሱ የአዛገዡን ትእዛዝ በማያስፈጽምበት ወቅት "የሚቀጥለው ያንተው ተራ ይሆናል ፣ አንተ አድር ባይ" እያሉ በይፋ ሲወርፋት በገዛ ጆሮው ሰምቷል ። አዛገዡም ማክሲሚችን እስር ቤት ባስገባው ዕለት ለምርመራ ሊያስቀርበው ተዘጋጅቶ ነበር ፣ ግን በደጋፊዎቹ ትብብር መሆኑ አልቦበት ። ሃምሳ አለቃው ከእስር ቤት አመለጠ ተባለ ።

የአዛገዡን ጭንቀት ያባባሰው ሌላ ድርጊትም ተከሰተ ። አንድ ባሽኪር የዓመፅ ወረቀት ሲበትን እጅ ተፍንጅ ስለተያዘ አዛገዡ እንደ ለመደው ቫሲሊሳ ዩጎሮቭናን በዘዴ አስወግዶ መኮንኖቹን እንደገና ለመሰብሰብ አቀደ ። ግን ኢቫን ኩዝሚች ግልጽና ሐቀኛ ሰው በመሆኑ ከዚህ በፊት ከተጠቀመው ቀላል ዘዴ በቀር ሌላ አማራጭ ብልሃት አጣ ።

"ስሚኝ ቫሲሊሳ ዩጎሮቭና" አላት ጉሮሮውን ጠራርጐ ። "አባ ጄራዚም ከከተማ ትኩስ ወሬ ደርሷቸዋል ይባላልና . . ." በማለት ሲጀምር "መዋሸትህ ይብቃ ኢቫን ኩዚሚች" ስትል አቋረጠችው ። "ወጣ ስልልህ ስለ ዘመቻችሁ ስብሰባ ጠርተህ የኤሚሊያ ፑጋቼቭን ወረራ ልታብጠለጥሉ ነው ።" ኢቫን ኩዚሚች ዐይኖቹን በለጠጠ ። "እንግዲያውስ ወዳጄ" አላት ፣ "ዐውቀሽ ቀልና ከፈለግሽ ከዚሁ ሁኚ ባለሽበት እንወያያለን ።" "እንዲያ ይሻላል አንጀቴ" አለችው "መዋሸት አያዋጣውም ። በል መኮንኖችህን አስጠራቸው ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደገና ተሰበሰብን ። በአንድ ማይም ብጤ ኮዛክ የተሞነጫጨረውን የፑጋቼቭን መግለጫ ኢቫን ኩዝሚች ባለቤቱ ባለችበት አነበበልን ። ወሮበላው ወደ ምሽጋ ችን በቅርቡ እንደሚመጣና ኮዛኮችም ሆኑ መደበኛ ወታ ደሮች ሁሉ እጃቸውን እንዲሰጡት ለመከላከል ቢሞክሩ ግን ሞት እንደሚጠብቃቸው የሚያስጠነቅቅ መልእክት ነበር ። ሆን ተብሎ መልእክቱ የረቀቀው ባልተገራና የዋ ሆችን በሚያሸብር ቋንቋ ነበር ።

" ሞላጫ ! " አለችው የአዛዡ ሚስት ። " ምንኛ ቢደፍረን ነው እንዲህ ያለ ድርድር ያቀረበልን ! ሔደንለት እግሩ ሥር ልንበረከክለት ! አይ ውሾ ! ለዐርባ ዓመታት በውትድርና ሞያ በመቆየታችን ብዙ ነገሮችን እንደምና ውቅ መገንዘብ ተሳነው ? ይህን ወሮበላ የሚሰማ አዛዥ ይኖራል ማለት ዘበት ነው ። "

" የሚሰማ የለም በይ " አላት ኢቫን ኩዝሚች ፤ " ወንበዴውኮ ብዙ ምሽጎችን ማርኳል ይባላል ። "

" እረ ኃይለኛ ነው" አለ ሽቫብሪንም ።

" ያን በቅርቡ እናረጋግጣለን " አለ አዛዡ ። " ቫሲ ሊሳ ዬጉሮቭና የመጋዘኑን ቁልፍ አምጪ ። ኢቫን ኢግ ናቲች ያን ባሽኪር አምጣውና እግረ መንገድህንም ዩላይ ጅራፉን ይዞ ብቅ እንዲል ንገረው ።"

" እስቲ ትንሽ ታገሥ ኢቫን ኩዚሚች " አለችው ቫሲሊሳ ዬጉሮቭና ከተቀመጠችበት እየተነሣች ። " ማሪያ ኢቫኖቭናን ከቤት ላስወጣት ፤ ጩኸቱን ስትሰማ ትደነግ ጣለች ። እኔም ራሴ ብሆን እውነቱን ነው ፤ እንዲህ ያለውን ምርመራ አልወደውም ። ያበርታችሁ !"



t.me/OLDBOOKSPDF

ከጥንት ጀምሮ እስረኛን ማሰቃየት በሕጋዊነት ሥር የሰደደ በመሆኑ ያን ለመስረዝ የወጣው የምሕረት ዐዋጅ ከቶ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም ነበር ። አንድ ወንጀለኛ ጥፋቱን ማመኑ ወንጀለኛነቱን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል የሚለው እምነት መሠረት ቢስ ከመሆኑም በላይ ከፍትሕ ጋር ይቃረናል ፤ ምክንያቱም እስረኛው ወንጀለኛነቱን መካዱ ነጻ እንደሚያደርገው ሁሉ አምኖ መቀበሉም ወንጀለኛነቱን አያረጋግጥም ። ዛሬም ቢሆን ፤ ዐልፎ ዐልፎ ፤ ያ የጭካኔ ልምድ በመወገዱ የሚያጉረመርሙ ጊዜ ያለፈባቸው ዳኞች አይታጡም ። በዚያን ዘመንም ዳኞችም ሆኑ ተከሳሾች ቁም ስቃይ የማሳየቱን ተግባር አስፈላጊነት እምብዛም አልተከራከሩበትም ። ስለሆነም የአዛዡ ትእዛዝ በዙሪያው የነበሩትን ሰዎች አላስገረማ ቸውም ፤ ወይም አላስደነገጣቸውም ። ኢቫን ኢግናቴች ወደ ባሽኪሩ ሔዶ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እስረኛውን ይዞ መጣ ፤ አዛዡም እንዲቀርብለት ትእዛዝ ሰጠ ።

እግሮቹ በእግር በረት የተጠፈሩት ያ ባሽኪር ቆቡን አውልቆ እንደያዘ እንደ ምንም ብሎ በማዝገም ደፉን ዐልፎ በሩ ሥር ቆመ ። ገና ስመለከተው በረዶ ሆንኩኝ ። ያን ሰው ከቶ ልረሳው አልችልም ። የሰባ ዓመታት ገደማ ሰው ይመስላል ፤ አፍንጫውና ጆሮዎቹ የሉም ። ጭንቅላቱን ተላጭቷል ። የሚታየው ግራጫ ሪዘ ብቻ ነው ። አጠር ያለ ሰው ሲሆን ያገጠጠ ወ ዐፅሙ እንደ ደጋን ቢጐብጥም ዐይኖቹ እሳት ይተፋሉ ። “ ታዲያስ ?” አለው አዛዡ። በፊቱ ላይ ያሉት አስቃቂ ምልክቶቹ ቀደም ሲል በ1741 ተፋፍሞ የነበረውን የባሽኪሮችን ዐመፅ ለማፈን ሲል የዘውድ አገዛዙ ፈጽሞባቸው የነበረውን የጭካኔ ቅጣት አስታወሱት ። “ ለካስ ከዚህ በፊት ከወጥመዳችን የገባህ ልማደኛ ተኩላ ነህ ። ከጭንቅላትህ መገመስ እንደምገ



t.me/OLDBOOKSPDF

መግመው ስታምፅ የመጀመሪያ ጊዜህ አይደለም ። ጠጋ በል ፤ ለመሆኑ ማን ነው ወዲህ የላከህ ?"

ባሽኪሩ አንዲት ቃል ሳይተነፍስለት ትክ ብሎ ተመለከተው ።" ተናገር እንጂ " ሲል ቀጠለ ኢቫን ኩዚሚች ። " ሩሲያንኛ አይገባህም ? ወደ ምሽጋችን ማን እንደላከው እስቲ በቋንቋችሁ ጠይቀው ዩላይ ፡ "

ዩላይም በታርታሮች ቋንቋ የአዛገዥን ጥያቄ ደገመለት ። ባሽኪሩ ግን ፡ በድን ሆኖ ከመታየቱ በቀር ምንም ዐይነት ቃል አልወጣውም ።

" እሺ !" አለ አዛገዡ ። " አሁኑኑ ትናገራታለህ ! ይህን እንደ ጨሌ ጥብቆ የተኾራመተ ልብሱን አውልቀህለት ጀርባውን ገሽልጥልኝ ! ልብ አድርግ ዩላይ ፤ ሞቅ አድርገህ በልልኝ !"

ሁለት ጠና ያሉ ወታደሮች ልብሱን አወላለቁለት ። ያ ምስኪን ሰው እንደ መደንገጥ አለ ። ሕፃናት እንደሚያዋክቡት እንስሳ ተርበተበተ ። ከወታደሮቹ አንደኛው በብብቱ ሰቅስቆ እንዖቶ ሲያዝለውና ዩላይ ጅራፉን ብድግ አድርጐ ሲያጮህበት ባሽኪሩ ራሱን እንደደፋ አፉን ከፈት ከደን በማድረግ የሲቃ ድምፅ አሰማ ። በምላሱ ፋንታ ብቅ ጥልቅ ያለው ጁሽ ጣት የመሰለ አካል ነው ።

ሁሉም ግርም አላቸው ።" ከዚህ ወዲያ " አለ አዛገዡ " ከዚህ ሰው ምንም ዐይነት ፍንጭ ለመስማት የምችል አይመስለኝም ። ወደ እስር ቤቱ መልስልኝ ፤ ዩላይ ። ከእንግዲህ ከቡራን ! ወደሚጠብቁን ሌሎች ቁም ነገሮች እንመለስ ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ውይይታችንን ለመከፈት በዝግጅት ላይ እንዳለን ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና እየተንቀጠቀጠችና ቁና ቁና እየተነፈ ሰች ከክፍሉ ዘው ብላ ገባች ።

" ምን ሆንሽ ?" አላት አዛዡ በድንጋጤ ።

" ጉድ ሰምቼ መጣሁ ልጄ !" አለች ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና።ከሐይቁ በታች ያለው ምሽግ ዛሬ ጠዋት ተያዘ ፣ የአባ ጄራሲም አሽከር ከዚያው ገና አሁን መምጣቱ ነው ። ሲወረር በዐይኑ አይቷል ። አዛዡና መኮንኖቹ በሙሉ ተሰቅለዋል ። ወታደሮቹንም በሙሉ አስረዋቸዋል ።አን ዱን ሳንጨብጠው ወንበዴዎቹ እኛም ዘንድ መድረሳ ቸው ነው ።"

ባልታሰበው መርዶ ሁሉም ክፉኛ ደነገጡ ። ትሁ ትና ዝምተኛ ወጣት የነበረው የዚያን ምሽግ አዛዥ ዐው ቀዋለሁ ። ከሁለት ወራት በፊት እርሱና ሚስቱ ወደ ኦሬ ንበርግ ሲያልፉ ኢቫን ኩዚሚች ቤት ዐርፈው ነበር ። ምሽጋቸው ከምሽጋችን እምብዛም አይርቅም ። የፑጋ ቼቭ ወረራ በራችንን እያንኳኳ ነው ። የማሪያ ኢቫኖቭናን ዕጣ አሰላሰልኩና በሐዘን ተዋጥኩ ።

" ኢቫን ኩዚሚች !" አልኩት አዛዡን ፤ " ምሽጋ ችንን እስከ መጨረሻዋ የደም ጠብታችን ድረስ ከወራሪ ዎቹ መጠበቁ ተግባራችን ነው ። ይህን ሁላችንም እን ገነዘባለን ። ግን ለሴቶቹ ደህንነት ማሰብ አለብን ። ወደ ኦሬንበርግ ወይም ወንበዴዎቹ ወደማይደርሱበት ደህና ምሽግ ሴቶቹን ላካቸው ።"

ኢቫን ኩዚሚች ወደ ሚስቱ ዘወር ብሎ ፣ " እስቲ አድምጪኝ ሆዴ ፤ ወንበዴዎቹን ተቋቁመን እስከምን መልሳቸው ድረስ ወደ ሆነ ሥፍራ ብንልካችሁ አይሻልም?" አላት ።


t.me/OLDBOOKSPDF

“ ኧረ ኤዲያ ! ” በማለት መለሰችለት ። “ ለመሆኑ ጥይት የማይነካው ምሽግ አለ ? ይኸው ቤሎጎርስክስ መች አመለጠ ? በዚህ ምሽግ ለሐያ ሁለት ዓመታት ኖረናል ። ጌታ ያውቅልናል ። ጥንት ከባሽኪሮችና ከኪርጊዞች ወረራዎች እንዳዳነን ሁሉ ዛሬም ከፑጋቼብም ወረራ ነጻ ያወጣናል !”

“ እንግዲያውስ እንጀራ ” አላት ኢቫን ኩዚሚች ” በምሽጋችን ከተማመንሽበት ከዚሁ ቆይ ። ግን ማሻን ምን እናድርጋት ? ድል ከተቀዳጀን መልካም ። ምሽጋችንን ቢያጥለቀልቁትስ ?”

“ ቢሆንም . . . ” ብላ ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ከመጠን በላይ ስለ ተደናገጠች ንግግሯን ለመጨረስ አልቻለችም።

“ አይሆንም ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ” አላት አዛገፉ ፤ ምናልባትም በሕይወቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ምክሩ እንደሚሠራለት ተገንዝቦ ፤ “ ማሻ ከዚህ መቆየት የለባትም ። ወደ ኦሬንበርግ ክርስትና እናቷ ዘንድ መላክ ይኖርብናል ። ከዚያ በቂ ወታደሮችና መድፎች አሏቸው ፤ የከተማቸውም ግምብ የሚበገር አይደለም ። ስለዚህ አብራችሁ እንድትሔዱ እመክርሻለሁ ። በዕድሜሽ የገፋሽ ሰው ነሽና ምሽጋችን ከተወረረ ሊደርስብሽ የሚችለውን ማን ያውቃል !”

“ ይወረራ !” አለች ቫሲሊሳ ዩጉሮቭና ። “ ማሻን እንላካት ፤ እኔን ግን ትሔድልኛለች ብለህ አታልም ፤ አላደርገውማ ። በዚህ ዕድሜዬ ተለይቼህ ሔጄ በማላውቀው አገር ብቻዬን መቃብር አላስስም ።አብረን እንደኖርን አብረን እንሞታለን ።”

“ በዚሁ እንደምድመዋ” አላት አዛገፉ ። “ እንግዲያውስ እንዘግይ ። ሔጂና ማሻን ለጉዞዋ አዘጋጃት ።ነገ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውኑ በማለዳ እንልካታለን ፤ ትርፍ ሰው ባይኖረንም እንደ ምንም ብለን ሽኚ እንዲያጅባት እናደርጋለን ። ለመሆኑ አሁን የት ነች ?”

“ አኩሊና ፖምፊሎቭና ቤት ” አለችው ማሲስቱ። “ የሐይቁ ዳርቻ ምሽግ መያዙን ስትሰማ አጥወልውሏት ነበር ። ሳትታመም አልቀረችም ። አይ ፊጣሪዬ ! እንዳው ምን አመጣህብን !”

ቫሲሊሳ ዬጉሮቭና ልጅዋን ለመሸኘት ቀረጠች ። በአዛገዞ ክፍል ውስጥ ውይይቱ እንደቀጠለ ነበር ፤ ግን እኔ አልተሳተፍኩበትም ፤ ምን እንደ ተባባሉም በውል አልሰማሁም ። ማሪያ ኢቫኖቭና ገርጥታና ዐይኖቿ ደም መስለው ወደ ገበታ ቀረበች ። አለወትሮዋችን በዝምታ ጉራርሰን ወዲያውኑ ተነሣን ። ተሰነባብተንም ወደ የመኝታችን አመራን ። እኔ ግን ሰይፌን የረሳሁ መስዬ እንደገና ተመለስኩ ። ማሪያ ኢቫኖቭናን ብቻዋን ለማግኘት ፊል ጌያለሁ ። እንደ ተመኘሁትም በሩ ላይ ተገናኘንና ሰይፌን አቀበለችኝ ። “ ደህና ሁንልኝ ፖይትር አንድሬይች” አለችኝ እየተንሰቀሰቀች ። “ ወደ ኦሬንበርግ መሔዴ ነው ። በደስታ ኑርልኝ ። ጌታችን ፈቃዱ ከሆነ ፤ እንደገና እንገናኝ ይሆናል ። ካላለልንም . . . ደህና ሰንብችልኝ እንጂ ቴ፤ አለኝታዬ ! ምንም ልሁን ምን ሐሳቤና ጸሎቴ ሁሉ ለአንቺው ብቻ መሆኑን ተረጂልኝ !” ማሻ ደረቴ ላይ ተለጥፋ ተንሰቀሰቀች ። ጭምቅ አድርጌ ስሚያት ከቤቷ ውልቅ አልኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሰባት

### ማጥቃት

ስማኝ ጭንቅላቴ ፣ አንተ የኔ ራስ
ሠላሳ ሦስት ዓመት ያለማሰለስ
ስትባትል ቆይተህ ልብህ እስኪፈርስ !
ስንዝር ፈቅ ሳትል ካለህበት ቦታ
አጠገብህ ሳይደርስ ሀብትም ሆነ ደስታ
በፈጸምከው ጀብዱ ሳታገኝ እርካታ
በገመድ መሽምቀቅ ሆነ ያንተ ውለታ ።

( ከባህል ዘፈን የተወሰደ )

ማሪያ ኢቫኖቭናን ስታልፍ ለማየትና ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰናበት ስል ጉዞህ ሲቀድ ከምሽጋችን በር ላይ ለመ ገናኘት ስላሰብኩ አልተኛሁም ፣ ልብሴንም አላወለቅሁም። በራሴ ላይ ታላቅ ለውጥ እንደ መጣብኝ ተገነዘብኩኝ ። እስ ካሁን ከደረሰብኝ ሐዘንና ትካዜ ይልቅ በዛች ሰዓት የወ ጠረኝ የአእምሮ ጭንቀት በጣም ከባድ ነበር ። ከመለየት ስቃይ ጋር የተሳሰረ ፣ እጅግ የሚያስደስቱ የተስፋ ጭላንጭ ሎች ፣ ማለትም የመጣብንን አደጋ በወኔ የመጠባበቅና አኩሪ ተግባር የመፈጸም ጽኑ ፍላጐትም በውስጤ ሠር ጿል ። ሌሊቱ እንደ ምንም ዐለፈ ። ልክ ልወጣ ስል በሩ ተከ ፍቶ አንድ ዐሥር አለቃ ፊቴ ከቸች አለና ከእኛ ጋር የነ



t.me/OLDBOOKSPDF

በሩት ኮዛኮች በሌሊት ምሽጉን ጥለው እንደሔዱ ፣ ዱላ ይንም እስገድደው እንደ ወሰዱትና ያልታወቁ ሰዎች በአ ካባቢው በፈረስ እንደሚዘዋወሩ ገለጸልኝ ። ማሪያ ኢቫ ኖቭና በቶሎ ጉዞዋን ለመጀመር አለመቻልዋ አስደነገጠኝ። ለዐሥር አለቃው ጥቂት መመሪያዎች በጥድፊያ ከሰጠሁት በኋላ ወደ አዛዡ ቤት ገሠገሥኩ ። በመንጋት ላይ ነበር ። መንገዱን ይገፍ በፍጥነት በመራመድ ላይ እያለሁ ስሜ ሲጠራ ሰማሁ ። ቆምኩኝ ። " ወዴት ነው የምትከንፈው?" አለኝ ኢቫን ኢግናቲች እየደረሰብኝ ። " ኢቫን ኩዝሚች ከምሽጉ ስገነት ላይ ነው ። ወዳንተ ልኮኛል ። ፑጋቼቭ መጣኮ " አለ ። " ማሪያ ኢቫኖቭና ሔዳለች ?" ብዬ ጠየ ቅሁ ልቤ ታምቡር እየመታ ። " ስለ ዘገየች አልተሳካላ ትም " ሲል መለሰልኝ ኢቫን ኢግናቲች ። " ወደ ኦሬን በርግ የሚወስደው መንገድ ተዘግቷል። ምሽጉም ተከቧል ፣ አሥጊ ሁኔታ ላይ ነን ፣ ፖይቶር አንድሬይች ።" በተፈጥ ሮው ጉብታ ወደ ሆነውና በአጥር ወደ ተከለለው ምሽጋችን ስገነት አመራን ። የምሽጉ ነዋሪዎች በሙሉ ከዚያ ታጉ ረዋል ። ወታደሮቹ ጠብመንጃዎቻቸውን እንግተው በተ ጠንቀቅ ቆመዋል ። ከአንድ ቀን በፊት እየተሳበ የተወሰ ደው መድፍ ተጠምዷል ። አዛዡም ላይና ታች በመንጐ ራደድ አነስተኛ ጦሩን ይጐበኛል ። የአደጋው መቃረብ የአባት ጦረኞቹን ወኔ የቀሰቀሰ ይመስላል ። ሐያ የሚሆኑ ፈረሰኞች ከምሽጉ ብዙም ከማይርቀው አውላላ ሜዳ ላይ ሽምጥ እየጋለቡ ነው ። ኮዛኮች ይመስላሉ ። በረጃጅም መለ ዮዎቻቸውና በቀስት ማንደራቸው በቀላሉ ተለይተው የሚ ታወቁት ባሽኪሮችም በመካከላቸው ይገኛሉ ። አዛዡ ጦሩን ከጐበኘ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ተናገረ ፣" እንግዲህ ጐበዝ ፣ ዛሬ ለውዲቷ ንግሥታችን ጋሻ መሆን አለብን ። ቆራጥና ታማኝ አሽከሮች መሆናችንን ለመላው ዓለም በይፋ ማሳየት ይኖርብናል ።" ወታደሮቹ ከፍ ባለ ድምፅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወኔያቸውን ገለጹ ። ሽቫብሪን አጠገቡ ቆሞ ወደ ጠላት አተኩሮ ያያል ። በአውላላው ሜዳ ላይ ያሉት ፈረሰኞች የምሽጋችንን የውስጥ እንቅስቃሴ በመመልከታቸው ተሰ ባስበው ስለ ሁኔታው ውይይት ይዘው ነበር ። አዛዡ ኢቫን ኩዝሚች ወደ እነሱ መድፉን እንዲያዞር በማዘዝ ራሱ ተኮሰው ። የመድፉ ጥይት አደጋ ሳያደርስ በእናታ ቸው ላይ በረረ ። ፈረሰኞቹም ተበታትነው እየጋለቡ ከመ ቅጽበት ተሰወሩ ። አውላላው ሜዳ ዕርቃኑን ቀረ ።

ወዲያው ቫሲሊሳ ዬጎሮቭና ልትለያት የማትሻውን ማሻን አስከትላ ከስገኑቱ ላይ ብቅ አለች ። " ታዲያስ ?" አለች የአዛዡ ሚስት ። " ጦርነቱ እንዴት ይዟችኋል ? ጠላትስ የት ደረሰ ?" ጭር ያለውን ሜዳ እየቃኘች አለች። አዛዡም "ከዚህ ብዙም አይርቅ ። እግዚአብሔር መጨ ረሻውን ያሳምርልን ። ፈራሽ እንዴ ማሻ ?" አለ ። " እን ዲያውም አባዬ " ስትል መለሰች ማሪያ ኢቫኖቭና ፤ " ይበልጥ የምፈራው ብቻዬን ወና ቤት ታቅፌ መቀመጡን ነው ።" ይህን ተናግራ ወደ እኔ በመመልከት የሞት ሞት ዋን ፈገግታ አሳየችኝ ። ትናንት በእጅዋ የሰጠችኝ ጐራዴ ታወሰኝና ለፍቅረኛዬ ሕይወት ዘብ የቆምኩ ይመስል እጀ ታውን ሳላውቀው አፈፍ አደረኩት ። ልቤ በውስጤ ነደደ፤ ጋሻዋ ነኝ ብዬ አሰብኩ ። ለጣለችብኝ አደራ ብቁነቴን ለመግለጽ የምችልበትን ወሳኝ ወቅት በታላቅ ጉጉት እጠ ባበቅ ጀመር ።

ከምሽጋችን ግማሽ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ካለው ጉብታ በስተጀርባ ሌሎች ፈረሰኞች እየተንጋጉ ብቅ ብለው ሜዳው እንደገና ጦር በሚሰብቁ ፣ ቀስትና ደጋን በታጠቁ ሰዎች ተጥለቀለቀ ። በመካከላቸው ሐምራዊ እጀ ጠባብ የለበሰ አንድ ሰው ጐራዴውን መዞ ነጭ ድንጉላ ይጋልባል፤ ፑጋቼቭ ራሱ ነው ። ፈረሱን አቆመውና አፍታ ሳይቆይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተከበበ ። በዮጋቼቭ ትእዛዝ አራት ፈረሰኞች ሽምጥ ጋልበው ወደ ምሽጋችን ተጠጉ ። ከመካከላቸውም ከድተውን የሔዱትን ሰዎች ለይተን ዐወቅን ። አንደኛው ሉክ ብጤ ወረቀት ከራሱ በላይ ከፍ አድርጐ ይዟል ። ሌላው ደግሞ ጫፉ ላይ የዩላይ ጭንቅላት የተሰካበት ጦሩን ከነቀነቀው በኋላ ፣ ጭንቅላቱን በአጥሩ ላይ አሻግሮ ወደ እኛ አንከባለለው ። የምስኪኑ ጭንቅላት አዛዥ እግር ሥር ዱብ አለ ! ሽፍቶቹም በጩኸት “ አትተኩሱ ፤ከንጉሡ ፊት ቅረቡ ፤ ንጉሡ እዚህ ናቸው ” አሉን ።

“ እኔው ‘ ንጉሥ እሰጣችኋለሁ ” ሲል አምባረቀ ኢቫን ኩዝሚች ። “ ጐበዝ ፤ ተኩስ ከፈቱ !” ወታደሮቻችን የጥይት እሩምታ አወረዱ ። ደብዳቤውን ይዞ የነበረውን ኮዛክ ከኮርቻው ላይ አጋድሎ ወደ መሬት ወደቀ ። የቀሩት እየጋለቡ ተመለሱ ። ማሪያ ኢቫኖቭናን አየት አደረግኋት ። በደም የተለወሰውን የዩላይን ጭንቅላት ማየት ስለሰቀጠጣትና የጥይት እሩምታው ስላስደነገጣት በከፊል ልቧን የሳተች ትመስላለች ። አዛዡ አንዱን የዐሥር አለቃ ጠርቶ ከሞተው ኮዛክ እጅ ወረቀቱን እንዲወስድ አዘዘው። ዐሥር አለቃው ወደ ሜዳው ጋልቦ የሞተውን ሰውዬ ፈረስ በልጓም እየሳበ ተመለሰ ። ደብዳቤውንም ለአዛዡ አስረከበ ። ኢቫን ኩዝሚች ካነበበው በኋላ ቦጫጨቀው ።ነገር ግን ወንበዴዎቹ ለማጥቃት በመዘጋጀት ላይ መሆናቸው በግልጽ ይታይ ነበርና ወዲያው ጥይቶቻቸው እያፏጩ በጆሯችን በኩል ሽው ይሉ ጀመር ። ጥቂት ቀስቶችም በአካባቢያችንና ዙሪያችን ባለው አጥር ላይ ተሰገሰጉ ።“ቫሲሊሳ ዩጐሮቭና ” ሲል ተጣራ አዛዡ ። “ ይህ ለሴቶች የሚሆን ቦታ አይደለም ። ማሻን ወዲያ ውሰጂያት ። እስቲ ተመልከቺ ፤ በድን ሆናለችኮ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ቫሲሊሳ ዬጉሮቭና በጥይቱ እሩምታ ተሸማቃ ስት ፈራ ስትቸር እንገትዋን አቃንታ ሜዳው ላይ የሚደረገውን ሸብ ረብ ተመለከተች ። ቀጥሎም ወደባልዋ ዞወር በማለት " ኢቫን ኩዝሚች ፣ ብንሞትም ብንተርፍም ያለነው በእ ግዜር እጅ ነው ። በል ማሻን መርቃት ። ማሻ ሒጂ አባትሽ ዘንድ ።"

ማሻ ዐመድዋ ቡን ብሎ እየተብረከረከች ኢቫን ኩዝ ሚች ዘንድ ቀርባ ከጫማው ላይ ወደቀች ። አዛውንቱ አዛዥ በላይዋ ላይ ሦስት ጊዜ ካማተበ በኋላ ብድግ ያ ድር ጓት ሳማትና በሚንቀጠቀጥ ድምፅ እንዲህ አላት ። " እን ግዲህ ማሻ ደስታ አይለይሽ ፣ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ ፣ እርሱም ጥሎ አይጥልሽም ። እግዚአብሔር ፍቅሩንና ምክ ሩን ይለግስሽ ፣ ጥሩ ባልም ያጋጥምሽ ። ቫሲሊሳ እና እኔ አብረን እንደኖርን አንቺም አብረሽው ኑሪ ። ደህና ሁኚ ማሻ ! ቫሲላሳ ዬጉሮቭና ፣ በይ በአስቸኳይ ከዚህ ገለል አድርጊያት ። " ማሻ እትከሻው ላይ ተጠምጥማ ተንሰቀ ሰቀች ።" እኛም እንሳሳም እስቲ" አለች የአዛገዞ ሚስት ወደ ባሏ ተጠግታ እያነባች ። " ደህና ሁን የኔ ኢቫን ኩዝሚች ፣ አንተን ለማሳዘን የፈጸምኩት ካለ ማረኝ !" " ደህና ሁኚ ወለላዬ ፣ደህና ሁኚ !" አለ አዛገዞ እሮጊት ዋን ሚስቱን እቅፍ አድርጎ ። " እንግዲህ ይብቃ ! ወደቤት ሒጂ ! በይ ቶሎ በይ !"

እናትና ልጅ ሔዱ ። ማሪያን አተኩሬ አየኋት ። እሷም ወደ እኔ ዞወር ብላ አንገቷን ደፋ አደረገችልኝ ። ቀጥሎም ኢቫን ኩዝሚች ወደ እኛ ተመልሶ ሙሉ ትኩረቱን ከጠ ላት ላይ አሳረፈ ። ወደ አለቃቸው በማልቢያ ያመሩ የነበ ሩት ወንበዴዎች ወዲያውኑ ከየፈረሶቻቸው ላይ ዱብ ዱብ ማለት ጀመሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ቆራጥ ሁኑ" አለ አዛገ ።-" ሊፋለሙን ነው ።"
በዚያ ወቅት አስደንጋጭና የሚሰቀጥጥ ድምፅ ተሰማ ። ወንበዴዎቹ ባላቸው ኃይል ሁሉ ወደ ምሽጉ እየተንደረደሩ ነበር ። መድፋችን ጉረሰ ። ጠላቶቻችን በጣም እስኪቀር ቡን ድረስ ዕድል ከሰጠናቸው በኋላ በድንገት ተኮስን ። ጥይቱ እወንበዴው መንጋ መኻል ዐረፈ ። ወንበዴዎቹ በግራና በቀኝ ተበታትነው አፈገፈጉ ። መሪያቸው ብቻ ውን ፊት ለፊት ቆሞ ቀረ ። ጉራዴውን እየሰበቀ በጉጉት የሚያደፋፍራቸው ይመስላል ። ጋብ ብሎ የነበረው ጩኸ ትና የሚሰቀጥጥ ድምፅ ወዲያውኑ እገረሸ ። " እንግዲህ ጉበዝ " አለ አዛገ " በሩን ከፊቱና ንጋሪት ጉስሙ ። ወደፊት ! ጉበዝ ተከተሉኝ !"

አዛገ ፣ ኢቫን ኢግናቲችና እኔ ራሴ ወዲያው በስገ ኑቱ በእንደኛው ወገን ቦታችንን ያዝን ። ቃፊሮቹ ከመሸ በረቻው የተነሣ ደርቀው ቀሩ ። " እዚያ ምን ገተራችሁ ጉበዝ ?" በማለት ጮኸ ኢቫን ኩዝሚች ።" መሞት ካለ ብን መሞት ይኖርብናል ። የወታደር ዕጣው ይኸው ነው ።" እፍታ ሳንቆይ ወንበዴዎቹ ምሽጉን በኃይል ጥሰው ወረሩን ። የነጋሪቱ ድምፅ ጸጥ አለ ። ቃፊሮቹ ጠበንጃዎ ቻቸውን ወረወሩ ። ተገፍትሬ ወድቄ ነበር ። ሆኖም እን ደገና ተነሥቼ ከወንበዴዎቹ መሐል ገባሁ ። አዛገችን ራሱን ተመትቶ ቁልፎቹን እንዲያስረክብ ሲያዋክቡት እየሁ ። ልደርስለት በመጣደፍ ላይ ሳለሁ ጥቂት የፈረጠሙ ስዛኮች እፈፍ አድርገውኝ ፣" ንጉሡን በመቃወምህ ዋጋ ህን ታገኛለህ " እያሉኝ በቀበቶዋቸው ጠፈሩኝ ። በየጐ ዳናው ላይ ተጐተትን ። ነዋሪዎቹ ዳቦና ጨው ይዘው ከየ ቤታቸው ወጡ ። የቤተክርስቲያን ደወሎች እስተጋቡ ። " ወዲያው 'ንጉሡ' አደባባዩ ላይ ሆኖ ታማኝነታቸውን በቃለ መሐላ ለመግለጽ ከፊቱ የሚቀርቡትን እስረኞች



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጠባበቅ ላይ መሆኑን የሚገልጽ ጥሪ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ተሰማ ። ሰዉ ወደ አደባባዩ ጐረፈ ። እኛም ወደዚያው ተነዳን ።

ጉጋቼቭ ከአዛዡ መኖሪያ ቤት በረንዳ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ተኮፍሷል ። በሐር ጉንጉን የተከፈፈ ቀይ እጀ ጠባብ ለብሷል ። እሳት ከሚተፉት ዐይኖቹ ላይ ባለወርቅ ዝምዝም ቆቡን ደፋ አድርጓል ። የማውቀው መሰለኝ ። የኮዛክ አዛውንት ዙሪያውን ከበውታል ። አባ ጂራዚም ከበረንዳው ፊት ለፊት ቆመውና ፊታቸው የተቀቀለ ሳምባ መስሎ እያንቀጠቀጣቸው ፤ መስቀላቸውን በእጆቻ ቸው እንደያዙ ቅጣት የሚጠብቃቸው ሰዎች ይቅርታ እንዲ ደረግላቸው በለሆሳስ ድምፅ የሚማፀኑ ይመስላሉ ። አደ ባባይ ላይ መስቀያ እንጨት በጥድፊያ እየተተከለ ነበር። እኛ እንደ ደረስንም ባሽኪሮቹ ሕዝቡን እየገፈታተሩ ከጉ ጋቼቭ ፊት አቀረቡን ። የደወሉ ድምፅ ጸጥ አለ ። ሙሉ ጸጥታ ነገሠ ። “ አዛዡ የትኛው ነው?” ሲል ጠየቀ ጉጋቼቭ ከድቶን የሔደው ሃምሳ አለቃ ከሕዝቡ መሐል ነጠል ብሎ ወደ ኢቫን ኩዝሚች አመለከተው ። ጉጋቼቭ ሽማግሌውን በሚስበልብ ግልምጫ ከገረፈው በኋላ እንዲህ አለው ። “ እኔን ንጉሥህን ለመውጋት እንዴት ደፈርክ በል ?” በመቁሰሉ ምክንያት የተዳከመው አዛዡ እንደ ምንም ብርታቱን አሰባስቦ ጐላ ባለ ድምፅ ፤ “ አንተ የኔ ንጉሥ አይደለህም ። አንተ ወሮበላና አስመሳይ ነህ ። አዎን ወሮ በላ ነህ ፤ ትሰማኛለህ?” በማለት ወረፈው ። ጉጋቼቭ በሚያ ስፈራ አኳኋን ግምባሩን ቋጥሮ አንድ ነጭ መሐረብ አውለበ ለበ ። ጥቂት ኮዛኮች ሽማግሌውን አዛዥ እንቀው መስቀያው እንጨት ሥር ወረወሩት ። ከሁለት ቀን በፊት የተገረ ፈው አካለ ጐደሎው ባሽኪር መስቀያው ላይ እግሮቹን አንፈራጦ ቆሟል ። በእጆቹ ገመድ ይዞ ነበር ። ከአንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደቂቃ በኋላም ምስኪኑን ኢቫን ኩዝማች አየር ላይ ተን ጠልጥሎ አየሁት ። ቀጥሎም ኢቫን ኢግናቲች ከፑጋ ቼቭ ፊት እንዲቀርብ ተደረገ ። “ ቃለ መሐላ ፈጽም ” አለው ፑጋቼቭ ። “ የታማኝነት ቃለ መሐላህን ለእኔ ለን ጉሥህ ፖይቶር ፍዮዶሮቪች ግለጽ ” “ አንተ የእኛ ንጉሥ አይደለህም ” ሲል መለሰለት ኢቫን አግናቲች በቆራጥ ነት ። “ አንተ ወሮበላና አስመሳይ ነህ ! ” ፑጋቼቭ እን ደገና መሐረቡን አውለበለበ ። ከዚያም ያ ተወዳጅ መቶ አለቃ ከአዛዡ መኮንኑ አሬሣ ጐን ይወዛወዝ ጀመር ።

ቀጥሎም የኔ ተራ ደረሰ ። ፑጋቼቭን በልበ ሙሉነት አየሁት ። የቆራጦቹን ጓዶቼን ቃላት ለመድገም ተዘጋ ጀሁ ። ሽፍቶቹ የኮዛክ እጀ ጠባብ ለብሶና በኮዛክ ሞድ ጸጉሩን ተቆርጦ በወንበዴዎቹ መካከል ቆሞ በማየቴ በጣም ተገረምኩ ። ወደፑጋቼቭ ሔዶም ጥቂት ቃላት በጆ ሮው ሹክ አለው ። “ ስቀሉት !” አለ ፑጋቼቭ እምብዛም ወደ እኔ መልከት ሳይል ሸምቀቆ በአንገቴ ላይ ተጠለቀ ። ጸሎት ማድረስ ጀመርኩ ። እግዚአብሔር ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር እንዲለኝና የምወዳቸውን ሁሉ እንዲጠብቅልኝ ተማ ፀንኩኝ ። ወደ መስቀያው ተጐትቼ ተወሰድኩ ። “ አት ፍራ ! ” አሉኝ የያዙኝ ሰዎች በመደጋገም ፤ ምናልባትም ሊያጽናኑኝ ፈልገው ይሆናል ። “ ቆዩ እናንተ እርጉሞች! ቆዩ ! ” የሚል የእሪታ ድምፅ ሰማሁ ። የሞት ቅጣት ፈጻሚዎቹ ዝግጅታቸውን አቋረጡ ። ዙሪያዬን ተመለከ ትኩ ። ሳቬሊች ፑጋቼቭ ጫማ ላይ ወድቋል ። “ ርኅሩኅ ጌታዬ ሆይ !” ብሎ ጮኸ ምስኪኑ ሞግዚቴ ፤ “ የጌታዬን ልጅ አይግደሉብኝ ። ይልቀቁት ፤ ወላጆቹ በምትኩ ገን ዘብ ይከፍሉዎታል ። ካስፈለገም ከእሱ ይልቅ እኔን ሸማ ግሌውን እንዲሰቅሉኝ ይዘዟቸው ።” ፑጋቼቭ አንድ ምል ክት ሰጠና እኔም ወዲያውኑ ተፈትቼ ተለቀቅሁ ። “ ንጉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳችን ምሕረት አደርገውልሃል ” አሉኝ ይዘውኝ የነበሩት ሰዎች ። በዚያን ወቅት በመትረፌ ተደስቼያለሁ ለማለት አልችልም ፤ ቁጭትም አላደረብኝም ። የዋጠኝ ስሜት ከመጠን በላይ መላቅጡ የጠፋ ነበር ። ፑጋቼቭ ዘንድ በድጋሚ እንድቀርብና ከፊቱ እንድንበረከክ ተደረገ ። ፑጋቼቭም ጅማታም እጁን ወደ እኔ ዘረጋ ። “ እጃቸውን ሳም! እጃቸውን ሳም !” የሚል ድምፅ ከሁሉም አቅጣጫ ሰማሁ።

እንደዚህ ካለ ከፍተኛ ውርደት ይልቅ ያን እጅግ የሚያስቅቅ የሞት ጽዋ ብቀምስ እመርጥ ነበር ። “ ጌታዬ ፓዮቶር አንድሬይች ! “ አለኝ ሳቬሊች በሹክሹክታ ከኋላዬ ሆኖ እየነካካኝ ” እልኸኛ አትሁን ! ምን አሻህ ፡ እንትፍ ብለህ አረመኔውን . . . ሳም ፡ እጁን ሳም ማለቴ ነው ።’

እኔ ንቅንቅ አላልኩም ። ፑጋቼቭ እንደገና እጁን ሰብስቦ ፡ “ ምናልባት ክቡርነታቸው በደስታ ሰክረው ይሆናልና በሉ እስቲ አቁሟቸው ! ” ሲል አፌዘብኝ ። በዚህ አኳኋን በነጻ ተለቅቄም ግፉ ሲቀጥል የዐይን ምስክር ለመሆን በቃሁ ። ነዋሪዎቹ በየተራ እየቀረቡ መስቀል በመሳለምና ለአስመሳዩ በመስገድ ታማኝነታቸውን መግለጽ ያዙ። ወታደሮቻችንም ከዚያው ነበሩ ። ዱልዱም መቀስ ያነገበ የክፍለ ጦሩ ልብስ ሰፊ ወታደሮች እየጐነጐኑ እንደ ጅራት ያንጠለጠሉትን ጸጉራቸውን እየጐመደ ጣለባቸው ። እነሱም ጸጉራቸውን እያራገፉ የፑጋቼቭን እጅ ከሳሙ በኋላ ምሕረት እየተደረገላቸው ከጭፍሮቹ ጋር ተቀላቀሉ ። ትርዒቱ ሦስት ሰዓት ያህል ፈጀ ። በመጨረሻም ፑጋቼቭ ከወንበሩ ተነሥቶ በመኰንኖቹ አጃቢነት ከበረንዳው ወረደ ። በጌጥ ያሸበረቀና ሻሽ የመሰለ ፈረስ ቀረበለት ። ሁለት ኰዛኮች ብብቱን ይዘው ወደላይ በማንሣት ከኮርቻው ላይ አወጡት ። አብረውት ምሳ እንዲበሉ አባ ጂራዚም ተጋበዙ ። ወዲያው የእንዲት ሴት እሪታ ተሰማ ። ጥቂት ወን


t.me/OLDBOOKSPDF

በደጆዎች ቫሲሊሳ ዩጎሮቭናን እርቃን ሥጋዋን አስቀርተው ጸጉርዋ እንደ ተንጨፈረረረ ወደ በረንዳው ሲጎትትዋት አየሁ ። ከወንበዴዎቹ አንዱ ወፍራም ጃኬትዋን ለብሶ ሲን ጎማለል ፡ ሌሎቹ ደግሞ በላባ የተጠቀጠቁ ፍራሾች ፡ የሚ ያማምሩ ሳንዱቆች የሻይ ማቅረቢያ ዕቃዎች በእጅ ሥራ የተዋቡ የሐር ጨርቃጨርቆችና የቤት ቁሳቁሶች በያ ይነቱ ወደውጭ ሲያግዙ ተመለከትኩ ። “ ጌቶቼ ! ”በማ ለት ትጮኽለች ምስኪንዋ አሮጊት ፡ “ በሰላም ልሙት ። ይቅር ባይ አባቶቼ ፡ ኢቫን ኩዝሚች ዘንድ ውሰዱኝ ! ” በድንገት ወደ መስቀያው ስትመለከት የባልዋን አስከሬን ለይታ በወቀችና “ አረመኔዎች ! ” ስትል ጮኸች ። በሲቃ የምትይዝ የምትጨብጠው ጠፍቷት ፡ “ እንዲህ ታደር ጉት ? ኢቫን ኩዝሚች ፡ ያይኔ ብርሃን ፡ ጀግናው ወታደር ! የፕሩሲያ ሳንጃና የቱርክ ጥይት እንኳ ዝንብህን እሽ አላ ሉትም ነበር ። በእንዲያ በመሰለው ክቡር የጦር ሜዳ ሳይ ሆን በአንድ ወሮበላ እጅ ሕይወትህ አለፈች ! ” እያለች በምትንቀሳቀስበት ወቅት “ የዚህችን አሮጊት ሹል ምላስ አሳርፍልኝ ” አለ ፑጋቼቭ ። ወዲያው አንድ ወጣት ኮዛክ እናትዋን በጐራዴ ተረከከውና ከበረንዳዋ ደረጃዎች ላይ ተዘረረች ። ፑጋቼቭ መንገዱን ቀጠለ ። ሕዝቡም ተከት ሎት ጐረፈ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ስምንት

## ያልተጠራ እንግዳ

አካባቢዬ ጭር ብሏል ። ከነበርኩበት ቦታ ደርቄ ቆሜ ያለሁ ። በሚያሸብሩ ስሜቶች ግራ ተጋብቼ ሐሳቤን ለመ ሰብሰብ ተስኖኛል ።

ከሁሉም ይልቅ ፣ ከፍተኛ ጭንቀት ላይ የጣለኝ የማ ሪያ ኢቫኖቭናን ዕጣ አለማወቄ ነበር ። የት ትሆን ? ምን ሆና ይሆን ? ለመደበቅ ችላለች ? የተደበቀችበት ሥፍራስ የሚያድናት ነው ? እንዲህ በሚያስጨንቁ ሐሳቦች ተውጬ ወደ አዛዡ ቤር አመራሁ ። ሁሉም ነገር ድብልቅልቁ ወጥቷል ። ወንበሮቹ ፣ ጠረጴዛዎቹና ቁም ሳጥኖቹ ተሰባብ ረዋል ። ሣህኖቹ እንክትክት ብለዋል ። ሁሉም ነገር ተዘ ርፏል ። ወደ መኝታው ቤት የሚወስደውን ደረጃ በአንድ ትንፋሽ ወጥቼ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከማሪያ ኢቫኖ ቭና ክፍል ገባሁ ። አልጋዋ ተመሰቃቅሏል ። የልብስዋ ቁም ሳጥን ተሰብሮ ውስጡ የነበረው ተወስዷል ። አንዲት መብራት ጭል ጭል እያለች ነበር ።

መስኮቶቹ አጠገብ የተሰቀለው መስተዋት አልተሰ በረም ። የዚች ትንሽ ክፍል ባለቤት ፣ ያች ልጃገረድ የት ይሆን ያለችው ? አስደንጋጭ አሳብ በአእምሮዬ ብልጭ አለብኝ ። እነዚያ ወንበዴዎች እጅ ገብታ ታየችኝ ። ልቤ ቀጥ ያለ መሰለኝ ። የፍቅረኛዬን ስም ጮክ ብዬ እየጠራሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

በምሬት አለቀስኩ ። ከዚያም ዝቅተኛ ድምፅ ሰምቼ ዞር ስል ከቁም ሳጥኑ ኋላ ፓላሻን አየኋት ። በጣም ገርጥታለች ። እየተንቀጠቀጠች ፣ " እየ ጉድ ፓይቶር እንድሬይች " አለ ችኝ ተስፋ በመቁረጥ መልክ " ከቶ ምን ቀን ነው ! ምን ዐይነት መቅሠፍት ነው !"

" ማርያ ኢቫኖቭና የት እንዳለች ታውቂያለሽ ?" ስል ጠየቅሁዋት በመቅበጥበጥ ። " ማርያ ኢቫኖቭና ደህና ትሆን ?"

" እሷስ ደህና ነች " ብላ መለሰችልኝ ፖላሻ ። አኩ ሊና ፓምፊሎቭና ቤት ተደብቃለች ።"

" እቄሱ ቤት ! " አልኩ በድንጋጤ ። " የእግዚር ያለህ ! ፑጋቼቭ ያረፈው ከዚያው ነው ኮ !" ከዚያች ክፍል ውልቅ ብዬ ከመቅጽበት ወጣሁና በመንገዴ ያጋጠመኝን ሁሉ ልብ ሳልል ወደቄሱ ቤት ገሠገሥኩ ። በቤቱ ውስጥ ዋካታ ፣ ጫቅና ዘፈን ደርቷል ። ፑጋቼቭ ከጓደኞቹ ጋር እየ ፈንጠዘ ነበር ። በሩጫ የደረሰችብኝን ፖላሻን የቄሱን ባለ ቤት በምስጢር እንድትጠራልኝ ላኳት ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቄሱ ባለቤት ከበረንዳው ላይ ብቅ አለችልኝ ፣ እንደ ባዶ ጠርሙስ ታቅፋ ።

" ስለ እግዚር ብለሽ ፤ ማሪያ ኢቫኖቭና የት እንዳለች ንገሪኝ !" አልኳት በጭንቀት ተውጬ ።

"ጓዳ ውስጥ አልጋዬ ላይ ጋደም ብላለች" በማለት መለ ሰችልኝ ። " እያድርስ እኮ ነው ፖይቶር እንድሬይች ! እስ ቃቂ ነገር ሊገጥመን ነበር ። ግን ለእግዚር ምስጋና ይግ ባውና ሳይሆን ቀረ ። ወንበዴው እራቱን ሊበላ ገና ዐረፍ እንዳለ ፣ ያች ምስኪን ከእንቅልፏ ነቅታ ኢቃሰተች ። ከቆ ምኩበት ቦታ ውሃ ሆንኩ ። እሱም ሰምቶ ኖሮ ' ማን ነው የሚያቃስተው አባክሽ ? ' ሲል ጠየቀኝ ። ዝቅ ብዬ እጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከነማሁ በኋላ ፤ ‘ የእህቴ ልጅ ነች ፤ ጌታዬ ። ታማለች ። ያልጋ ቁራኛ ከሆነች አንድ ሳምንት አለፋት ’ አልኩት ። ‘ ለመሆኑ ወጣት ነች ?’ ‘አዎን ጌታዬ’ ስለው ‘እንግዲያስ አስተዋውቂኛ ’ አለኝ ። የልቤ ምት ጨመረ ተጨነቅሁ ። ‘ እሺ ጌታዬ ፤ ግን ልጅትዋ ተኝታ ከቡርነትዎ ዘንድ ለመ ምጣት አትችልም ’ አልኩት ። ‘ ግዴለም ፤ እኔው እራሴ ሔጄ አያታለሁ ’ አለኝና ያ እርጉም ወደ ጓዳ ገባ ። ከዚያስ ምን ያደረገ ይመስልሃል ? መጋረጃውን ገልጦ ጭልፊት ዐይኖቹን ተከለባት ። አበቃላት ብዬ ነበር ! እግዚአብሔር ቸር ነው ። ሽማግሌው ባለቤቴ እና እኔ የሰማዕታት ሞት ለመቀበል ቆርጠን ነበር ። ወንድሜ ሙት ፤ ደግነቱ ያች ገብል ለይታ አላወቀችውም ። የኃያሉ ፈጣሪ ያለህ ! ኧረ ምኑን ሊያሳየን ነው ያቆየን ! ወይኔ ! አይ ኢቫን ኩዝሚች! አይቫሲላሳ ዩጉሮቭና ! አይ ኢቫን ኢግናቲች ! . . . ’’ አለች የሞቱትን እስታውሳ ። “ አንተስ እንዴት ለቀቁህ ? አሌክሲ ኢቫኒች ሽቫብሪንማ ጸጉሩን እንደ ኮዛኮቹ ተቆርጦ በገዛ ቤታችን እየፈነጠዘ ነው ፤ ብልሃተኛ አይደለም ? ስለ ሕመ ምተኛዋ የእህቴ ልጅ ስናገር እንዴት እንደ ገረመመኝ ባየ ኸው ፤ በዐይኖቹ ስርስሮኝ የገባብኝ ነው የመሰለኝ ።ግን አሳልፎ አልሰጠኝም ። ለዚህም ልናመሰግነው ይገባል ። በዚህ ጊዜ የእንግዶቹ የስካር ሁካታ ተጋግሎ ነበር ። በመሀሉ የአባ ጂራዚም ድምፅ ተሰማ ። እንግዶቹ ቮድካ ስለ አዘዙ ለሚስቱ ይህንኑ ነግሯት ወዲያና ወዲህ ትራወጥ ጀመር ። “ ወደ ቤትህ ሒድ ’’ አለችኝ ። “ ከዚህ መቆየት የለብህም ። ወንበዴዎቹ ተሳክረው እየተራበሹ ነውና ከዚህ ዝር እንዳትል ። ደህና ሁን ፖይቶር አንድሬይች ፤ የሚሆነው ይሆናል ። ምናልባት እግዚአብሔር ይረዳናል ።

የቄሱ ሚስት ወደ ቤት ገባች ። ትንሽ ተንፈስ ብዬ ወደ መኖሪያዬ ተመለስኩ ። አደባባዩን ሳቋርጥ ጥቂት ባሽ


t.me/OLDBOOKSPDF

ኪሮች ተሰባስበው በመስቀያው ላይ የሚወዛወዙትን ሬሳ ዎች ቦት ጫማ ሲያወላልቁ አየሁ ። ጣልቃ መግባቱ እን ደማያዋጣኝ ተገንዘብኩና ንዴቴን በሆዴ አመቅሁ ። ወንበዴዎቹ ላይና ታች እየተሯሯጡ የመኮንኖችን መኖ ሪያ እየዘረፉ ነበር ። ከቢት ስደርስ ከሳቪሊች ጋር በር ላይ ተገናኘን ። ገና ሲያየኝ “ ተመስገን አምላኪ !”አለ ። “ እንደገና ወንበዴዎቹ እጅ ገብተሃል ብዬ ተጨንቄ ነበር ። እንዲያው ምን ታስባለህ ጌታዬ ፖይቶር አንድሬይች ? እነዚህ ወሮበሎች ንብረታችንን ሙልጭ አድርገው ዘር ፈውናልኮ ። ልብስ ፣ አንሶላ ፣ ሳህን . . . ምንም አልቀ ራቸው ! ግን ምንም አይደል ፣ አንተን ከነሕይወትህ በመ ልቀቃቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው ። ለመሆኑ የወንበዴዎቹን መሪ አውቀኸዋል ጌታዬ ? ”

“ የለም ፣ አላወቅሁትም ። ማነው እሱ ?”

“ ምነዋ ጌታዬ ! ሆቴል ሳለህ የቆዳ ኮትህን የሸለ ምከውን ያን ሰካራም ፍጡር እረሳኸው ? አዲስ ኮት ነበ ርኮ ፣ ለመልበስ ሲሞክር እጅጌውን ተረተረው እንጂ !” ግርም አለኝ ። በእርግጥም የፑጋቼቭና የዚያ ሰው መመ ሳሰል የሚያስደንቅ ነበር ። አሁን ገና ፑጋቼቭና ያ ሰው አንድ መሆናቸውን ተረዳሁ ። ምሕረት የተደረገልኝ ምክ ንያት ምን እንደሆነም ደረስኩበት ። “ እንዲህ ያለ እንግዳ ነገር አያስደንቅም ? ለዚያ በረንዳ አዳሪ የሸለምኩት ኮት እኔን ከስቅላት ማዳኑና ከሆቴል ሆቴል ይንከራተት የነበ ረው ያ ሰካራም ዛሬ ምሽግ እየጣለ መንግሥትን በማናጋት ላይ መሆኑ ይገርማል ! እህል ብጤ አፍህ አታደርግም ?” ሲል ጠየቀኝ ሳቪሊች ። “ እስከዚህ የሚጥም ነገር እንኳ የለም ፣ ግን ላንተ የምትሆን ታህል እንኳ እስቲ ልፈላልግ” ብሎኝ ወጣ አለ።ብቻዬን በመሆኔ ሐሳብ ውስጥ ተዘፈቅሁ፣ ምን ማድረግ አለብኝ ? እዚሁ ምሽግ ውስጥ ለወንበዴው



t.me/OLDBOOKSPDF

እየሰገዱ መቆየትም ሆነ ከጭፍሮቹ ጋር መቀላቀል ለአንድ መኰንን ውርደት መሆኑ ይገባኛል ። በዚች ቀውጢ ወቅት ለእናት አገሬ ልዕልና ልሠለፍ በምችልበት ስፍራ መዋል እንዳለብኝ ሕሊናዬ ያስገነዝበኛል . . . ፍትር ደግሞ ከማሪያ ኢቫኖቭና ጐን እንድቆምና ጥላ ከለላዋ እንድ ሆን በግዴታ ይገፋፋኛል ። ሁኔታው በቅርብ ጊዜ ውስጥ መለወጡ እንደማይቀር ቢታየኝም የገጠማትን ከባድ ፈተና ፡ ማሰቡ ያንቀጠቅጠኛል ።

ከኰዛኮቹ መካከል አንዱ በመምጣቱ ከሐሳቤ ባነንኩ ፣ እሱም እየተጣደፈ ገብቶ “ ንጉሡ እንድትመጣ አዘውሃል” ብሎ ነ ስታወቀኝ ። “ የት ነው ያሉት ?” ስል ጠየቅሁት ትእዛዙን ለመፈጸም እየተዘጋጀሁ ። “ ከአዛዡ ቤት” ሲል መለሰልኝ ኰዛኩ ። “ ከምሳ በኋላ ጌታችን ወደ መታጠ ቢያ ቤት ገብተው ነበር ። አሁን ዕረፍት ላይ ናቸው ።ሰው ዬው የሚያስፈሩ ከባድ ሰው ሳይሆኑ አይቀሩም ። ሁለት የዓሣማ ግልገሎች ጥብስ ሙጥጥ አድርገው በመብላታቸው አስተናጋጁ ታራስ ኩሮችኪን ደንግጠና በላብ ተዘፍቆ ፣ የጠረጴዛ መወልወያውን ለወጥቤቲቱ ለፎምካ ቭከሊቭ ከወረወረላት በኋላ፣ ወደ ወንዝ ወርዶ ሲዘፈቅ ቢውልም ትን ፋሹ ገና አልተመለሰለትም ። እርስዎም ሲያዩዋቸው ምን እንደሚሰማዎት እንጃ ! አድራጐታቸው ሁሉ ከባድ ነው ። ጌቶች ከመታጠቢያ ቤት ውስጥ እንዳሉም በደረታቸው ላይ የተነቀሱትን የብር መኃለቅ የሚያክሉ መንታ ንሥሮ ችና የራሳቸውን ምስል አሳይተውናል ። የሚያመለክቱትም ንጉሣዊ ዘር እንዳላቸው ነው ።”

የኰዛኩን አሳብ መቃወም አግባብ ሆኖ አላገኘሁትም ። ከፑጋቼቭ የሚቀርብልኝን ጥያቄ እያሰላሰልኩ አብሬው ወደ አዛዡ ቤት አመራሁ ። እንባቢ በቀላሉ እንደሚገም ተውም በጥሪው አልተደሰትኩም ።


t.me/OLDBOOKSPDF

እዛገቶ ቤት ስደርስ ቀኑ ደንገዝገዝ እያለ ነበር ።መስ
ቀያው እንጨት ጽልመት ለብሶ ከሚወዛወዙት እሬሳ
ምች ጋር እጅግ ያስፈራል ። የምስኪንዋ የቫሲሊሳ ዩጎሮቭና
ሬሳ አሁንም ከበረንዳው ላይ ተዘርግቶ በአቅራቢያው
ሁለት ተረኛ ኮዛኮች ዘብ ቆመዋል ። ያጀቡኝ ኮዛኮች መም
ጣቴን ለማስታወቅ ከገቡ በኋላ ፤ ወዲያውኑ ተመልሰው
ከሁለት ቀናት በፊት በጥልቅ ስሜት ከማሪያ ኢቫኖቭና
ጋር ወደ ተወያየንበት ክፍል መሩኝ ።

የሚያስገርም ትዕይንት ከፊቴ ድቅን አለ ። ነጭ
ጨርቅ በሶበሰውና ጠርሙስና ብርጭቆ በተደረደሩበት
ጠረጴዛ ዙሪያ ፑጋቼቭ ዐሥር በሚሆኑ ረጅም መለዮ በደ
ፋና ደማቅ ሸሚዝ ባጠለቁ ኮዛኮች ተከብቦ ተቀምጧል ።
ሁሉም በመጠጥ ተጋግለው ፊታቸው ቀላልቷል ። ዐይኖ
ቻቸውም ይምቦገቦጋሉ ። አዲስ ምልምሎቹ እንዚያ ከሐ
ዲዎች ሽቫብሪንና ማክሲሚች በመካከላቸው አልነበሩም ።
“ ታዲያስ ጌታው !” አለኝ ፑጋቼቭ ሲያየኝ ። “ እንኳን
ደህና መጣህ እኛን ምሰላ ፤ እስቲ ዐረፍ በል !” ቦታ ተለቀ
ቀልኝና በዝምታ ተቀመጥኩ ። አጠገቤ የተቀመጠ ዘለግ
ያለና የደስ ደስ ያለው አንድ ወጣት ኮዛክ ቮድካ ቀዳልኝ ፤
ሆኖም አልነካሁትም ። በዙሪያዬ ያሉትን ሁሉ በአንክሮ
ተመለከትኳቸው ። ፑጋቼቭ ክርኑን ጠረጴዛው ላይ አስደ
ግፎና በተንዠረገገው ጥቁር ጢሙ ውስጥ መጋፊያ የሚ
ያህል መዳፉን ቀብሮ ተቀምጧል ። በመጠኑም ቢሆን የደም
ግባት የተላበሰው አስደሳች ገጽታው የቁጣ ምልክት አይ
ነበብበትም ። ደጋግሞ ዘወር በማለት አንዳንዴ መስፍን
ሆይ ፣ አንዳንዴ ቲሞፊች ፣ አንዳንዴ ደግሞ አጎቴ እያለ
በመጥራት የሚያናግረው ፤ በግምት ሃምሳ ዓመት የሚሞ
ላው አንድ ሰው አጠገቡ ነበር ። የአለቃና የጭፍራ ልዩነት
ሳያደርጉ ሁሉም የሚተያዩት በጓደኝነት ነው ። የጭወ ው


t.me/OLDBOOKSPDF

ታቸው ርእሶችም ስለ ተካሔደው ፍልሚያ ፡ በመፁ ስላስ ገኘው ድል እና ስለወደፊት ተግባሮቻቸው የሚያወሱ ነበሩ ። ሁሉም ጉራቸውን እየነዙና ራሱን ፑጋቼቭን ሳይ ቀር እየተከራከሩ አስተያየቶቻቸውን በመዝናናት ይሰነዝ ራሉ ። በዚህ ዐይነት ባልተለመደ ወታደራዊ ስብሰባ ላይ ወደ ኦሬንበርግ ለመዝመት ወሰኑ ። ከፍተኛ እልቂት የሚ ጋብዝ እንቅስቃሴ መሆኑን መተንበይ አያዳግትም ። ዘመ ቻው በማግሥቱ እንደሚሆንም ተነገረ ። “ አሁን እንግ ዲህ ወንድሞቼ ” አለ ፑጋቼቭ :“ ከመተኛታችን በፊት የምወዳትን ዘፈን ዝፈኑልኝ ። ቹማኮቭ ! አንተ ጀምር ! አጠገቤ የነበረ አንድ ሰው ስንጥርጥር ባለ ድምፁ የሆነ ዜማ ማንጐራጐር ጀመረ ፤ ሁሉም ተቀበሉት ።

እናት ለምለም ጫካ እባክሽን ስሚ !
ለማሰብ እንድችል ማጉረምረም አቁሚ ።
በሚያስፈራው ዳኛ በንጉሡ ፊት
ነገ ቀራቢ ነኝ ፍርዱን ለማግኘት ።
ከሴም ይጀምራል እንዲህ በማለት ፤
“ አንተ የገበሬ ልጅ ንገረኝ እውነቱን ፤
ከማን ጋር ሆነህ ነው ያስኬድከው ስርቆቱን ?
በዘረፋው ተግባር የተባበሩህ
እነማን ነበሩ ባልደረቦችህ ?
ለመዝረፍ ካንተ ጋር አብረው የዘመቱ
በብዛት ነበሩ ወይስ በጥቂቱ ?”
እኔም ጥያቄውን ከሰማሁ በኋላ
“ ከሐቅ በስተቀር አይወጣኝም ሌላ !”
በማለት ለንጉሥ አረጋግጥና
ታሪኬን ነግራለሁ እንዲህ በጥሞና ፡-
“ ታላቁ ንጉሥ ሆይ ፤ እንዲህ ነው ነገሩ ፤
የኔ ግብረ አበሮች አራት ነበሩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

እንዱ ጨለማ ነው ፤ ሌላው ስለ ጎራዴ ፤
ሦስተኛው ፈረሴ ያ ታማኙ ጓዴ ፤
አራተኛው ደጋን የተወጠረው ፤
የቀስቴ አመላላሽ የተላላኪው ።"
ከዚያም ደጉ ንጉሥ ይመልስልኛል ፦
" አንተ የገበሬ ልጅ ጀግና ነህ " ይለኛል ።
" የወገን ፤ የወዳጅ ምስጋና ይድረስህ ፤
የእሰራረቅ ዘዴህ እንደ ተዋጣልህ
መልስ አሰጣጡንም ትችልበታለህ ።
ለፈጸምከው ጀብዱ መታሰቢያ እንዲሆን
አንድ ትልቅ ፎቅ ቤት እሰጥሃለሁ አሁን ።
አውላላ ሜዳ ላይ የሚገኘው ቤት
በጣም እረጅም ነው ምሰሶው ሁለት ፤
አንድ አውታር ባናቱ የሚገኝበት ።"

በስቅላት ስለሚቀጡ ሰዎች የሚያወሳው ይህ እንጉርጉሮ የስቅላት ሞት በሚጠብቃቸው ሰዎች መዘፈኑ ያሳደረብኝን ስሜት ለመግለጽ ያዳግተኛል ። አስፈሪው ፊታቸው ፤ የሚጥም ቃናቸው ፤ ትካዜ ያጠላበት ገጽታቸው ከተዋበት ቃላት ጋር ተዳምረው ከፍርሃት ያልተለየ ስሜት አፈለቁብኝ ። እንግዶቹ በሙሉ አንዳንድ መለኪያ በተጨማሪ ወራውረው ከገበታው እየተነሡ ፑጋቼቭን ተሰናበቱት። እኔም እነሱን ተከትዬ ለመሔድ ስቃጣ ፑጋቼቭ ጠርቶ አስቀመጠኝና ፤ " ላነጋግርህ እፈልጋለሁ " አለኝ ። ብቻችንን ቀረን ።

ለጥቂት ጊዜ ማንኛችንም አልተናገርንም ። ፑጋቼቭ ዐይኖቹን ለጥቂት ጊዜ ከተከለብኝ በኋላ በግራ ዐይኑ እየጠቃቀሰኝ ልክ እንደ ዱርዬ አላገጠብኝ ። በመጨረሻም ከጣራ በላይ ሥቆ እኔንም አሣቀኝ ።" መልካም ነው ጌታዬ " አለኝ ፤ " ተከታዮቼ ሽምቀቆውን አንገትህ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ባጠለቁ ጊዜ ፊርቱህ እንደነበር እመን ! ከመጠን በላይ ተርበደብደህ የምትይዝ የምትጨብጠውን እንዴ አማህ እርግጠኛ ነኝ ። እኔ ባለውለታህ ባልደርስልህ ኖሮ ገና ዱሮ ተንጠልጥለህ ነበር ። እንተነትህን ወዲያውኑ አስታወስኩ ። በአንድ ቀውጢ ወቅት ወደ ሆቴል የመራሁህ እኔው ራሲ መሆኔ ትዝም አላለህ ፣ ብሎሃል እንዴ ጌታው ?” ይህን አለኝና የሆዱን በሆዱ ይዞ በጉራ ተወጠረብኝ ። “ በጣም በድለኸኛል ” በማለትም ቀጠለ ፣“ ግን ከጠላቶቹ ለመደበቅ በምራወጥበት ወቅት ውለታ ስላደረግህ ልኝ ምሬሃለሁ ። ብቻ ፣ እስቲ ዕድሜ ይስጠን ። ግዛቴን ሳስመልስ የማያደርግልህ ብዙ ነገር አለኝ ። በታማኝነት ልታገለግለኝ ፈቃደኛ ነህ ?”

የዚህ ወሮበላ ጥያቄና ግብዝነቱ በጣም ስላስገረመኝ ሣቅ አመለጠኝ ።

“ ምን ያሥቅሃል ? ” ሲል ጠየቀኝ ተኮሳትሮ ። “ ታላቁ ንጉሥ መሆኔን አታምንም ማለት ነው ? እውነቱን ንገረኝ ።”

ጭንቀት ወረረኝ ። ይህን ዱር አዳሪ እንደ ገዥዬ አድርጌ ማስቡ አልዋጥልህ አለኝ ። ገዥነቱን እምኘ በቀላሉ ይቅርታ የማይደረግለት ፍርሃት መስሎ ታየኝ ። እጭበርባሪ መሆኑን ፊቱ ብገልጽለት ደግሞ ከቦ ማፍረስ ሆነብኝ ። እናም ያኔ ከመስቀያው ሥር በተሰበሰበው ሕዝብ መሐል ፣ በዚያ ባፍላ ቁጣዬ ወቅት ያላልኩትን አሁን መናገሩ አጉል ጀብዱ መሰለኝ ። አወላወልኩ ። ፑጋቼቭም በአርምሞ እየተመለከተኝ መልሴን ይጠባበቃል ። በመጨረሻም ፣ በየዋህነት ድፍረት ተገፋፍቼና የኃላፊነት ስሜት ድክመቱን አሸንፎልኝ “ ደህና ፣ እውነቱን አፈረጥርጬ እነግርሃለሁ ። ገዥነትህን አሜን ብዬ እቀበልልህ እንደሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

እስቲ አንተው ራስህን ጠይቅ ! ትክክለኛ ሰው ነህና ግልጽ መሆን አለ መሆኔ ያኔ ወለል ብሎ ይታይሃል ” በማለት ለፑጋቼቭ መለስኩለት ።

“ ታዲያ ባንተው ግምት ፣ ማን እመስልሃለሁ ? ”

“ አንተነትህን እግዜር ይወቀው ። ግን ማንም ሆንክ ማን በእሳት ነው የምትጫወተው ።”

ፑጋቼቭ ላፍታ ትክ ብሎ አየኝ ። “ ንጉሥ ፒዮቶር ፊዮድሮቪች መሆኔን አታምንም ማለት ነው ? ” አለኝ ። “ በጣም ጥሩ ። ማታ ማታ ድል የሚመታው ምንጊዜም ልበ - ሙሉው አይደል ? ግሪሽካ ኦትሬፑየቭ በጥንት ዘመን አልነገሠም ? የምትለኝን በለኝ ፤ ግን አብረኸኝ ቆይ ። ማንስ ብሆን ምን ቸገረህ ? ስም ብቻውንስ ላንተ ምን ይበጅሃል ? በታማኝነትና በሐቅ አገልግለኝ ፤ ጠቅላይ አዛዥና ልዑል አደርግሃለሁ ። እናስ ምን ታስባለህ ?”

“ በጭራሽ !” አልኩት በቆራጥነት ። “ የመኳንንት ልጅ ነኝ ። ለንግሥቲቱም ታማኝነቴን ገልጫለሁ ። አንተን አላገለግልም ። ደህንነቴን ከተመኘህልኝ ወደ ኦሬንበርግ እንድሔድ ፍቀድልኝ ። ”

ፑጋቼቭ በጉዳዩ አሰበበት ። “ እንድትሔድ ከፈቀድኩልህ ” አለኝ ፤ “ ዓላማዬን በሚያደናቅፉብኝ ቦታ እንዳትደነቀርብኝ ቃል ትገባልኛለህ ?”

“ እንዴት ብዬ ? ” ስል መለስኩለት ። “ እንዲያ ማድረግ እንደማልችልማ አንተው ራስህ ታውቀዋለህ ።

---

* ግሪሽካ ኦትሬቪየብ ልዑል ዲሚትሪ ፣ የጨካኙ ኢቫን ልጅ ነኝ በማለት ያምታታ የነበረ መነኩሴ ነው ። የፖላንዶች ወኪል ነኝ ባዩ “ የሀሰት ዲሚትሪ ” በ1605 እና በ1606 መሐል ለአሥራ አንድ ወራት የሞስኮ ዙፋን ላይ ወጥቶ ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካንተ ጋር እንድዋጋ ከታዘዝኩ የመጣው ቢመጣ ፊቱን አላዞርም ። አንተ ራስህ አሁን በሥልጣን ላይ ነህ ። ከተ ከታዮችህ ታማኝነትን ትሻለህ ። የእኔም አዛገሮች ከእኔ የሚጠብቁት ይህንኑ ነው ። በእርግጥ ሕይወቴ በመዳፍህ ውስጥ ነች ፣ ግን እንድሔድ ከፈቀድክልኝ አመሰግናሃለሁ፤ ስቅላት ከፈረድክብኝም እግዚአብሔር የእጅህን ይስጥህ፤ እነስም በዛም ቃሉ ይኸው ነው ።”

ግልጽነቴ ቱጋቼቭን አስደነቀው ። “ ደህና ፣ እንግ ዲህ ” አለኝ ትከሻዬን እየተመተመ ። “ ስቀጣ እቀጣለሁ ስምር እምራለሁ ። የፈለግህበት ሒድ ፤ የፈለግኸውን አድ ርግ ። ነገ ብቅ ብለህ ተሰናበተኝ ። አሁን ወደ ቤትህ ሒደህ ጋደም በል ፤ እኔም እንቅልፍ ተጫጭኖኛል ።”

ፑጋቼቭን ትቸው ውልቅ አልኩ ። ረጭ ያለ ብርዳማ ምሽት ነበር ። አደባባዩንና መስቀያውን ሥፍራ ጨረቃና ከዋክብት አድምቀውታል ። በዚያ ምሽግ ውስጥ ጸጥታ ሰፍኗል ። ሁካታ የሚሰማው የመብራት ውጋጋን ከሚታ ይበት ከአንድ መጠጥ ቤት አቅጣጫ ብቻ ነው ። ወደ ቄሱ ቤት መልከት አደረግሁኝ ። መስኮቶቹና መዝጊያው ተዘ ግተዋል ። እሱንም ዝምታ ውጦታል ።

መኖሪያዬ ስደርስ ሳቪሊች በመዘግየቴ ተጨንቆ ሲተ ክዝ አገኘሁት ። በነጻ የመለቀቄ ዜና ከመጠን በላይ አስ ፈነደቀው ። “ ምስጋና ይግባህ ፈጣሪዬ !” አለ እያማተበ። “ ይህን ምሽግ ገና ጐህ ሲቀድ እንለቅና ወደሚበጀን ሥፍራ እንጓዛለን ። ምግብ ብጤ አዘጋጅቼልሃለሁ ። እስቲ አፍህ አድርግና ጌታዬ ፣ በእግዚአብሔር ምሕረት ተጽናንተህ እስከሚነጋልን ዐረፍ በል ።”

ምክሩን ተቀብዬ እስክምጠግብ በላሁና አካሌም መንፈሴም ዝሎ ስለነበር ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስንብት

ፍቅርሽን መቅመሱ መመገብ ነውና የወለላ ፍትፍት ፤
ካላንች በስተቀር ከልቤ ማኅደር ማንም አይገባበት ።
በድን እሆናለሁ ካንች መለየቴ ሞት እየመሰለኝ ፤
ባዘን እዋጣለሁ ነፍሴ ከሥጋዬ ስትርቅ እየታየኝ ።

ኩራስኮቭ *

ጠዋት በማለዳ የነጋሪት ድምፅ ከእንቅልፌ ቀስቅሶኝ በቀጥታ ወደ መሰብሰቢያው ቦታ ሔድኩ ። የትናንቱ መከረኞች ዛሬም እንደ ተንጠለጠሉ ከሚወዛወዙበት መስቀያ አካባቢ የፑጋቼቭ ሰዎች እየተሰለፉ ነበር ። ኮዛኮች በየፈረሶቻቸው ላይ ቁብ ብለዋል ፤ እግረኞቹም ጠመንጃዎቻቸውን እንግበዋል። ባንዲራዎች ይውለበለባሉ ፤ ጥቂት መድፎች ፡ የእኛንም ጨምሮ ፡ ጋሪዎች ላይ ተጭነዋል። ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ፑጋቼቭን ይጠባበቃል ። የሚያምር ነጭ ፈረስ በልጓሙ ይዞ አዛዡ በር ላይ አንድ ኮዛክ ቆሟል ። የአዛዡን ሚስት ሬሳ ለማየት ግራና ቀኝ ፣ ማተርኩ።ወደ አንድ ጎን ገፋ አድርገውት ጆንያ ብጤ አልብሰውታል ። በመጨረሻም ፑጋቼቭ በረንዳው ላይ ብቅ አለ ።

---

* “ መለያየት ” ከተሰኘውና በሚካኤል ኩራስኮቭ ( 1733-1807 ) በተደረሰው ዜማ የተወሰደ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሕዝቡ ከንብንቡን ዝቅ አደረገ ፤ ፑጋቼቭም ሰላምታ አቀረበ ። ከተከታዮቹ አንዱ ሳንቲም የታጨቀበት ከረጢት አቀረበለትና ፑጋቼቭ እየዘገነ ለሕዝቡ መበተን ጀመረ ። ሕዝቡም ሳንቲሞቹን ለመለቃቀም አንዱ በሌላው ላይ ተረባረበ ፤ የተጎዳውም ጥቂት አልነበረም ። ፑጋቼቭን ከከበቡት ቀንደኛ ፣ ማካሪዎች አንዱ ሽቫብሪን ነበር ። ዐይን ለዐይን ተጋጨን ። በእርሱ ላይ ያለኝን ጥላቻ ከግንባሬ ላይ አንብቦ እርሱም ጥላቻውንና ርግማኑን ፊቱን በማዞር ገለጸልኝ ። ፑጋቼቭ ከሕዝቡ መሐል ለይቶኝ ራሱን ዝቅ በማድረግ ሰላምታ ከሰጠኝ በኋላ ወደ እርሱ ቀረብ እንድል ጠራኝ ። "በቀጥታ ወደ ኦሬንበርግ ሒድና በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እንደምጐበኛቸው ለአገረ ገዢውና ለጄኔራሎቹ ንገራቸው ። በንጹሕ ልቦና እንዲያፈቅሩኝና በእንክብካቤም እንዲቀበሉኝ ምከራቸው ።
አለበለዚያ ከሞት ሞት ቅጣቴ አያመልጡም ። መልካም ጉዞ ይሁንልህ ፡ጌታው !" በማለት አሰናበተኝ ።ቀጥሎም ወደ ሠልፈኞቹ ዞሮ ሽቫብሪንን እየጠቆማቸው "አዲሱ መሪያችሁ እርሱ ነው ፤ ጉበዝ !" ሲል አስተዋወቃቸው ። " ማንኛውንም ትዕዛዙን እንድትቀበሉ ። ለእናንተና ለምሽጋችን ተጠያቂው እርሱ ነው ። " እነዚህ ቃላት ልቤን በድንጋጤ ተረከኩት ። ሽቫብሪን የምሽጉ አዛዥ ከሆነ ማሪያ ኢቫኖቭና ከእጁ መግባቷ ነው ! የእግዜር ያለህ ! ዕጣዋ ምን ይሆን ? ፑጋቼቭ የበረንዳውን ደረጃዎች ወረደ ፤ ፈረሱም ቀረበለት ። ኮዛኮቹ ሊደጋግፉት ከመድረሳቸው በፊት ፑጋቼቭ እመር ብሎ ኮርቻው ላይ ቁጭ አለ ።

በዚያን ወቅት ሳቬሊች ሆዬ በሕዝቡ መሐል እየተጋፋ ፀልፎ ለፑጋቼቭ ወረቀት ሲያቀርብለት አየሁ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ስለምን እንደሆነ ግን መገመት አልቻልኩም ። "ምንድን ነው ?" ሲል ጠየቀው ቶጋቼቭ በቁጣ ።

"ያንብቡልኝና ምን እንደሚል ይረዱልኝ" አለው ሳቪሊች ። ቶጋቼቭም ወረቀቱን ተቀብሎት ለረጅም ጊዜ በአንክሮ ተመለከከተው ። "ጽሕፈትህ ሙንጭርጭር ነው" አለው ። "ብሩሁ ዐይኖችን ምንነቱን እንኳ ሊለ ዩልን አልቻለም ።"

"አንደኛ ጸሐፊዬ የታለ ?"

የደምብ ልብስ ያጠለቀ አንድ ወጣት ዐሥር አለቃ ወደ ቶጋቼቭ ተጠጋ ። ቶጋቼቭም ወረቀቱን ሰጠውና ጮህ ብለህ አንብብልኝ" ሲል አዘዘው ። ሳቪሊች ለቶጋቼቭ እንዲጽፍ ምን እንዳሳሰበው ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝ ። አንደኛ ጸሐፊው ቃላቱን አንድ በአንድ እየቆጠረ ጉላ ባለ ድምፅ የሚከተለውን አነበበ ።

"ሁለት የማዕረግ ልብሶች ፤ አንድ የጥጥና አንድ ደግሞ ባለ መሥመር የሐር ብትን ጨርቆች -6 ሩብል ።

ቶጋቼቭ ግንባሩን ኮስኩሶ "ምን ማለት ነው ?" ሲል ጠየቀው ሳቪሊችን ።

ሳቪሊችም "እንዲቀጥል ይንገሩት" አለው በጥሞና አንደኛ ጸሐፊውም ቀጠለለት ።

"አንድ ውሃ አረንጓዴ የደምብ ልብስ - 7 ሩብል ።

"12 የሆላንድ ሸሚዞች ከነእጀታ ማፈኛዎቻቸው 10- ሩብል ።

"አንድ ሳንዱቅ ከሙሉ የሻይ ማቅረቢያ ጋር - 2 ሩብል ከ50 ኮፒክ ።"

"ምንድን ነው ይህ ሁሉ ?" በማለት ቶጋቼቭ ደነፋ። "ስለ ሻይ ማቅረቢያ ሰንዱቅ ፤ ስለሱሪና ስለ እጀታ ማፈኛ . . . እኔ ምን አውቅልሃለሁ ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳቪሊች ጉሮሮውን ጠራርጎ ማስረዳት ጀመረ ። “ እዩ ጌታዬ ! ወረበሎቹ የዘረፉን የጌታዬ ንብረት ዝር ዝር መሆኑን ልብ ይበሉልኝ ። ”

“ የምን ወረበሎች ? ” ሲል ፑጋቼቭ አጓራ ።

“ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፤ የአፍ ወለምታ ነው” አለው ሳቫሊች ። ” ማለቴ ወረበሎች ሳይሆኑ ቤታችንን በዝብ ዘው ያሻቸውን የነጠቁን አሽከሮችዎ ናቸው ። ፈረስ አራት እግሮች ቢኖሩትም እንኳ መደናቀፉ አይቀርለትምና በእኔም ላይ አይፍረዱብኝ ። ንባቡን እንዲቀጥል ይዘዙት ።

“ ቀጥል !” አለው ፑጋቼቭ ። ጸሐፊውም ቀጠለ

“ አንዱ ከጥጥ ፡ ሌላው ደግሞ ከሐር ብጤ ጨርቅ የተሠሩ ሁለት የአልጋ ልብሶች - 4 ሩብል ።

“ አንድ ቀዳ ካፖርት ባለ ጸጉር ገበር - 40 ሩብል ።

“ አንድ ቀዳ ካፖርት ፤ በአንድ ሆቴል ውስጥ ለክ ቡርነትዎ የተበረከተ 15 ሩብል ። ” ዐይኖቹ እየተንቀለ ቀሉ፣” ይህ ሁሉ ጉድ ምንድን ነው ?” በማለት ፑጋቼቭ ጮኸ ።

ለምስኪኑ ሳቪሊች መደንገጤን አልሸሸግሁም ። ሳቪ ሊች ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ሲቃጣው ፑጋቼቭ አቋረጠው ። “ ለማይረባ ጉዳይ እኔ ዘንድ መቅረብ እን ዴት ብትደፍረኝ ነው ? ” በማለት አምባረቀበት ። ወረ ቀቱንም ከጸሐፊው እጅ መንጨቀና ፊቱ ላይ ወረወረለት። “ ክብት ሽማግሌ ! ደግሞ ተሰረቅን ይላል ፤ ያሳዝናል ! አንተን ከእንጌታህ እንደዚያ ዳተኞች ስላላንጠለጠልኳችሁ ለእኔና ለተከታዮቼ ዕድሜ ልካችሁን ልትጸልዩልን በተ ገባችሁ ። ደግሞ ቀዳ ካፖርት ! ከፈለግህ ቀዳ ካፖርት እሽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልምሃለሁ ! ወይም በቁምህ አስገፍፌ ቆዳህን ለኮትነት ማስተልተል እንደምችል አታውቅም ? ”

“ እንዳሻዎ ” አለው ሳቬሊች ። “ እኔ አሽከር እንደ መሆኔ ለጌታዬ ንብረት ተጠያቂ ነኝ ።”

ፑጋቼቭ ይኸኔ በእርግጥ ልቡ ተነካ ። ሌላ ቃል ሳይ ተነፍስ ከፊቱ ዘወር ብሎ ጉዞውን ቀጠለለት ። ሺቫብሪ ንና ሌሎቹም ተከተሉት ። ሰልፈኛውም ደምቆ ከምሽጉ መሰስ አለ ። የፑጋቼቭን አሸኛኘት ለማየት ሕዝቡም ንቅል ብሎ ወጣ ። በአደባባዩ ሳቬሊችና እኔ ብቻ ተገት ረን ቀረን ። ሳቬሊች በእጁ ያንጠለጠላትን ዝርዝር በከ ባድ ሐዘን ተውጦ ተመለካከታት ።

ከፑጋቼቭ ጋር የነበረኝን መልካም ግንኙነት ተመ ርኩዞ ጥቅም ሊያገኝ አስቦ ነበር ። ግን ያ የየዋህነት ምኞቱ አልተሳካለትም ። ስለ እንጉል ድፍረቱ ልወቅሰው አስቤ ሣቄ አመለጠኝ ። “ መሣቅ ትችላለህ ጌታዬ ” አለኝ ሳቬሊች ፤ “ ግን እንደገና ጉጆ ስንቀልስ ነው አስቂኝ መሆን አለመሆኑን በሚገባ የምትረዳልኝ ።”

ማሪያ ኢቫኖቭናን ለማየት ወደ ቄሱ ቤት ገሠገሥኩ ። የቄሱ ሚስትም በሐዘን ተቆራምዳ ቆየችኝ ። ማሪያ ኢቫ ኖቭና ትናንት ማታ ኃይለኛ ትኩሳት ለቅቆባት ዛሬ ራሷን ስታ እንደምትቃዥ ነግራኝ ወደ ክፍሏ ወሰደችኝ ። እር ምጃ ሳላሰማ ወደ አልጋዋ ተጠግቼ ብመለከታት ገጽታዋ ተለዋወጠብኝ ። እርሷም ልታስታውሰኝ አልቻለችም ። አባ ጄራዚምና ሚስታቸው ከሚያነበንቡልኝ የማጽናኛ ቃላት አንዱን እንኳ ሳላዳምጥ አልጋዋ አጠገብ ተገትሬ ቆየሁ ። ክፉ ፣ ክፉ ሐሳቦች ወረሩኝ ። አውሬ በሆኑ ዐመፀ ኞች እጅ የወደቀችውን የዚህችን መከታ ያጣች ምስኪን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዕንለማውታ ሁኔታና ዐቅመ ቢስነቴን አገናዝቤ በጭንቀት ተዋጥኩ ።

ከሁሉም ይልቅ የሽግብሪን ጉዳይ አእምሮዬን አስ ጨንቀው ። በጉጋቼቭ ተሹሞ ሽግብሪን ፈላጭ ቆራጭ በሆነበት በዚህ ምሽግ ውስጥ የዚህች ዕድለ ቢስና በጠ ላትነት የምትታይ የዋህ ልጅ መኖር ወደ ምን ዐይነት የጭካኔ እርምጃ እንደ ሚመራው ማውቁ ያዳግታል ። እኔስ ምን ላደርግላት እችላለሁ ? ምን ዐይነት እርዳታ እን ዳው በምን ዐይነት ዘዴ ከዚህ ወንበዴ መዳፍ ፈልቅቄ ላወጣት እችላለሁ ? እንደሚስቴ የማያትን ያችን ሐዘን ያጠላባትን ልጅ በአደራ አስረክቢያቸው ቄሱንና አኩ ሊና ፖምፊሎቭናን ተሰናበትኩ ። የዚያችን ምስኪን ልጅ እጅ አንቄ በእንባዬ እያጠብኩ ሳምኩት ። “ ደህና ሁን ” አለችኝ የቄሱ ሚስት ! በሩ ድረስ እየሸኘችኝ ። “ ደህና ሁን ፖይቶር አንድሬይች።እግዜር ካለልን በደህና ጊዜ እን ገናኛለን ።እትርሳን ፤በየጊዜውም ጻፍልን ። ይህች ምስኪን ማሪያ ኢቫኖቭና ካላንተ በቀር አይዞሽ የሚላት ወይም የሚደግፋት የላትም ።”

ወደ አደባባዩ ብቅ ብዬ ቆም ካልኩ በኋላ መስቀያ ውን ተመለካከትኩትና ተሳልሜው እንደ ጥላዬ ከኋላ ኋላዬ የማይለየኝን ሳቬሊችን አስከትዬ ከምሽጉ ክልል በመውጣት የኦሬንበርግን ጉዳና ተያያዝኩት ።

በሐሳብ ተውጬ በመኳተን ላይ ሳለሁ በድንገት የፈረሶች ኮቴ ሰማሁ ። ዘወር ብል አንድ ኮዛክ ፈረስ እየ ጐተተና ምልክት እያሳየኝ ከምሽጉ ወጥቶ ወደ እኔው ሲጋ ልብ አየሁ ። ከእኛ ወገን ከድቶ ለጉጋቼቭ የገባ ሃምሳ አለቃ መሆኑን ወዲያው ለየሁ ። እንደደረሰብኝም ከፈረሱ ዘልሎ ወርዶ ይጐትት የነበረውን ፈረስ ልጓም እያስጨበጠኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

" ክቡር ሆይ ! ጌታችን ይህን ፈረስና ካፖርታቸውን አውልቀው ልከውለዎታል " አለኝ ። አንድ ቆዳ ካፖርት ከኮርቻው ጋር ተጠፍሯል ። " በተጨማሪም " ብሎ ጥቂት ካሰበ በኋላ ፣ ድምፁ እየተቆራረጠበት "50 ኮፒክ ልከውልዎታል - ግን እባክዎ ይቅር ይበሉኝ - መንገድ ላይ ወድቆብኛል" አለኝ ። ሳቬሊች በዐይኑ ቂጥ እያየው " "መንገድ ላይ ጠፋብህ - እ ? ኪስህ ውስጥ የሚቅጨለጨለውስ ምንድን ነው ? አሳፋሪ ፍጡር ! " በማለት አጉተመተመ ። "ኪሴ ውስጥ የሚቅጨለጨለው?" አለው ሃምሳ አለቃው እምብዛም ሳይደነግጥለት ።" ኧረ እግዜር ይቅር ይበልዎ አባቴ ፤ የሚቅጨለጨለው ልጓሙ እንጂ ገንዘብ አይደለምኮ ! "

" በጣም ጥሩ ነው ባማለት ጭቅጭቃቸውን አሳጠርኩላቸው ። " የላከህን ሰው አመስግንልኝ ። የወደቀብህን ሃምሳ ኮፒክ ስትመለስ አንሣውና ፉት በልበት አልኩት ። " ምስጋና ይግባዎ ክቡር ሆይ ! " ብሎኝ ፈረሱን አዞረ ። " ዘወትር እጸልይልዎታለሁ ። " ይህን ተናግሮኝ የመልስ ግልቢያውን ቀጠለ ፤ በአንድ እጁ የሸሚዙን መካፈቻ አፍን አድርጐ ይዞ በደቂቃ ውስጥ ከዐይኔ ተሰወረ ።

ቆዳ ካፖርቴን አጠለቅሁና ሳቬሊችን ከኋላዬ አፈናጥጬ ኮርቻዬ ላይ ቁብ አልኩ ። " አየህ ! ጌታዬ " አለኝ ሽማግሌው፤" ለዚያ ጃውሳ ማመልከቻዬን ማቅረቤ በጀን ፣ ያ ሌባ በድርጊቱ አፍሯል ። አንድ ከሲታ መጋዣና አንድ ቆዳ ካፖርት ብቻቸውን ተከታዮቹ ከወሰዱብን ንብረት ከፊሉን እንኳ አይመጥኑም ፤ ያውም አንተ በቸርነትህ የሸለምከውን ሳይጨምር ። ቢሆንም ይጠቅማል ፤ እርቃን ከመቅረትም የተመላለጠ የውሻ ቆዳ እንኳ መልበሱ ይበጃል ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዐሥር

## የከተማዋ ከበባ

በሠራዊቱ አጥሮ ኮረብታ ሜዳውን ፤
በየሸንተረሩ አስልፎ መድፉን ፤
መጥቶ እያንዣበበ እንደ ንሥር አሞራ ፤
ከተማዋን ያያል የሠራዊቱ አውራ ።
ቀን መሸት ሲል ያያታል ስትርድ ፤
መድፉ ሲያጓራባት ልክ እንደ ነጐድጓድ ።

### ኪራስኮቭ *

ወደ ኦሬንበርግ ስንቃረብ ራሳቸውን የተላጩና በሥቃይ በትር ከሰውነት ዳር የወጡ በርካታ ሰዎች አጋጠሙን ። በአካለስንኩላን ወታደሮች ተቆጣጣሪነት በምሽጉ አካባቢ በሥራ ተጠምደዋል ። ለመከላከያ ተብሎ በምሽጉ ዙሪያ ከተቆፈረው ሰፊና ጥልቅ የውሃ በይ ገሚሶቹ ቆሻሻ እየጠረጉ ሲያጓጉዙ ፤ ገሚሶቹ ደግሞ ይቆፍራሉ ። ግምበኞች ከተማዋን የከበባትን ግምብ ለማደስ ሸክላ እየተሸከሙ ሽቅብና ቁልቁል ይራወጣሉ ። ከዋናው መግቢያ ላይ ዘቦች አስቁመውን የይለፍ ወረቀቶቻችንን ጠየቁን ። ሣምሳለቃው ከቤሎጉርስክ ምሽግ መምጣቴን ሲሰማ ወዲያውኑ ወደ ጀኔራሉ ቤት መራኝ ።

---

* በ1552 ካዛን በኢቫን ጨካኙ እጅ ስለመውደቋ ማስታወሻ እንዲሆንላት "ዘሮሲያዳ" በሚል ርዕስ ኪራስኮቭ ከተቀኘላት ረጅም ግጥም የተወሰደ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጄኔራሉ የበልግ ውርጭ የመታቸውን የፍራፍሬ ዛፎ ቹን በአትክልት ሥፍራው ውስጥ ሲመለከቱት አገኘሁት። በአንድ ሽማግሌ አትክልተኛ ረዳትነት የዛፎቹን ግንዶች በፍቅር ስሜት እየዳሰሰ በድርቆሽ ሣር ይሸፋፍን ነበር ። ገጽታው አፎይታን ፣ ጤንነትንና ደስታን ያንጸባርቃል ። እኔን በማየቱ ደስ ብሎት ስለደረሰብን አሠቃቂ ሁኔታ የዐ ይን ምስክርነቱን ጠየቀኝ ። ሁሉንም ነገርኩት ። የደረቁ ትን ቅርንጫፎች እየቀነጣጠበ በጥሞና አዳመጠኝ “ አዬ ሚኖርቭ ! ” አለ አሳዛኝ ታሪኬን ስደመድምለት “ እን ዴት ያሳዝናል ! ቆፍጣና መኰንን ነበር ።

ወይዘሮ ሚኖርቭም በጣም ደግ ሴት ነበረች ፣ ከእን ጉዳይ የምትሠራው ምግብ ጣት ያስቆረጥማል ። ለመሆኑ የ፤ ዛገፉ ልጅ ማሻስ እንዴት ነች ? “ በዚያው ምሽግ ውስጥ ቄሱ ሚስት ዘንድ በአደራነት እንደምትገኝ ነገርኩት ። “በጣም አደገኛ ነው” አለኝ ጄኔራሉ ፤ “በጣም መጥፎ!” ወንበዴዎቹ ሥነ ምግባር የላቸውም ኮ “ እንዲያው ምን ይበጃት ይሆን ?” አለ በሐዘኔታ።የቢሎጎርስክ ምሽግ ከዚህ እምብዛም ስለማይርቅ ባስቸኳይ ወታደሮች አዝምቶ ያን መከራ የሚያይ ሕዝብ ነጻ እንደሚያወጣው በእርሱ ላይ ያለኝን እምነት ገለጽኩለት ። ጄኔራሉ ራሱን በጥር ጣሬ ነቀነቀብኝ ። “ እናያለን ፣ እስቲ እናያለን ” አለ ። “ ያን እንኳ በወቅቱ እናነሣዋለን ። አሁን ጐራ እንበልና ሻይ ብጤ እንቅመስ ። ዛሬ ዘመቻውን በተመለከተ ስብ ሰባ እጠራለሁ ። ፑጋቼቭ ስለሚባለው አሰሌና ስለተከታ ዮቹ ትክክለኛውን ማስረጃህን ያኔ ታቀርብልናለህ ። እና እስከዚያ ዐረፍ በል ። ”

ሳቤሊች ወደ አስማመረልኝ ማረፊያዬ ሔጄ የቀጠሮ ሰዓቱን በትዕግሥት ስጠባበቅ ቆየሁ ። እንባቢ በቀላሉ እንደሚገነዘብልኝ ዕድሌን ከሚወስነው ከዚያ ስብሰባ አል


t.me/OLDBOOKSPDF

ቀረሁም።ልክ በተባለው ሰዓት ጄኔራሉ ቤት ከቸች አልኩ። ጉንጮቹ የተንፋፉና እንደቲማቲም የቀሉ ፣ የተብለ ጨለጩ ሱቲ ያጠለቀ አንድ ሰው ፣ ባልሳሳት የጉምሩክ መሥሪያ ቤት ዲሬክተር ይመስለኛል ፣ ቀድሞኝ አገኘ ሁት ። የብዙ ዓመታት ጓደኛዬ ነበር ስለሚለው ስለኢቫን ኩዝሚች ይጠያይቀኝ ጀመር ። ምንም እንኳ የዕውቀቱን ደረጃ ባይገልጽልኝም፣በንግግሬ መሐል ጣልቃ እየገባ ከሚ ያቀርብልኝ ጥያቄዎችና ከሚሰነዝርልኝ ሐሳቦች በመንደ ርደር ሰውዬው ስለ ወታደራዊ ሳይንስ ጥሩ ግንዛቤ እንዳ ለው መረዳቴ አላዳገተኝም ። በመጨዋወት ላይ እንዳለን እንግዶቹ ገብተው ተጠናቀቁ ። ከጄኔራሉ በስተቀር አንዳ ቸውም ወታደር አልነበሩም ። ሁሉም ሥፍራ ሥፍራቸ ውን ከያዙና ሻይ ከተቀዳላቸው በኋላ ጄኔራሉ የወቅቱን ሁኔታ በተመለከተ ዝርዝር ገለጻ አደረገላቸው ።"ስለዚህ ክቡራን" በማለት ንግግሩን ቀጠለ ።" በጠላቶቻችን ላይ ምን ዐይነት እርምጃ መውሰድ እንደሚገባን መወሰኑ የእኛ ፋንታ ነው — የማጥቃት ተግባር ጠላትን ባስቸኳይ ለመ ደምሰስ ሲያስችል የመከላከል ተግባር ደግሞ ፣ አስተማማ ኝና ከጉዳትም የሚያድን ነው ። ስለዚህ በተገቢው መን ገድ ድምፅ እንስጥበት ፣ ማለትም ከበታች አለቆች በመ ጀመር እስቲ ድምፅ ስጡበት !" ካለ በኋላ ወደ እኔ ዞሮ "እስቲ አንተም አስተያየትህን አትንፈገን" ሲል ጠየቀኝ።

እኔም ተንሥቼ ስለፑጋቼቭና ተከታዮቹ በመጠኑ ገል ጨላቸው የወንበዴው ቡድን መደበኛ ወታደሮችን መቋ ቋም እንደማይችል ጠቆምኳቸው ። ሹማምንቱ አስተያየ ቴን የተቀበሉት በግልጽ ቅሬታ ሆነ ። አባባሌ በጉርምስና ግልቢያና ግብዝነት የተሸፋፈነ መሰላቸው ። ማጉረምረም ተጀመረ ፣ እንዳውም ዝቅ ባለ ድምፅ የተወረወረች "ቡችላ!" የምትል ጥርት ያለች የስድብ ቃል ጆሮዬ ጥልቅ


t.me/OLDBOOKSPDF

አለች ። ጀኔራሉም በፈገግታ እየተመለካከተኝ “ እጀቻ ችሁን ከፍ አድርጉ ! ” በማለት የድምፅ ቆጠራ ተግባ ሩን ቀጠለ ። “ በወታደራዊ ስብሰባዎች ላይ ለድምፅ አሰ ጣጥ ቅድሚያ የሚኖራቸው ነጥቦች በአመዛኙ ማጥቃት ወደሚለው እርምጃ የሚያዘነብሉት ናቸው ። ከእንግዲህ ድምፃችንን እናስቆጥር ። አማካሪያችን ፣ አስተያየትዎን ቢለግሱን ። ”

አረቂ ጠብ የሚደረግበት ሦስተኛ ፍንጃል ሻዩን የጨ ለጠውና ያ ብልጭልጭ ሱቲ ያጠለቀው ሰው ፣ “ ክቡር ሆይ ፣ በበኩሌ የማጥቃትም ሆነ የመከላከል እርምጃ መው ሰድ የለብንም እላለሁ ” ሲል መለሰለት ።

“ እንዴ ፣ አማካሪያችን ! ” አለው ጄኔራሉ በመደ ንገጥ ፣ “ ሌላ አማራጭ የለንምኮ — በጭራሽ ፣ መከላከል ወይም ማጥቃት እንጂ . . . ”

“ ጠላትን በመግዛት ዘዴም መጠቀም እንችላለን ፣ ክቡር ሆይ ! ” አለው ቀልጠፍ ብሎ ።

“ እሃሃሃ ! አስተሳሰብዎ በሚገባ ተቀባይነት ያለው ነው ። ጠላትን በመግዛት ዘዴ መቋቋም ያለ ነውና በምክ ርዎ መጠቀም እንችላለን ። ሰባ ሩብል ፣ ለምን መቶ አይ ሆንም — ከምስጢር ካዝናችን አውጥተን ለወንበዴዎቹ መሪ ብንሰጥ . . . ”

“ እንዲያ ካደረግንማ ወንበዴዎቹ አለቃቸውን እጅና እግሩን ጠፍረው ካላስረከቡን በግ እንጂ አማካሪ አትበ ሉኝ ! ” በማለት የጉምሩክ ዲሬክተሩ ፎከረ ።

“ ይህን የውሳኔ ሐሳብ በሚገባ እናብላላው ” አለ ጄኔራሉ ። “ ሆኖም ወታደራዊ እርምጃ መውሰድም አስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፈላጊ ይሆናል ። ክቡራን ፤ ውሣኔውን እስቲ በደምቡ መሠረት እናጽድቅ ። ”

የተሰጡት አስተያየቶች በሙሉ የእኔን ሐሳብ የሚቃረኑ ነበሩ ። የስብሰባው ተካፋዮች በሙሉ የመደበኛ ወታደሮቹ አቋም እንደማያስተማምን ፤ ድል የማድረጉም ጉዳይ እንደሚያጠራጥር ፤ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ . . . ጠቃቀሱ ። ከፑጋቼቭ የመድፍ ጥይት ለማምለጥ የከተማዋን ግምብ ከለላ ማድረጉ እንጂ ወጥቶ ከፑጋቼቭ ጦር ጋር በአውላላ ሜዳ ላይ ጦርነት መግጠሙ የማያዋጣቸው መሆኑን ሁሉም አመኑበት ። በመጨረሻም ጄኔራሉ የሁሉንም አስተያየቶች ካዳመጠ በኋላ የፒፓውን ፤ ዐመድ አራግፎ የሚከተለውን ንግግር አደረገ ።

“ ክቡራን ! በበኩሌ ሐሳባችሁን ሙሉ በሙሉ የተቀበልኩት መሆኔን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ ። ምክንያቱም ውሳኔያችን በውጊያ ሕጐች የተደገፈ ፤ አቋማችንም በመከላከል ላይ ያተኮረ ይምሰል እንጂ ወደማጥቃቱ እርምጃ ያዘነበለ መሆኑ ለማንኛችንም ስውር አይደለም ።”

እዚህ ላይ ንግግሩን ቆም አድርጎ የትምባሆውን ማጨሻ እንደገና በትምባሆ ቅጠል መጠቅጠቅ ጀመረ።ኩራት ተሰማኝ ፤ በኩርፊያና በጭንቀት ወደሚያንሾካሽኩት ሹማምንት የንቀት አመለካከቴን ወርወር እንዳረግሁባቸው ፤

“ ግን ክቡራን ” በማለት ጄኔራሉ ቀጠለ ፤ ከረጅም ትንፋሹ ጋር ጢሱን ቡልቅ አድርጐ ፤ “ በግርማዊትነታቸው በታላቋ ንግሥት የተሰጠኝን ግዛት የመጠበቅ ታላቅ አደራ በበኩሌ እንዲህ በመሰለ መንገድ ለመወጣት አልሞክርም ። ስለዚህ በብዙኃኑ ውሳኔ መሠረት በከተማችን ክልል ውስጥ አድፍጠን በመሣሪያ ኃይላችን ፤ ቢቻልም



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣ በማለት ፣ ጠላትን መዋጋቱ በቂና የሚበቃን እርምጃ መሆኑን ተቀብዬዋለሁ ። ”

አሁን ደግሞ ፣ ሹማምንቱ በተራቸው ይቀላልፉብኝ ጀመር ። ስብሰባው ተበተነ ። ከእምነቱ ውጭ የእነዚያን ደንቆሮዎች እንጭጭ አስተሳሰብ ለተቀበለው የጦር መሪም አዘንኩለት ።

ይህ ስብሰባ በተካሔደ በጥቂት ቀናት ውስጥ ፑጋቼቭ ቃሉን ጠብቆ ወደ ኦሬንበርግ ዘመተ ። ከከተማዋ ግምብ ማማ ላይ ሆኜ ወታደሮቹን ከሩቅ አየኋቸው ። እኔው ራሴ በፊተኛው ውጊያ ወቅት ከተገነዘብኩት በላይ በእጅጉ ቁጥራቸው ጨምሯል ። ፑጋቼቭ ቀደም ሲል ካንበረከካ ቸው ምሽጎች በማረካቸው መሣሪያዎችም ተጠናክሯል። የወታደራዊው ስብሰባ ውሳኔ ድቅን አለብኝና ኦሬንበርግ ለረጅም ጊዜ እንደምትከበብ ተገንዝቤ በንዴት ላለቅስ ምንም ያህል አልቀረኝ ።

ከእኔ ወሬ ይልቅ ሁኔታውን ታሪክ መዝግቦታልና ስለኦሬንበርግ ከበባ ለማውሳት አልሻም ። እንዲያው በተ ቻለኝ መጠን ፣ ባጭሩ ለመጠቀም ያህል ፣ ከአስተዳደሩ ግዴለሽነት የተነሣ ከበባው በነዋሪው ሕዝብ ላይ አስከፊ ረኃብና ስቃይን አስከተለ ። በቀላሉ መገንዘብ እንደሚቻ ለው በኦሬንበርግ መኖር እሚያስመርር ሆነ ። ሁሉም ተስፋ በመቁረጥ የመጨረሻ ዕጣቸውን መጠባበቅ ያዙ ፣ የከተማዋ ነዋሪዎች የተከመረባቸውን የዋጋ ቅጥያ ሊቋ ቋሙት አልቻሉም ። በየደጃፋቸው ዱብ የሚለውን የመ ድፍ ጥይትም ተላመዱት ። የራሱ የፑጋቼቭ መምጣት እንኳ እምብዛም አላስፈራቸውም ። በበኩሌ በመሰልቸት ብቻ ልሞት ሆነ ። ጊዜው ተራዘመ ። ከቤሎጉረስክ ምንም ደብዳቤ አልደረሰኝም ። መንገዶቹም በሙሉ ተዘግተዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከማሪያ ኢቫኖቭና መለየቱን አልቻልኩትም ። የሚደር ስባትን ፍዳ ሳስበው ዘገነነኝ ። ሐሳቤን የሚከፍልልኝ የፈ ረስ ግልቢያ ብቻ ነበር ። ለጭ ጋቼቭ ምስጋና ይግባውና ያለ ኝን ምግብ የሚጋራው ጥሩ ፈረስ ስለ ነበረኝ ከጭጋቼቭ ፈረ ሰኞች ጋር ተኩስ ለመለዋወጥ በየቀኑ ከከተማዋ ወጣ እላ ለሁ ። አብዛኛውን ጊዜ ድሉ የሚያመዝነው በሚገባ ወደ ሚመገቡት ፣ በቂ መጠጥ ወዳላቸውና ትጥቃቸው ወደተ ሟላው ወደ ወንበዴዎቹ ነበር ። በረኃብና በጥማት የተጐ ሳቆለው የከተማዋ ፈረሰኞች ከፍለ ጦር ምናቸውም አይ ደርስ ። ረኃብ ያጠወለገው እግረኛው ጦርም ዐልፎ ዐልፎ ለግምባር ፍልሚያ ብቅ ቢልም፣ እስከ ጉልበት በሚ ያሰምጠው የበረዶ ክምር ምክንያት ተበታትኖ የሚገጥ መውን የወንበዴ ጦር ለመቋቋም አልቻለም ። መድፎቻ ችን ከየተጠመዱበት ጉራ ላይ የሚያጓሩት በከንቱ ስለ ሆነ ከየወደቁበት ሥፍራ ተሰክተው የሚቀሩትን ጥይቶች ፈረሶች እየጐተቱ ለመንቀል መከራቸውን ያዩ ነበር ። ወታደራዊ እንቅስቃሴዎቻችን ፣ የኦሬንበርግ ሹማምንት በጥንቃቄና በጥበብ የነደፏቸው የውጊያ ስልቶች ይህን መሳይ ገጽታ ነበራቸው ።

በአንድ ወቅት ፣ እንደምንም ብለን አንድ የወንበዴ ጦር ግምባር ድል መትተን ካፈራረስን በኋላ ፣ ድል ከተመ ታው ጦር ተነጥሎ የሚሸሽ አንድ ኮዛክ ማሳደድ ያዝኩ ። ደረስኩበትና ጐራዲዬን ላሳርፍበት ስቃጣ ቆቡን አውልቆ “ ፒዮትር አንድሬች ! እንዴት ነህ ! ” በማለት ጩኸት የተላበሰ ሰላምታ አቀረበልኝ ።

እየሁትና ያን ዐሥር አለቃ አስታወስኩት ። እሱን በማየቴ የተሰማኝን ደስታ መግለጽ ያዳግተኛል ። “እንዴ ማክሲሚች ነህ ! ” አልኩት “ ከቤሎጉርስክ ከመጣህ ቆይተሃል ? ”


t.me/OLDBOOKSPDF

" በቅርቡ ነው ፣ ፒየትር እንድሬች ፣ ጌታዬ ። ገና ትና ንት ነው የመጣሁት ። ማስታወሻም ይዤልሃለሁ ። "

" የታለ ? " አልኩት ፣ ላብ እያሰጠመኝ ።

" ይኸው ! " በማለት እጁን ሸሚዙ ውስጥ ከተተ ። "እንደምንም ብዬ እንዳደርስላት ለማሪያ ቃል ገብቼላት ነበር ። " የተጣጠፈ ወረቀት አስጨብጦኝ በግልቢያ ገሠገሠ ። ደብዳቤውን ዘረጋጋሁትና በጉጉት ተውጬ የሚከተሉትን መስመሮች አነበብኩ ።

" እግዚአብሔር ሲፈርድብኝ አባትና እናቴን በድ ንገት አሳጣኝ ። በምድር ላይ ዘመዴም ሆነ አለኝታዬ የም ለው አንድም ሰው የለኝም ። እርዳታህን ለሚሹ ሁሉ ፈጥ ነህ የምትለግስ አንተ እንደሆንክ ዐውቃለሁና መልካሙን የምትመኝልን አንተኑ እማፀናለሁ ። ደብዳቤዬን በእጅህ እንዲያስገባልኝ ለእግዚአብሔር እጸልያለሁ ። ማክሲሚ ችም እንደሚያደርስልኝ ቃል ገብቶልኛል ። ወጣ ስትሉ ዘወትር እንደሚያይህና ለራስህም ሆነ ስለአንተው እንባቸ ውን እየረጩ የሚጸልዩልህን ችላ እንዳልክ ከማክሲሚች ሰምቻለሁ ። ለረጅም ጊዜ ታምሜ ነበር ። እናም ሻል ሲለኝ በአባቴ ቦታ የምሽጋችን አዛዥ የሆነው ሺቫብሪን አባጂ ራዚም እኔን እንዲያስረክቡት ፣ ካላስረከቡት ግን ለፑጋ ቼቭ እንደሚያሳጣቸው አስፈራርቷቸው ዛሬ ከእነርሱ ቤት ወጥቼ የምገኘው ከእኛው ቤት በጥበቃ ሥር ነው ። ሺቫ ብሪን እኔን ለማግባት የማያደርገው ሙከራ የለም ። እኩ ሊና ፓምፊሌቭና እኔን ከወንበዴዎቹ ለማዳን ብላ የእህቷ ልጅ ስታደርገኝ ሰምቶ እንዳልሰማ በመምሰሉ በሕይወት ሊያቆየኝ እንደ ሞከረ በማውራት ይመጻደቅብኛል ። በበ ኩሌ ሽቫብሪንን ከማገባ ሞቴን እመርጣለሁ ። ጭካኔ በተ መላበት አኳኋን ዘወትር ያስፈራራኛል ። ሐሳቤን ለውጬ


t.me/OLDBOOKSPDF

እሺታዬን ባልገልጽለት ወደ ወንበዴዎቹ ሠፈር እንደሚ ወስደኝና የሊዛቤታ ካርሊቫ ዕድል እንደሚጠብቀኝ ያስ ጠነቅቀኛል ። ጊዜ እንዲሰጠኝ ለምኘዋለሁ ። ለሦስት ቀናት እንደሚታገሠኝ ተስማምቶ፣ በእነዚህ ቀናት ውስጥ እርሱን ላለማግባት ከወሰንኩ ምሕረት እንዳማያደርግልኝ ዛቻውን ሰንዝሮብኛል ። የምወድህ ፒየትር አንድሬች ! መከታዬ አንተው ነህ ። እኔን ዕድለቢሷን ከጉድ አው ጣኝ ! ጄኔራሉና ሹማምንቱ እርዳታ ባስቸኳይ እንዲልኩ ልኝ ለምንልኝ፣ አንተም ራስህ ኩተቻለህ ናልኝ ።

ያንተው አባትና እናት የለሿ
" ማሪያ ሜርኖቭና "

የዚህ ደብዳቤ አቤቱታ ሕሊናዬን ሊያስተኝ ምንም አልቀረውም ። ፈረሴን ያላንዳች ሐዘኔታ እየሸነቆጥኩት ወደ ከተማ ጋለብኩ ። መንገዱን በሙሉ ያችን ምስኪን ልጅ እንዴት እንደማድናት አሰላስል ነበር ። ግን ምንም ፍንጭ አላገኘሁም ። እንደ ደረስኩም ተንደርድሬ ጄኔራሉ ቤት ዘው አልኩኝ ። ፒፓውን እንደ ጉረሰ በክፍሉ ውስጥ ይንጐራደድ ነበር ። ሲያየኝ ቀጥ አለ ። ሁኔታዬ ሳያስደነ ግጠው አልቀረም ፤ እያከነፈ ያመጣኝ ምክንያት ምን እንደ ሆነ በርጋታ ጠየቀኝ ። " ክቡር ሆይ ! " አልኩት ፣ " እንደ አባቴ ነው የማይዎ ። ስለ እግዚአብሔር ብለው ልመ ናዬን ስሙኝ ። ሕይወቴ መጨለሚ ነው ። "

" ምን ሆንክ ፣ ጓዴ ? " ሲል ጠየቀኝ ከአባትነት ስሜት ። " ምን ላድርግልህ ? ተናገር ! "

" ክቡር ሆይ ፣ ጥቂት ኩዛኮች እንዲከተሉኝ ይፍቀ ዱልኝና የቤሎጉርስክን ምሽግ ከወንበዴዎቹ ላጽዳው ! "


t.me/OLDBOOKSPDF

እእምሮዬን የሳትኩ ሳይመስለው አልቀረም ። ይህ ንኑ በቀጥታ ባይነግረኝም ፡ በእርምጦ ተመለከከተኝ ።

“ ምን ? የቢሎግርስክን ምሽግ ላጽዳው ?” አለኝ የእ ኔኑ ቃላት መልስ በማስተጋባት ።

“ ጠላትን ድል እንደምመታ አረጋግጥልዎታለሁ ” ስል መለስኩለት በጥድፊያ “ ብቻ ይፍቀዱልኝ ! ”

“ አይሆንም ፡ ልጄ ” አለኝ ራሱን እየነቀነቀ ። “በእ ንዲያ ያለ ርቀት ላይ የሚገኝ ጠላት ያለምንም ችግር ከዋ ናው ጦር ሠፈር ነጥሎህ ድል ሊያደርግህ ይችላል ። ከዋ ናው ጦር ሠፈር ከተነጠልክ . . . ”

ስለውጊያ ስልት ወሬውን እንዳይዘረጋብኝ ፈራሁና ቀልጠፍ ብዬ አቋረጥኩት ። “ የአዛገፑ ልጅ ፡ ሚሮኖቭ ደብዳቤ ጽፋልኛለች ” አልኩት ። “ ርዳታ ትለምናለች ። ሺቫብሪን አስገድዶ ሊያገባት እየጣረ ነው ። ”

“ ነው እንዴ ? አዎ ፡ ሺቫብሪን ኃይለኛ ወንበዴ ነው ! በእጄ ቢገባልኝ በሐያ አራት ሰዓታት ውስጥ አስፈርጄበት በዚያው ምሽግ ውስጥ እንደማስረሽነው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ! ግን ለጊዜው ትዕግሥት ያስፈልገናል ! ”

“ ጉድኮ ነው ! ” በማለት ጄኔራሉ የጭንቀቴ ተካ ፋይ ሆነ ። “ ኧረ የባሰም ሊገጥማት ይችላል ! ለጊዜው የሽቫብሪን ሚስት ብትሆን ይበጃታል ፡ መጠጊያ እንኳ ታገ ኛለች ፡ ከተረሸነም በኋላ ባል እንፈልግላታለን — እግ ዜር ካለ ባሏ የሞተባት ቆንጆ ሴት ቆማ አትቀርም ፡ ማለቴ ከልጃገረድ ይልቅ ባሏን ያጣች ሎጋ የሚያገባትን በቀላሉ ማጥመድ ትችላለች ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለሽቫብሪን ከምለቅለት ሞቱን እመርጣለሁ !" ስል ጮህኩበት በቁጣ ።

" እረ ! " አለኝ ሽማግሌው ። " አሁን ገና ገባኝ ! ለካስ አንተው ራስህ ማሪያ ኢቫኖቭናን ወደሃታል ። ዓላማህ አሁን ገና ቁልጭ አለልኝ ። በምንም አኳኋን አጃቢ ኮዛኮች አልፈቅድልህም ። እንዲያ ያለ ዘመቻም ፈጽሞ ተገቢ አይደለም ። ኃላፊነቱንም አልወስድም ። "

ተስፋ ቆርጬ ራሴን ደፋሁ ። በድንገት አንድ ዘዴ ብልጭ አለልኝ ። አበው ደራሲያን እንደሚያደርጉት ፥ ያን ዘዴ በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ እገልጽላችኋለሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## የወንበዴዎቹ መንደር

ከጀኔራሉ ዘንድ ወጥቼ ወደ መጠለያዬ ተመለስኩ ። ሳቬሊችም በተለመደው ስሞታው ተቀበለኝ ። " ከሰካራም ወሮበሎች ጋር ለመጋጨት ለምን ትሮጣለህ ጌታዬ ! ይህ የጨዋ ልጅ ድርጊት ነው ? አንድ ነገር ቢደርስብህ በከንቱ ደመከልብ ሆነህ መቅረትህ ነውኮ ! . . . "

ንግግሩን አቋርጬው ምን ያህል ገንዘብ እንደ ተረፈኝ ጠየቅሁት ። " ገንዘብስ አታጣም " አለኝ በተረጋጋ መንፈስ ። " ወሮበሎቹ ቢዘርፉንም ትንሽ ለመደበቅ ችያለሁ " ይህን ብሎኝ በብር መሐለቆች የተሞላች አንዲት ከረጢት ከኪያው መዘዘ ። " እስቲ ቀረብ በል ፣ ሳቬሊች" አልኩት ፣ " ግማሹን ስጠኝና የተቀረውን ለራስህ ተጠቀምበት ። ወደ ቤሎጎርስክ ምሽግ መጓዜ ነው ። "

" ጌታዬ ፓዩትር አንድሬች ! " አለኝ ሳቬሊች በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ። " ስለ እግዚአብሔር ብለህ ! ወሮበሎች በየጐዳናው ባይፈጡበት በዚህ ቀውጢ ወቅት እንዴት ብለህ ትጓዛለህ ? ለምንስ ብለህ ? እንዳው ለምን ተብሎ ? ታገሥ ወንበዴዎቹን ወታደሮች በቁጥጥር ሥር ማዋላቸው እንደሁ አይቀር ። ከዚያም በኋላ ወደ ፈለግህበት ሒድ ። "

" አንዴ ቆርጫለሁና ጭቅጭቅ አልፈልግም " አልኩት ። "እሔዳለሁ ብያለሁ ፣ መሔድ አለብኝ ። አትዘንብኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳቬሊች ። እግዚአብሔር ቸር ነውና ምናልባት እንገናኝ ይሆናል ። ልብ አድርግ ፤ ከመጠን በላይ በመንቆጣቆጥ ራስህን አትበድል ። ዋጋው ዐሥሬ ቢቆለልም የሚያስፈል ግህን ከመግዛት ወደኋላ አትበል ። ገንዘቡን የተውኩልህ በስጦታ ነው ። በሦስት ቀናት ውስጥ ባልመለስ . . . ”

“ምን ማለትህ ነው ጌታዬ!” ሲል ጮኸብኝ ሳቬሊች በንግግሬ መሐል ጣልቃ ገብቶ ። “ብቻህን የምለቅህ መስ ሎሃል ! እንዲያ ያደርጋል ብለህ ጭራሽ አታስብ ! ለመ ሔድ አንድዬ ቊርጠህ ተነሥተሃልና በእግሬም ቢሆን እብሬህ እሔዳለሁ እንጂ ፈጽሞ ብቻህን አልለቅህም ። ከአንተ ተለይቼ እዚህ ከተማ ውስጥ በሰላም የምቀይህ ይመስልሃል አብጄያለሁ ? የፈለግኸውን በለኝ ፤ ጌታዬ ፤ ብቻህንስ አልለቅህም ።” ከሳቬሊች ጋር መከራከሩ ፋይዳ እንደሌለው ተረዳሁኝና ለጉዞዋችን ዝግጅት እንዲያደርግ ፈቀድኩለት ። ከግማሽ ሰዓት በኋላም እኔ በፈረሴ ላይ ፤ መቀለብ ያልቻለ አንድ ከተሜ በሸለመው እንካሳ ጌኛ ላይም ሳቬሊች ቁብ ብሎ ጐን ለጐን ተያየን ። ወደ ዋናው ቢሮም አመራን ። ዘበኞቹ አሳለፉን ። ኦሬንበርግን ተሰና በትናት ።

መሸትሸት እያለ ነበር ። መንገዳችን የፑጋቼቭ ዋነኛ ምሽግ የሆነችውን የቢርዳን መንደር ያቋርጣል። መንገዱ በበ ረዶ ቢሸፈንም የመንገደኞች ኮቴ በየሥፍራው ወለል ብሎ ይታያል ። እፈጥን ስለነበር ሳቬሊች ሊደርስብኝ ባለመቻሉ ያለማቋረጥ “ቀስ በል እንጂ ጌታዬ! እረ በፈጣሪ ! ቀ ስ ! ይኸ የተረገመ ጌኛ ከስንጋ ፈረስህ እኩል ሊጋልብ አይች ልምኮ ! ጥድፊያህስ ለምን ነው ? ወደ ግብዣ ቦታ የምን ሔድ ይመስል ፤ የምንጓዘው ለስቅላት አይደል ፤ ምን አለ በለኝ ! ፒዮትር አንድሬች . . . ጌታዬ ፤ . . . ይቅር በለኝ ! አይ አንተ ፈጣሪ ! የጌታዬ ልጅ መሞቱ ነው ! ”


t.me/OLDBOOKSPDF

የቢሪዳ መብራቶች ብቅ አሉ ። የመንደሪቱ የተፈጥሮ ተገን ወደ ሆነው ገደላማ ሥፍራ ደረስን ። ሳቪሊች የማያ ቋርጥ ጸሎቱን እያነበነበ ከኋላዬ አልተለየኝም ። መንደሪ ቱን በሰላም እናልፋታለን ብዬ ብመኝም ፣ ቆመጥ ዱላ ያነ ገቡ አምስት ያህል ቃፊሮች ጨለማን ተገን አድርገው እን ደቆሙ ከፊት ለፊቴ አየኋቸው ። ሥፍራው የፑጋቼቭ ጣቢያ መዳረሻ ነው ። ጠሩን ። ምን እንደ መልስላቸው ግራ ተጋብቼ በዝምታ መንገዳችንን ቀጠልን ። ግን ከመቅ ጽበት ከበቡንና አንደኛው የፈረሱን ልጓም አፈፍ አደረገ ብኝ ። ጐራዴዬን መዘዝኩና አናቱን ተረከከሁለት ። ሌሎቹ ተደናግጠው ፈረጠጡ ። የወቅቱን ፋታ በመጠቀም ፈረሱን ኮረኮርኩና የሽምጥ ጋለብኩ ። ጨለማውም ሽፋን ሆኖኝ አምልጬ ነበር ፣ ግን በድንገት ዘወር ብዬ ብመ ለከት የሳቬሊች ሽታው የለም ። በዚያ በአንካሳ ጌኛው ከወንበዴዎቹ ያመልጣል ማለት ዘበት ነው ። ምን ላድርግ ? ለጥቂት ጊዜ ጠበቅሁትና ይዘውት ይሆናል በማለት መን ፈሴን አረጋግቼ ልደርስለት ፈረሴን ጠመዘዝኩ ።

ገደላማው ሥፍራ ላይ እንደ ደረስኩ ንትርክ ሰማሁ ። በመሐሉ የሳቬሊችን ድምፅ ለመለየት ቻልኩ ። በፍጥነት ገሥግሼም እንዚያ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ደንቃራ ሆነ ውብኝ የነበሩት ሰዎች መሐል ዘው አልኩ ። ሳቬሌች ተከ ብቧል ። ከፈረሱ ጐትተው ከአወረዱት በኋላ ሊያስሩት በመጣደፍ ላይ ነበሩ ። በቦታው በመገኘቴ ደስ ብሏቸው እየተጭዋጭዋሁ ተረባረቡብኝና እኔንም በደቂቃ ውስጥ ከፈረሴ አወረዱኝ ። ከመካከላቸው አንድ ፤ መሪያቸው መሆን አለበት ፣ በቀጥታ ወደ ንጉሡ ዘንድ እንደሚወስደኝ አስታወቀኝ ። “ እናም ፣ ንጉሣችን ” አለ በተጨማሪ ፣ “ ዛሬውኑ ወይም ሲነጋ ስቅላት ይወስንባችኋል ። ”


t.me/OLDBOOKSPDF

ለመከላከል አልሞከርኩም ። ሳቬሊችም የእኔን አርአያ በመከተሉ እየፈነደቁ ይዘውን ሔዱ ።

ከገደላማው ሥፍራ በአንደኛው ጥግ በኩል ወደ መንደሪቱ ዘለቅን ። ጕጆዎቹ በሙሉ በርተዋል ። ሁካታ ከየአቅጣጫው ያስተጋባል ። መንገዱ በሰው ቢጣበብም ከመጨለሙ የተነሣ ልብ ያለን ፤ ወይም የኦሬንበርግ መኮ ንን መሆኔን የለየ ማንም አልነበረም ። ሁለት መንገዶች ከሚያቋራርጡበት ማዕዘን ላይ ወደ ቆመች አንዲት ጕጆ መሩን ። ደጃፉ ላይ ጥቂት የውሃ በርሚሎችና ሁለት መድ ፎች ተገትረዋል ። “ ቤተመንግሥቱ ይኸ ነው ” አለ ከቃ ፊሮች አንዱ ። “ ገባ ብዬ መምጣታችሁን ልንገራ ። ” ወደ ጕጆዋ ጐራ አለ ። ሳቬሊችን መልከት አደረግሁት ። ሽማግሌው እያማተበ ጸሎቱን ተያይዞታል ። ለረጅም ጊዜ ከጠበቅነው በኋላ ሰውዬው ተመለሰና ገባ ። “ንጉሡ የነ ገሩኝ መኮንኑን እንዳስገባ ነው ” በማለት ሳቬሊችን አስ ቀረው ።

ወደ ጕጆዋ ፤ ወይም ቃፊሮቹ ቤተመንግሥት ወደ ሚሉት ቤት ገባሁ ። ሁለት ሻማዎች የሚንጨለጨሉበት ሲሆን ግድግዳዎቹም በወረቀት ተለብጠዋል ። ከዚህ በስ ተቀር በውስጡ የሚታዩት ፤ እንደ ማንኛውም ጕጆ ፤ አግ ዳሚ ወንበሮች ፤ አንድ ጠረጴዛ ፤ የተሰቀለ የፊት መታጠ ቢያ ሳህን ፤ ከምስማር ላይ የተንጠለጠለ ፎጣ ፤ በአንድ ጥግ የእሣት መቆስቆሻ ሁለት ብረቶችና በድንጋይ ጉልቻ ላይ የቆሙ ማሰሮዎች ብቻ ናቸው ። ፑጋቼቭ በአንድ ስማዕት ምስል ሥር ጃኖ የመሰለ ልብስ አጥልቆና ቆቡን ደፍቶ ወገቡን እንደያዘ ጉብ ብሏል ።

ከቀንደኞቹ ረዳቶቹ ብዙዎቹም በሐሳብ የተመሰጡ መስለው በአቅራቢያው ቆመዋል ። ከኦሬንበርግ አንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

መኰንን የመምጣቱን ዜና ወንበዴዎቹ የተቀበሉት በከፍተኛ አድናቆት መሆኑንና በክብር ለማስተናገድ ማቀዳቸውም በግልጽ ይታወቅባቸዋል ። ጒጋቼቭ ከመቅጽበት ለይቶ ዐወቀኝ ። የታላቅነት ግርማ ሞገሱ ወዲያውኑ ተገፈፈ ። “ ታዲያስ ፣ ጌታው ! ” አለኝ በደስታ ። “ እንዴት ነህ ? ምን እግር ጣለህ ጃል ? ” ለግል ጉዳይ በመጓዝ ላይ ሳለሁ ተከታዮቹ እንደያዙኝ ነገርኩት ። “ ጉዳይህ ምን ነበር ? ” ሲል ጠየቀኝ ። ምን እንደምመልስ አላወቅሁም። ጒጋቼቭ በሰው ፊት ለመናገር ያልፈለግሁ መስለውና ቆመው የነበሩትን አሰናበታቸው ። ሁለት ብቻ ሲቀሩ የተቀሩት በሙሉ ውልቅ አሉ ። “ እነዚህ ፊት የፈለግኸውን ማለት ትችላለህ “ አለኝ ጒጋቼቭ ። “ ከእነርሱ የምደብቀው ምስጢር የለኝም።” ጓደኞቹን ስርቅ አድርጌ አየኋቸው።አንደኛው ሸበቶ ጢም ያለው ፣ ደቃቃና የጒበጠ ሽማግሌ ሲሆን ከሰው ዐይን ሊያስገባው የሚያስችል ነገር ቢኖረው በካፖርቱ ላይ ጣል ያደረጋት አንዲት ሰማያዊ ጥብጣብ ብቻ ናት ። ሌላውን ሰው ግን ፣ እስከ ዕለተ ሞቴ አልረሳውም ። ዐርባ አምስት ዓመት ገደማ የሚጠጋው ፣ ረጅምና ትከሻው የሰፋ ጠብደል ነው ። ድልህ የመሰለው ጢሙ ፣ የሚንቦገቦጉት ግራጫ ዐይኖቹ ፣ የአፍንጫው ቀዳዳ ስፋት ፣ ፊንጣጣ የጠቀጠቃቸው የሚመስሉት ጉንጮቹና ግንባሩ በአስከፊ ገጽታው ላይ አስፈሪነትን አክለውለታል ። በቀይ ሸሚዙና እጀ ጠባብ ከሚመስለው ልብሱ በታች የኮዛክ ጠባብ ሱሪ አጥልቋል ። የመጀመሪያው ሰው በኋላ እንደደረስኩበት ፣ ቤሎቦሮዶቭ የሚባል ኩብላይ ዐሥር አለቃ ሲሆን ሁለተኛው አፋናሲ ሶኮሎቭ በቅጽል ስሙ ክሎፑሻ ፣ ከሳይቤሪያ ማዕድናት ማውጫ ሥፍራ ሦስት ጊዜ ያመለጠ ወንጀለኛ ነው ። ስሜቴ ቢመሰቃቀልም በድንገት ያጋጠሙኝ እነዚያ ሰዎች ሳልወድ በግድ አእምሮዬን ማረኩት ። ሆኖም ጒጋቼቭ “ ከኦሬንበርግ ያመጣህ ጉዳይ


t.me/OLDBOOKSPDF

ምንድን ነው ? ተናገር ! ” በማለት ወደ ወቅቱ ጉዳይ መለ ሰኝ ።

እንግዳ ነገር በሕሊናዬ ብዥ አለብኝ። የእግዜር ድጋፍ ለዳግመኛ ጊዜ ወደ ፑጋቼቭ መርቶኝ ዓላማዬን ለማ ሟላት ዕድል የሰጠኝ መሰለኝ ። ይህን ዕድል ልጠቀምበት ወሰንኩና በውሳኔዬም ሳላወላውል ለፑጋቼቭ ጥያቄ መል ሴን እንዲህ በማለት አቀረብኩ ።

“ እንዲት ሥቃይዋን የሚያሳይዋትን ዕጓለ ማውታ ለማዳን ወደ ቤሎጉርስክ በመገሥገሥ ላይ ነኝ ። ”

የፑጋቼቭ ዐይኖች ተቁለጨለጩ ። “ ከእኔ ሰዎች መሐል ዕጓለ ማውታ ለማሰቃየት የደፈረው ማነው እባ ክህ? ” ሲል ጮኸ ። “ ምንም መሠሪ ቢሆን ከፍርዴ አያ መልጥም ! ተናገር ፤ ለመሆኑ ይህ አረመኔ ማን ነው ? ”

“ ሽቫብሪን ! ” በማለት መለስኩለት ። “ ያችን ቄሱ ቤት ያየሃትን ሕመምተኛ ልጅ በቁጥጥሩ ሥር አው ሏት እንድታገባው እያስገደዳት ነው ። ”

“ ሺቫብሪንን የምሱን እሰጠዋለሁ ” አለ ፑጋቼቭ ጥርሶቹን ነክሶ ። “ከትእዛዜ ውጭ መፏለልና ሕዝቤን ማሰቃየት ምን እንደሚያስከትልበት አሳየዋለሁ ። ይን ጠለጠላታል ። ”

“ እንዲት ቃል እንድናገር ይፈቀድልኝ ” አለ ክሎ ፑሽካ ጉርነን ባለ ድምፅ ። “ ሽቫብሪንን የምሽጉ ጠቅላይ አዛዥ ለማድረግ ያልተጣደፍከውን ያህል አሁን ደግሞ ልትሰቅለው ትጣደፋለህ ። ከመኳንንት ዘር ፣ ያውም እር ሱን በመሾምህ ኮዛኮችን አስቀይመህ እንዳልነበር ሁሉ አሁን ደግሞ በእንዲት አቤቱታ ብቻ እርሱን ለሞት በመ ዳረግ መኳንንቱን እታስበርግግ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ማንም ይሁን ማን፣ ጥፋተኛ ሆኖ እስከ ተገኘ ድረስ በነጻ የሚለቀቅበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም " አለ ሰማያዊ ጥብጣብ ያደረገው ሽማግሌ ። " ሽፍቶቹን መስቀል ምንም ጉዳት አያመጣም ። ደግሞም ይህንን ሰው ጠበቅ አድርጐ መመርመሩ አይከፋም ። ከዚህ ምን አመጣው ? ገዥነትዎን ሳይቀበለው ፍርድዎን እንዴት ይሻል ? ተቀብያለሁ የሚል ከሆነስ ከለየላቸው ጠላቶችዎ ጋር በኦሬንበርግ ውስጥ ይሆን ያህል ጊዜ ምን አቆየው ? እስቲ ወደጣቢያ ልውሰደውና ብረት ላግል ። ጌታው ከኦሬንበርግ ሹማምንት የተላከብን ሰላይ ለመሆኑ ቆሌዬ እያስጠነቀቀኝ ነው ። "

የሽማግሌው አስተሳሰብ እውነትን የተመረኮዘ ይመስላል ። በእነማን መዳፎች ውስጥ እንደ ገባሁ ሳስብ መላ አካላቴ ደነዘዘ። ጭንቀት እንደ ተሰማኝም ፑጋቼቭ ዐወቀ። " እናስ ጌታው ? " አለኝ ፣ በዐይኖቹ ጠቀስ አድርጐኝ ። " የጦር አበጋዜ አባባል ከልብ የሚገባ ይመስለኛል ። አንተስ ምን ትላለህ ? "

የፑጋቼቭ ጉትጐታ ብርታቴን መለሰልኝ ። በቁጥጥሩ ሥር ውያለሁና ተገቢ የመሰለውን እርምጃ ሊወስድብኝ እንደሚችል በጥሞና ነገርኩት ።

" ጥሩ " አለኝ ፑጋቼቭ ። " ለመሆኑ ከተማችሁ እንዴት ናት ? "

" እግዜር ምስጋና ይግባው ፣ ሁሉም መልካም ነው" አልኩት ።

" መልካም ነው ? " ሲል አስተጋባ ፑጋቼቭ ። ዝቡ በረኃብ እየረገፈ ! "



t.me/OLDBOOKSPDF

የተናገረው ሐቁን ነው ። እኔ ግን ቃለመሐላዬን ለመ ጠበቅ ስል የሚወራው ሁሉ ፍሬቢስ እንደሆነና በአሬን በርግ ምርት እንደ ተትረፈረፈ ላሳምነው ሞከርኩ ።

" ተመልከቱልኝ " በማለት ሽማግሌው ጣልቃ ገባ ። " አፊትዎ ይዋሻል ። የኮበለሉት ሁሉ የሚነግሩን በአሬን በርግ ረኃብና ወረርሽኝ መስፋፋቱን ፣ ጥንብ እንኳ ቢያገኙ ለመብላት እንደማይመለሱ ነው ። ጌታው ደግሞ ምርት ተትረፍርፏል ይለናል ። ሺቫብሬን ለመስቀል ከፈለጉ ይህንንም ደፋር ጉረምሳ ከጉኑ አብረውት ያንጠልጥሉትና የምቀኝነት ንትርካቸውን ያስወግዱልን ። "

የዚህ ክፉ ሽማግሌ ቃላት ጭጋጬቭን ከነከኑት ። ይኸኔ ክሎፑሻ የጓደኛውን ንዴት ሊያቀዘቅዝ ሞከረ ። "ይበቃል ፣ ኖሚች" አለው ። "አንተ ሁሉም ይታነቅ፣ ይታ ረድ ማለት ይቀናሃል ። ቆመህ መሔድህ ሰው አስመስሎ ሃል ። ግን ነፍስህ ከሥጋህ እየተመነጠቀች መሆኗን ? ት ዘንጋ ። አንተ ራስህ ከመቃብር አፍ ላይ እያለህ ሌሎችን ለማጥፋት ትመኛለህ ። የሰው ደም በከንቱ ሲፈስ አይዘ ገንንህም ? "

" አንተስ መልአክ መሆንህ ነው ? " በማለት መለ ሰለት ቤሎቦሮዶቭ ። " እንዲህ በድንገት ልብህን በርኅ ኄራ ያቀለጠው ምን ይሆን ? "

" እኔም ኃጢአተኛ እንደሆንኩ ይገባኛል " አለው ክሎፑሻ " ይህ ክንዴ " እንደ አጥንት የጠነከረ መዳፉን ጨብጦና እጅጌውን ሰብስቦ ጸጉራም ክንዱን እያሳየው ፣ " ይህ ክንዴ የብዙ ክርስቲያኖችን ደም አፍስሷል ። ግን ጠላት እንጂ ወዳጅ አልገደልኩበትም ። ጠላቴንም ያጋ ደልኩት በአደባባይ ወይም በደን ውስጥ እንጂ በጉጆ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ምድጃ ዳር ተጉልቼ አይደለም ። የገደልኩትም በቆመጥ ወይም በመጥረቢያ እንጂ በባልቴት አይደለም ። ”

ሽማግሌው ፊቱን በንቀት እያዞረ፣ “ ድፍጥጥ አፍንጫ ! ” በማለት ሰደበው ።

“ ምን አልክ ፡ አንት ሬሳ ? ” ሲል ክሎፑሻ ደነፋ ። “አፍንጫህን እደፈጥጥልሃለው ጠብቅ ፣ ጊዜህ ሩቅ አይሆንም ! እግዜር ካለው አንተም የጋለ ብረት ታሽታለህ ። እስከዚያው ጺምህን እንዳልነጭብህ ! ” “ ክቡራን ጄኔራሎች ! ” አለ ፑጋቼቭ ኮስተር ብሎ ። “ ጭቅጭቃችሁ ይብቃ ! የኦሬንበርግ ውሾች በሙሉ ቢንጠለጠሉ ደንታ አይኖረኝም ። ግን የእኛው ውሾች የእርስ በእርስ ንክሻ ያሳስበኛል ! ከእንግዲህ ይብቃ ! ”

ክሎፑሻና ቤልቦሮዶቭ ቃል ሳይተነፍሱ አንገቶቻቸውን እንደደፉ ተያዩ ። ከዚያ ጣጣ ውስጥ የከተተኝን ርዕስ መለወጡ አስፈላጊነቱ ታየኝና በፈገግታ ወደ ፑጋቼቭ ዘወር ብዬ “ እንዳው ፡ ስለ ሽለሙኝ ካፖርትና ፈረስ እስካሁን ሳላመሰግንዎት . . . ያለ እርስዎ ርዳታ ከተማ ሳልደርስ መንገድ ላይ በብርድ ተቆራምጄ እሞት ነበር ” አልኩት ።

ዘዴዬ ሠራ ። ፑጋቼቭ ተደሰተ ። “ በጐ ማድረግ ዋጋ አለው ” አለኝ ጠቀስ ካደረገኝ በኋላ አጨንቁሮ እያየኝ ። “ ያቺ ሺቫብሪን የሚያሰቃያት ወጣት ላንተ ምንህ እንደሆነች እስቲ አጫውተኝ ? እንዳው በነገራችን ላይ ፣ ፍቅረኛህ ነች እንዴ ? . . . እ ? ”

“ ዕጮኛዬ ነች ” አልኩት ። ሁኔታው ስለተረጋጋ ሐቁን ልደብቀው አልፈለግሁም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“እጮኛህ !” ሲል ጮኸ ፑጋቼቭ ። “ ታዲያ ለምን እንዲያ አላልከኝም ? አጋብተናችሁ ሠርጋችሁን እንበላለን ። ” ከዚያም ወደ ቤሎቦሮዶቭ እየተመለከተ “ስማ ! ጌታውና እኔ የጥንት ወዳጆች ነን ። ገበታ ይቅረብልን ። ጉዳዩን በንጹሕ ሕሊና ሲነጋ ብናየው መልካም ነው። ምን ማድረግ እንዳለብን ነገ እንወስናለን ። ”

ግብዣውን ላለመቀበል መግደርደር ፈልጌ ነበር ፤ ግን አልቻልኩም ። የቤቱ ጌታ መለሎ ልጆች ጠረጴዛውን ነጭ ጨርቅ አለበሱትና ዳቦ ፣ የዓሣ ሾርባ ፣ የቮድካና የቢራ ጠርሙሶች ደርድረውልን በድጋሚ ከፑጋቼቭና የተከበሩ ጓደኞቹ ጋር ማዕድ ለመካፈል በቃሁ ።

ያለውዴታዬ የምካፈለው ፈንጠዝያ እስከ ውድቅት ሌሊት ተራዘመ ። በመጨረሻም ሁሉም በመጠጡ ተሸከሙ ። ፑጋቼቭ እንደ ተቀመጠ ማንጐላጀት ጀመረ፣ ጓደኞቹም እንድንወጣለት ምልክት አሳዩኝና አብረን መሰስ አልን ። በክሎፑሻ ትእዛዝ ዘቦቹ ወደሆነ ሥፍራ ወሰዱኝና ከሳቬሊች ጋር ቆለፉብን ። ሳቬሊች በዕለቱ አጋጣሚ በጣም ተገርሞ ስለነበር አንዲት ጥያቄ እንኳ አላነሣብኝም። ጨለማ ውስጥ ተጋድሞ ቁና ቁና ሲተነፍስና ሲያቃስት ለረጅም ጊዜ ቆየ ። በመጨረሻም ማንኰራፋት ሲጀምር በሐሳብ ተውጬ በዐይኔ እንቅልፍ ሳይዞር ነጋ ።

ፑጋቼቭ በማለዳ አስጠራኝና ወደ ጐጆው አመራሁ። ደጃፉ ላይ በሦስት ፈረሶች የሚሳብ ሠረገላ ቆሟል ። መንገዱ ላይ ሰዎች ይርመሰመሳሉ ። ፑጋቼቭን በሩ ላይ አገኘሁት ። ቆቡን አጥልቆና ጸጉራም ካፖርት ደርቦ እርሱም ለጉዞ ተዘጋጅቷል ። ጓደኞቹም ከትናንት ማታ ይልቅ በዛሬው ዕለት ተረጋግተው ዙሪያውን ከበውት ቆመዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፑጋቼቭ የሞቀ ሰላምታ አቀረበልኝና ሠረገላው ውስጥ እንድገባ ጋበዘኝ ።

" ወደ ቤሎጉርስክ ምሽግ ! " አለው ፑጋቼቭ ደረቱ ሰፊውን ሠረገላ ነጅ ። ልቤ ታምቡር መታ ፈረሶቹ ተንቀሳቀሱ ፤ ቃጭሎቻቸውም ተቅጨለጨሉ፣ ሠረገላችን በበረዶው ላይ ተንሳፈፈ ።

" ቆይ ! ቆይ ! " አለ አንድ የማውቀው ድምፅ ፡ ሳቬሊች ከኋላችን ሲሮጥ አየሁት ። ፑጋቼቭም ሠረገላው እንዲቆምለት አዘዘ ። " ጌታዬ ፡ ፒዮትር አንድሬች ! " አለ ሳቬሊች " በእርጅና ዘመኔ ከእነዚህ ወሮበ . . . "

"ወቸጉድ ! አንተ ሽማግሌ" አለው ፑጋቼቭ ። "እግዜር በምሕረቱ ለዳግመኛ ጊዜ አገናኘን ። በል ና ውጣ ። "

" አመሰግናለሁ ፣ ክቡር ሆይ ! አመሰግናለሁ ፡ አለኝታዬ ! " አለ ሳቬሊች መቀመጫው ላይ እየተደላደለ ። " ለእንደእኔ ላለ ደካማ ሰው ላሳዩት ደግነት እግዚአብሔር ለመቶ ዓመት ጤንነት እንዲለግስዎ ዕድሜዬን በሙሉ እጸልይልዎታለሁ ፤ ካሁን ወዲያ ስለቆዳ ካፖርቱም አላነሣም ። "

የቆዳ ካፖርቱ ጉዳይ ፑጋቼቭን ያናድደዋል ብዬ ፈርቼ ነበር ። ደግነቱ ሳቬሊችን አልሰማውም ፡ ወይ አባባሉን ከቁም ነገር አላስገባውም ። ፈረሶቹ ይጋልባሉ ፡ ፑጋቼቭም ግራና ቀኝ እጅ ይነሣል ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ መንደሪቷን ለቀን ጥርጊያ ጐዳናውን ተያያዝነው ።

በዚያን ወቅት የነበረኝን ስሜት በቀላሉ መገመት ይቻላል ። እስከ ምንጊዜውም እንዳጣኋት የቆጠርኳትን ያችን ሰው በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ላያት ነው ። ስንገናኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምን እንደምንሆን ለማየት ሞከርኩ . . . በእንግዳ አጋ ጣሚዎች ስለተቆራኘኝና ዕድሌን በመዳፉ ውስጥ ስለአደ ረጋት ስለፑጋቼብም አሰብኩ ። ፍቅረኛዬን ነጻ የሚያወ ጣልኝ ይህ ሰው ደም የሚጠማው ጨካኝ መሆኑን በው ቃለሁ ። የምሽጋችን አዛዥ የነበረው የሚሮኖብ ልጅ መሆ ኗን ፑጋቼብ ገና አላወቀም ። ሺቫብሪንም ይህን ይፋ ከማ ውጣት ወደኋላ አይልም ። በዚህም ሆነ በዚያ ፑጋቼብ እው ነቱን ይደርስበታል ። ታዲያ ያኔ ማሪያ ኢቫኖብናን ምን ይውጣታል ? ቅዝቃዜ ተሰማኝ ፡ ጸጉሬ ቆመ ።

በድንገት ፑጋቼብ ወደ እኔ ዞሮ " ጌታው ፡ ምነው በሐ ሳብ ተዋጥክ ? " በማለት አባነነኝ ።

" አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮች ሞልተውኛል " አልኩት ። "መኮንንና የጨዋ ልጅ ነኝ ። ትናንት ስዋጋህ እንዳልነበ ርኩ ሁሉ ዛሬ ደግሞ በአንድ ሠረገላ ውስጥ ከጐንህ ተቀ ምጫለሁ ። ለወደፊቱ ሕይወቴም እስደሳችነት ወሳኙ አን ተው ነህ ። "

" አልክ ? " አለኝ ፑጋቼብ ። " ፈራኸኝ እንዴ ? "

ከዚህ በፊት ከሞት አፋፍ ያዳነኝ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ረዳቴ እርሱው መሆኑን ገለጽኩለት ።

" ልክ ነህ ፣ እግዚአብሔርን ትክክል ነህ ! " አለኝ ። "የእኔ ሰዎች እንዴት እንደ ተመለከቱህ አይተሃል ። ሽማ ግሌው ሰላይ መሆንህን አምኖበት በዛሬዋ ዕለት ተሰቃይ ተህ ልትሰቀል ነበር ። ግን አልተስማማሁለትም ። "ሳቬ ሊችና ሠረገላ ነጂው እንዳይሰሙትም ድምፁን ዝቅ አድ ርጐ ፡ " የጋበዝከኝን ቮድካና የሸለምከኝን ቆዳ ካፖርት አስታውሳለሁ።እናንተ እንደምትሉኝም ደም የሚጠማው እውሬ እንዳልሆንኩ ልብ በልልኝ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

የቢሴግሮስኪን ምሽግ ሲጠር ምን እንዳደረገ እይቻ ለሁ ፤ ግን መከራከሩ አግባብ ስላልመሰለኝ አንዲት ቃል አልተነፈስኩም ።

ትንሽ ከቆየ በኋላ ፤ “ አሬንበርጐች ምን ይሉኛል ? ” ሲል ጠየቀኝ ።

“ የማትበገር ሰው ነው ይሉሃል ። አንተን የማያውቅ አንድም የለ ። ”

ፊቱ በኩራት ፈካ ። “ እዎ ” አለ በደስታ ተሞልቶ ። “ ውጊያ ዐዋቂ ነኝ ። አሬንበርጐች የዩዚዮቫዩን ጦርነት ያወቁ ይሆን ? ዐርባ ጀኔራሎች የተገደሉበትና ዐርባ ብር ጌዶች የተማረኩበት ነው ። አንተስ ምን ትላለህ ? ለመሆኑ የፕሩስያ ንጉሥ የሚቋቋመኝ ይመስልሃል ? ”

ፑጋቼቭ አቅሙን አለማወቁ አስገረመኝ ። “ አን ተው ራስህ ምን ይመስልሃል ? ” ስል ጠየቅሁት ። “ፍሬ ድሪክን አሸንፈዋለሁ ትላለህ ? ”

“ ፍሬድሪክን ? ለምን አላሸንፈውም ? ጀኔራሎቻ ችሁ በእጄ ናቸውና ዋጋውን ይሰጡታል ። እስካሁን ክንደ፡ አልተበገረም ። ቆይ ታያለህ ፤ ሞስኮ እስክገባ ጠብቅ ! ”

“ ሞስኮም ላይ ለመዝመት ታስባለህ ? ”

ጥቂት ዐረፍ ብሎም ትንፋሹን ዋጥ አደረገና ፤“እግ ዚአብሔር ምስክሬ ነው ! ሰውነቴ ስለተሳሰረ ነጻነት ያስ ፈልገኛል ። ተከታዮቼን የሚኮረኩራቸው ነገር አለ ። ዋዛ እንዳይመስሉህ ። በሆዴ ያመቅሁት ጉድ አለ ። የመሸነፍ ዕጣ ቢገጥመንም የእኔንም ሆነ የራሳቸውን አንገት ያድ ናሉ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ይሁና ! ” አልኩት ። “ ይልቅስ አሁንት ፣ ጊዜ እያለህ ፣ ከእነርሱ ርቀህ እጅህን ለንግሥታችን ብትሰጥ አይሻልህም ? ”

ፑጋቼቭ በቁጭት ስሜት ከትከት ብሎ ሣቀብኝ ። “ በጭራሽ ” አለ ። “ ለመጸጸት ጊዜው አልፎብኛል ። ምንም ዐይነት ምሕረት አይደረግልኝም ። እንደ ጀመርኩ እገፋበታለሁ ። ማን ያውቃል ? ምናልባትም ድሉ የእኔው ይሆን ይሆናል ! ግሪሽካ አትሬፕዮቭስ ሞስኮን በሚገባ ገዝቶ የለ ? ”

“ መጨረሻው ታዲያ እንዴት እንደሆነ ታውቅ የለ ? በመስኮት ነበር የተወረወረው ። ጭንቅላቱ ተቆርጦ ፣ ሬሣው ተቃጥሎና ዐመዱ በመድፍ አፈሙዝ ተጠቅጥቆ በአየር ላይ አልተበተነም ? ”

“ ስማኝ እስኪ ” አለኝ ፑጋቼቭ የሆነ ስሜት ፈንቅሎት ። “ ልጅ ሆኜ አንዲት ባልቴት የነገረችኝን ታሪክ ላጫውትህ ።

“ አንድ ንስር አሞራ አንዱን ቁራ እንዲህ ሲል ጠየቀው ፡ ‘ እስቲ አጫውተኝ ፣ እያ ቁራ ፣ አንተ በምድር ላይ ለሦስት መቶ ዓመታት ለመቆየት ስትችል እኔ ለምን ነው በሠላሳ ሦስት ዓመታት ብቻ የምቀጨው ? ’ ምክንያቱም ወንድሜ አለው ቁራው ሲመልስለት ፣ ‘ አንተ የሕያዋ ንን ደም ትመጣለህ ፣ እኔ ግን የምኖረው ሬሳ እየበላሁ ነው ። ’ ንስሩ በአባባሉ አሰበበትና ‘ እስቲ እኔም ፣ አንተ እምት በላውን ለመብላት እሞክራለሁ ’ አለው ። መልካም ። ንስ ርና ቁራ አንድ ላይ ተጓዙ ። አንድ የሞተ ፈረስ አግኝተ ውም አንድ ላይ ሠፈሩበት ። ቁራው እየጐራረሰ ስለ ጣፋጭ ነቱ ሲያወራ ንሥሩ አንዴ ብቻ ቦጨቅ አድርጐለት ክንፎ ቹን እያራገበ ‘ ይቅርብኝ ወንድሜ ፣ ጥምብ እየተመገብሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሦስት መቶ ዓመታት ከምኖር ለአንዲት ቀን የአንድ ሕያው ደም ቀምሼ እግዜር እንዳሻው ያድርገኝ ' ብሎት ዐረፈው ። ይህን ተረት እንዴት ታየዋለህ ? "

" ግሩም " ነው አልኩት ። " ግን በበኩሌ ግድያን ዝርፊያን ጥምብ ከመብላት ለይቼ አላያቸውም ። "

ቺጋቼቭ በመገረም ትክ ብሎ ከማየት በቀር አልመለሰልኝም ። በየሐሳባችን ተውጠን ሁለታችንም ጭጭ አልን ። ሠረገላ ነጂው ያንጐራጉራል ። ሳቤሊችም በተቀመጠበት ያንጐላቻል ። ሠረገላው በጥርጊያ ጐዳናው ላይ ይመዘገዘጋል . . . በድንገት የያይክ መንደር ጉብታን አየሁ ፡ ከሩብ ሰዓት በኋላም ወደ ቤሎጎርስክ ምሽግ ስተት ብለን ገባን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

## ዕንለማውታዋ

የፍሬ ዛፉችን አልለመለመችም ፣
አብባ ልትፈካ ከቶ አልታደለችም ።
ውቧም ሙሽራችን የላት አባት ፣ እናት ፣
እሚያሽሞነሙናት ፣ ስም እሚመርቃት ።

### የሠርግ ዘፈን

ሠረገላው ከእዛዝዋ ቤት በረንዳ ሥር ደርሶ ቆመ ። የፑጋቼቭ መሆኑን የተገነዘቡ ሁሉ ዙሪያውን አሰፈሰፉ ። ሺቫብሪንም አለቃውን ወጥቶ ተቀበለው ። የኮዛክ ልብሱን አጥልቋል ፣ ጢሙንም አንዠርግጓል ። ደስታውንና ታማኝነቱን ለመግለጽ በታላቅ መሽቆጥቆጥ ፑጋቼቭን ከሠረገላው ላይ ደጋግፎ አወረደው ። እኔን በማየቱ ቢደነግጥም ስሜቱን እንደ ምንም ብሎ በመቆጣጠር እጁን ለሰላምታ ዘረጋልኝና ፣ " አንተም ከእኛው ዘንድ ገብተሃል ፤ አበጀህ ! " የሚሉ ቃላት ወረወረልኝ ። ቃል ሳልመልስለት ፊቴን አዞርኩበት ።

ያለፈ ዘመን ትዝታን ለመቀስቀስ በመቃብር ድንጋይ ላይ እንደ ሠፈረ ጽሑፍ እስከ ዛሬ ከግድግዳ ያልወረደውን የሟቹን አዛዥ ዲፕሎማ በዚያች በማውቃት ክፍል ውስጥ ተንጠልጥሎ ስመለከት ልቤ በሐዘን ተሰነጠቀ ። ኢቫን ኩዚሚች ባለቤቱ እሽሩሩ እያለችው ተቀምጦ ያሸልብበት



t.me/OLDBOOKSPDF

የነበረው ሶፋ ላይ ፑጋቼቭ ዐረፍ አለ ። ሽቫብሪን ቮድካ አቅርቦለትም ፉት ካለ በኋላ ወደ እኔ እያመለከተ “ ለእ ርሱም አቅርብለት እንጂ ! ” አለው ። ሽቫብሪን መጠጡን አመጣልኝ ፤ ግን አሁንም ፊቴን ጠመዘዝኩበት ። በጭን ቀት ተውጧል ። ፑጋቼቭ በእርሱ ላይ ቅሬታ እንዳለውም ጠርጥሯል ። ጌታው ፊት ሽር ጉድ እያለ በጥርጣሬ አመለ ካከት እኔንም ይቃኘኛል ። ፑጋቼቭ ስለምሽጉ ይዞታ ፤ ስለ ጠላት የሚነፍሰውን ወሬና የመሳሰሉትን ከጠያየቀው በኋላ በድንገት “ ስማ እስኪ ፤ ወንድም ፤ በቁጥጥርህ ሥር ያዋልካት ወጣት ለመሆኑ ማነች ? እስቲ አሳየኝ ” አለው።

ሽቫብሪን ዐመዱ ቡን አለ ። “ ጌታዬ ፤ በቁጥጥሬ ሥር አላዋልኳትምኮ ” በማለት መለስለት እየተንተባ ተበ ። “ በጠና ታማለች ። የምትገኘውም መኝታ ቤቷ ነው ። ” “ ውሰደኝ ! ” አለው ፑጋቼቭ ከተቀመጠበት እየተነሣ ። አሻፈረኝ ማለቱ እያዋጣውምና ፑጋቼቭን ወደ መኝታ ቤቷ መራው ። እኔም ተከተልኳቸው ።

መዳረሻው ላይ ሽቫብሪን ቆም ብሎ “ ጌታዬ ! እር ስዎ የሚጠይቁኝን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ ” አለ ፤ “ግን ወደ ባለቤቴ መኝታ ቤት ሌላ እንግዳ አያምጡብኝ።”

ክፉኛ ደነገጥሁ ። “ ምን ? አገባሃት እንዴ ? ” አል ኩት ፤ በጥርሴ ልዘለዝለው እየዳዳኝ ።

“ ሽሽሽሽሽ ! ” በማለት ፑጋቼቭ ጣልቃ ገባ ። “ይህን ማውጣጣቱ የእኔው ተግባር ነው።እና አንተ ደግሞ” ብሎ ወደ ሽቫብሪን እየተመለከተ ፤ “ አጉል ሥሌንት አታ ብዛ ። ሚስትህ ሆነች አልሆነች ይስማማታል የምለውን ባል እምመርጥላት እኔው ነኝ ። ተከተለኝ ፤ ጌታው ! ” በማለትም ድጋፉን ገለጸልኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ በሩ ስንጠጋ ሽቫብሪን እንደገና ጸጥ አለና ድምፁ እየተቆራረጠበት “ ጌታዬ ! ከፍተኛ ትኩሳት ለቅቆባት በታላቅ ሥቃይ ውስጥ ስትገኝ ሦስተኛ ቀኗ መሆኑን ይወቁልኝ ” አለ ።

“ በሩን ክፈት ” አለው ፑጋቼቭ ።

ሽቫብሪን ኪሱን ደባብሶ መክፈቻውን እንዳላመጣ አስታወቀው ። ፑጋቼቭም በሩን በርግጫ ጠለዘው ። ቁልፉ ተሰበረ ፤ በሩ ወለል አለና ጐራ አልን ።

እንደዬ መልከት አድርጌ ባለሁበት ደርቄ ቀረሁ ። ገር ጥታ ፤ መንምናና ጸጉሯ ተመሰቃቅሎ በዘባተሎ የባላገር ልብስ እንደ ተጠቀለለች ማሪያ ኢቫኖቭና ወለሉ ላይ ተኮ ራምታለች ። ከጐኗም በጉማጅ ዳቦ የተከደነ አንድ ማን ቆርቆሪያ ውሃ ተቀምጦላታል ። ገና ስታየኝ መንሰቅሰቅ ጀመረች ። ስለአዞረኝ በዚያች ወቅት የሆንኩትን አላው ቅም ።

ፑጋቼቭ ሽቫሪንን በቁጣ አመለካከት እያንገበገበው “ ጥሩ ሆስፒታል አለህ ! ” አለው ። ከዚያም ወደ ማሪያ ኢቫኖቭና ቀረብ ብሎ “ ንገሪኝ እስቲ ፤ ልጄ ፤ ባልሽ እን ዲህ እሚያሰቃይሽ ለምንድን ነው ? እንዳው ፤ ምን ብትበ ድይው ይሆን ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ ባልሽ ! ” በማለት የሰማችውን አስተጋባችለት ። “ ባሌ አይደለም ። እኔም ሚስቱ አይደለሁም ። እርሱን ከማገባ ሞቴን መርጫለሁ ። ከእርሱ እሚያላቅቀን ካጣ ሁም መሞቴ እማይቀር ነው ። ”

ፑጋቼቭ አውሬ መስሎ ሽቫብሪን ላይ እንዳተኮረ “ ብለህ ብለህ ልታታልለኝ ደፈርክ ? ” አለው ። “ አንተ ከብት ፤ ምስህ ምን እንደሆነ ታውቃለህ ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽቫብሪን ተንበረከከ . . . ጥላቻዬና ቂጣዬ በአንድነት ገነፈለብኝ ። ጨፌዋ ነኝ ባዩ ሽቫብሪን እንደ ወንበዴ እግር ሥር ወድቆ ሲንከባለል ማየቱ አቅለሸለሸኝ ። ፑጋቼቭ ቀዘቀዘ አለ ። " አሁን ምሬሃለሁ " አለው ። " ለጻ ግመኛ ጊዜ ብታስቆጣኝ ግን . . . " ወይ. ማሪያ ኢቫኖቭና ም ዘወር ብሎ በርኅራኄ ድምፅ " ነይ ውጪ ፣ ልጄ ፣ እኔ ንጉሥሽ ነጻነትሽን አቀዳጅሻለሁ " አላት ።

ማሪያ ኢቫኖቭና መልከት አደረገችውና ከወላጆቿ ገዳይ ጋር ግምባር ለግምባር መፋጠጧን ተገነዘበች ። ፊቷን በእጆቿ ሸፍና አዞራትና የኋልዮሽ ተዘረረች ። ላን ጣት ስንደረደር ፖላሻ ሮጣ ገብታ ትንከባከባት ጀመረ ። ሽቫብሪንና እኔ እየተከተልነው ፑጋቼቭም ከክፍሏ ወጣ ።

" ታዲያስ ጌታው ? " አለኝ ፑጋቼቭ እየሣቀ ። " ቆንጂትህን ነጻ አወጣንልህ ። ከእንግዲህ ቄስ አስጠርተን ጋብቻችሁ እንዲፈጸምላችሁ ብናደርግ ምን ይመስልሃል ? እኔ የውል አባትህ እሆናለሁ ፣ ሽቫብሪንም ሚዜህ ይሆናል ። "

የፈራሁት ደረሰ ። የፑጋቼቭ አባባል ሽቫብሪንን በንዴት አንዘፈዘፈው ። " ጌታዬ ! " አለው እየተርበተበተ ። " ጥፋተኛ ነኝ ። ዋሽቼዎታለሁ ። ግራኔብም እታሎዎታል ። ይህች ወጣት ይህን ምሽግ በያዝንበት ወቅት የተሰቀለው የኢቫን ሚሮኖቭ ልጅ ናትኮ ! "

ፑጋቼቭ እሳት የለበሱትን ዐይኖቹን ተከለብኝና " ምን ? " ሲል አፈጠጠብኝ ።

" ሽቫብሪን የሚለው ትክክል ነው " በማለት መለስኩለት ትክ ብዬ እያየሁት ።

" ይህን አልነገርከኝማ ! " አለኝ ፑጋቼቭ ፊቱን ጥቁርቁር አድርጎ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እርስዎው ይፍረዱኝ ! ” አልኩት ፡ “ የሚኖሮብ ልጅ መኖሯን በዚያን ወቅት በሰዎችዎ ፊት ብገልጽልዎ ኖሮ እዚያው በቁሟ ይዘለዝሏት ነበር ። ምንም መዳኛ አል ነበራትም ። ”

“ ልክ ነህ ” አለኝ ፑጋቼብ ። “ እነዚያ ሰካራሞች አያተርፏትም ነበር ። የቄሱ ሚስት መዋሸቷም አግባብ አለው ። ”

“ ይስሙኝ ” አልኩት ቀጠል በማድረግ ወደ እኔ እን ዳዘነበልልኝ ተገንዝቤ ፡ “ ምን ብዬ እንደምጠራዎ ግራ ይገ ባኛ ል ። ስለውለታዎ ግን ፡ ሕይወቴን በደስታ ልሠዋልዎ ዝግጁ ነኝ ። ብቻ ፡ ክብሬን የሚያጐድፍብኝና ሕሊናዬን የሚቆጠቁጠኝ ትዕዛዝ እንዳይሰጡኝ ። እለኝታዬ ነዎት ፡ እንደ ጀመሩልን መጨረሻችንንም ያሳምሩልንና ይህች ምስ ኪን ዕጓለማውታና እኔ እግዚአብሔር ወደሚመራን እን ሔዳለን ። ከኃጢአትዎ እንዲያነጻዎ ዕድሜያችንን በሙሉ ጌታን እንለምንልዎታለን . . . ”

የፑጋቼብ ቁጡነት ገነፈለ ። “ እንዳሻችሁ ! ” አለኝ። “ ሰውን መስቀል ከፈለግሁ እንጠለጥላለሁ ፡ ምሕረት ማድረግ ካሰኘኝም እምራለሁ ። አቋሜ ይኸው ነው ። ውቢቷን ፍቅረኛህን ውሰዳት ፡ ከፈለግህበት ቦታ አድር ሳት ። የእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋም አይለያችሁ ! ”

ይህን ብሎኝ ወደ ሽቫብሪን በመዞር በቁጥጥር ሥር በዋሉት ምሽጐችና ከተሞች በሙሉ በነጻነት እንድጓዝ የሚያስችለኝን የይለፍ ፈቃድ እንዲያስወጣልኝ አዘዘው ። ሽቫብሪን በድንጋጤ ክው አለ ። ፑጋቼብ ምሽጉን ለመጐ ብኘት ሲነሣም ተከተለው ። እኔም ለጉዞዬ ልዘጋጅ ወደ ኋላ ቀረሁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ማሪያ ኢቫኖቭና ክፍል በርሬ ብደርስ በሩ ተዘ ግቷል ። አንኳኳሁ ። " ማነው ? " አለችኝ ፖላሻ " እኔው መሆኔን ነገርኳት ። የማሪያ ኢቫኖቭናም ጣፋጭ ድምፅ በሩን ዐልፎ በጆሮዬ ተንቆረቆረልኝ ። " እንዴ ፣ ፒዮትር አንድሬቭች ። ልብሴን እየቀየርኩ ነው ። ወደ አኩሊና ፖምፊሎቭና ቤት ሒደህ ጠብቀኝ ። አሁን መጣሁ ። "

በትእዛዟ መሠረት ወደ አባ ጂራሲም ቤት አመራሁ ። እነርሱም እየሮጡ መጥተው ተቀበሉኝ ። መምጣቴን ሳቬሊች ቀደም አድርጎ ነግሯቸው ነበር ። " እንዴት ነህ ፣ ፒዮትር አንድሬቭች ? " አለችኝ ሚስቲቱ ። " የእግዜር ፈቃዱ ሆኖ ይኸው በዐይኔ — ሥጋ ለመገናኘት በቃን ። ሳናነሣህ የዋልንበት ቀን የለም ። ማሪያ ኢቫኖቭናም የቁም ሥቃይ ዋን ስታይ ከረመች ። ጌታዬ ፣ ከዙጋቼቭ ጋር እንዲህ ስምም ለመሆን እንዴት ቻላችሁ ? ያን ወሮበላ ለዚህ እንኳ እና መስግነው እንጂ ! "

" አንቺ ደግሞ እንዳው ሁሉን ልወቅ አትበይ ። ቅል ብልብ ምላስ በጐ ነገር አያመጣም ። ጐራ በል እባክህ ፣ ፒዮትር አንድሬቭች ! ከተለያየን ብዙ ጊዜ ሆነንኮ ! " አለ አባ ጂራሲም ጣልቃ ገብቶ ።

ሚስቲቱ ያለዕረፍት እያነበነበች ያላትን ምግብ አቀ ራረበችልኝ ። ሽቫብሪን ማሪያ ኢቫኖቭናን እንዲሰጡት እንዴት እንዳስጨነቃቸው ፣ ማሪያ ኢቫኖቭናም ስትሰና በታቸው እንዴት እንዳነባችና ግን በፖላሻ በኩል ፣ ፖላሻ በጣም ብልህ ልጅ ከመሆኗ የተነሣ ሰውዬውን እንደ እን ዝርት ታሽከረክረዋለችና ፣ እንዴት ሊገናኙ እንደቻሉ . . . ነገረችኝ ። የእኔንም ታሪክ ባጭሩ አወጋሁዋቸው ። ያታለሉት መሆኑን ፑጋቼቭ እንዳወቀባቸው ስነግራቸው ባልና ሚስቱ በድንጋጤ አማተቡ ። " እግዜር ይቅር ይበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለን ! ” አለች አኩሉና ፖምፊሎቭና ። “ ፈጣሪ ማዕበሉን ያስታግሥልን ። ያ መሠሪ ሽቫብሪን ሥርቶልናላ ! ” በዚያች ወቅት በሩ ተንኳኳና ማሪያ ኢቫኖቭና ፊገግታ ተላብሳ ጉራ አለች ። ያን የባላገር ድሪቶዋን አውልቃ ጥላ ፣ ባትሽቀረቀርም እንደ ቀድሞዋ ለባብሳለች ።

ለረጅም ጊዜ እጅዋን ግጥም አድርጌ ከመያዝ በቀር አንዲት ቃል መናገር ተሳነኝ ። ልቦቻችን ግን ፣ በቃላት ተሞልተዋል ። አስተናጋጆቻችንም ምስጢራችንን ላለማሰማት ወስነው ክፍሉን ለቅቀውልን ወጡና ብቻችንን ቀረን ። የየልባችንን ሐሳብ ተለዋወጥን ። ምሽጋችን በጠላት እጅ ከወደቀበት ጊዜ አንሥቶ የገጠማትን አሠቃቂ ሁኔታ ፣ ያ ውሻ ሽቫብሪን ያደረሰባትን ፍዳ ሁሉ አንድ በአንድ ነ ጫወተችኝ ። ያሳለፍነውንም የደስታ ዘመን አስተውሰን . . . ተላቅሰን . . . በመጨረሻም ዕቅዴን አዋየኋት ” በሽቫብሪን ጥላ ሥር ፣ በጉጋቼቭ ባለሥልጣንነት በዚያ ምሽግ ውስጥ እንደማልተዋት ገለጽኩላት ። በከበባው ሳቢያ እልቂት ወደሚያንዣብብባት ኦሬንበርግም እንደማልወስዳት ነገርኳት ። በምድር ላይ ምንም ዘመድ የላትም ነበርና ወደ ወላጆቼ እንድትሔድ መከርኋት ። በመጀመሪያ ላይ ተጠራጠረች ። ምክንያቱም አባቴ ስለእርሷ ያለውን ጥላቻ ታውቀዋለች ። ስመጥር ጦረኛ ለነበረና ሕይወቱን ለሀገሩ ለሰዋ ዕውቅ ሰው ልጅ አጋር ለመሆን አባቴ ይህን አጋጣሚ እንደሚጠቀምበት ጠቁሜያት ፍርሃቷን ላስወግድላት ሞከርኩ ። በመጨረሻም “ውዷ ማሪያ ኢቫኖቭና ሆይ ” አልኳት ፣ “ ባለቤቴ እንድትሆኚ እመኛለሁ ። እንግዳ አጋጣሚዎች አቀራርበውናል ። ካሁን ወዲያ ምንም ነገር ሊያራርቀን አይችልም ። ” ማሪያ ኢቫኖቭና መሽኮርመምና የእምቢታ ምልክት ሳታሳየኝ በቀሞና አዳመጠችኝ ። ዕድሏ ከእኔው ጋር እንደ ተጣመረ ገብ


t.me/OLDBOOKSPDF

ቷታል ። ሆኖም ልንጋባ የምንችለው ወላጆቹ ቢፈቅዱልን ብቻ መሆኑን በድጋሚ ገለጸችልኝ ። ከዚህ በላይ ልገፋፋት አልፈለግሁም ። ከልባዊ ፍቅር በመነጨ ስሜት ተሳሳምንና ጉዳያችንን በዚሁ ደመደምነው ።

በአንድ ሰዓት ውስጥ የፑጋቼቭ ፈርማ የተሞነጫጨረበት የይለፍ ፈቃድ መጣልኝ ። ፑጋቼቭም ዘንድ እንድቀርብ ተነገረኝ ። እርሱም ራሱ ለጉዞ ሲዘጋጅ አገኘሁት ። ለእኔ ካልሆነ በስተቀር ለሌላው ፍጹም አረመኔ የሆነውን ይህን ሰው ስሰናበት የወረረኝን ስሜት ለመግለጽ ያስቸግረኛል ። ለምን እውነቱን አላወጣም ? በዚያች ቅጽበት በጣም አዘንኩለት ። ከሚያጅቡት ወንበዴዎች መሐል ቶሎ ብዬ አውጥቼው ከሚጠብቀው የስቅላት ቅጣት ላድነው ከልብ ተመኘሁለት ። የሽቫብሪንንና የሌሎች በዙሪያው የተገረገሩ ሰዎች መኖር በልቤ ያመቅሁትን ስሜቴን በቃላት ከመግለጽ አገደኝ ።

በወዳጅነት ተለያየን ። ፑጋቼቭ አኩሊና ፓምፊሎቭናን ከተሰበሰበው ሕዝብ መሐል ነጥሎ በዐይኑ ጠቅሷት " ሠራሽልኝ አይደል ? " በሚል ስሜት ጣቱን አወዛወዘባት ። ከዚያም ወደ ሠረገላው ገብቶ ነጂውን ወደ ቢርዳ እንዲወስደው አዘዘው ። ፈረሶቹ ሲንቀሳቀሱ ራሱን ብቅ አድርጎ " ደህና ሁን ፤ ጌታው ! አንድ ቀን እንደገና እንገናኝ ይሆናል ! " አለኝ በኋላ ድምፅ ። በእርግጥም ለመገናኘት በቅተናል ፤ ግን በምን ዐይነት አጋጣሚ !

ፑጋብቼቭ ነጉደ ። ከፊት ለፊቴ የተንጣለለውን መስክ አቋርጦ እስከሚሰወር ሠረገላውን በዐይኖቼ ተከተልኩ ። ሕዝቡ ተበተነ ። ሽቫብሪንም ተሰወረ ። እኔም ወደ ቄሱ ቤት ተመለስኩ ። የጉዞ ዝግጅታችን ስለ ተጠናቀቀ ልዘገይ አልፈለግሁም ። ዕቃዎቻችን በአዛገፑ አሮጌ ሠረገላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ተጫኑ ። ነጂው ፈረሶቹን ለንጉመ ። ማሪያ ኢቫኖቭናም ከቤተክርስቲያኑ ጓር የተቀበሩትን የወላጆቿን መቃብር ለመሰናበት ሔደች። አብሬያት እንድሔድ ጠይቂያት ነበር፣ ግን አከላከለችኝ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እያነባች ተመ ለሰች ። ሠረገላው ተዘጋጅቷል ። አባ ጄራዚምና ባለቤቱ በረንዳቸው ላይ ብቅ አሉ ። ሠረገላ ውስጥ የተቀመጥነው ሦስት ነበርን — ማሪያ ኢቫኖቭና ፣ ፖላሽና እኔ ። ሳቬሊች የተጫነው ከላይ ነው ።

“ ደህና ሰንብች ፣ ማሪያ ኢቫኖቭና ፣ ልጄ ። ደህና ሁን ፈጥኖ ደራሹ ፒዮትር እንዲረች ! ” አለችን ሩኅሩኅዋ የቄሱ ሚስት ፣ “ መልካም ጉዞ ፣ እግዜር ጥላ ከለላ ይሁና ችሁ ! ” ጉዞ ጀመርን ። ሽቫብሪን አዛዡ መስኮት ላይ ቆሞ አየሁት ። ንዴት እንዳከማተረው ገጽታው ይመሰክራል ። ‘ በወደቀ እንጨት ላይ ምሳር ይበዛበታል ’ ከሚያሰኝ አድ ራጐት ለመራቅ ስል ፊቴን ዘወር አደረግሁ ። ከዚያም በዋ ናው በር በኩል መስስ ብለን በመውጣት የቤሉጉርስክን ምሽግ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበትን ።


t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## መያዝ

" እንግዲህ ጌታዬ — መቆጣት አያሻም ፣
ፍርዴን ለመሰንዘር ወደ ኋላ አልልም ፣
ተግባሬ ነውና አአወላውልም ። "
" እኔ ለመቀበል ተዘጋጅቻለሁ ፣

ግን — የልቤን ለመግለጽ ፈቃድ ለምናለሁ ፣
እንደማይነፍጉኝም እተማመናለሁ ። "

የጠዋቱ ገጽታዋ እንዲያ ከዘገነነኝና ከምወዳት ፍቅረኛዬ ጋር ሳይታሰብ ለመተቃቀፍ ያበቃንን ሁኔታዎች ሳስብ ባዶ ሕልም ስለሚመስለኝ ዕድሌን ላምነው አልቻልኩም ። ማሪያ ኢቫኖቭናም ሐሳብዋን ለመቋጨት ግራ እንደ ተጋባች ሁሉ ፊዝዛ እንደ እኔን ፣ አንዴ መንገድ መንገድዋን ትመለከታለች ። ሁለታችንም በዝምታ ተዋጥን ። ልባችን ቀለጠ ። ጊዜውም ሳይታወቀን በረረና ከሁለት ሰዓታት በኋላ በፑጋቼቭ መዳፍ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ምሽግ ደረስን ። ፈረሶቹም ተለወጡልን ። የጠቅላይ አዛዥነቱን ሹመት ከፑጋቼቭ የተቀበለው አንድ ጢማም ኮዛክ ፣ ይህን የነገረን ወሬኛው ሠረገላ ነጂያችን ምስጋና ይድረሰውና የሞቀ አቀባበል ያደረገልንና ፈረሶቻችንን በፍጥነት የለወጠልን ለካስ ከፍተኛ ባለሟል መስዬው ኖሯል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዞዋቸችንን ቀጠልን ። መሽትሽት ሲልም ፣ ያ የበፈቱ ምሽግ አዛዥ እንደ ጠቆመን ፣ ከፑጋቼቭ ጦር ጋር ለመቀላቀል የሚዘጋጅ እንድ ጠንካራ ባታልዮን ከሠፈረበት ሥፍራ ደረስን ። ቃፊሮቹም አስቆሙን ። “ ማነው ? ” ለሚለው ጥያቄያቸው ሠረገላ ነጂው “ የንጉሡ ባለሟልና ባለቤቱ ! ” የሚል መልስ ሰጣቸው ። ከመቅጽበት ከበቡንና የስድብ መዓት አወረዱብን ። “ውጣ ፣ የሰይጣን ባለሟል !” ሲል እምባረቀብን እንድ ጢማም መጋቢ ሃምሳ አለቃ ። “ እንተም ሆንክ ባለቤትህ ፣ ምላችሁን ታገኛላችሁ ! ”

ከሠረገላው ዱብ አልኩና ወደ አዛዣቸው እንዲወስዱኝ ጠየቅሁ ። መኰንን መሆኔን ሲያዩ ወታደሮቹ ጸጥ አሉ። መጋቢ ሃምሳ አለቃውም ወደ መቶ አለቃው መራኝ ። “ የንግሥቲቷ ባለሟሎች ናቸውና ፣ ወቸጉድ ! ከእሳቱ ወደ ረመጡ ! አይ እንተ ፈጣሪ ! መጨረሻችን ምን ይሆን ? ” እያለ ሳቢሊች ከጉኔ አልተለየኝም ። ሠረገላውም በዝግታ ይከተለናል ።

በአምስት ደቂቃ ውስጥ ከአንዲት ደማቅ ጉጆ አደረስን ። መጋቢ ሃምሳ አለቃው ከዘብ ጋር ትቶን ለማስታወቅ ገባ ። ወዲያው ተመልሶም ከቡርነታቸው ሊቀበሉኝ ጊዜ የሌላቸው መሆኑንና እኔን ወደ እስር ቤት ፣ ባለቤቴን ደግሞ ወደ እርሳቸው እንዲያደርስ የታዘዘ መሆኑን አስረዳን ።

“ ምን ማለታቸው ነው ? ” ስል በቁጣ ጮኽኩ ። “ አብደዋል እንዴ ? ”

“ አላውቅም ፣ ጌታዬ ” ሲል መለሰልኝ ። “ የማውቀው ከቡርነታቸው ከቡርነትዎን ወደ እስር ቤት እንድወስድና ክብርት ባለቤትዎን ወደ ከቡርነታቸው እንዳደርስ መታዘዜን ብቻ ነው ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ በረንዳው ተንደረደርኩ ። ዘቦቹም ሊመልሱኝ ስላልሞከሩ ፡ እንደሮጥኩ አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ካርታ ከሚጫወቱበት ክፍል ዘው አልኩ ። አጫዋ ቾቹውም መቶ አለቃው ነበር ። ግርም ያለኝ በሲምብሪስክ ሆቴል ገንዘቤን ሙልጭ አድርጐ የበላኝ ያ ኢቫን ኢቫኖ ቪች ዙሪን የሚባለው ሰው መሆኑ ነው ።

" እንዴት ይሆናል ? " አልኩ በጩኸት ። " አንተ ነህ እንዴ ፡ ኢቫን ኢቫኒች ? "

" እንዴ ፡ ፒዮትር አንድሬቾ ! ምን እግር ጣለህ እባ ክህ ? ከወዴት ነው የምትመጣው ? ሰላም ፡ ወንድሜ ! ጨብጠኝ እንጂ ! "

" በቅድሚያ ማረፊያ ቦታ ብታሳየኝ ? "

" ማረፊያ ቦታ ? ከእኔው ዘንድ ቆይ ። "

" አልችልም ፡ ብቻዬን አይደለሁምኮ ! "

" ታዲያ ምናለበት ! ለሁለታችሁም ይበቃል ። "

" ጓደኛዬ እንዲት እመቤት ናት ። "

" እመቤት ? ከየት ቀለብካት ? እህሳ ወንድም ! "

ካለኝ በኋላ ፉጨቱን በመልቀቅ የተቀሩትንም አሣቀብኝ ። እኔም ግር አለኝ ።

" በል እስቲ " በማለት ቀጠለ ዙሪን " ይሁና ። ክፍል ይሰጥሃል ። ግን አዝናለሁ . . . እንደ ቀድሞው ሞቅ ባለ ግብዣ ላይ ብንጫዋወት መልካም ነበር ። ግን . . . የፑ ጋቼቭን ወዳጅ ለምን አታመጣትም ? እስቲ ጋሪ ብጤ ናት እንዴ ? ' አትፍሪ ' በላት ፡ ' ሰውዬው ጨዋ ነው ፡ አይጐ ዳትም ። ' ግትር ከሆነችም አንድ ጥሩ ጥፊ አቅምሳት ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ምን ማለትህ ነው ? ” አልኩት ። “ የቹጋቼቭ ወዳጅ ? የሚቺ ፡ የአዛዡ ሚሮኖቭ ልጅ ናትኮ ! ከእስር ቤት አውጥቻት ወላጆቹ ዘንድ ላኖራት እየሸኘኋት ነው ” “ ምን ? አሁን የነገሩኝ ስለእንትት መምጣት ኖሯል ! ይገር ማል ! ይገርማል ምን ጉድ ነው ? ”

“ ሁሉንም በኋላ እሚውትሃለሁ ። በእግዚአብሔር ቶሎ ብለህ ልጅቷ እሮይታ የምታገኝበትን ሁኔታ ፍጠ ርልኝ ። ዘቦችህ ክፁ አድርገዋታልኮ ! ”

ዙሪን ወዲያው ትእዛዝ አስተላለፈ ። ራሱ ሔዶም ስለ ተፈጠረው አለመግባባት ማሪያ ኢቫኖቭናን ይቅርታ ከመጠየቁም በላይ ፡ በከተማው ምርጥ ከተባሉት ማረፊያ ቤቶች አንዱ እንዲያዝላት መጋቢ የአምላ አለቃውን አዘ ዘው ። እኔን ከእርሱው ቤት እንዳርፍ አደረገኝ ።

ከእራት በኋላ ብቻችንን ስንሆን ያጋጠመኝን ሁሉ በዝርዝር አወሳሁት ። ጆሮዎቹን ተክሎ አዳመጠኝ ። ታሪ ኬን ስደመድምለት ራሱን ነቅንቆ ፡ “ የነገርከኝን ሁሉ ተቀ ብዬዋለሁ ወንድም ፤ ግን የማልወድልህ አንድ ነገር አለ። ለጋብቻ የሚያከንፍህ ምንድን ነው ? ከልቤ መሆኑን እምልልሃለሁ ። ይግሞም እመነኝ ፡ ጋብቻ ጣጣ ነው ። የሚ ስትና የማቲዎች ጫጫታ ምን ሊበጅህ ? እርሳው ! አድ ምጠኝ ፡ ከዚህች ልጅ ጋር ያለህን ግንኙነት አቁም ። የሲ ምብርስክን ጉዳና አጽድቼዋለሁና የሚያስፈራ ነገር ስለ ሌለ ነገውን እርሷን ብቻዋን ወደ ወላጆችህ ቤት ልከህ አንተ ከእኔው ዘንድ ክረም ። ወደ እሬንበርግ መመለስም አይኖርብህም ። እንደገና በወንበዴዎቹ እጅ ብትወድቅ ለድጋሚ ጊዜ ማምለጥህን እንጃ ። ያሳበደህ ፍቅርም ይበር ድልህና እሮይታ ታገኛለህ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሉ በሙሉ ባልስማማበትም ፣ በንግሥቲቷ ጦር ሠፈዊት ውስጥ ያለብኝ ግዳጅና የተሰጠኝ ማዕረግ ስለከበ ዱኝ የዙሪንን ምክር በመቀበል ማሪያ ኢቫኖቭናን ለመሸ ኘትና እኔ በዚህ ምድብ ውስጥ መቆየት ወሰንኩ ።

ሳቪሊች ወደ መኝታ ክፍሌ ብቅ አለ ። ሲነጋ ከማ ሪያ ኢቫኖቭና ጋር እንዲሔድ ነገርኩት ። በመጀመሪያ ተቃ ወመኝ ። " ምን አልክ ፣ ጌታዬ ? ብቻህን ልተውህ ? ማን ይረዳሃል ? ወላጆችህስ ምን ይሉኛል ? "

ግትርነቱን ስለማውቅ በፍቅርና በማባበል ለማሳመን አሰብኩ ። " ሳቪሊች ፣ የምወድህ ጓዴ ! " አልኩት ። " ጥያቄዬን ተቀበለኝ ፣ እባክህ ! እዚህ አገልጋይ አያስፈ ልገኝምና አንተው ማሪያ ኢቫኖቭናን ካላደረስክልኝ ሰላም አላገኝም ። እንዲያ በማድረግህ ደግሞ እኔኑ ማገልገልህ ነው ፤ ምክንያቱም ሁኔታዎች እንደ ተመቻቹልኝ ላገባት ወስኛለሁ ። "

ይህን ሲሰማ ሳቪሊች እጆቹን በድንጋጤ እያወራጨ ፣ " ልታገባት ! " ቢል አምባረቀብኝ ። " ልታገባት ታስባ ለህ ! እንዴው አባትህ ምን ይሉ ? እናትህስ ምን ይላሉ ? "

" ይስማማሉ ፣ በእርግጥ ይስማማሉ " በማለት ላሳ ምነው ሞከርኩ ። የማሪያ ኢቫኖቭናን ምንነት ሲገነዘቡ ጋብቻችንን ያጸድቁልናል ። እምነቴን በንተው ላይ ጥያ ለሁ ። እናቴና አባቴ ያምኑሃልና አንተም በሽምግልና ትረ ዳኛለህ ፣ አትረዳኝም ? "

ሽማግሌው ልቡ ተነካ ። " አዬ ፣ ፒዮትር አንድሬች ጌታዬ ! " አለ ። "ስለ ጋብቻ ለማሰብ እንኳ ገና ነህ ። በእ ርግጥ ማሪያ ኢቫኖቭና ሽጋ ልጅ ናትና ይህን ዕድላችሁን መቅጨት ኃጢአት ነው ። እንግዲህ ይሁና ፤ ይህችን ቆንጆ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላድርሳትና ለወላጆችህም ስለ ጋብቻችሁ እንዲያስቡበት በትሕትና ልገልጽላቸዋ ። ”

ሳቪሊችን አመስግኜ ወደ ዙሪን መኝታ ክፍል ሔድኩ ። ከመቅበጥበጤ የተነሣ ብዙ አወራለሁ ። በመጀመሪያ ላይ ዙሪን በጥሞና ያዳምጠኝ ነበር ። ግን ነገሩ ሁሉ የማ ይጨበጥ ስለ ሆነበት ፣ መተኛቱን መርጦ ወዲያውኑ ማንኳ ረፍ ጀመረ ። እኔም መዘላበዴን አቁሜ እርእያኑቱን ተከ ተልኩ ።

ጠዋት በማለዳ ማሪያ ኢቫኖቭና ዘንድ ሔጄ ዕቅዱን አዋየሁዋት ። መልካም ሆኖ አግኝታው ወዲያውኑ ተስማ ማችልኝ ። የዙሪን ወታደሮችም የዚያኑ ዕለት ከተማዋን ይለቅቁ ነበር ። መዘግየትም አልተቻለኝም ። ሳቪሊች እን ደሚንከባከባት ነግሬያትና ለወላጆቼ የምትወስድላቸውን ደብዳቤ አስጨብጫት ማሪያ ኢቫኖቭናን በዚያው ተሰና በትኳት ። አለቀሰች ። “ ደህና ሁን ፣ ፒዮትር አንድሬች” አለችኝ በኩሰሰ ድምፅ ። “ እንደገና አንተን ማየት አለ ማየቴን የሚያውቅልኝ እግዚአብሔር ብቻ ነው ። ግን እስከ ሕይወቴ መጨረሻ አልረሳህም ። እስከ ዕለተ ሞቴ በልቤ ውስጥ ትኖራለህ ። ” አንዲት ቃል ለመሰንዘር አልቻልኩም ። ሰዎች ከብበውን ስለነበር ፣ ስሜቴን በእነ ርሱ መሐል መዘክዘኬን አልወደድኩም ። በመጨረሻም ተጓዘች ። እኔም በትካዜና በዝምታ ተውጬ ወደ ዙሪን ዘንድ ተመለስኩ ። እርሱ ሊያጽናናኝ ተጣጣረ ። እኔም እርሷን የምረሳበትን መንገድ ሁሉ ለማግኘት ሞከርኩ ። ቀኑ እንደ ምንም ዐለፈ ። ሌቱ ደግሞ ስለ ዘመቻው ጉዞዋ ችን ስንነጋገር ነጋ ።

የካቲት መግባደጃ ላይ ነው ። ወታደራዊ እንቅስቃ ሴን የሚገታው የክረምቱ ወቅት ስለ ተገባደደ ፣ ጀነራሎቻ ችን ኃይላቸውን በማስተባበር የማጥቃት እርምጃ ለመው



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰድ የሚዘጋጁበት ወቅት ነበር ። ፑጋቼቭ አሬንበርግን ከብቦ እንዳስጨነቃት ቢሆንም፣ መደበኛ ወታደሮች እየተሰ ባሰቡ ወደ ምሽጉ በማምራት ወንበዴዎቹን በየአቅጣጫው እያጠቁ ነው ። ወታደሮቻችን ብቅ ሲሉ የየመንደሩ ነዋሪ ዎች እግሬ አውጭኝ ይላሉ ፤ ወሮበሎቹም ይፈረጥጣሉ ። የድል አርምጃችን ፈጣንና የማያዳግም እየሆነ መጣ ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ልዑል ጐሊስቲን ፑጋቼቭን ከታቲስቼ ምሽግ አባርሮ፣ የተከታዮቹንም ምሽግ ከሰበረና ኃይላቸውን ከበታተነ በኋላ ፤ አሬንበርግንም ነጻ በማውጣቱ የወንበዴው ቡድን ከፋኛ ተዳከመ ። በዚያን ወቅት ዙሪ ንም ወደ አንድ አቅጣጫ አዝምቶን ከመድረሳችን በፊት ወንበዴዎቹ ስለ ፈረጠጡ እንዳቸውን ለማየት እንኳ አል በቃንም ። የጸደይ ዝናብ በአንዲት መንደር አቆየን ። ወን ዞች ሞሉ ፤ መንገዶችም ተዘጉብን ። ከለየላቸው ወሮበ ሎችና አውሬዎች ጋር የተያያዝነው ይህ እጉል ጦርነት ብአስቸኳይ የሚደመደምበትን ጊዜ እያሰላሰልን ራሳችንን በማጽናናት ጊዜያችንን እንደ ምንም ገፋነው ።

ፑጋቼቭ ግን አልተያዘም ። ወደ ሳይቢርያ የብረት ማዕድናት በሰውና በመሣሪያ ከተጠናከረ በኋላ፣ እኩይ ተግ ባራቱን ቀጠለ ። እንደገናም ድል ማግኘቱ ተወራለት ። በሳ ይቤሪያ ውስጥ የሚገኙትን የመደበኛ ጦር ምሽጐች ድም ጥማጣቸውን እንዳጠፋ ሰማን ። ወዲያውኑ ደግሞ ካዛንን ጨብጦ ወደ ሞስኮ የማምራቱ ዜና የወንበዴው ኃይል ተኮ ላሽቷል በሚል ሰበብ እንቅልፋቸውን ሲለጥጡ የነበሩትን መኮንኖች አባነናቸው ። ዙሪንም ወደ ቮልጋ እንዲዘምት ታዘዘ ።

ስለ ዘመቻችንና ስለ ጦርነቱ ፍጻሜ በዝርዝር አላወሳ ችሁም ። ሕዝቡ በሥቃይ ማለቁን መጥቀሱ ይበቃኛል ። ብወንበዴዎቹ ዝርፊያ አናቸውን የቀሩትን መንደሮች ስናቋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርጥ እኛም ያለ የሌለ ስንቃቸውን ከእነዚያ ያልታደሉ ሰዎች እንነጥቅ ነበር ። የአስተዳደር ሥርዓት መላቅጡ ጠፍቶ ባለመሬቶች ሳይቀሩ ጫካ ገብተዋል ። በየሥፍራው የወረበሎች መንጋ እየመሸገ የጠብ እሳት ይለኩሳል ፤ የመደበኛ ወታደሩ ክፍልም እንዳሻው ይቀጣል ፤ ይምራል ። በአጠቃላይ ፤ በጦርነት እሳት የሚንቀለቀለው ያ ግዛት በእጅጉ የሚያስጠላ ነበር ። እግዜር ከእንደዚያ የመሰለ መላቅጡ የጠፋ ትርዒት ይሰውራችሁ !

በኢቫን ኢቫኖቪች ሚኤልስን እየተባረረ ፑጋቼቭ ይሮጣል ። በየት አቅጣጫ እንደ ሸመጠጠም እንሰማለን ። በመጨረሻም ያ አስመሳይ መያዙ ለዙሪን መልእክት ደረሰዉና ጦርነቱን እንድናቆም ታዘዝን ። ውጊያው ተፈጸመ። ወደ ወላጆቼ ቤት የመመለስ ምኞቴም ሠመረልኝ ። ከእቅፋቸው የመግባቴና የማሪያ ኢቫኖቭናን ወይን የማየት ጉጉቴ አስፈነደቀኝ። እንደ ሕፃን ዘለልኩ። ዙሪን ትከሻውን ከፍና ዝቅ እያደረገብኝና እየተንከተከተ፣ “መጨረሻህ እያምረኝም ! ካልክ አግባና ዕረፈው !” አለኝ ።

ግን የሆነ ስሜት ደስታዬን በረዘብኝ ። በንጹሐን ደም የታጠበውን የፑጋቼቭን አሟሟት ከጭንቅላቴ ማውጣት አቃተኝ ። ‘ ለምን ደረትክን ለሳንጃ ፣ ግንባርክን ለጥይት ሆን ብለህ አልሰጠህም ? ከዚያ ለራስህ የበለጠ የሚበጅህ ምን ነገር አለ ? ’ አልኩት በሆዴ ። ከዚያ የተሻለ ምርጫ አላገኘሁለትም ። በሕይወቴ ውስጥ በገጠሙኝ ቀውጢ ጊዜያት የደረሰልኝንና ዕጮኛዬን ከዚያ ሺቫብሪን ከሚባል መናጢ እጅ ፈልቅቆ ያወጣልኝን ፑጋቼቭን ከአእምሮዬ ከቶ ልፍቀው አልቻልም ።

ዙሪን በፈቃድ አሰናበተኝ ። በጥቂት ቀናት ውስጥ በቤተሰቤ መሐል ልገኝ፣ የማፈቅራትን ማሪያ ኢቫኖቭናንም ላያት ነው . . . ግን በድንገት መብረቅ ወረደብኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በጉዞዬ ቀን ፤ እንደውም መንገዴን ለመጀመር በተነ ሣሁበት ሰዓት ፤ ዙሪን በጣም ተረብሾና ብጣሽ ወረቀት እንጠልጥሎ ከጎጆዬ ዘው አለብኝ ። ልቤን ውጋት ሰቀ ዘው ። ለምን እንደሁ እንጃ ፍርሃት ተሰማኝ ። የተመደበ ልኝን ረዳቴን አስወጥቶ የሚነግረኝ እንድ መልእክት እን ዳለው አስታወቀኝ ። "ምን ይሆን ?" ስል ጠየቅሁት በድ ንጋጤ ። "አያስደስትህ ይሆናል" አለኝ ወረቀቱን እያስ ጨበጠኝ ። "አሁን ነው የተላከልኝ ፣ አንብበው" ብሎኝ ወረቀቱን አስጨበጠኝ ። ማንበብ ጀመርኩ ፤ ወታደራዊ ባለሥልጣኖች በተገኘሁበት ሥፍራ በቁጥጥር ሥር እንዲያውሉኝና የጕጋቼቭን ጉዳይ ወደሚመረምረው ኮሚሽን ፣ ወደ ካዛን ፣ በጥበቃ እንዲልኩኝ የሚያስጠነቅቅ ምስጢራዊ ትእዛዝ ነበር ።

ወረቀቱ ከእጄ አምልጦኝ ሊወድቅ ምንም ያህል አል ቀረውም ። "ምንም ማድረግ አይቻልም" አለኝ ዙሪን። "ይህን ትእዛዝ የማስፈጸም ኃላፊነት አለብኝ ። ከጕጋቼቭ ጋር ያደረግኸው የወዳጅነት ሽርሽር ፣ በዚህም ሆነ በዚያ ፣ መንግሥት ጆሮ ሳይደርስ አልቀረም ። ሆኖም ኮሚሽኑን አሳምነህ መጨረሻህ እንደማይከፋ እምነቴ ነው ። አይ ዞህ ! ጉዞህን አሁኑኑ ጀምር ።" ተረጋጋሁ ። የሚጠብቀ ኝንም ብያኔ አልፈራሁትም ። ግን እንዲያ የትንንሁለት ቀን መዘግየቱ ፣ ምናልባትም በወራት ፣ በእጅጉ አስመረረኝ ። ጋሪው ተዘጋጀ ። ዙሪንም ተሰናበተኝ ። ሻምላቸውን በመ ዘዙ ሁለት ወታደሮች ታጅቤ ጉዞዬን ተያያዝኩት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## ክ ስ

ወሬ እንደ ሰደድ እሳት አገር ይፈታል ።

(ምሳሌ)

ዐይነተኛው ጥፋቴ ከኦሬንበርግ ያለሕጋዊ ፈቃድ ወጥቼ መኮረሜ እንደሆነ ዐውቄዋለሁ ። ይህን ለማሳመን አይችግረኝም ። በደፋ ክልክል ባይሆንም በዚያን ወቅት ወታደራዊ ሥርዓት ጠብ መጫር ብዙውን ጊዜ የሚበረታታ ተግባር ስለነበር ግፋ ቢል ክስ የሚመሠረትብኝ በአጉል ጀብደኝነት እንደሚሆን ገመትሁ ። በአንጻሩ ደግሞ ከፑጋቼቭ ጋር ስለነበረኝ ግንኙነት የሚመስክርብኝ ሰው ቁጥር አያሌ በመሆኑ በከዳተኝነት መጠርጠሬ አልቀረም ። የሚጠብቀኝን ምርመራ እያሰላሰልኩና መልሴንም እያውጠነጠንኩ ዳኞቼን በግልጽነትና በሐቀኛው መንገድ በሀቀኛው ለመቅረብ ወሰንኩ ።

ከፈራረሰችውና ከተቃጠለችው ከካዛን ከተማ ደረስኩ ። ያለጣራና መስኮት የቆሙትና የተለበለቡት ግድግዳ ዎች አግጠዋል ፣ መንገዶቿ በከሰል ክምር ተጨናንቀዋል። ፑጋቼቭ የተወው ቅርስ ይኸው ነበር ! ከፍርስራሹ መሐል ብቻውን ወደተገተረ ወደ አንድ ምሽግ ተወሰድኩ ። እጅ በው ያደረሱኝ መታደሮች ለተረኛ ዘቦች ሲያስረክቡኝ እነ ዚያ ደግሞ በተራቸው አንጥረኛ አስጠርተው በእግር



t.me/OLDBOOKSPDF

ብረት አስቀፈደደኝ ። በብረት ፍርግርግ የተሸፈነች ፉካ ብጤ መስኮት ወዳላት አንዲት ጠባብና ጨለማ ክፍልም ተወስጄ ታሰርኩ ።

ከእንዲህ ያለ ጅምር መልካም ውጤት አይጠበቅም ። ሆኖም መንፈሴ አልተኮላሸችም ፤ ተስፋ አልቆረጥኩም ። በሥቃይ የሚዋትቱ ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ከንጹሕ ፣ ግን ከተጣጠበች ልቤ የመነጨ የእውነተኛ ጸሎት ቃናን አጣጥሜ ፤ ወደፊት ለሚጠብቀኝ ጣጣ ራሴን ሳላስጨንቅ በሰላም እንቅልፍ ተዋጥኩ ።

በማግሥቱ ጠዋት የእስር ቤቱ ዘበኛ ቀስቅሶኝ ኮማ ሽኑ ዘንድ እንደምቀርብ ነገረኝ ። ሁለት ወታደሮችም ወደ እዛዡ ቤት ወሰዱኝና እነርሱ ከውጭ ቀርተው ብቻዬን ወደ ውስጥ እንድዘልቅ ፈቀዱልኝ ።

አዳራሹ ሰፋ ያለ ነው ። ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል ። አንዱ ኮስታራና ቁጡ የሚመስል ሽማግሌ ጄነራል ሲሆን፣ ሌላው የሐያ ስምንት ዓመት ገደማ ጣቂታ ፡ ንቁና ፡ ተጫ ዋች ብጤ ወጣት ሻለቃ ነው ። ቃሌን ለመመዝገብ የተመ ደበው ጸሐፊ መስኮት አጠገብ ከሚገኘው ጠረጴዛው ላይ ማንጐሉን ጆሮው ላይ አጋድሞና ወረቀቱ ላይ አቀርቅሮ ተቀምጧል ።

መስቀልኛ ጥያቄ ተጀመረ ። ስሜንና ሥራዬን ተጠ የቅሁ ። የአንድሬ ፒትሮቪች ግረኔቭ ልጅ መሆን አለመ ሆኔን ጄነራሉ ጠየቀኝ ። መልሴን በአዎንታ ሳቀርብለት ቆጣ ብሎ፤“እንደዚያ ያሉ የተከበሩ ሰው እንዳንተ ያለ ወራዳ ልጅ ማፍራታቸው ያሳዝናል ! ” አለኝ ። የተመሠ ረተብኝን ክስ በሀቅ እንደምቋቋመው ያለኝን ተስፋ በተ ረጋጋ እንደበት ገለጽኩለት ። ልበ ሙሉነቴ አላስደሰተ ውም ። “ ብልጣብልጥ ትመስላለህ ” አለኝ ግንባሩን ከስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ክሶ ። “ ግን ከንት የበሰጡ ብልጣብልጦችን የእጃቸውን እንዲያገኙ አድርገናል ። ”

ወጣቱ ሰውዬም በበኩሉ እንዴትና መቼ ጕጋቼብን ማገልገል እንደ ጀመርኩና በምንስ ያህል ክፍያ እንደ ተቀ ጠርኩ ጠየቀኝ ።

መኰንንና የጨዋ ልጅ እንደ መሆኔ የጕጋቼብ አገል ልጋይ እንዳልሆንኩና ከእርሱም ምንም ዐይነት ክፍያ እንዳልተቀበልኩ ኮራ ብዬ መለስኩለት ።

“ ታዲያ ” አለኝ መርማሪዬ “ ጓደኞቹ በግፍ ሲታ ረዱ እንዴት አንድ መኰንንና የጨዋ ልጅ ብቻ ከዚያ ወን በዴ ምሕረት ሊያገኝ ይችላል ? እንዴትስ ይኸው መኰን ንና የጨዋ ልጅ ከወሮበሎች ጋር ተወዳጅቶ ይገባበዛል ፣ ከዚያ ቀንደኛ ወንበዴ የቆዳ ካፖርት ፣ የፈረስና የሃምሳ ኮፒክ ስጦታዎች ይቀበላል ? በከሃዲነት ወይም ደግሞ ከፍ ርሃት በመጣ የአድርባይነት ግፊት ካልሆነ በቀር እንዴት እንዲህ የመሰለ እንግዳ ደራሽ ወዳጅነት በሁለታችሁ መሐል ይፈጠራል ? ”

በመኰንኑ ቃላት ክፉኛ ቆሰልኩና ሽንጤን ገትሬ ለመከራከር ተነሣሁ ። ከጕጋቼብ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተ ገናኘነው በአውላላ ሜዳ ውስጥ የበረዶ ውሽንፍር በሚ ያፏጭብን ወቅት እንደ ነበርና የቤሎጕርስክን ምሽግ በወ ረረ ጊዜ ጕጋቼብ እንዳስታወሰኝና ምሕረትም እንዳደረገ ልኝ ነገርኩት ። ከእርሱ ቆዳ ካፖርትና ፈረስ ያላንዳች መግ ደርደር መቀበሌን አምኘለት የቤሎጕርስክን ምሽግ ከወ ራሪዎች ለማዳን በተደረገው ጥረት ውስጥ ግን እስከ መጨ ረሻው ድረስ መታገሌንም አወሳሁት ። በመጨረሻም በኦ ሬንበርግ አደገኛ ከበባ ወቅት ስላሳየሁት ጀግንነት የምሽ ጉን አዛዥ በምስክርነት አቀረብኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኮስታራው ሰውዬ ጠረጴዛው ላይ የነበረ አንድ ዶብ ዳቢ አንሥቶ ማንበብ ጀመረ ። “ ግሬጌቭ የተባለው መኰንን የውትድርናና ሥርዓትን በመጣስና መሐላውንም በማፍረስ በወቅቱ በመዕ ውስጥ ስለ መካፈሉና ከወንበዴዎቹ መሪ ጋር ግንኙነት ስለመፍጠሩ ከቡርንትም ላቀረበው ጥያቄ ምላሹን እንደሚከተለው ላቀርብ ክብር እየተሰማኝ ነው ። ግሬጌቭ የተባለው መኰንን ከጥቅምት እስከ ጥር 1773 በኦሬንበርግ ሲያገለግል የቆየ ቢሆንም ፣ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ከከተማዋ በመጥፋት በምድቤ ውስጥ ከሚገኙት ወታደሮች ተሰውሮ ከርሟል ። ከፑጋቼቭ ጋር በአንዲት መንደር ውስጥ ተገናኝተውም አንድ ላይ በመሆን ቀድሞ ሲያገለግልበት ወደነበረው ወደ ቢሎጎርስክ ምሽግ እንደሔዱ የደረሰን ማስረጃ ይጠቁማል ። ጠባዩን በተመለከተም ያለኝ . . . ” ንባቡን ከዚህ ላይ አቋርጦ ፣ “አንተስ ስለዚህ የምትለው አለህ ? ” ሲል ደነፋብኝ ።

ከማሪያ ኢቫኖቭና ጋር ስለአለኝ ዝምድናና ከዚያው ጋር ስለ ተያያዙት ጉዳዮች ቀደም ሲል እንዳደረግሁት ሁሉ በግልጽ ለማስረዳት አሰብኩ ። ግን ለማፈን የማልችለው ስሜት ተናነቀኝ ። ስሟን ማንሣቱ ለምርመራ ወደ ኮሚሽኑ ዘንድ እንደሚያስጉትታትና አልባሌዎች በሚነዙብኝም ሐሜት አብራኝ የመበከሏ ጉዳይ ስለ ዘገነነኝ ተርበተበትኩና የምለው ጠፋኝ ።

የመደናገጤን ሁኔታ በጥሞና ያዳምጡኝ የነበሩትን ዳኞችን መንፈስ በርዞብኝ ጥርጣሬያቸውን አባባሰብኝ ። ወጣቱ መኰንንም ከዋነኛው ጠቋሚ ጋር ፊት ለፊት እንድ ገናኝ ሐሳብ አቀረበ ። ጀኔራሉ “ የትናንቱን ወንበዴ ” እንዲያስገቡት አዘዘ ። የጠቆመብኝን ሰው በይን ለማየት በጉጉት ወደ በሩ ዞርኩ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም የሰንሰለት ድምፅ ሰማሁ ። ወዲያውም በሩ ተከፈተና ሽቫብሪን



t.me/OLDBOOKSPDF

ገባ ። እንዴት እንደ ተለወጠ ገረመኝ ። ከፋኛ ከስቷል ፤ ገር ጥቷል ። ረጅም ጢሙ ተንጨፍሯል ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጥቁር የነበረው ጸጉሩ ሽበት ወርሮታል ። የምስክርነት ቃሉን በደከመ ግን ግልጽ በሆነ አቋም ደገመላቸው ። እንደ አባባሉ ጉጋቼቭ ወደ ኤሬንበርግ የላከኝ ሰላይ ሆኛለሁ ። በየቀኑ ተዋጊ በመምሰል ከምሽጉ ወጣ እያልኩ በከተማዋ ውስጥ ስለሚደገረው ሁሉ ማስረጃ ለጉጋቼቭ አስተላልፍ ነበር። ከዚያም ለይቶልኝ ወደ እርሱው ገብቼ ከአንድ ምሽግ ወደ ሌላው አብሬው እየተንሸራሸርኩ ጓደኞቼን ሁሉ በማጥ ፋት ሥፍራቸውን ለመውሰድና ለመሸለም በተቻለኝ መጠ ን ጥረት እንዳደረግሁ መሰከረብኝ ። በዝምታ ሳዳምጠው ቆይቼ በአንድ ነገር እፎይታ አገኘሁ ። ይኸውም በዚያ አስ ከፊ ሰው አንደበት የማሪያ ኢቫኖቭና ስም አለመነግቱ ነበር ። ምናልባትም በጥላቻ ስለአሽቀነጠረችው ስሜቱ ከፋኛ ቆስሎበት ይሆናል ስለእርሷ ለማንግት ያስፈለገው ። ምናልባትም እርሷን በተመለከተ እኔን ምላሴን እንድሰብ ስብ ያስገደደኝ ዐይነት ስሜት እርሱም ተጭሮበት ይሆ ናል ። ያም ሆነ ፤ ይህ የቢሎጎርስክ ምሽግ አዛዥ ልጅ ስም በኮሚሽኑ ፊት አልተነሣም ። ዳኞቹ ለሽቫብሪን ቃል መቃወሚያ ይኖረኝ አይኖረኝ እንደሁ ሲጠይቁኝ ፤ በቀድ ሞው ቃሌ እንደምፀናና የምጨምረው ምንም ሐሳብ እንደሌለኝ መለስኩላቸው ። ጀነራሉ እንድንወጣ አዘዞና ኙን ለጕን አብረን ወጣን ። ሽቫብሪንን በእርምጃ ተመለ ከትኩት ። ግን አንዳችም ቃል አልወጣኝም ። በጥላቻ እየገለ ፈጠና ሰንሰለቱን እየጐተተ ፊት ለፊቴ በችኰላ ኩስኩስ አለ ። እኔም ወደ ታሰርኩበት ክፍል ተመልሼ ለመስቀለኛ ጥያቄ እንደገና ሳልቀርብ ቀረሁ ።

ከአሁን ወዲያ ለአንባቢ ስለማቀርባቸው ድርጊቶች የዐይን ምስክር አይደለሁም፡ሆኖም ደጋግሜ ስለሰማኋቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ቋልጭ ብለው በእጅምርዬ ውስጥ ተሰለዋልና ልክ በወትቱ በሥፍራው እንደ ነበርኩ አድርጌ አወጋችኋለሁ ።

ወላጆቼ ማሪያ ኢቫኖቭናን የተቀበሏት የጥንት አባቶቻችን ያሳዩት በነበረው ታላቅ እንክብካቤ ነበር ። ዕጓለ ማውታዋን ለማስጠጋትና ፍቅራቸውን ለማካፈል ያበቃቸው የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሆነ አመኑ ። የሚያውቋት ሁሉ ይወዷት ነበርና እነርሱም ወዲያውኑ እቅፋቸው ውስጥ አስገቧት ። አባቴ ስሜቴን በልጅነት ጠባይ እየተረጎመ ብኝ ማጥላላቱን ተወ ፤ እናቴም ብትሆን ከጋብቻችን ወዲያ የምትመኝልኝ ምንም ነገር አልነበራትም ።

የመያዤ ዜና ቤተሰቤን በጣም አድርጎ አስገረማቸው ። ከፑጋቼቭ ጋር ስለነበረኝ እንግዳ ግንኙነት ማሪያ ኢቫኖቭና ለወላጆቼ የነገረቻቸው አቃልላ ስለነበር ከልባቸው እሣቃቸው እንጂ አላስደነገጣቸውም ነበር ። የዘውዱን አገዛዝ ለመገርሰስና የባላባቱን ሥርዓት ለማፈራረስ ከተጠነሰሰ ዐመፅ ውስጥ የእኔን መሳተፍ አባቴ ፈጽሞ ሊቀበለው አልቻለም ። ሳቬሊችም ቢሆን የፑጋቼቭ ተጋባኝ መሆኔንና አንዳንድ ስጦታዎችንም ከወንበዴው መቀበሌን ይናገር እንጂ በከኃዲነት እንደማልጠረጠር ምሎላቸዋል ። እነርሱም በዚህ ተጽናንተው መጨረሻዬ እንደሚያምር በታላቅ ጉጉት ይጠባበቃሉ ። ማሪያ ኢቫኖቭናም ምንም እንኳ ጉዳዩ ቢያሳስባትም ፤ በትሕትናና በበጎ ምግባር የተኮተኮተች በመሆኗ ምንም አላለችም ።

ሳምንታት ዐለፉ . . . እናም አንድ ቀን አባቴ በፒተርስበርግ ከተማ ከሚኖርና የልዑልነት ማዕረግ ካለው ዘመዳችን አንድ ደብዳቤ ደረሰው ። ደብዳቤውም የሚያወሳው ስለእኔው ነበር ። ከተለመደው የሰላምታ መግቢያ በኋላ ልዑሉ የእኔ በዐመፁ ውስጥ መሳተፍ በበቂ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማስረጃ የተደገፈ በመሆኑ ከባድ ቅጣት ተበይኖብኝ እንደ ነበር ፡ ነገር ግን ንግሥቲቷ የአባቴን አገልግሎትና የዕ ድሜውን መግፋት አመዛዝና በእኔ በእርኩሱ ልጁ ላይ የተወሰነብኝን የሞት ቅጣት በዕድሜ ልክ የቁም እስራት በማሻሻል ወደ ሳይቤሪያ እንደምላክ ያትታል ።

ያልታሰበው ይህ የነገር በትር አባቴን የሞት ያህል አደነዘዘው ። የተለምዶው ኩስታራነቱ ጠፋና በመረረ ሐዘን እንባውን አዘነበው ። "ምን ?" በማለት ደግሞ ደጋ ግሞ እየጮኸ ፡ "ልጄ የጉጋቼቭ ግብረአበር ! አንተ እግ ዜር ፡ ምን አመጣህብኝ ! ንግሥቲቷ ምሕረት አደረገችለት ! ፍርዱን አሻሻሉለት ! ምነው ሞቶ ባረፈው ኖሮ የተቀደሰ ዓላማ ነው ብሎ ላመነበት ጉዳይ እንደ ተንጠለጠለው አንዱ የቀድሞ ዘመዴ ! አባቴም ከቦሊኒስኪና ከኩሮችቭ ጋር በስቅላት ሰማዕትነትን ተቀብሏል ። እንዴት አንድ የጨዋ ዘር መሐላውን አፍርሶ ከወንበዴዎች ፡ ነፍሰ ገዳዮ ችና መድረሻ ቢስ ጥራጊዎች ጋር ይሠለፋል ! ዘር አሰ ዳቢ ! " በማለት ንዴቱን ይገልጻል ። በቁጣው የተደናገጠ ችው እናቴ በድብቅ እንባዋን እየረጨች የወሬን ዝባዝን ኬንነት የሚያስረዱ ታሪኮችን በመደርደር ልታጽናናው በተ ቻላት ሁሉ ሞከረች ። አባቴ ግን የሚሰማት አልሆነም ።

ከሁሉም በላይ የተሠቃየችው ማርያ ኢቫኖቭና ነበ ረች ፡ ለእርስዋ ስል እንጂ ራሴን ነጻ ለማውጣት እንደማይሳ ነኝ አመነች ። ለሐቁ መሸፋፈንና ለገጠመኝ ፍዳ ራስዋን ተጠያቂ አደረገች ። እንባዋንና ሐዘኗን ከማንም ደብቃ ነጻ የምወጣበትን ዘዴ እዘውትራ ማሰላሰል ያዘች ።

በአንድ ምሽት ወቅት አባቴ ሶፋ ላይ ተቀምጦ የፍ ትሕ መጽሔት ያገላብጣል ። ግን በሐሳብ ርቆ ሔዶ ነበርና መጽሔቱ እንደ ወትሮው ስሜቱን አልኮረኮረለትም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የአርበኝነት ዜማ በታፊነ ፋጨት ያንጐራጉራል ። እናቴ እየቆያየች እንባዋን ዱብ በማድረግ የሹራብ ሥራ ይዛለች። ጉንዋ ተቀምጣ ስትጠልፍ የነበረችው ማሪያ ኢቫኖቭና ወደ ፒተርስበርግ መሔድ እንዳለባትና መጓጓዣም እንደ ሚያስፈልጋት በድንገት ገለጸችላቸው ። እናቴ ይብልጥ አዘ ነች ። " ለምንድን ነው ወደ ፒተርስበርግ የምትሔጂው ?" ስትል ጠየቀቻት ። "አንቺም ትተሽን ልትሔጂ ነው እን ዴ ፣ ማሪያ ኢቫኖቭና ? " ጉዞው የወደፊት ሕይወቷን ምን ነት እንደሚወስነውና በታማኝነት ሲታገል የወደቀ አር በኛ ልጅ እንደ መሆኗ የአንድ ዕውቅ መኳንንት እርዳታ ለመሻት እንደምትሔድ ነገረቻቸው ።

አባቴ አንገቱን ደፋ ። " የልጁን ወንጀል የሚያስታ ውሰው ማንኛውም ጉዳይ ስድብ ስለሚመስለው ጭብጥ ኩርምት ያደርገዋል ። " ሒጂ፣ ልጄ " ብሏት በረጅሙ ተነ ፈሰ ። " ደስታሽን ለማጨለም አንፈልግም ። የወጣለት ከሃዲውን ሳይሆን መልካሙን ባል እግዜር ያድልሽ " ብሏት ከተቀመጠበት ተነሣና ክፍሉን ለቅቆ ወጣ ።

ከእናቴ ጋር ብቻቸውን እንደቀሩ ማሪያ ኢቫኖቭና ስለ ጉዞዋ ዓላማ በመጠኑ አጫወተቻት ። እናቴ አቅፋት በእንባዋ እያጠበቻት ዕቅድዋ እንዲሳካላት ጸለየችላት ። ማሪያ ኢቫኖቭና በታማኝ አገልጋይዋ ፓላሻና ሳይወድ በተ ለየኝ ፣ ግን እጮኛዩን በማገልገል ራሱን በሚያጽናናው ሳቬሊች እየተረዳች ለጉዞዋ የሚጠቅማትን ዝግጅት አጠ ናቀቀች ።

ማሪያ ኢቫኖቭና በሰላም ሶፊያ ከተማ ገባች ። በዚያን ዘመን ቤተመንግሥቱ ወደነበረበት ዛርስካይ ሲሎ ወደ ተባ ለው ቦታ አምርታ በአቅራቢያው ማረፊያ ቤት ተከራየች። ብአንድ ጐኑ ከፖስታ ቤት ጋር የተያያዘ ቤት ነበር ። የፖ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስታ ቢቱ ኃላፊ ባለቤት ጋር ተወዳጅታ ወዲያውኑ ጨዋታ ጀመሩ ። ሴትየዋ አጐቷ የቤተመንግሥት ባለሟል እንደ ሆነና ንግሥቲቷ በስንት ሰዓት ከአልጋዋ እንደምትነሣ ፣ መቼ ቡና እንደምትቀምስ ፣ ለሸርሸር ምን ጊዜ ብቅ እንደ ምትልና እነማንስ እንደሚያጅቧት ፣ ቀን ቀን ከእነማን ጋር እንደምትውልና ለእነማንስ ትሁትነቷን እንደምታሳይ ፣ ማታ ማታ ደግሞ ምን ዐይነት እንግዶችን እንደምታስተ ናግድ በመጠቀም ስለቤተ መንግሥት ሚስጢራዊ ሕይ ወት በስፋት አወሳቻት ። ባጭሩ ፣ የዚያች ሴት ፣ የእና ቭላ ሲቭና ፣ ሐተታ ታሪክ እንደመሆኑ ለዝንተዓለም በቤተ መዘክር ሊቀመጥ በተገባው ። ማሪያ ኢቫኖቭና በጥሞና አዳመጠቻት ። ወደ መናፈሻ ሥፍራም አብረው ወጣ አሉ። እና ቭላሲቭና የእያንዳንዱን ጉዳናና ድልድይ ታሪክ እየነ ገረቻት ዞረው ቢታቸው እስኪመለሱ ድረስ ባልንጀርነታ ቸው በይበልጥ ተጠናከረ ።

ማሪያ ኢቫኖቭና በማግሥቱ በጠዋት ተነሥታ ለባበሰ ችና ወደ መናፈሻው ሥፍራ አዘገመች ። በበልግ ቅዝቃዜ ቅጠሎቻቸው ወደ ወርቃማነት ቀለም በተለወጡት ዛፎች እናት ላይ ፀሐይዋ ተግ ብላ የዕለቱን ውበት አዳምቃዋለች። ሰፊው ሐይቅ እያበራ ረግቶ ተንጣልሏል ። በጠርዙ ላይ እጅብ ብለው ካጠለሉት ቁጥቋጦዎች ሥር ዳክየዎች ቱር ቱር እያሉ በመውጣት በላዩ ላይ ይንሳፈፉሉ ። የል ዑል ፒዬትር አሊክሳንድሮቪች ሩምንትሴቭን የቅርብ ጊዜ ድሎች የሚያበሥር ሐውልት የቆመበትን አንድ ለም ለም መስክ ማሪያ ኢቫኖቭና ስታቋርጥ በድንገት አንዲት ሴት ወይዘሮ ተቀምጣ ተመለከተች ። አጠገቧም ሔዳ ዐረፍ አለች ። ሴት ወይዘሮዋ ትክ ብላ እንደምትመለከታት ሁሉ ማሪያ ኢቫኖቭናም ሰረቅ እያደረገች ከላይ እስከ ታች ቃኘ ቻት ። ሴት ወይዘሮዋ ነጭ ፒጃማ ፣ ቆብና ባለወፍራም



t.me/OLDBOOKSPDF

ገበር ጃኬት ለብሳለች ። የዐርባ ዓመት ገደማ ዕድሜ እንደ ሚኖራት ማሪያ ኢቫኖቭና ገመተች ። የደም ገምቦነቷ ክብ ሯንና ጨዋነቷን ሲጠቁም ሰማያዊ ዐይኖችዋና ፈገግታዋ ልብ ይሰውራሉ ። ዝምታቸውን ለመግፈፍ ሴት ወይዘሮዋ ጨዋታ ጀማሪ ሆነች ።

" የዚህ ሠፈር ነዋሪ አይደለሽም ፡ ነሽ እንዴ ? " ስትል ጠየቀቻት ።

" አይ ፡ አይደለሁም ። ከገጠር ገና ትናንት መግባቴ ነው ። "

" ከቤተሰቦችሽ ጋር ነው የመጣሽው ? "

" አይደለም ፡ እመቤቴ ! ብቻዬን ነው ። "

" ብቻሽን ? ለዚያ አልደረስሽምኮ ! "

" አባትም እናትም የለኝም ። "

" ለሆነ ጉዳይ የመጣሽ ይመስለኛል ። "

" አዎ ፡ እመቤቴ ! ለንግሥቲቷ አቤት ለማለት ነበር የመጣሁት ። "

"አባትና እናት የለኝም ብለሽኛልና ምናልባት የደረሰብሽን በደል ለመግለጽ ሳይሆን አይቀርም አመጣጥሽ !።"

" አይደለም እመቤቴ ! የመጣሁት ርዳታ እንጂ ፍትሕ ፍለጋ አይደለም ። "

" ማንነትሽን ብትነግሪኝ ? "

" የሻለቃ ሚሮኖቭ ልጅ ነኝ ። "

" ሻለቃ ሚሮኖቭ ! ከኦሬንበርግ ምሽጎች የአንደ ኛው አዛዥ የነበሩት ? "

" አዎ እመቤቴ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

ሴት ወይዘሮዋ ልቧ ተነካ ። “ ይቅርታ አድርጊልኝ ” አለቻት በርኅራኄ ድምፅ ፣ “ በጣል ሕይወትሽ ጣልቃ ገብቼ ከሆነ ። ከቤተ መንግሥት ሰዎች ጋር እግባብ ስላለኝ ችግርሽን ስትገልጪልኝ ምናልባት እረዳሽ ይሆናል ። ” ማሪያ ኢቫኖቭና በአክብሮት ብድግ ብላ ምስጋናዋን ገለጸ ችላት ። የዚህች እንግዳ ሴት ርኅራኄ ጉልበት ሰጣት ። የተ ጣጠፈች ወረቀት ከኪሷ አወጣችና ለዚህች ለአለኝታዋ ሰጠቻት ፣ እርሷም በዝምታ ተቀበለቻት ።

በመጀመሪያ በጥሞናና በሐዘኔታ መንፈስ አነበበ ችው ። ግን ወዲያውኑ ገጿ ሲለዋወጥ ማሪያ ኢቫኖቭና አስ ተዋለች ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሰላም ጸዳል ተላብሶ ያስደስት የነበረው ፊቷ ሲኮሳተር አይታ በድንጋጤ ተዋ ጠች ።

“ ለግሪኔቭ አማላጅ መሆንሽ ነው ? ” አለቻት በቸ ልተኝነት ። “ ንግሥቲቷ ይቅርታ የሚያደርጉለት አይመ ስለኝም ። ወደ ወንበዴው ያስኮበለሉት የሥነ ምግባር ብል ሹነቱና አደገኛ ጋጠወጥነቱ እንጂ አለማወቅና ልጅነቱ አይደሉም ። ”

“ አዬ ! ኧረ እንዲያ አይደለም ፣ እመቤቴ ! ። ”

“ አይደለም ? ” በማለት ተቆጣች ሴት ወይዘሮዋ ፊቷ እየቀላ ።

“ አይደለም ፤ ጉዳዩን በዝርዝር ዐውቀዋለሁና እም ልልዎታለሁ ። ሁሉንም ላጫውትዎ እንዲያ ያለ ሥቃይ ውስጥ የገባው ለእኔ ሲል ብቻ ነው ። ከተመሠረተበት ክስ ራሱን ነጻ ለማውጣት አለመሞከሩም እኔን በጉዳዩ ውስጥ ላለማስገባት ሲል ብቻ ነው ” በማለት አንባቢ የሚያው ቀውን ታሪክ በሙሉ አወሳችላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት ወይዘሮዋም ፣ ሁሉንም ልቅም አድርጋ አዳምጠ ቻት ። " ለመሆኑ የት ነው ያረፍሽው ? " ስትል ጠየቀ ቻት ። ማሪያ አድራሻዋን ነገረቻት ። ቤትየዋም የእና ቭላሴ ቭናን ስም ስትሰማ ፈገግ ብላ " ገባኝ ፣ ዐውቃለሁ ! ደህና ሁኚ ፣ መገናኘታችንን ግን ለማንም ሰው እንዳትነግሪ ! በቅ ርቡም ለደብዳቤሽ መልሱን እንደምታገኚ ተስፋ አደርጋ ለሁ " አለቻት ።

ይህን ብላት ጉዞዋን ቀጠለች ፣ ማሪያ ኢቫኖቭናም በተስፋ ተሞልታ ወደ እና ቭላሴቭና ተመለሰች ።

እና ቭላሴቭና ማርያን በበልግ ወቅት በማለዳ የእግር ጉዞ እንዳታደርግ እያስጠነቀቀቻትና ሻይ ፉት እያሉ ማለ ቂያ የሌለውን የቤተ መንግሥት ወሬዋን ስትጠርቅላት እንደ ሠረገላ ከደጃፋቸው ከቆች አለ ። ገጁው ዘው ብሎ ገብቶ ለማሪያ ኢቫኖቭና የንግሥቲቷን የአክብሮት ጥሪ አቀረበ ።

እና ቭላሴቭና ቅጥ አምብሩ ጠፋት ። " የእግዜር ያለ ህ ! " ስትል ጮኸች ። " ንግሥቲቷ ቤተመንግሥታቸው ድረስ ጠሩሽ ! ከዚህ መኖርሽን እንዴት ሊሰሙ ቻሉ ? እን ዴትስ ብለሽ ፊታቸው ትቀርቢያለሽ ፣ ልጄ ? የቤተመንግ ሥትን ሥርዓትና ወግ የምታውቂ አይመስለኝም . . . . አብሬሽ ብሔድ አይሻልም ? በመጠኑም ቢሆን እረዳሻለሁ ። በዚህ ያዘቦት ልብስሽስ እንዴት ብለሽ ትቀርቢያለሽ ? የአ ንድ ባልንጀራዬን ብጫ ቀሚስ ልዋስልሽ ይሆን ? " ይኼኔ መልእክተኛው ጣልቃ ገብቶ ንግሥቲቷ የፈለጉት ማሪያ ኢቫኖቭናን ብቻ እንደሆነና በአዘቦት ልብሷ ልትቀርብ መቻሏንም ነገራቸው ። ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ማሪያ ኢቫኖቭና ከሠረገላው ገብታ ጉዞዋን ወደ ቤተመን ግሥት ቀጠለች ፣ የእና ቫልሲቭናን ምክርና መልካም ምኞት ተቀብላ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሪያ ኢቫኖቭና ዕድልዋ እንደሚቃናላት ገምታ ፣ ልቧ እንደ ታምቡር ሲመታ እንዳልቆየ ሁሉ በድንገት ቀጥ ያለ መሰለ ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥም ሠረገላው ቤተ መንግሥቱ ደጃፍ ላይ ደርሶ ቆመ ። ማሪያ ኢቫኖቭና ደረጃዎቹን እየተንቀጠቀጠች ወጣቻቸው ። በሮቹ ወለል ተደርገው ተከፈቱላት ። የእልፍኝ አስከልካዩ ፊት ለፊቷ እየሮጠ በመምራት የሚያማምሩ ባዶ ክፍሎችን አቋረጠች ። በመጨረሻም በአንድ በተዘጋ በር ደጃፍ ላይ አቁሟት መምጣቷን ለመንገር ወደ ውስጥ እንደሚዘልቅ አስታ ውቃት ።

ንግሥቲቷን ፊት ለፊት የማየቱ ነገር ስለ አስፈራት ማሪያ ኢቫኖቭና መቆም አቃታት ። በጥቂት ጊዜም ውስጥ በሩ ተከፍቶላት ወደንግሥቲቷ ልዩ ክፍል ጐራ አለች ።

ንግሥቲቷ አንዲት ኮመዲኖ አጠገብ ተቀምጣለች። ያሉት ጥቂት አጋፋሪዎችም ለማሪያ ኢቫኖቭና ሥፍራ ለቀቁላት ። ንግሥቲቷ በርኅራኄ በምታነጋግራት ወቅት ማሪያ ኢቫኖቭና ድምጿን ለየች ። ያች ከመናፈሻ ሥፍራ ላይ በግልጽ ያነጋገረቻት ሴት ወይዘሮ መሆንዋን ተገነዘበች ። "ቃሌን ጠብቄ ምኞትሽን ላሟላልሽ በመቻሌ በጣም ደስ ይለኛል ። ችግርሽ መፍትሔ አግኝቷል ። የዕጮኛሽን ንጽሕና ደርሼበታለሁ ። ለወደፊቱ አማችሽ የምታደርሽልኝን ይህን ደብዳቤም ተቀበይኝ ። "

ማሪያ ኢቫኖቭና በሚንቀጠቀጡ እጆቿ ደብዳቢውን ተቀብላ ንግሥቲቷ እግር ላይ ስትደፋ ንግሥቲቱ አቃንታ ሳመቻት ። ከዚያም ንግሥቲቱ " ሀብት እንደሌለሽ ዐውቃለሁ " አለቻት ፣ " እናም የቫለቃ ሚሮኖቫ ውለታ ስላለብኝ ስለ ወደፊት ኑሮሽ አትጨነቂ ። የወደፊት ሕይወትሽን በእኔ ላይ ጣይው ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

ያችን ዕጓለማውታ ንግሥቲቱ በታላቅ ርኅራኄ ካስ ተናገደቻት በኋላ አሰናበተቻት ። በዚያው በሰረገላ ማሪያ ኢቫኖቭናም ወደ ማረፊያዋ ተመለሰች።በጉጉት ስትጠብ ቃት የቆየችው አና ቭላሲቭና ጥያቄ አዘነበችባት ! ማሪያ ኢቫኖቭናም በተቻለ መጠን መልሷን ደረደረችላት ። የማ ሪያ ኢቫኖቭና የማስታወስ ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ከባላገ ርነቷ ዐይናፋርነት የመነጨ ስለ መሰላት ፣ አና ቭላሲቭና ብላ ጠይቃ ላልተሰጣት መልስ ማሪያን አልተቀየመችም ። ማሪያ ኢቫኖቭናም ፒተርስበርግን በቅጡ እንኳ ሳትጎ ብኝ የዚያኑ ዕለት ወደ መጣችበት አገር ተመለሰች ።

የፒየትር አንድሬች ግረኔቭ ታሪክ በዚሁ ያበቃል ። የቤተሰቡ አፈታሪክ እንደሚያወሳው በ1774 መባቻ ላይ በንግሥቲቱ ትእዛዝ ከእስር የተለቀቀው ፒየትር አንድሬች የፑጋቼቭ አንገት በተቀነጠሰበት ሥፍራ ተገኝቷል ፤ ያ ከጥ ቂት ደቂቃዎች በኋላ በደም የታጠበው ጭንቅላትም እር ሱን ከሕዝቡ መሐል ለይቶ ለሰላምታ ያህል ዘንበል እንዳ ለለት ይናገራል ። በዚያው ሰሞን ፒዮትር አንድሬች ማሪያ ኢቫኖቭናን አግብቶ ዛሬ ዝርያዎቻቸው በሲምብረስክ ግዛት ውስጥ አብበዋል ። በዚያ ግዛት አቅራቢያም አንዲት መንደር አለች ። በመንደሪቷ ውስጥ በሚገኝ አንድ ቤተ መዘክር ውስጥም በዳግማዊት ካትሪን የእጅ ጽሑፍ የሠ ፈረና በሥርዓት የተቀመጠ አንድ ደብዳቤ አለ ። የተጻፈ ውም ለፒዮትር አንድሬች አባት ሲሆን፣ ስለልጁ መፈታ ትና ስለ ካፒቴን ሚሮኖቭ ልጅ ፣ ስለማሪያ ኢቫኖቭና የመ ንፈስ ብርታትና የልብ ንጽሕና ያወሳል ። ይህን ታሪካዊ ሰነድ ለማየት የበቃነውም በአያቱ የተተረከውን የዚያን ወቅት ሁኔታ እንደምናጠና በተገነዘበልን በፒዮትር አን ድሬች ግሪኔቭ የልጅ ልጆች ፣ በአንደኛው አማካኝነት ነበር ።



396/90

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋ ብር 3.25

t.me/OLDBOOKSPDF